# ያመንነውን ለምን አመን
(Amharic)

**By**
**J.C.Choate**

**Published by:**
**World Evangelism Publications**
**Winona, Mississippi**

© Copyright, World Evangelism Publications

This printing - 5,000 copies - 2023 – **Amharic**

**InDesign Layout**: Shane Fisher

**Translated by**: Belay Kebede Areri
**WhatsApp number**:  0913611000.
**Email**: ddcoc321@yahoo.co.uk

**Websites**:
www.worldevangelismlibrary.org
www.gospelgazette.com
www.worldevangelism.org
www.worldevangelismmedia.com

**ማሳሰቢያ ይህ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ንብረት ነው፡፡ ይህ ትምህርት በነፃ የሚሰጥ ነው፡፡ በየትምህርቱ መጨረሻ ጥያቄ አለው፡፡ መልሶቻችሁን በራሳቸው ነጭ ወረቀት ላይ ፅፋቸው መልስ መስጫውንና መጽሃፉን መልሱልን፡፡ ስትልኩ ለድሬዳዋ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፖስታ ሳጥን ቁጥር 1376 ድሬዳዋ፡፡ ብላችሁ ላኩልን፡፡ ለበለጠ መረጃ 0913611000 ላይ መጠየቅ ይቻላል**

**Printed by**:
World Evangelism Publications
Winona, MS 38967

## ማውጫ


ትምህርት 1 ለምን በእግዚአብሄር እናምናለን ........................4
ትምህርት 2 ለምን በክርስቶስ እናምናለን............................7
ትምህርት 3 ለምን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን......................11
ትምህርት 4 ለምን በመፅሐፍ ቅዱስ እናምናለን.....................14
ትምህርት 5 በሕግ ሥር ያለሆንነው ለምንድነው.....................18
ትምህርት 6 መዳን ለምን አስፈለገን..................................22
ትምህርት 7 ወንጌል ለምን የእግዚአብሄር የማዳን ኃይል ሆነ..........25
ትምህርት 8 እምነት አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው.....................29
ትምህርት 9 ንሠሀ መግባት ለምን አስፈላጊ ሆነ.......................33
ትምህርት 10 ለምን እንጠመቃለን......................................37
ትምህርት 11 በመታዘዝ ለምን እናምናለን............................40
ትምህርት 12 ለምን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ሆንን.............44
ትምህርት 13 ለምን ክርስቲያን ብቻ ተባልን..........................48
ትምህርት 14 ለምን በአንድነት እናምናለን............................51
ትምህርት 15 ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለምን ሞተ......................55
ትምህርት 16 ለምን ክርስቶስ ከመቃብር መነሳቱን አመንን............58
ትምህርት 17 የክርስቶስን ዳግም መምጣት እናምናለን...............62
ትምህርት 18 ዛሬ ክርስትና ለምን አስፈለገ............................65
ትምህርት 19--- በክርስቶስ ደም ውስጥ ኃይል ለምን ኖረ...............69
ትምህርት 20 -- መሰረቱ ለምን በጣም አሰፈላጊ ሆነ....................73
ትምህርት 21--- ለምን አዲስ ልደት እንሰብካለ .........................77
ትምህርት 22--- ዛሬ ለምን አንዲት ጥምቀት ብቻ ሆነ....................82
ትምህርት 23 ---ለምን ሕሊናን እንደ አስተማማኝ መመሪያ አንቀበልም
...........................................................................86
ትምህርት 24---- ለምን የጌታን ስም እንጠራለን........................90
ትምህርት 25---- ለምን ጥሩ ሥነምግባር መኖር ብቻውን ለደህንነት በቂ አይሆንም.....................................................................94
ትምህርት 26---- ለአምልኮ ለን እንሰበሰባለን............................98
ትምህርት 27----- ለምን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንሰበሰባለን....101
ትምህርት 28 ----ለምን የጌታ እራትን እንወስዳለን...................105
ትምህርት 29 ----ለምን በአምልኮ ላይ በራሳቸን ድምፅ ብቻ እንዘምራለን
.........................................................................108
ትምህርት 30 --- ለምን በፀሎት እናምናለን...........................113
ትምህርት 31-- ወደ መንግሥተ ሰማያት ለምን አንድ መንገድ ብቻ ሆነ.117
ትምህርት 32 ----ሠይጣን መኖሩን ለምን እናምናለን.................121
ትምህርት 33 ----ለምን ሰማያት እናምናለን............................125
ትምህርት 34 ----ለምን ገሃነም መኖሩን አመን.........................130
ትምህርት 35---- ለምን በመጨረሻው ፍርድ ቀን እናምናለን..........134
ትምህርት 36 ----ክርስትና ለምን ልዩ ሆነ........................... 138

## ትምህርት 1

## ለምን በእግዚአብሄር እናምናለን

ዓለም ዛሬ በፓራዶክስ ወይም እርስ በርሱ በሚጋጭ ሀሳብ ውስጥ ናት፣ በአንድ በኩል የእግዚአብሄርን ህልውና ወይም መኖሩን የማያምኑ ሰውች አሉ፣ የእግዚአብሄርን መኖር ይክዳሉ፣ ዓለም የተፈጠረው በአጋጣሚ ነው፣ ሰው ደግሞ የታቸኛው አካል ዘር ነው ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ከሰው ለሚፈጠረው ማንኛውም ነገር ተጠያቂ ከሰው ከራሱ ውጪ ምንም የለም የለም። በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬ በዓለም ላይ አንድ ወይም ብዙ አማልክት እንዳሉ የሚያምኑ አሉ ፣ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ምስሎችና ጣኦታት አማልክቶቻቸውን ይወክላሉ ብለው ያምናሉ፣ አንተ ከነዚህ ውስጥ ከዬትኞቹ ነህ? ምንን ታምናለህ ?

እኔ ክርስቲያን እና የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነኝ፣ ስለዚህ እኔ እና ወንድሞቼ በእግዚአብሄር እናምናለን። እውነተኛ እና ሕያው አንድ እግዚአብሄር ብቻ እንዳለ እናምናለን እርሱም የሁሉ ነገር ፈጣሪ እርሱ ኃያል ፣ ሁሉን የሚያውቅ፣ ሁሉን የሚያይ ሁሉን የሚችል እና ዘላለማዊ እንደሆነ እናምናለን፣ እርሱ መንፈስ ነው፣ እና እርሱ በሁሉም ቦታ አለ፣ አንተም በእሱ እንድታምን እናበረታታሃለን።

በእግዚአብሄር ለምን እንደምናምን ታስብ ወይም ትገረም ይሆናል፣ ጥያቄ ካለህ ስለእምነታችን ልትጠይቀን ሙሉ መብት አለሕ ስለዚህ በእርሱ የምናምንበትን አንዳንድ ምክንያቶችን ልንሰጥዎ እንፈልጋለን። በመጀመሪያ በእግዚአብሄር እናምናለን፣ ምክንያቱም እርሱ እንዳለ እና የሁሉ ፈጣሪ ነው ብሎ ማመን ምክንያታዊ ነው፣ ምድር ከሕያዋን ፍጥረታት ጋር መኖሯ ራሱ ለርሷ ተጠያቂ የሆነ አንድ ሰው እንዳለ ያሳያል። መፅሐፍ ደራሲ እንዳለው፣ ቤትም የገነባው እንዳለው፣ መኪናም ሰሪ ፈጣሪ እንዳለው ሁሉ የዚህ ምድር እና ነዋሪዎቿ እግዚአብሄር ነው፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ቃላቶች እንዲህ ይላሉ "በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" የሚል እናነባለን (ዘፍጥረት 1፡ 1)

ሁለተኛ በምድር ላይ ስላለው የማሰብ ችሎታ ያለው ህይወት የሁሉን ነገር ፈጣሪ በሆነው በሰማያት አምላክ እግዚአብሄር እናምናለን። ምድር ከዕፅዋትና ከእንስሳት ህይወት ጋር መኖር ብቻ ሳይሆን ሰውም በምድር ላይ ይኖራል እና ከሌሎች ነገሮች ጋር ሲወዳደር የላቀ ፍጡር ነው። የሰው ልጆች የማሰብና የማመዛዘን ችሎታ አላቸው። ይህ ብቻ ሣይሆን ሰው በዕውቀቱ ያደገው በጊዜ ሂደት ነው። ይህም ማለት የመማር እና የቀደሙትን ዕውቀት ላይ ለመገንባት ችሎታ አለው ማለት ነው። ይህ ማለት አስተዋይ ፈጣሪ ለሰው ተጠያቂ ነው ማለት ነው ነገር ግን የእንስሳትን ህይወት እንደገና ተመልከት ፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ ተመሳሳይ ነው ይህ ማለት ጥበበኛ ፈጣሪ የእንስሳትን ህይወት

እና ሌሎች ነገሮችን ሁሉ እዚህ ለሰው ጥቅም አስቀምጧል ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ዘፍጥረት ስንመለስ እድዚአብሄር ሰማይንና ምድርን እንደፈጠረና በቀጣዩቹ ቀናትም በምድር ላይ የሚሳቡትን፣ የሰማይ ወፎችንና ዓሣዎችንን ጨምሮ በውስጣቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ እንደፈጠረ ተነግሮናል ፣ የባሕሩ ከዚያም ወንድና ሴት እንደፈጠረ እናነባለን “እግዚአብሄርም ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፣ ግዟትም፣ የባሕርን ዓሶችና የሰማይ ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዟቸው” አላቸው (ዘፍጥረት 1፡28)

ሦስተኛ ፦ እግዚአብሄር የሰው ፈጣሪ ነው ብለን እናምናለን ምክንያቱም ሰው መንታ ፍጡር ነው፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍጡርም ነው።”እግዚአብሄርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሄር መልክ ፈጠረው፣ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው”(ዘፍጥረት 1፡27)ተብለናል፣ እንደገናም “እግዚአብሄር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ በአፍንጫውም የህይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ” (ዘፍጥረት 2፡7) ይህን ለመረዳት እግዚአብሄር መንፈስ የመሆኑን ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል (ዮሐንስ 4፡24)፣ ሰው በአምሣሉ ተፈጠረ ብሎ ሲናገር፣ እግዚአብሄር ለሰው በራሱ የሚመስለውን ነገር ሰጠው ማለት ነው፣ በእርሱ ውስጥ ፈፅሞ የማይሞትን ውስጣዊ አካልን፣ መንፈስን፣ ነፍስን አኖረ፣ ጠቢቡ ሰለሞን ስለሥጋና ነፍስ ሲናገር “አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሄር ሣይመለስ ፈጣሪህን አስብ” ይለናል (መክበብ 12፡7)፣ ይህ የሚያመለክተው ሥጋዊ አካል ሞቶ ወደ ምድር አፈር ሲመለስ የሰው መንፈስ በህይወት ይኖራል፣ ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሄርም ይመለሣል፣ ይህ በራሱ ሰው በእግዚአብሄር እንዲያምን ሌላ ማበረታቻ ነው፣ መሞትን የሚፈልግ እና የሁሉም ነገር መጨረሻ እንዲሆን ማን ይፈልጋል? እግዚአብሄርን የሚክዱ ሰዎች እንደሚሉት ይህን ሞት ብቻ ነው ሰው በጉጉት የሚጠብቀው፣ ነገር ግን በእግዚአብሄር ለሚያምን ግን በህይወት ለመኖር ይህ ህይወት ብቻ ሳይሆን ከሥጋ ሞት በኃላ መንፈሱ ወይም ነፍሱ ለዘላለም ህያው እንደሚሆን እናውቃለን፣ ክርስቶስ እንዲህ አለ “በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካምም የደረጉ ለህይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታንቁ” ብሏል (ዮሐንስ 5፡28~29)።

አራተኛ፦ እግዚአብሄርን የምናምነው በፍጥረቱ አንድነት ነው፣ ወቅቶች፣ የአየር ንብረት ፣ የዕፅዋት ህይወት፣ የባህር ህይወት እና የሰው ህይወት ሁሉም ፕላኔቷ ምድር ላይ ጎን ለጎን ይኖራሉ እናም እያንዳንዳቸው ሌላውን ያሟላሉ ፣ እያንዳንዱ በሌላው ላይ የተመካ ነው፣ ግን ስለፀሐይ እና ጨረቃ እና ክዋክብጽ ? ሁሉም በትክክለኛው ርቀት ላይ ተቀምጠዋል፣ ለምሣሌ ፀሐይ በጣም ቅርብ ብትሆን ምድር

በከባድ ሙቀት ትጠፋ ነበር፣ ሆኖም ፀሐይ በጣም ርቃ ብትሆን ምድር ትቀዘቅዛለች፣ የእግዚአብሄር ፍጥረት እንዴት ድንቅ ነው !! በጥንት ዘመን መዝሙረኛው ዳዊት እንዲህ ብሏል “ ሰማያት የእግዚአብሄርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ የወራሉ፣ ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፣ ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች ፣ ነገር የለም መናገርም የለም፣ ድምጻቸውም አይሰማም። ድምጻቸው ወደ ምድር ሁሉ፣ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ፣ በእነርሱም ውስጥ የፀሐን ድንኳን አደረገ፣ እርሱመንደሙሽራ ከእልፍኙ ይወጣል፣ እንደአርበኛ በመንገዱ ለመሮጥ ደስ ይለዋል” (መዝሙር 19፡1~5)

አምስተኛ ፦ በእግዚአብሄር መኖር እናምናለን ምክንያቱም መፅሐፍቅዱስ ይህንን ስለሚያስመር መጽሐፍቅዱስም የእግዚአብሄር ቃል ሆኖ ስለተገለፀ በዓለም ሁሉ ታላቅ መጽሐፍ ነው (ምሣሌ 26፡ 10) ኃያል አምላክ (ኢሳያስ 9፡5)፣ እውነተኛና ሕያው አምላክ (ኤርሚያስ 10፡10)፣ እንደመንፈስ (ዮሐንስ 4፡24) እንደ ፍቅር (1ኛ ዮሐንስ 4፡1) እሱ የማያዳላ አምላክ፣ (ሮሜ 2፡11)፣ እና ሊፈተን የማይችል (ያዕቆብ 1፡13) አምላክ እኛን ለማስተዋወቅና ፍጥረቱን እንዴት እንደሚይዝ እንድገነዘብ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ነገሮች ተናግሯል

ስድስተኛው ፦ በእግዚአብሄር የምናምነው አንድ ስለሆነ ነው፣ ከእሱ በቀር ሌላ ምንም የለም፣ ጳውሎስ ይህንን ሲያውጅ “ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ” (ኤፌሶን 4፡6)፣ እግዚአብሄር ቀናተኛ አምላክ ነውና ፍጥረታቱ ሕይወት ለሌላቸው ፣ስሎችና ጣኦታት እንዲሰግዱ አይፈቅድም፣ በጥንት ዘመን “ሌላ አምላክን አታምልክ” (ዘፀአት 34፡14)፣ እንደገና “ ቀልጠው የተሰሩትን አማልክት ለአንተ አታድርግ” (ዘፀአት 34፡17)፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ “በላይ በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድር ካለው፣ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሣሌ፣ የተቀረፀውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አጽገድላቸው፣ አታምልካቸውምም፣ በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛ እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጥያት በልጆች ላይ የማመጣ፣ ለሚወዱኝ፣ ተዕዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺ ትውልድ ድረስ ምህረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሄር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና “ ይላል(ዘፀአት 20፡4~6)ቅዱሣት መጽሐፍት የጣኦት አምልኮን ከንቱነት የሚያሳዩት ዛፍ ስለቆረጠ ሰው በመናገር ነው፣ ከፊሉን ምግቡን ያበስል ነበር ሌላውን ክፍል ደግሞ ለማሞቅ ያቃጥለዋል፣ በመጨረሻም ሌላ ቁራጭ ለአምልኮ ጣኦት ይሠራል” (ኢሳያስ 44፡15~16)

ሰባተኛ ፦ እኛ እንድንበትና የዘላለም ህይወት ተስፋ እንዲኖረን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመላክ ምህረቱን ስለዘረጋልን በእግዚአብሄር እናምናለን (ዮሐንስ 3፡16፣17፣ ኤፌሶን 2፡ 8፣9)

እና በመጨረሻም በእግዚአብሄር እናምናለን፣ ምክንያቱም

ብቸኛው አማራጭ ነውና፡፡ ዳሩ ግን የእግዚአብሄርን እና የዘላለም ህይወትን ሐሳብ አለመቀበል እና ሁሉም ነገር በአጋጣሚ የተከሰተ እና ሰዎች እንደ ዝንጀሮ ከዝቅተኛ እንስሳ የወጡ ናቸው የሚለውን ሐሳብ መቀበል ነው፡፡ ይህ ፅን ሐሳብ ብቻ ነው ያልተረጋገጠ፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ነገር ነው፣ መዝሙረኛው ዳዊት "ሰነፍ በልቡ እግዚአብሄር የለም ይላል" ብሏል (መዝሙር 14፡1)፣ እነዚህ ሰውች ይህን ማለት መብታቸው ቢሆንም የተባልነው "እኔ ህያው ነኝ ይላል ጌታ፡፡ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፣ መላስም ሁሉ እግዚአብሄርን ያመሰግናል ተብሎ ተፅፏልና፣ እንግዲህስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሄር መልስ እንሰጣለን" ይላል (ሮሜ 14፡11~12)

በእግዚአብሄር ታምናለህ ? ካላደረግክ እባክህን በቁም ነገር አስብበት፣ በእግዚአብሄርና በእግዚአብሄር ልጅ በክርስቶስ ካመንክ ከኃጥያትህ ንሠሀ ግባ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ በአግህ መስክር፣ ለኃጥያትህ ሥርየት በውኃ ከተጠመቅክ፣ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምርሃል፣ ይህን እንድታደርግ ወደ እግዚአብሄር እንፀልያለን፣

## ትምህርት ሁለት
## ለምን በክርስቶስ እናምናለን

አንድ ሰው አንድን ነገር ካመነ የሚያምንበት አንዳንድ ምክንያቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡ በእኔ እና በእግዚአብሄር ቤተሰብ አባላት በክርስቶስ ቤተክርስትያን ይህ እውነት ነው፡፡

በእግዚአብሄር የምናምንበትን አንዳንድ ምክንያቶች አስቀድሜ ሰጥቻችኋለሁእና አሁን ለምን ኢየሱስ ክርስቶስን የሐያው የእግዚአብሄር ልጅ እንደምናምን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡

በመጀመሪያ ኢየሱስ ሌላ ሰው ብቻ እንዳልሆነ ላስረዳ፡፡ ሐሰተእኛ መምህር አልነበረም የሞተው ወደ ፊት እንዳይኖር አይደለም፡፡ ሁለተኛ ክርስቶስ በመጀመሪያ ከእግዚአብሄር ጋር የነበረ (ዘፍጥረት 1፡1) እና ሁሉም በእርሱና በርሱ ሆነ (ዮሐንስ 1፡1~3) እንደ አብ ሳይሆን እንደእግዚአብሄር ልጅ አልተነገረም፣ በሐዋሪያት ሥራ 17፡39፣ ሮሜ 1፡20፣ ቆላስያስ 2፡9 እንደተጠራው በመለኮት ውስጥ ሦስት የተለያዩ አካላት እንዳሉ አስታውስ፡፡ እግዚአብሄር አብ፣ ክርስቶስ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ የሰጠው ቃሉ ወይም የቅዱሣት መፃህፍት ባለቤት ማን ነው (ኤፌሶን 4፡1~6) እንደገና ቅዱሣት መፅሃፍት ስለ አንድ አምላክ እና ከዚያም በጢሞቴዎስ 2፡5 እና 17፣ ላይ እንደተገለፀው ስለአንድ አምላክ ይናገራሉ. አንዳንዶች ይህን ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ ይህንንም ለማስረዳት ሲሞክር ኢየሱስ አምላክ ነው ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስም ነው የሚሉ አሉ ነገር ግን ቅዱሣት መጻሕፍት ደጋግመው የሚገልጹት

የተለያዩ ስብዕና ያላቸው፣ እርስ በእርሳቸው የሚነጋገሩ፣ እርስ በርሳቸው የሚሠሩ ወዘተ ናቸው፣ (ዮሐንስ 17፡5፣ ዮሐንስ 16፡13)፣ ከዚያም ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ ከሆነ እግዚአብሄር ማግባት ነበረበት ማለት ነው ብለው የሚከራከሩ አሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ የሰውን ባህሪያት እና ሕጎች ከአምላክነት ጋር ማወዳደር አይቻልም። ክርስቶስ በመጀመሪያ ከእግዚአብሄር ጋር ነበረ፣ ከእግዚአብሄር ጋር እኩል ስለነበረ እንደ ልጅ ተነግሯል፣ ነገር ግን ወደዚህ ዓለም ለመምጣት ራሱን አዋረደ፣ ከሴትም ተወልዶ ስለዓለም ኃጥያት ሊሞት መጣ፣ ዓለም በሱ አምኖ ይድን ዘንድ የዘላለም ህይወት ተስፋም ይኑረው ዘንድ ይህ ሆነ፣ አምላክን ሙሉ በሙሉ ባንረዳም እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች ሙሉ በሙሉ ማወቃችን አስፈላጊ አይደለም። ሰው እንደመሆናችን መጠን እግዚአብሄር እንዴት ሊኖር እንደሚችል እና ለዘላለምም እንደሚኖር አንረዳም፣ ነገር ግን በእምነት እንቀበለዋለን። ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑም እንዲሁ።

የአምላክ ልጅ በሆነው በክርስቶስ እና በትንሣኤው የተነሣውን ጌታ የሰው አዳኝ ለመሆን ለምን እንደምናምን አንዳንድ ምክንያቶች ሰጥተን እንቀጥል፣ ይህም ማለት ክርስቶስን እንደ ነቢይ ወይም እንደ ታላቅ መምህር አድርገን እንመለከተዋለን ነገር ግን እጅግ እንደ ወደደን በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም እንድንድን ስለእኛ ሊሞት ወደደ ማለት ነው።

በክርስቶስ እናምናለን ምክንያቱም እርሱ ሁል ጊዜ ይኖራል፣ ዘፍጥረት 1፡1፣ በመጀመሪያ ከእግዚአብሄር ጋር ነበረ፣ በዮሐንስ 1፡1~2፣ ላይ ስለክርስቶስ ስንናገር ስለእርሱ እንዲህ እናነባለን “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሄር ነበረ፣ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፣ “ (ዮሐንስ 1፡1~2)

እኛ በክርስቶስ እናምናለን ምክንያቱም በእርሱ ሁሉም ነገር ተፈጥሯልና፣ በዘፍጥረት 1፡1 ላይ በተነገረለት በመፍጠር ውስጥ ተሳትፏል፣። በዘፍጥረት 1፡26፣27 ሰውን በመፍጠር ከእግዚአብሄር ጋር ተቆራኝቷል፣ በዮሐንስ 1፡3 ላይ እንዲህ ተብሏል “ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ያለእርሱ አልሆነም” ይላል። ያ ማለት በዙሪያችን ስንመለከት እና ያለውን ነገር ስናይ ይህ ሁሉ የመጣው ከአንድ ቦታ ነው ማለት ነው፣ ግን ከዬት መጣ ? በማን ተፈጠረ ? በክርስቶስ ፣ እውነት ከሆነ ስለእኛ ያለውን ሁሉ ስናይ እና ስለራሳችን ስናስብ እንኳን ክርስቶስን እናስታውሳለን፣ ታዲያ በእርሱ ማመን እንዴት ያቅተናል? ጳውሎስ ስለክርስቶስ ሲናገር “እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፣ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጥያትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን፣ እርሱም የማይታይ አምላክ ምሣሌ ነው፣ የሚታዩትና የማይታዩትም፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም

አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው፣ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋል፣ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል” (ቆላስያስ 1፥14~17)

በክርስቶስ እናምናለን ምክንያቱም እሱ እንደሚመጣ በትንቢት ተነግሯል ከዚያም እነዚያ ትንቢቶች በመምጣቱ ፈጻሚያቸውን አግኝተዋል።በኤደንንገነትሰውከወደቀቦኃላእናሰውሰውከእግዚአብሄር ከተለየ ቦኃላ ክርስቶስ ሰውን ለማዳን ይመጣል ተባለ (ዘፍጥረት 3፥15) ነቢያት ብዙ ጊዜ ስለ መሲሁ መምጣት ተናግረዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ስለእሱ መምጣት ብዙ ነገሮችን ጠቁመዋል። የሚወለድበት፣ ከንጉስ ቁጣ ለማምለጥ ወደ ግብፅ እንዴት እንደሚወሰድ፣ ከገዛ ወገኑ እንዴት እንደሚከዱት ፣ ከዚያም ቦኃላ ለሐሰት ፍርድ እንደሚሰጥ፣ እንዲሰቀል፣ እንዲቀበር እና ከሦስት ቀን ቦኃላ ከሞት እንደሚነሣ፣ በመጨረሻም ወደ ሰማይ ወዳለው አባቱ እንደሚመለስ ፣ ለምሣሌ ኢሳያስ 53 ስለክርስቶስ ሲናገር በሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ ፊሊጶስ ከኢትዮጵያ ለመጣው ሰው ስለክርስቶስ እንዳስተማረው ከብሉይ ኪዳን ምንባብ እንዳነበበለት እናያለን፣ በእርግጥ ይህ አጋጣሚ አይደለም።

በክርስቶስ እናምናለን ምክንያቱም እሱ በተአምራት ባልተለመደ መንገድ ተወልዷልና፣ ስለሱ ትንቢት ኢሳያስ ከብዙ ዓመታት በፊት እንዲህ አለ “ስለዚህ ጌታ እራሱ ምልክት ይሰጣቸዋል፣እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች” (ኢሳያስ 7፥14) ይህም ትንቢት ቦኃላ መፈፀሙን ደግሞ እንዲህ እናነባለን “የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማሪያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሣ ተገኘች፣ እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ፣ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ እነሆ የጌታ መልዓክ በሕልም ታየው፣ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ከእርሷ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፣ ልጅምትወልዳለች፣እርሱሕዝቡን ከኃጥያታቸውያድናቸዋልና፣ስሙን ኢየሱስ ትለዋለሕ በነቢይ ከጌታ ዘንድ `እነሆ ድንግል ትፀንሣለች ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኗኤል ይሉታል` የተባለው ይፈፀም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፣ ትርጓሜውም እግዚአብሄር ከእኛ ጋር የሚል ነው።ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልዓክ እንዳዘዘው አደረገ፣ እጮኛውንም ወሰደ ፣ የበክር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፣ ስሙንም ኢየሱስ አለው፣” (ማቴዎስ 1፥18~25) ይህ ማለት ክርስቶስ ምድራዊ አባት አልነበረውም ነገር ግን ከአባቱ ከሰማይ ከአባቱ ዘንድ መጥቷል። ክርስቶስ እንደማንኛውም ሰው ከምድራዊ አባት እና እናት ተወልዶ ቢሆን ኖሮ ሰው ብቻ ስለሆነ አዳኝ ሊሆን አይችልም ነበር።

በክርስቶስ እናምናለን ምክንያቱም እርሱ ከእግዚአብሄር መሆኑን ለማረጋገጥ ተአምራትን አድርጓል። ድውያንን ፈውሷል፣ ዕውሮችን አብርቷል፣ደንቆሮዎችን እንዲሰሙ፣ዲዳዎችን እንዲናገሩ አንካሶችን እንዲሄዱ አድርጓል። በሠርግ ድግስ ላይ ውኃ ወደ ወይብ ጠጅ ለወጠ፣ አውሎ ነፋስን ፀጥ አደረገ፣ በውኃ ላይ ተራመደ ሙታንናስነስቷል፣ የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስ፣ እና የዮሐንስ ወንጌላት የኢየሱስን ተአምራትን ሁሉ ዘግበዋል፣ " በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ ያደረገሁን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ" (ዮሐንስ 2፥ 23) ፣ የአይሁድ አለቃ እና መምህር የሆነው ኒቆዲሞስ እንዲህ ሲል መስክሯል "መምህር ሆይ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችልና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን" አለው (ዮሐንስ 3፡2) መጨረሻ ላይ እንዲህ የሚል እናነባለን "ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ፣ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተፅፏል" ይለናል ቃሉ (ዮሐንስ 20፡30~31)

በክርስቶስ እናምናለን ምክንያቱም እግዚአብሄርም፣ ሐዋሪያቶችም፣ ሌሎች ስዎችም፣ ሌላው ቢቀር ጠላቶቹም መስክረዋልና፣ እግዚአብሄር ሲናገር "እርሱም ገና ሲናገር እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፣ እነሆም ከዳመናው ፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ" (ማቴዎስ ወንጌል 17፡5)፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጴጥሮስና ሐዋሪያቱ በማቴዎስ 16፡16~18፣ ላይ መሰከሩ፣ ይህ በእውነት አጋጣሚ ሳይሆን ለዓላማ ከእግዚአብሄር ዘንድ የሆነ ነው፣ ጌታም ያለው ይህንን ነው።

በክርስቶስ እናምናለን ምክንያቱም እርሱ ኃጥያት የሌለበት ህይወት ስለኖረ፣ ሰው እንዲድን ሞተ እና ከመቃብርም ተነሣ። ጴጥሮስ በእርሱ ምንም ኃጥያት እንደሌለ ተናግሯል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡22)፣ ጳውሎስም ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞተ ብሏል (ሮሜ 5፥ 8) በተጨማሪም ይቅርታችንን ሊያረጋግጥልን ክርስቶስ አዳኛችን እና የዘላለም ተስፋ ሊሆነን ከመቃብር በድል ተንሣልን (1ኛ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~4)።

በክርስቶስ ታምናለህ ? የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምናለህ ? ክርስቶስ ሲናገር በእግዚአብሄር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ ብሏል (ዮሐንስ 14፡1) ክርስቶስ በሰው ፊት ብንመሰክርለት እሱ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቱ ፊት እንደሚመሰክርልን ተናግሯል (ማቴዎስ 10፥ 32~33)። ስለዚህ መዳን በክርስቶስ ባለን እምነት ላይ የተመሰረተ ነው።

በክርስቶስ እንድታምን አበረታታሃለሁኝ፣ ከኃጥያትህ ንስሀ

እንድይገባ፣ ኢየሱስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እንድትመሰክር እና ለኃጥያትህ ስርየት እንድትጠመቅ ወይም በውኃ እንድትቀበር አበረታታሃለሁ፣ ይህን ካደረግክ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል (ማርቆስ 16፡16፣ የሐዋሪያ ሥራ 2፡47)

## ትምህርት 3
## በመንፈስ ቅዱስ ለምን እናምናለን

የማደርገውን የማምንበት ትክክለኛ ምክንያቶች አሉኝ እና አማኝ ካልሆንክ አንድ ትሆን ዘንድ እነዚህን ላካፍልህ እፈልጋለሁ፣ በእርግጠኝነት በእምነቴ ብቻዬን አይደለሁም፡፡ እንደ እኔ የሚያምኑ በክርስቶስ በዓለም ዙሪያ ያሉ ወንድሞች እና እህቶች አሉኝ፣ በአንድ እግዚአብሄር ስለምናምን አንድ ዓይነት እምነት አለን፣ በክርስቶስ፣ እናምናለን፣ በአንድ መንፈስ እናምናለን፣ እናም ይህ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው የእግዚአብሄር ቃል ትምህርቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ለምናደርገው ጥናት በመንፈስ ቅዱስ እና በሚሠራው *ሥራ* ለምን እንደምናምን እንነግርሃለን፣ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት ውስጥ ሦስተኛው አካል ነው፣ ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡4~6፣ ላይ አንድ አምላክ፣ አንድ ጌታና አንድ መንፈስ እንዳለ ተናግሯል፡፡ ጳውሎስ ስለክርስቶስ ሲናገር "በእርሱ *ሥራ* ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና" ብሏል (ኤፌሶን 2፡18)፣ ዳግመኛም እዚህ ክፍል ላይ ሦስቱ የመለኮት አካላት በግል ተጠቅሰው እናገኛለን፣ እንዲህ ይላል "ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፣ ዮሐንስ ግን `እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን ? ብሎ ይከለክለው ነበር፡፡ ኢየሱስም መልሶ ፦አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው፡፡ ያን ጊዜ ፈቀደለጥ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኃላ ወዲያው ከውኃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሄርም መንፈስ እንደእርግብ ሲወርድ በእሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ" (ማቴዎስ 3፡13~17) ኢየሱስ ሲጠመቅ ፣ መንፈስም እንደእርግብ በእርሱ ላይ እንደወረደ እና እግዚአብሄር በልጁ ላይ ያለውን ሞገስ ለመግለጽ ከሰማይ እንደተናገረ አስተውል፡፡ ያም ማለት በእግዚአብሄር ካመንን እና ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ፣ እኛ ደግሞ በዚያ መንፈስ ማመን አለብን፣ እንደገና እንዲህ የሚል እናነባለን "መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው" (1ኛ ዮሐንስ 5፡7) ቃልም ክርስቶስን ተክቶ ተነግሯል (ዮሐንስ 1፡1) መንፈስ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል መሆናቸውንም መታወቅ አለበት፣ ይህንን ካላወቁ በስተቀር ግራ የሚያጋባ ሊሆን ይችላል፡፡

በምመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ምክንያቱም ማሪያም ኢየሱስን ጸንሣ የወለደችው በመንፈስ ቅዱስ ነው፣ እንዲህ ይነበባል "የኢይሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበር፣ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሣ ተገኘች" (ማቴዎስ 1፡18) የእግዚአብሄርም መልዓክ ለዮሴፍ ተገልጦ በመንፈስ ቅዱስ ስለጸነሰች እንዲወስዳት ነገረው (ማቴዎስ 1፡20)፣ ማርያም ከወንድ ሳልገናኝ እንዴት ልወልድ እችላለሁ ብላ ስትጠይቅ "መልዓኩም መልሶ እንዲህ አላት ፦ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልኡልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሄር ልጅ ይባላል" (ሉቃስ 1፡35) በሌላ አነጋገር ማርያም ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ የመጀመሪያ ልጇን የወለደችው ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ መሆኑ ነው።

በመንፈስ ቅዱስ እንአምናለን ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹት ቅዱሣት መጻህፍት የመንፈስን ምስክርነት ወይም የመንፈስን ቃል ይወክላሉ፣ ለብዙ መቶ ዓመታት መንፈስ ቅዱስ የአምላክን ፈቃድ እንዲጽፉ የተለያዩ ሰዎችን መርቷቸዋል፣ ለዚህም ነው እንዲህ የሚል የምናነበው "የእግዚአብሄር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል። (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16~17)፣ ቃል መንፈስ ነው፣ ህይወትም ነው፣ እሱ እውነትን ይወክላል፣ እሱ ነጻም ያወጣል (ዮሐንስ 8፡32፣ ዮሐንስ 17፡17)

በክርስቶስና በሐዋሪያት ዘመን የሠራው ሥራ በመንፈስ ቅዱስና በሥራው እናምናለን፣ ክርስቶስ መንፈሱ ያለልክ እንደሆነ እናነባለን "እግዚአብሄር የላከው የእግዚአብሄርን ቃል ይናገራልና፣ እግዚአብሄር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና" (ዮሐንስ 3፡34)
መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር አደረ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ አጠቃቀሙ አልተገደበም ማለት ነው። ነገር ግን ጌታ መንፈሱን ያለልክ ከተቀበለ ሌሎች መንፈስ ቅዱስን በመጠን ተቀበሉ ማለት ነው።

ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የእግዚአብሄር መንግሥት በኃይል እንደምትመጣ ተስፋ ሰጥቶአቸዋል፣ (ማርቆስ 9፡1)፣ ይህ የሚያመለክተውውነታው ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደምትመሰረት ነው። ቦኃላ ላይ ክርስቶስ አፅናኙ ወይም መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ይህ መንፈስ ቅዱስም እንደሚወርድባቸው ተናግሯል። በቅርብ እራሱ ወደ ሰማይ እንደሚሄድ ያውቅ ነበር። ሐዋሪያቶቹ ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ሊሳሳቱ ሊረሱ እንደሚችሉ ያውቃል፣ ስለዚህም ነው የማይሣሣተውን መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸውና በእነሱ ላይ እንደሚሆን ተስፋ የሰጠው፣ ይህ

መንፈስቅዱስእሱየተናገራቸውንሁሉያስታውሳቸዋል፣ወደእውነትም ሁሉ ይመራቸዋል፣ በሌላ ቋንቋም እንዲናገሩ፣ ድንቅና ተአምራትን እንዲያደርጉ ኃይል ይሰጣቸዋል። በዮሐንስ 15፡26፣ ላይ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን አፅናኝ ብሎ ገልጾታል። በዮሐንስ 16፡13 እውነትን ሁሉ እንደሚነግራቸው ይህንም እውነት ከእሱ ወስዶ እንደሚነግራቸው ገልጿል፣ ስለዚህ በዚህ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሚያደርጉት ድንቅና ተአምራት ጋር ቃሉን በሚሰሙት ሰዎች ልብ፣ ቃሉን አብሯቸው ሆኖ ያፀና ነበር።

ጌታ ከመሞቱ ከመቀበሩ እና ከትንሣኤው ቦኃላ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት እንዲህ ብሏቸው ነበር "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፣ በኢየሩሣሌምም፣ በይሁዳም ሁሉ በሰማሪያም፣እስከምድርዳርምምስክሮቼትሆናላችሁአለ" የሐዋሪያት ሥራ 1፡8)። ከዚያም በሐዋሪያት ሥራ 2፡1~4 ላይ እንዲህ እናነባለን "በዓለ ሳምሣ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሣሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደእሳትም የተከፋፈሉ ልሣኖች ታዩአቸው፣ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው፣ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሣኖች ይናገሩ ነበር" (የሐዋሪያት ሥራ 2፡1~4) ሐዋሪያቶች በሌላ ቋንቋ ሲናገሩ ህዝቡ በመገረምና በመደነቅ ግማሹ እንደሰከሩ ገምተው ጉሽ ጠላ ጠጥተው ነው ይሉ ነበር፣ ነገር ግን ጴጥሮስ ተነስቶ ይህ ሰክረው እንዳልሆነ ዳሩ ግን በሥጋ ለባሽ ላይ ከመንፈሴ አፈሣለሁ ተብሎ በኢዩኤል የተነገረው ትንቢት ሲፈፀም ነው አላቸው። ዘገባውም እንደሚለው በሐዋሪያት እጅ ሌላ ብዙ ድንቅና ተአምራት ተደረገዋል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡43) ነገር ግን ይህ ድንቅና ተአምራትን የማድረግ ተስፋ የተሰጠው ለማን ነበር? በርግጥም ለሐዋሪያቶች ነው።ስለዚህም እነሱ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ መንፈስም ወረደባቸው ተአምራትንም ድንቅንም አደረጉ የዚህ ተአምራትና ድንቅ እንዲሁም ስብከት ውጤት በዚያን ቀን ቃሉን ሰምተው ንሠሀ ገብተው ለኃጥያታቸው ሥርየት ወንጌልን የታዘዙ 3000 ነፍሳት እንዲጠመቁ ውጤት ሆኗል። እነዚህም የታዘዙት የዳኑትን ጌታ ወደ ቤተክርስቲያኑ ጨምሯቸዋል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣40፣ 47)።

ነገር ግን ሐዋሪያት ሥራውን ሁሉ በራሳቸው መሥራት ስላልቻሉ ጌታበተመረጡየተወሰኑቁጥርላይእጃቸውንእንዲጭኑአስችሏቸዋል። ስለዚህም እንዲሁ በሌሎች ቋንቋዎች እንዲናገሩና ሕዝቡን እንዲያሳምኑ ተአምራትን እንዲያደርጉ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል፣ ቃሉን ይናገር ዘንድ ከእግዚአብሄር የተላኩ ነበሩ (የሐዋሪያት ሥራ 6፡ 1~8)።

ከሐዋሪያትም በቀር እና ሐዋሪያቶች እጃቸውን ከጫኑባቸው በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ ተራውን የመንፈስ ቅዱስ መለኪያ ወይም ስጦታ ነው የተቀበሉት፣ በሐዋሪያት ሥራ 10 እና 11 ላይ እንደተገለፀው አንድ የተለየ ነገር ነበረ፣ ቆርኔሌዎስ እና ቤተሰቡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀብለዋል አህዛብ በጌታ ዘንድ እንደ አይሁዳዊያን መቀበላቸውን ለማረጋገጥ።

በመጨረሻ ሐዋሪያና እጃቸውን የጫኑባቸው ሲሞቱ፣ በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የጌታን ቃል እንዲፅፉ የተለያዩ ሰዎችን መርቷቸዋል፣ ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የእግዚአብሄርን ቃል በማንበብ ወይም በመስማት ብቻ እምነት በሰው ልብ ይፈጠራል እናም ለጌታ የሚታዘዙ ሁሉ ይድናሉ። ተአምራዊ ባልሆነ የመንፈስ ቅዱስ መለኪያ፣ ምልክቶች ተአምራት እና ድንቅ ነገሮች ከእንግዲህ አያስፈልጉም፣ይህም ቃሉ የተረጋገጠ ስለሆነ በሌሎች ቋንቋዎች ወይም ልሣኖች መናገርን ይጨምራል። ስለዚህ ዛሬ መንፈስ ተአምራትን ለማድረግ በሰው በኩል አይሰራም፣

መንፈስ ቅዱስ ተአምራትን ለማድረግ ካልፈቀደልን እንዴት መንፈስ ቅዱስ ሊኖረን ይችላል? የመንፈስ ቅዱስ ዓላማ ምንድነው መንፈሥ በውስጣችን ያደረበት ዓላም ምንድነው? ስለእግዚአብሄር ወይም ስለክርስቶስም እንዲሁ ሊጠየቅ ይችላል። መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው የመንፈስን ምስክርነት እናምናለን። ጌታን አምነን ፈቃዱን ስንታዘዝ ያድነናል፣ መንፈስ ቅዱስም ይሰጠናል(የሐዋሪያት ሥራ 2፡38) ከዚያም መንፈስ በቃሉ ይመራናል (ሮሜ 8፡1) የእግዚአብሄር ልጆች መሆናችንን መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር እንደሚመሰክር ተነግሮናል (ሮሜ 8፡16) መንፈስ ስለእኛ ይማልዳል (ሮሜ 8፡16) መንፈስ የመዳናችን መያዣ ነው (ኤፌሶን 1፡14) የመንፈስ ቃል ሰይፍ ነው (ኤፌሶን 6፡17)

ብዙ ሐሰተኛ መንፈሶች አሉ ነገር ግን እውነተኛው የእግዚአብሄር መንፈ መንፈስ ቅዱስ ነው፣ በመንፈ ቅዱስ ታምናለህ? እሱ በአንተ ውስጥ አለ? እሱን መንፈስ ከሌለህ የእግዚአብሄር ልጅ አይደለህም።

በጌታ ካመንክ ከኃጥያትህ ንሠሀ ከገባህ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ከመሰከርክና ለኃጥያትህ ሥርየት ከተጠመቅክ ጌታ ያድንሃል፣መንፈሱንም ይሰጥሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል። ካላድረግክ እንድታደርገውና እንድትታዘዝ እንፀልያለን።

## ትምህርት 4

## መጽሐፍ ቅዱስን ለምን እናምናለን

መጽሐፍ ቅዱስ ጥንታዊ መጽሐፍ ነው። ለመጻፍ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታት የፈጀ ይመስላል። ደርሳሲዎቹ የተለያዩ የኃላ

ታሪክ ነበራቸው፡፡ ሆኖም ሁሉም አንድ ላይ ሲጣመሩ፣ አንድ ሙሉ ጥራዝ ተሠራ፣ ክፍጥረት መጀመሪያ ተጀምሮ በምድርና በውስጧ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ያካተተ ነጥቦቹን አንድ ላይ ለሰው ልጆች አዳኝ እንደሚያስፈል በማሳየት የሰውን ታሪክ ይነግራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ማለትም "መጽሐፍ" በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን ይከፈላል፣ አዲስ ኪዳን 27 መጽሐፍት አሉት ብሉይ ኪዳን 39 መጽሐፍት አሉጥ በአጠቃላይ 66 መጽሐፍት አሉጥ እሱ እራሱ በሦስት ዋና ዋና ህጎች እና የተለያዩ ጊዜያት ይከፈላል፡፡ የመጀመሪያው የአባቶች ህግ ወይ የአባቶች ዕድሜ ነው፡፡ ከአዳም ተጀምሮ ሙሴ ዘመን ድረስ ያለውን ማለት ነው ይህም 2500 አመታትን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሄር አባቶችን ተናግሮ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለቤተሰባቸው አባላት ይደርሳል፡፡ ሁለተኛው የሙሴ ህግ ወይም ዕድሜ ነው፣ በሙሴ ተጀምሮ እስከ ክርስቶስ ዘመን ድረስ 1500 ዓመታትን በማነፃፀር ቀጠለ፡፡ በዚህ ወቅት የሙሴ ሕግ ተብሎ ተነግሯል፡፡ ሦስተኛው የክርስቲያን ሕግ ወይም ዘመን ነው፣ ከክርስቶስ ሞት ጀምሮ እና እሱ ዳግም እስኪመጣ ድረስ የሚቀጥል ነው፣ ይህ ዘመን ወደ 2000 ዓመታት ያህል ሆኖታል እናም እስከ መቼ እንደሚቀጥል ማንም አያውቅም፣ ከእግዚአብሄር በስተቀር ማንም አያውቅም፡፡ የፓትሪያርክ ዘመን የከዋክብት ዘመን፣ የሙሴ ዘመን የጨረቃ ብርሃን ዘመን እና የክርስቲያን ዘመን የጸሐይ ብርሃን ዘመን ናቸው፣ እዚህ ያለው ሀሳብ በእያንዳንዱ ዘመን ብርሃን ተሰጥቶአል እና በእርግጥ የጸሐይ ብርሃን ዘመን ሙሉ ብርሃን ያለበትን ይወክላል፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጹት ሁለት አበይት ኪዳኖች ስላሉ የሁለቱን ልዩነት መረዳት አለብን፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሄር ፈቃዱን ለሕዝቡ ገልጾአል እናም ይህ በአባቶች እና በሙሴ ዘመን ቀጠለ/ ከዚያም እግዚአብሄር ለሕዝቡ አዲስ ሕግ አቋቋመ፡፡ ይህ ሕግ በክርስቶስ በኩል ተሰጥቶ እስከዛሬ ድረስ በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ እግዚአብሄር አዲስ ፈቃድ በሰጠ ጊዜ፣ ያ የፊተኛው ኪዳን አረጀ፣ ስለዚህ የመጀመሪያው ኑዛዜ እንደ ሕግ አስገዳጅ መሆኑን አቆመ፡፡ አሁንም እግዚአብሄር ታዛዥን እንደሚባርክ የማይታዘዙትን እንደሚቀጣ እና ሁሉም ሊጠቅሙ በሚችሉ መርሆች የተሞላ ታሪክ ሆኖ ያገለግላል ነገር ግን ካሁን ቦኃላ እንደ ሕግ አስገዳጅነት የሌለው ምሣሌ በመስጠት ታሪክ ብቻ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ዛሬ በሥራ ላይ ያለው ሕግ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ሕግ ነው፡፡ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ አዲስ ሕግን ይሰጥ ዘንድ አሮጌውን ህግ አስወገደ እስቲ የእብራዊያን ጸሐፊ የሚለውን እንመልከት "ኑዛዜ ያለ እንደሆነ የተናዛዡን ሞት ማርዳት የግድ ነውና፣ ሰው ሲሞት ኑዛዜው ይጸናልና፣ ተናዛዡ በህይወት ሲኖር ግን ከቶ አይጠቅምም" (ዕብራዊያን 9፡16~17) ይቀጥልና "ቀጥሎ እነሆ

አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ ብሏል፣ ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል፣ በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል" (ዕብራዊያን 10፡9~10)

ከላይ የተገለጸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ለምን ሌላ ታሪካዊ መጽሐፍ ወይም ልብ ወለድ አልሆነም ? እውነት እሱ ታሪካዊ መጽሐፍ ነው፣ እንዲሁም የጂኦግራፊ መጽሐፍ፣ የሳይንስ መጽሐፍ እና ታላቅ የሥነ ጽሁፍ ሥራ ነው፣ ነገር ግን ከሁሉም የበለጠ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄርን ቃል የያዘ መጽሐፍ ፣ በአምላክ መንፈስ መሪነት እንደተጻፈ እናምናለን (ኤርሚያስ 14፡1) ጳውሎስም እንድህ ብሏል "የእግዚአብሄር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16~17)፣ ጴጥሮስም እንዲህ ብሎ አውጆአል " ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፣ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፡፡ ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ተልከው ቅዱሣን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩ" 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡20~21)

በመጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን፣ ምክንያቱም እሱ የእግዚአብሄር ቃል ወይም የጌታ ቃል ነውና፣ ኢየሱስ ሲናገር "ቃልህ እውነት ነው" ብሏል (ዮሐንስ 17፡17)፣ ጳውሎስም እንዲህ ብሏል "የእግዚአብሄር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ በጥበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገስፁ፣ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሄር ዘምሩ" (ቆላስያስ 3፡16)፣ እንደገናም "እንግዲህ እምነት ከመስማት ነው፣ መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው" (ሮሜ 10፡17) አሁንም እንዲህ ብሏል "ቃሉን ስበክ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገስጽ ምከርም" (2ኛ ጢሞተዎስ 4፡2)፣ ያዕቆብም እንዲህ ብሏል "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ፣ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ" (ያዕቆብ 1፡22)፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል ነው፣ የጌታ ቃል ነው፣ የክርስቶስ ቃል ነው፣ ቃል ነው፣ ቅዱሣት መጽሐፍት ነው፣ የእግዚአብሄር ትዕዛዝ ነው፣ እውነት ነው፣ እናም በእሱ ልናምን ይገባናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን ምክንያቱም በዘመናችን ካሉት መመዘኛዎች ጋር የሚስማሙ የአርኪዮሎጂ፣ ታሪክ በጂኦግራፊ፣ በሣይንስ እና በሌሎች የትምህርት ዘርፎች ነው፡፡ ለምሣሌ፣ ከብዙ ታላላቅ የአርኪዮሎጂ ግኝቶች በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች ገልጾ ነበር፣ በቅርብ ጊዜያት ታላቅ ግኝቶች አንዱ የሙት ባህር ጥቅልሎች ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ጽሑፍ ከማግኘታቸው በፊት ከ900 እስከ 1000 በተጻፉ የእጅ ጽሁፎች ላይ

የተመሰረተ ነው፡፡ የሙት ባሕር ጥቅልሎች ግን ከአስቴር በሰቀር የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን በሙሉ የያዙት በ200 ዓ ዓ መካከል ነው፡፡ እነዚህ ጽሁፎች እና ከ68 ዓ ም፣ እነዚህ ጽሑፎች የብሉይ ኪዳን ቅዱሣት መጽሐፍት እውነተኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳሉ፣ ታሪክን በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እና ዓለማዊ ታሪክ ይስማማሉ፡፡ በጂኦግራፊ ውስጥ ዛሬ የምናውቃቸው ከተሞች፣ ተራራዎች፣ ወንዞች እና ባህሮች በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል ወደ እኛ መጥተዋል፣ አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስ እና ሣይንስ አይስማሙም ብለው ያስባሉ ነገር ግን ይህ እውነት አይደለም፡፡ "ሣይንስ" የሚለው ቃል በእውነተኛ እውነታዎች ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በእርግጠኛነት መጽሐፍ ቅዱስ ከእውነት ጋር አይቃረንም፣ ቅዱሣት መጽሐፍት እና የውሸት ሣይንስ ወይም የሰዎች ጽንሰ ሀሳቦች በእርግጥ እርስ በርሳቸው ይጋጫሉ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እና የሣይንስ ስምምነት አንዱ ምሣሌ ብድር ክብ መሆኗ ነው (ኢሳያስ 40፡22፣ ኢዮብ 26፡7)፡፡ እነዚህን ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ምሣሌውች አሉ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል መሆኑን እናምናለን፣ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉት ትንቢቶች ሁሉ ተፈፅመዋልና፣ ከነዚህም ውስጥ ድንግል ትጸንሣለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች " ተብሎ (ኢሳያስ 7፡14) ላይ የተፃፈው በማቴዎስ 1 ላይ ተፈፅሟል፣ ሌላው በኢዩኤል 2፡28~29፣ ላይ በመጨረሻው ዘመን በሥጋ ለባሽ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ተብሎ የተነገረው ትንቢት በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ ተፈፅሟል፣ ሌሎችም በደርዘንና ደርዘኖች የተነገሩ ትንቢቶች ተነግረው ተፈፅመዋልና መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል መሆኑን እናምናለን፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን ምክንያቱም ለታላላቅ የሕይወት ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ሆኖአልና፡፡ ሰው ከዬት እንደመጣ ለምን በዚህ ምድር ላይ እንደሚኖር ወደ ዬት ደግሞ እንደሚሄድ የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ ጥያቄኦችን ሁሉ መልሷል፣ "ለመዳን ምን ማድረግ አለብኝ?" ለሚለው ጥያቄ መልስ ሰጥቶአል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡37~38፣ የሐዋሪያት ሥራ 16፡30~33)

መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን ምክንያቱም ለመልካም ነገሮች በሰዎች ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ነው፣ እሱ ሰዎች በኃጥያት እንዳይኖሩ ነገር ግን በጽድቅ እንዲኖሩ የሚያስተምር ነውና፣ ዓለም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተነሣ ወደ ትክክለኛ ህይወት ትመራለች

በመጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን ምክንያቱም የእግዚአብሄር ቃል መቼም አያልፍምና፡፡ ክርስቶስ ሲናገር "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ቃሌ ግን አያልፍም" (ማቴዎስ 24፡35)፣ ጴጥሮስም "ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፣ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሄር

ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ” (1ኛኛ ጴጥሮስ 1፡23)፣ ክርስቶስ ሲናገር በመጨርሻው የሚፈረድብን በቃሉ እንደሆነ ተናግሯል (ዮሐንስ 12፥ 48)

እውነታው መፅሐፍ ቅዱስ ብዙ ጠላቶች አሉት ነገር ግን እነሱ ይመጣሉ ይሄዳሉ ይህ የእግዚአብሄር ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡ ስለዚህ መፅሐፍ ቅዱስ አንተ ምን ዓይነት አስተያየት ወይም ሀሳብ አለህ? ታምንበታለህ? ብዙዎች አድርገውታል፡፡ እንደውነት ከሆነ በዓለም ዙሪያ ብብዙ ቋንቋ በመባዛት የሚወዳደረው የለም፣ በሽያጭም እሱ ተወዳዳሪ የለውም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን እንድታነብ አበረታታሃለሁ፣ ኢየሱስ ሲናገር “ እናንተ በመጽሐፍት የዘላለም ህይወት እንዳላቻሁ ይመስላቸዋል፣እነርሱን ትመረምራላቸሁ፣እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው” (ዮሐንስ 5፡39) ጳውሎስም መጽሐፍ ቅዱስን እንድናጠና ያበረታታል “የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሄር ልታቅርብ ትጋ” (2ኛ ጢሞተዎስ 2፡15) ኢየሱስም “ሰው ከእግዚአብሄር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጄራ ብቻ አይኖርም” ብሏል (ማቴዎስ 4፡4)፣ ሐዋሪያው ዮሐንስም ሲናገር “ዘመኑ ቀርቧልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተፃፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው” ይላል (ዮሐንስ ራዕይ 1፡3)፣

የእግዚአብሄርን ቃል እንድታነብ አበረታታሃለሁ፣ ብታነብና ብታጠና እንዲሁም በትምህርቱ አምነህ፣ በእግዚአብሄር አምነህ፣ ንሠሃ ገብተህ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክረህ፣ በውኃ ውስጥ ለኃጥያትህ ሥርየት ብትጠመቅ ፣ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል”(ማርቆስ 16፡16፣የሐዋሪያ ሥራ 2፡38፣ 47)፡፡

## ትምህርት 5
## በሕግ ሥር ያልሆንነው ለምንድነው

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ላይ ባደረግነው ጥናት በሦስት ዋና ዋና የሕግ ወቅቶች እንዴት እነደሚከፈል አይተናል/ የመጀመሪያው የፓትርያክ አባቶች ሕግ ነበር፣ ሁለተኛው የሙሴ ሕግ ነበር፣ ዛሬ የምንኖረው በክርስቶስ ሕግ ሥር ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ሕጎች በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን በመከፋፈል እንድንለይ ይረዳናል፡፡ የአባቶች እና የሙሴ ህግጋቶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ፣ የክርስቶስ ሕግ ግን በአዲስ ኪዳን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ በራሱ የብሉይ ኪዳን ሕግ አስገዳጅነት እንደሌለው እንድንረዳ ይረዳናል፣ ነገር ግን አዲስ ኪዳን ሕግ እስከመጨረሻ የሚቆይ ነው፣ በጥናታችን ስንቀጥል እነዚህን ከቅዱሣት መጽሐፍት እናያለን፡፡

አወቅክም አላወቅክም ዛሬ በዓለም ላይ ሦስት የተለያዩ ዋና ዋና ትምህርቶች ከብሉይ ኪዳን ጋር እምነታቸውን ያያዙ አሉ፣ እነዚህ ራሳቸው በዚህ ተይዘው ሌሎችንም በዚህ እንዲታሰሩ ይፈልጋሉ፣ እስቲ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተሳሳቱበትን እናሳያለን

ኑዛዜ የኑዛዜ ማጣቀሻ ስላለው አሁን ላብራራ፣ ለምሣሌ ስለዚህ ሰው ወይም ስለዚያ ሰው የመጨረሻ ፈቃድ ወይም ቃል ኪዳን እንነጋገራለን። በዘመናችን ያሉ ብዙ ሰዎች ከሞቱ ቦኋላ በገንዘባቸው እና በንብረታቸው ላይ ምን ሊደርስባቸው እንደሚገባ ኑዛዜ ያቀርባሉ። ከመሞታቸው በፊት ከአንድ በላይ ኑዛዜ ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ይህ የሆነበት ምክንያት ከተወሰነ ጊዜ ቦኋላ በሕይወታቸው ውስጥ የመጀመሪያውን ኑዛዜ እንደማይወዱ ስለሚወስኑ እና አዲስ ኑዛዜ ያደርጋሉ። በህይወት እስካሉ ድረስ የፈለጉትን ያህል ኑዛዜ ማድረግ እንደሚችሉ መታወስ አለበጥ በሀብታቸው የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን አንድ ጊዜ ከሞቱ ቦኋላ የመጨረሻው ኑዛዜ ከሆነ ገንዘቡ እና ንብረቱ በኑዛዜው መሠረት መወገድ አለበት

በተመሣሣይም እግዚአብሄር ለሕዝቡ በመቶ ለሚቆጠሩ ዓመታት የቀጠለውን ቃል ኪዳን ኑዛዜ ሰጥቷል። ነገር ግን እግዚአብሄር አዲስ ኪዳን ያደረገበት ቀን መጣ። ፈቃዱን በሰጠ ጊዜ እና በክርስቶስ ሞት በታተመ ጊዜ ፊተኛው ኪዳን አረጀ። ስለዚህም ነው ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን የምንጠቅሰው። በዚህች ሀገር በዓለማዊ ሕግጋት ከመቶ ዓመት በፊት እንደነበረው ሰው መኖር እንደማይችል ሁሉ እኛም ስለኛ ነገሮች ወደ ብሉይ ኪዳን ሕግ ልንመለስ አንችልም። በኃይማኖት ስም ማድረግ ሳይሆን ይልቁንም በዚህ ዘመን ያሉ ሰዎች አሁን ባለው ሕግ መኖር አለባቸው፣ እንደዚሁም እኛ ዛሬ የምንኖረው በአዲስ ኪዳን በተገለጠው በክርስቶስ ሕግ በመመራት ረክተን መኖር አለብን።

አሁን የሚያስተምሩት ይህ መሆኑን ለማየት ወደ ቅዱሣት መጽሐፍት እንሂድ፣ በአዲስ ኪዳን ወደ ዕብራዊያን መጽሐፍ ከእኔ ጋር ኑና እንይ ይህ ጸሐፊ ስለክርስቶስ ሲናገር “ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ህኝ የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለሆነ የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፣ ኑዛዜ ያለ እንዲሆን የተናዛዡን ሞት ማርዳት የግድ ነውና፣ ሰው ሲሞት ኑዛዜው ይፀናልና፣ ተናዛዡ በህይወት ሲኖር ግን ከቶ አይጠቅምም” (ዕብራዊያን 9፡15~17) እባክህን አስተውል ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ በመጀመሪያ ኪዳን የታመኑት እንዲድኑ አድርጓል፣ ነገር ግን በሞተ ጊዜ የመጀመሪያውን ኪዳን አንስቶ በአዲስ ኪዳን ተክቷል፣ ኑዛዜ ሥራ ላይ የሚውለው ኑዛዜው ከሞተ ቦኋላ እንደሆነ ተነግሯል

ጥናታችንን ስንቀጥል የእብራዊያን ጸሐፊ እንዲህ ይላል “ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሣል ሣይሆን የነገር ጥላ

አለውና፣ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚያቀርቡትን ሊፈፅም ከቶ አይቸልም፣ እንደዚህማ ባይሆን የሚያመልኩትን አንድ ጊዜ ነፅተው ከዚያ ቦኋላ በሕሊናቸው ኃጥያትን ስላላወቁ ማቅረብን በተው አልነበረምን? ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጥያት መታሰቢያ አለ፣ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጥያትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ፦ መስዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትና ስለኃጥያት በሚሠዋ መስዋዕት ደስ አላለህም፣ በዚያን ጊዜ ፦እነሆ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለእኔ እንደተጻፈ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ ይላል፡፡ በዚህ ላይ፦ መሥዋዕትንና መባን በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትንም ስለ ኃጥያትም የሚሠዋ መሥዋዕትን አልወደድህም፣ በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ እነዚህም እንደ ሕግ የሚቀርቡት ናቸው፡፡ቅጥሎ፦ እነሆ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላድረግ መጥቼአለሁ ብሏል፡፡ ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል፣ በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈፅሞ በማቅረብ ተቀድሰናል” (ዕብራዊያን 10፡1~10) ጽሀፊው እያሳየ ያለው በብሉይ ኪዳን የተደነገገውን ሕግ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ በመቀጠልም በየዓመቱ የኃጥያታቸው መታሰቢያ እንደገና ስለሚታሰብ የሚቀርቡት መሥዋዕቶች ኃጥያትን ለዘለቄታው ሊያስወግዱ እንደማይችሉ አሳይቷል፣ ከዚያም ክርስቶስ ስለሰው ኃጥያት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሥዋዕት እንደሆነ እና መጥቶ ስለሰው ኃጥያት ራሱን ባቀረበ ጊዜ ፊተኛውን ማለትም ብሉይ ኪዳንን እንደ ወሰደ ያሳያል፡፡ ሁለተኛ ማለትም አዲስ ኪዳን አሁን ትቶ ማን ወደ አሮጌው ኑዛዜ ወይም አሮጌ ሕግ መመለስ ይፈልጋል? የክርስቶስን የመስቀል ሞት በተሻለ ሕግ ሥር እንዳለን ከተረዳን ማንም ሰው ይህን ማድረግ አይፈልግም፡፡

ክርስቶስ ራሱ በብሉይ ኪዳን እንደገለጸው በሙሴ ሕግ ሥር ህይወቱን ኖሯል፣ ነገር ግን በሞቱ ጊዜ በሚኖረው በአዲስ ኪዳን ሥር የሚጸኑትን እውነትንና መሠረታዊ ሥርዓቶችን ባማስተማር አሳልፏል፡፡ ክርስቶስ ኖረ፣ ሕግን ጠብቋል እናም ሌሎች እንዲያደርጉ አበረታቷል እንዲህ ሲል ይገለጻል “እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፣ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም፣ እውነት እውነት እላችዋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፉ ድረስ፣ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ” (ማቴዎስ 5፡17~18) እዚህ ላይ ክርስቶስ ሕጉ አይፈርስም ነገር ግን ይፈጸማል እያለ ነበር፡፡ ከተፈጸመ ቦኋላ ምን ይሆናል? በተፈጥሮ ያልፋል ወይም ቦኋላ አስገዳጅ አይሆንም፡፡

ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ

እስከታች ተቀደደ ወይም ተከፈለ (ማቴዎስ 27፡51) ይህ ቤተመቅደስ እና የአሮጌው ሕግ ነገሮች በሙሉ እየተወገዱ መምጣቱን የሚያሳይ ምሣሌ ነው፡፡ እና ከዚያ ቦኃላ እነዚህ በሰው ላይ የማይታሰሩ ይሆናል፡፡

በ2ኛ ቆሮንቶስ 3 ላይ ጳውሎስ "ፍደል ይገድላል፣ መንፈስ ግን ህይወትን ይሰጣል" ይላል፣ እኛ የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ተደርገናል ይላል፣ ሕጉ በድንጋይ ላይ የተጻፈ የክርስቶስ ደግሞ በመንፈስ የሆነ ሕግ ሲሆን ይቃረናሉ፣ ሕግ የሞት አገልግሎት እንደሆነ እና የክርስቶስ ሕግ ግን ህይወትን እንደሚያመጣ ያሳያል፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ሕኛ በአሮጌው ሕግ መካከል ያለውን ልዩነት እንዲህ ይገልጸዋል "እንግዲህ ሕግ ምንድነው ?ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከኛ እጅ በመላዕክት በኩል ስለሕግ መተላለፍ ተጨመረ፡፡መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሄር ግን አንድ ነው፡፡ እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሄርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? አይደለም ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ፅድቅ ከሕግ በሆነ ነበር፣ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጥያት በታች ሁሉን ዘግቶታል፡፡ እምናትም ሣይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር፡፡ እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኗል፡፡እምነት ግን መጥቷልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም፣ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁና፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችዋልና፣ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡ እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብረሃም ዘር እንደተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ" (ገላቲያ 3፡19~29) ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች ሕጉ ወደ ክርስቶስ እንዳመጣቸው እና አንዴ ከተደረገ ቦኃላ ከሕግ በታች እንዳልሆኑ እያሳያቸው ነው፡፡ የትምህርት ቢት መምህሩ ሕኝ ይወክላል፣ እምነት ደግሞ ክርስቶስን ይወክላል፣ በሌላ አነጋገር ሕጉ ዓላማውን አሟልቷል፡፡ ተወስዷል፡፡ አሁን ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ነን፣ ማለትም እርሱን ከታዘዝነው ማለት ነው፡፡

ከአሁን ቦኃላ በሙሴ ሕግ ወይም በብሉይ ኪዳን ወይም በሕግ ሥር እንዳልሆንን ይልቁንም አሁን በክርስቶስ ሕግ ሥር መሆናችንን በግልፅ የሚያሳዩ ቡ ሌሎች የቅዱሣት መፃሕፍት ክፍሎች አሉ፣ በሚሻል ፍጹም ሕግ ሥር በመሆናችን ምንኛ ተባርከናል

ወዳጆቼ ክርስቶስ እናንተ እንድትድኑ ሞቶላችዋል፡፡ በእርሱ ንታምኑ፣ ከኃጥያታችሁ ንሠሀ ብትገቡ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ

እንደሆነ ብትመሰክሩ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ ብትጠመቁ ኢየሱስ ያድናችዋል፣ ቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምራቸዋል።

## ትምህርት 6
## መዳን ለምን አስፈለገን

እስከዚህ ድረስ በእግዚአብሄር በክርስቶስ፣ በመንፈስ ቅዱስና በመጽሐፍ ቅዱስ የምናምንበትን ምክንያት ተመልክተናል። በመጨረሻው ትምህርታችን ለምን ከሕግ በታች እንዳልሆንን ማለትም የሙሴን ሕግ ወይም የብሉይ ኪዳንን ሕግ ተምረናል። ቅዱሣት መጽሃፍት በሕጉ ሥር የሚቻል ቢሆን ኖሮ የክርስቶስ መምጣት አስፈላጊ ባልሆነም ነበር የሚሉትን ነበር። ሕጉ ሰውን ማዳን ካልቻለና የግድ የክርስቶስ መምጣት አስፈላጊ መሆኑ ማረጋገጫ ነው።

ለምን መዳን እንደሚያስፈልገን እየተነጋገርን ያለነው፣ ይህ የሚያሳየው ሰው መጥፋቱን ነው፣ ይህ ደግሞ እውነት ነው፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ “ሁሉ ሓጥያትን ሠርተዋልና የእግዚአብሄርም ክብር ጎድሎአቸዋል” (ሮሜ 3፡23) በማለት ጽፏል፣ እንደገና በሮሜ 3፡10 ላይ “ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ” በማለት (ሮሜ 3፡10)፣ ይህ ማለት ትንንሽ ልጆችን ወይም ህጻናትን ይጨምራል? አይደለም ሓጥያተኞች በሮሜ 3 ላይ ውሸትን የሚናገሩ፣ የሚረግሙ፣ የሚገድሉ እና እግዚአብሄርን የሚቃወሙ መሆናቸው ይታወቃል። ይህ ትክክልና ስህተት የሆነውን ለማወቅ ያደረጉትን ይገልጻል። የተጠያቂነት ዕድሜ ላይ ያልደረሱ ሕጻናትን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደንጹሐን ተደርገው ተገልጸዋል። ኢየሱስ በዘመኑ የነበሩት ሰዎች ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ለመግባት እንደሕጻናት እንዲሆኑ አስተምሯል። (ማቴዎስ 18፡1~6) ኃጥያተኞች ከዚያ ንጽህነት ውጪ ናቸው፣ መልካሙንና ስሕተቱን የሚያውቁበት ዕድሜ ላይ ደርሰዋል። በዚህ ጊዜ ለድርጊታቸው ተጠያቂ ናቸው። ስለዚህም ኃጥያተኞች ዓመጸኞች የእግዚአብሄር ክብር ጎድሎአቸዋል፣ ኃጥያተኞችም ናቸው ይባላል፣ ኃጥያተኞችን የበለጠ ለመግለፅ ዮሐንስ እንዲህ ብሏል “ኃጥያትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመጽን ደግሞ ያደርጋል፣ ኃጥያትም ዓመጽ ነው” ይላል (1ኛ ዮሐንስ 3፡ 4)

ነገር ግን ወደ መጀመሪያው እንመለስና ኃጥያት እንዴት ወደ ሰው ልጅ እንደመጣ እንመልከት ። እግዚአብሄር ወንድና ሴትን ፈጠረ በኤደን ገነት ሲይስቀምጣቸው ያለ ኃጥያት ነበሩ። ሥራቸውም ኤደን ገነትን መንከባከብ ነበር፣እግዚአብሄርም በኤደን ገነት ውስጥ ያሉትን የዛፍ ፍሬዎችን ሁሉ እንዲበሉ ዱሩ ግን መልካምና ክፉውን የሚያሳውቀውን እንዳይበሉ ነገራቸው፣ ይህንን በበሉ ቀን እንደሚሞቱም ነግሯቸዋል፣እስቲ ወደ ዘፍጥረት 3 ሄደን የተፈጠረውን

እንደ "አባብም እግዚአብሄር አምላክ ከፈጠራቸው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሄር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላጥ ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፦ በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ እግዚአብሄር አለ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት ፦ ሞትን አትሞቱም፤ ከእርሱ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደእግዚአብሄርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሄር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባሏም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርሷ ጋር በላ፤ የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፤ እነርሱም ራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ" (ዘፍጥረት 3፡1~7) መዝገቡ በመቀጠል እግዚአብሄር እንዴት እንደተጋፈጣቸው እና ሁለቱም ሰበብ እንዳቀረቡ ይናገራል። አዳም ሄዋንን ወቀሰ ፤ ሄዋንም እባቡን ወቀሰች፤ ከዚያም እግዚአብሄር ባለመታዘዛቸው ምክንያት የተወሰነ መዘዝ ፍርድ ቅጣት እንደሚደርስባቸው ገለጸላቸው፤ ይህም እባቡን ይጨምራል። በእርግጥ ከተከለከለው ፍሬ በበሉበት ቀን እንደሚሞቱና በመንፈስም እንደሚሞቱ ተነግሯቸው ነበር፤ ያም ማለት ኃጥያት በእነርሱና በእግዚአብሄር መካከል ገባ፤ ስለዚህም በመለየታቸው የእግዚአብሄር ጠላቶች ሆኑ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ያለ ኃጥያት፤ ፊጹም እንደሆነ ያስተምራል፤ ቅዱሣት መጽሐፍት በተጨማሪ እግዚአብሄር ሊዋሽ እንደማይችል ይነግሩናል (ዕብራዊያን 6፡18) እንዲሁም እግዚአብሄር ማንንም አይፈትንም (ያዕቆብ 1፡13) ደግሞም ክርስቶስ ከኃጥያት ነፃ እንደነበረ ተነግሮናል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡22) ይህ ሁሉ እግዚአብሄር ፊጹም ስለነበር ኃጥያትንም ስለጠላ ሰው ግን ኃጥያተኛ ሆኖአል፤ ይህ ኃጥያት ከእግዚአብሄር ለያቸው፤ የእግዚአብሄር ነቢይ እንዲህ ይላል "እነሆ የእግዚአብሄር እጅ ከማዳን አላጠረችም፤ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፤ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች እንዳይሰማም ኃጥያታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል" አለ (ኢሳያስ 59፡1~2) ሐዋሪያው ጴጥሮስም እንዲህ ይላል "የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸውና ፤ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው ተከፍተዋል፤ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡12)

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ እግዚአብሄር ለኃጥያተኛው ሰው የእንስሳትን መስዋዕት በማቅረብ ኃጥያቱን እንዲያስተሰርይለት ይፈልግ ነበር፤ ይህም ሆኖ የሰው ኃጥያት በየዓመቱ ይታወሣል፤ ስለዚህም ያለማቋረጥ መስዋዕት መሆን አለበት፤ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም

ኃጥያትን ለዘላለም ሊያስወግድ አይቻልም ማለት ነው(ዕብራዊያን 10፥1~4) በመጨረሻ እግዚአብሄር የገዛ ልጁን ወደ ዓለም ላከው እሱም ለሰው ልጅ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፊጹም መስዋዕት ይሆን ዘንድ ነው (ዕብራዊያን 10፡5~10)፣ ጴጥሮስም እንዲህ ይላል "የተጠራቸሁለት ለዚህ ነውና፣ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሣሌ ትቶላቸሁ፣ ስለእናንተ መከራን ተቀብሏልና፣ እርሱም ኃጥያት አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘም፡፡ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፣ ነገር ግን በጽድቅ ለምፈርደው ራሱን ሰጠ፣ ለኃጥያት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጥያታቸንን በእንጨት ላይ ተሸከመ" ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 3፡21~24) ስለዚህ የሰው ልጅ ጠፍቷል፡፡ በኃጥያት ውስጥ ነው፣ ያለእግዚአብሄር ነው፣ ከጽድቅ ውጪ ነው፣ ታዲያ የራሱ የጽድቅ ሥራ ሊያድነው አይቻልም፣ መልካምነቱ ሊያድነው አይቻልም፣ በህግም ሊድን አይቻልም፣ ጳውሎስ ሲናገር "ነገር ግን የመድኃኒታቸን የእግዚአብሄር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረኘው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም" (ቲቶ 3፡5) እንደገና እንዲህ ብሏል "ይህም የእግዚአብሄር ሥጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፣ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌሶን 2፡8~9) ስለዚህ ይህ ጻድቅ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት ቅዱስ የሆነ መስዋዕት በመክፈል ለሰው ልጆቸ ሁሉ የመዳን ተስፋ እንዲኖራቸው አደረገ፣ ይህን ስናነብ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሄር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፣ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሄር ወደ ዓለም አልላከውም" (ዮሐንስ 3፡16~17)፣እንደገና የምናነበው በክርስቶስ ሞት የፈሰሰው ደሙ ለኃጥያታቸን መታጠብ መሆኑን ነው "በውድ ልጁም እንደጸጋው ባለጸግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታቸንን አገኘን እርሱም የበደላቸን ስርየት ነው" (ኤፌሶን 1፡7) ክርስቶስ እራሱ እንዲህ ብሏል "ስለብዙዎቸ ለኃጥያት ሥርየት የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ብሏ (ማቴዎስ 26፡28) ነገር ግን የክርስቶስ ደም ከኃጥያት የሚያነጻን እያንዳንዱ ሰው ይህንን ደህንነት ለማግኘት ማመን አለበት (ዮሐንስ 14፡1፣ የሐዋሪያት ሥራ 8፡37)፣ ከኃጥያት ንሠሀ መግባትንም አዟል (ሉቃስ 13፡3) እሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከር አለበት (ማቴዎስ 10፡32) እናም በመጨረሻ ለኃጥያቱ ሥርየት በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ አለበት ጴጥሮስ ለሕዝቡ ሲሰብክ ንሠሀ ግቡ፣ ኃጥያታቸሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳቸሁ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ ብሏል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38) ይህንን ስንታዘዝ ብቻ ነው የኃጥያት ሥርየትን አግኝተን ወደ እግዚአብሄር መመለስ፣ የእግዚአብሄር

ልጅ መሆን የምንችለው፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም የሚጨምረን እና በታማኝነት ስንቀጥል፣ ይህን ጊዜ ነው የክርስቶስ ደም ከኃጥያት ሁሉ የሚያነጻን (1ኛ ዮሐንስ 1፡7)፣ ክርስቲያን ምናልባት ኃጥያት ከሠራ ኃጥያቱ ከእግዚአብሄር ከለየው ኃጥያቱን ተናዝዞ ንሰሀ በመግባት እግዚአብሄር ምህረት እንዲያደርግለት መለመን አለበት (ያዕቆብ 5፡16) ክርስቶስ ለሰው ልጅ በሙሉ በሞተ ጊዜ የሆነው አማላጅ፣ ከእግዚአብሄር ጋር አስታራቂ፣ ጠበቃ፣ ሊቀ ካህን ሊሆን ነው ይህም በኃጥያት ከእግዚአብሄር የተለዩትን ወደ እግዚአብሄር ለማምጣት ነው፡፡ (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5፣ ኤፌሶን 2፡16፣ 1ኛ ዮሐንስ 2፡1፣ ዕብራዊያን 8፡1፣ ዕብራዊያን 10፡21)

ወዳጆቼ፦ እኛ ኃጥያተኞች ነን፣ ነፍሳችን ጠፍታለች፣ እናም እራሳችንን ማዳን አንችልም ወይም ማንም ሰው እና ሰው ሰራሽ ነገር አያድነንም ዬትኛውም ኃይመኖት አያድነንም፣ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ የራሳችን ፅድቅ ማንነታችን ወዘተ ሊያድነን አይችልም፡፡ ጌታን ከልብ መውደዳችን እሱን መፍራታችን ብቻም አያድነንም፣ ዳሩ ግን የተቀመጠልን እሱ ለመዳን ከእኛ የሚፈልገው፣ እንድናምን፣ ስለኃጥያታችን ንሰሀ እንድንገባ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በሰው ፊት እንድንመሰክር እና በመጨረሻ ለኃጥያታችን ስርየት እና ይህ ኃጥያት እንዲታጠብልን በውኃ ውስጥ በመቀበር እንድንጠመቅ ይፈልጋል(ማርቆስ 16፡16፣ ሐዋሪያ ሥራ 2፡38፣ ማቴዎስ 10፡32፣ ሮሜ 6)፣ ይህን ስናደርግ ጌታ ይቅር ይለናል፣ ያድነናል፣ ኃጥያታችንን ያጥብልናል፣ ቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምረናል፣ እናገለግለዋለን፣ እስከሞት ድረስ ታማኝ ሆነን እንኖራለን አንድ ቀን ወደ ሰማይ ሄደን ለዘላለም ከእሱ ጋር እንኖራለን፡፡

## ትምህርት 7

## ወንጌል ለምን የእግዚአብሄር የማዳን ኃይል ሆነ

ለምን ለሁሉም ሰው መዳን አስፈለገ ? አንድ ሰው መዳን አለበት ብሎ መናገር መጥፋቱ አደጋ ላይ አለና መዳን አለበት ማለት ነው፡፡ ሰው በራሱ በቂ እንዳልሆነ ያመለክታል፣ እንዲህ ባለ አስተሳሳብ የሚናደዱ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ በጣም በከፋ ሁኔታ ውስጥ ያሉት ናቸው፡፡ መጥፋትን ማወቅ በቂ ነው፣ ግን እንዴት መዳን እንዳለብህ ካላወቅክ መጥፋትህን እንዴት ልትረዳት ትችላለህ ? ብዙዎች ጠፍተዋል ነገር ግን ድነናል ብለው ያስባሉ ወይም በዳነ ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን አስገብተዋል ለእነዚህ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፣ ነገር ግን እነሱ ጋ ለመድረስ አስቸጋሪ ነው፡፡

ወደ ጥያቄዎች ስንመለስ ሰው እንዴት ጠፋ ? ሰው ጠፍቷል ምክንያቱም ሰው በኃጥያት ውስጥ ስለሆነ ኃጥያተኛ ወይም የጠፋ

ተባለ፣ ኃጥያት ህግን መተላለፍ ነው (1ኛ ዮሐንስ 3፡4)፣ ኃጥያት ሁሉ አመፅ ነው (1ኛ ዮሐንስ 5፡17)፣ ስለዚህ ኃጥያት መጥፎ ነገር ማድረግ ወይ የእግዚአብሄርን ሕግ መተላለፍ ነው ዮሐንስ ሲናገር "ኃጥያትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፣ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጥያትን ያደርጋልና" (1ኛ ዮሐንስ 3፡8)፣ ጳውሎስም ጻድቅ የለም አንድም ይላል (ሮሜ 3፡23፣ ሮሜ 3፡10)፣ጥሩ ነገር አለማድረግም ኃጥያት እንደሆነ ይናገራል "እንግዲህ በጎ ነገር ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጥያት ነው" (ያዕቆብ 4፡17)

ሰው በኃጥያት ውስጥ ከሆነና ከጠፋ እንዴት ነው ከዚህ ኃጥያት ነፃ የሚሆነው ወይም የሚድነው? እውነት ከተነጋገርን እራሱን ነፃ ማድረግ ወይም ማዳን አይችልም፣ ሌላ ኃጥያተኛም ሊያድነው አይችልም፣ የራሱ የሆነ መልካምነትም አያድነውም፣ ታዲያ ለዚህ ሰው ተስፋ አለ ? አዎን ተስፋ አለ። አዎን ያለን ተስፋ እኛን ከዚህ ኃጥያት ሊታደገን እራሱን የሰጠ ከኃጥያት የመውጫ መንገድ የሆነን አለ።

ለመቶዎች ዓመታት እግዚአብሄር የሰዎችን ኃጥያት ያስተሰርይ ዘንድ የእንስሳት መስዋዕት እንዲያቀርቡ ፈለገ፣ ነገር ግን ይህ መስዋዕት ቋሚ የኃጥያት ሥርየት ሳይሆን በየዓመቱ ሊታደስ የሚገባው ( ዕብራዊያን 10፡1~4) በመሆኑ እግዚአብሄር ዓለምን ስለወደደ ለቋሚ የኃጥያት ሥርየት ይሆን ዘንድ አንዲይስ ልጁን በመስቀል ላይ ሞቶ መስዋዕት እንዲሆን ሰጠ (ዮሐንስ 3፡16፣ ሮሜ 5፡8)፣ የዕብራዊያን ጸሐፊ እንዲህ ሲል ይገልፃል "እርሱ ግን ስለ ኃጥያት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀመጠ፣ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል፣ አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፊጹማን አድርጓቸዋልና" (ዕብራዊያን 10፡ 12~14)

ክርስቶስ ስለ ሰው ኃጥያት በመስቀል ላይ ሲሞት በተለይም ከተቀበረ እና ከተነሣ ቦኃላ እግዚአብሄር ልጅ እና አዳኝ መሆኑን ማረጋገጥ መልካም ዜና ነው።ምክንያቱም በዚህ ሲያምን እና ሲታዘዝ ሰው መዳንን ወደ ዘላለማዊ ህይወት የመግባት ተስፋ አለው፣ ይህም ወንጌል ተብሎ ይጠራል፣ ያም ማለት የክርስቶስ ሞት መቀበርና ትንሣኤ ማለት የምሥራች ማለት ነው። አሁንም መልካም ዜና ወይም የምሥራች ይሄ ነው፣ ይህ ሰው በህይወት ዘመኑ ሁሌም መልካም ዜና ሆኖ ይኖራል፣ ጳውሎስ እንዲህ ይላል "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፣ እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? በልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለሰባኪስ እንዴት እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩናቸው ተብሎ እንደተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?" (ሮሜ 10፡13~15) በመቀጠልም ጳውሎስ እንዲህ ይላል "ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እውዳለሁ፣ አባቶቻችን ሁሉ

ከደመና በታች ነበሩ፣ ሁሉም በባህር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባህር ተጠመቁ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፣ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ፣ እግዚአብሄር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም በምድረ በዳ ወድቀዋልና" (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1~4)

ነገር ግን እውነቱ እንዴት ያድናል? ስብከቱስ እንዴት ያድናል? ወይም ማመኑስ ያድናል? እስቲ ከቅዱሣት መጻሕፍት ቃሉ የሚለውን እንስማ፣ ክርስቶስ ከሞተ ከተቀበረ እና ከሞት ከተነሣ ቦኃላ እና ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ከመሄዱ በፊት ለሐዋሪያቶቹ እንዲህ ብሎ ነበር "እንዲህም አላቸው፦ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ ወንጌል 16፡15~16) ማቴዎስም የጌታቸንን ቃል እንዲህ አስቀምጧል "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃቸኋቸው ያዘዝኋቸሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራቸኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፊፃሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴዎስ 28፡19~20) ሉቃስም የጌታቸንን ቃል ሲነግረን "እንዲህም አላቸው ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፣ በስሙም ንሠሀና የኃጥያት ሥርየት ከኢየሩሣሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፏል" (ሉቃስ 24፡46~47)

በሶስቱም ቦታ ክርስቶስ ለሐዋሪያቶቹ ያለው ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ፣ለዓለም፣ለአህዛብሁሉ፣ለያንዳንዱሰውወንጌልንእንዲሰብኩ ነው። ወንጌልን ወይም የምሥራቸን የሚሰብኩት የክርስቶስን ሞት መቀበር እና ከመቃብር መነሣቱን ነው፣ ይሄ ነው ወንጌል፣ ይሄ ነው የምሥራቹ፣ እውነቱ ይሄ ሆኖ እያለ ከዚህ ሌላ የተለየ እንዲሰብኩ አዟቸዋል? ምንም አላዘዘም፣ ለሰዎቹ ወንጌልን ይሰብካሉ፣ ሰዎቹ ይሰማሉ፣ያምናሉ፣ከኃጥያታቸው ንሠሀ ይገባሉ፣ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ይመሰክራሉ፣ ያመኑትና ለመታዘዝ የወሰኑት በመጨረሻ በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲጠመቁ ነው። እንግዲህ በዚህ የክርስቶስን ሞት መቀበር እና ትንሣኤን የሰሙና የታዘዙት ከዚህ ጋር ምንድነው የሚሆነው? የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍን እንዳጠናነው ሰዎቹ ሰምተው ንሠሀ ገብተው ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክረው መጨረሻ ላይ ለኃጥያታቸው ሥርየት ተጠምቀው በመዳን ወደ ቤተክርስቲያን ጌታ ጨምሯቸዋል።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ከክርስቶስ ሞት፣ መቀበር እና ትንሣኤ ጋር ምን አገናኘው? ክርስቶስ የሞተው ሰው እንዲድን ብቻ ሳይሆን ከመዳን በፊት አንዳንድ ሁኔታዎችን አስቀምጧል ማለት ነው። የእግዚአብሄር

ልጅ ሆኖ፣ ሰውም እንዲድን በመስቀል ላይ የሞተው በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ስላለው ሰውን አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርግ የማዘዝ የማሳወቅ መብት ነበረው፣ በይዘቱም ሰው መዳን ከፈለገ ክርስቶስን ማመን አለበት እያለ ነው፣ ከኃጥያቱ ንሠሐ መግባት ወይም ከዚያ መጥፎ እና ስህተት መራቅ አለበት፣ ቀጥሎ እርሱ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከር አለበት፣ በመጨረሻም እርሱ መጠመቅ በውኃ ውስጥ መቀበር አለበት፣ ይህም ጥምቀት ኃጥያቱን ሊያጥብ ነው፣ ይህን ካደረገ እርሱ በክርስቶስ እንደሚያምን እና መዳን እንደሚፈልግ ለኢየሱስ አረጋግጦለታል፣ ጳውሎስ በወንጌል ውስጥ ኃይል እንዳለ ተናግሯል ይህም ጌታ በሞት በመቀበር እና ትንሣኤውን በማስመልከት እንዲህ ይላል ፦"በወንጌል አላፍርምና አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግ እግዚአብሄር ኃይል ለማዳን ነውና፣ ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሄር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና" (ሮሜ 1፡16~17)

በሮሜ 6 ጳውሎስ ክርስቶስ እንደሞተ፣ እንደተቀበረ እና ከመቃብር መነሣቱን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው ጌታን ሲታዘዝ ሞትን፣ መቀበርንና ትንሣኤን በሥራው እንደሚያሳየው ያሳያል፡፡ በሌላ አነጋገር አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ለኃጥያቱ ንሠሀ ሲገባ ወይም ለኃጥያቱ ሲሞት የክርስቶስን ሞት ያሳያል፣ ከጌታ ጋር ለመቀበር በጥምቀት ውኃ ውስጥ ሲወርድ ከጌታ ሞት ጋር ይገናኛል ይህም ከክርስቶስ ጋር መቀበርን ያሳያል እና በመጨረሻም አንድ ሰው ከውሃ ውስጥ ተጠምቆ ሲወጣ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር አንድ መሆኑን ያሳያል፣ ይህ ሰው ይቅር የተባለለት አዲስ ህይወት የሚኖር አሮጌው ነገሩ የተወገደለት እና ትንሣኤ የሆነለት ነው፡፡ ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል "ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ህይወት እንድንመላለስ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን፣ ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፣ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጥያት እንዳንገዛ የኃጥያት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን፣ የሞተስ ከኃጥያቱ ጸድቋልና" (ሮሜ 6፡3~6) ቀጥሎም እንዲህ ይላል "ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፣ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጥያት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ፣ ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጥያት ባሪያዎች ከሆናችሁ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለታዘዛችሁ ከኃጥያትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለተገዛችሁ ለእግዚአብሄር

ምስጋና ይሁን" (ሮሜ 6፡16~17) ትምህርቱ ወይም ዶክትሪኑ የክርስቶስ ሞት መቀበር እና ትንሣኤ ነው። የታዘዙት መሆናቸውን ተጠቀሰው መልክ ከትምህርቱ ጋር የሚመሣሰል ምሣሌ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው ለኃጥያታቸው በመሞት፣ በጥምቀት በመቀበር ከውኃ ውስጥም በመውጣት ትንሣኤውን የሚመስል ምሥል ሆኖ ተስሏል፣ ይህ ከውኃ ውስጥ መውጣት በኃላ ደግሞ በአዲስ ህይወት ለመመላለስ የዘላለም ተስፋን ይዞ የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን ነው።

በ2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7~9፣ ጳውሎስ ጌታ አንድ ቀን ተመልሶ ለወንጌል የማይታዘዙትን ሊበቀል እንደሚመጣ ተናግሯል። በተጨማርም ጴጥሮስ ለወንጌል የማይታዘዙ እንደሚጠፉ ተናግሯል (1ኛ ጴጥሮስ 4፡ 17) ስለዚህ ወንጌል አንድ ሰው ማመን ብቻ ያለበት ሳይሆን መታዘዝም ጭምር መሆን አለበት፣ አንድ ሰው አምኖ ሲታዘዝ ጌታ ያንን ሰው ያድናል እና ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምረዋል።

ወንጌል በትክክል የቅዱሣት መጽሐፍት ላይ በግልጽ እንዲሰበክ የታዘዘ ነው ጳውሎስ "ወንጌልን ካልሰበኩኝ ወዮልኝ" ብሏል (1ኛ ቆሮንቶስ 9፡16)፣ እንደዚሁም የተለየ ወንጌልን የሚሰብኩትን ጳውሎስ ረግሟል (ገላቲያ 1፡6~9)። እሱ ትክክለኛውንና እውነት የሆነውን አንዴ ሰብኳል፣ ከዚህ በተቃራኒ ያለውን የተለየ ወንጌል ለማሳት የሚሰብኩትን ደግሞ ረግሟል።

ወዳጆቼ ! የክርስቶስን ወንጌል ታዛቸዋል? አምናቸዋል? ይህንን እንድታደርጉ እጸልይላቸዋለሁ። ጌታ ከዚ ውጪ ሌላ የማዳኛ መንገድ የለውም።

## ትምህርት 8
## እምነት ለምን አስፈላጊ ሆነ

እምነት ምንድነው? እሱን የሚገልጽበት መንገድ አለ? ብዙ ጊዜ የምንሄደው ወደ ዕብራዊያን 11፡1 ላይ ሲሆን ጸሐፊው "እምነት ምተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው" ይላል፣ በምሣሌ ለማስረዳት እንደ አብረሃም፣ ሙሴ፣ ዳዊት ኤሊያስ፣ እና ታላላቅ ሰዎች እንዳሉ አምናለሁ፣ እና ሌሎችም ኖረዋል ግን አይቼያቸው አላውቅም። እንደ ኖሩ የሚጠቁሙ እውነታዎች እና ማስረጃዎች ወደ ኃላ አሉ፣ ታሪካቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቧል፣ መጽሐፍ ቅዱስን የምጠራጠርበት ምንም ምክንያት የለግም። ስለዚህ እንዲህ ያለውን ምስክርነት እቀበላለሁ፣ እናም ቅዱሣት መጻሐፍት ላይ ባለኝ እምነት እነዚያ በአንድ ወቅት እንደኖሩ አምናለሁ። እኔም ክርስቶስ፣ ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ እና ሌሎችም በመጀመሪያው መቶ ክፍለዘመን እንደኖሩ አምናለሁ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ  ጳውሎስ በሮሜ 10፡17 ላይ እንደጻፈው "እምነት ለመስማት ይመጣል፣ መስማትም የእግዚአብሄር

ቃል ነው” ይላል

በግሌ አግኝቻቸው የማላውቃቸው ብዙ ታላላቅ የዓለም መሪዎች ዛሬ አሉ ነገር ግን መኖራቸውን አምን ነበር። በመኖራቸው ላይ እምነት እምነት እንዲኖረኝ የሚያደርጉኝ አንዳንድ ማስረጃዎች አሉኝ። ስለእነሱ ዘገባዎች እና የጋዜጣ ምስሎች አሉ፣ በቴሌቪዥን አይቻቸዋለሁ እና በሬዲዮ ስርጭቶች ላይ ድምጻቸውን እሰማለሁ፣ በእነዚህ ሁሉ ማስረጃዎች እና ታማኝ ምንጮች የተገኙ ማስረጃዎች እነዚህ የዓለም መሪዎች እውነተኛ መሆናቸውን አምኜ ኖሬያለሁኝ።

እንደዚሁም እኔ እግዚአብሄርን በዓይኔ አላየሁም፣ ግን እኔ ብቻ አይደለሁም ፣ ዮሐንስ እንዲህ ይላል “እግዚአብሄርን ማንም ከቶ አላየውም፣ እርስ በእርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሄር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፌጹም ሆኗል” (1ኛ ዮሐንስ 4፡12) ነገር ግን እግዚአብሄርን ባላየውም አሁንም መኖሩን አምናለሁ። ለምን ? እሱ እውነት መሆኑን የሚያሳዩኝ ብዙ ማስረጃዎች ስላሉ ነው። ፍጥረት ሁሉ በእሱ (ዘፍጥረት 1፡1) ስለእሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (2ኛ ጢሞተዎስ 3፡16~17) ለሱ ያለን ታላቅ ፌላጎት (ኤርሚያስ 10፡23) ዕብራዊ ጸሐፊ እንዲህ ይላል “ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፣ ወደ እግዚአብሄር የሚደርስ እግዚአብሄር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል” ይለናል (ዕብራዊያን 11፡6)

ዕውር እምነት ወይም ከንቱ እምነት እንዳይኖረን፣ ጌታ ተናግሮናል፣ ስለዚህም እሱን እና ለሰው ያለውን ፈቃድ የበለጠ እንድናውቅ ነው። በልጁ በኩል ያናግረናል፣ በክርስቶስ ተአምራዊ ለውጥ እግዚአብሄር ከሰማይ ተናግሮ እንዲህ አለ “እርሱም ገና ሲናገር፣ እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፣ እነሆም ከደመናው፣ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ” (ማቴዎስ 17፡5) የዕብራዊያን ጸሐፊ እንዲህ ይላል “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሄር በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን ለእኛ ተናገረን” (ዕብራዊያን 1፡1~2) ግን እግዚአብሄር እንዴት ነው የሚናገረን? በክርስቶስ በኩል ይናገረናል፣ ያዕቆብ ፍጹም የሆነ የነፃነት ሕግ እንደሆነ ተናግሯል “ነገር ግን ነፃ የሚያወጣውን ፌጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፣ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሣ ያልሆነው፣ በሥራው የተባረከ ይሆናል” ይላል (ያዕቆብ 1፡25) ጳውሎስም “የእግዚአብሄር ሰው ፌጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ፣ የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለትግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል” (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16~17) ጴጥሮስም “በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ከዓለም ርኩሰት ካመለጡ ቦኋላ ዳግመኛ በእርሷ ተጠላልፊው የተሸነፉ ቢሆኑ

ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል፣ አውቀዋት ከተሰጣቸው ከቅድስት ትእዛዝ ከሚመለሱ የፅድቅን መንገድ ባላወቋት በተሻላቸው ነበርና” ይላል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡20~21)፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ “ለእውነት እየታዘዛቸሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማቾ መዋደድ ነፍሣችሁን አንፅታችሁ እርስ በእርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋድውዱ፣ ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፣ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሄር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ፣ ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፣ ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል፣ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። ወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው” (1ኛ ጴጥሮስ 1፡22~25)

አሁን እንግዲህ እግዚአብሄር ለእኛ የሚናገረን ከሆነ እናም ይህ የሚናገርበት መንገድ በጽሁፍ መልክ ተገልጦ መጽሐፍ ቅዱስ ሆኖ ከደረሰን፣ ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ የማንበብ የማጥናት ድርሻ የእኔ እና የአንተ ፋንታ ይሆናል። ጳውሎስ እንድናጠና ይነግረናል (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15)፣ ክርስቶስም ስለኔ ይናገራሉና መጽሐፍን መርምሩ ይላል (ዮሐንስ 5፡39) ነገር ግን ለምንድነው የምናነበው የምናጠናው? ምክንያቱም የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማወቅ እና እሱ ባስቀመጠው መሠረት እንድንታዘዝ ነው።

እግዚአብሄር እንዳለ እና ፈቃዱን የገለጠልን ቢሆንም የምንጠፋባቸው ሁለት መንገዶቾ አሉ፣ አንደኛው፦ የተናገረው ነገር ምንም ይሁን ምን በእግዚአብሄር ላለማመን ልንቃወም እንችላለን። ሁለተኛው፦ እግዚአብሄር መኖሩን ክርስቶስ ልጁ መሆኑን እና መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን እንደያዘ በአዕምሯችን ልንቀበለው እንችላለን ነገር ግን ቃሉን ለመታዘዝ ላንመርጥ እንችላለን፣ ዛሬ በዓለም ላይ እምነት ብቻ እንደሚያድን የሚከራከሩ ብዙዎቸ አሉ፣ ለዚህም የሚጠቀሙት ማስረጃ እንደ ዮሐንስ 3፡16፣ ይጠቁማሉ። ግን ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ በእውነት በጌታ የምናምን ከሆነ እርሱን እንድናደርግ ያዘዘውን አናደርግምን ? ትምህርቱን መታዘዝ ካልቻልን እሱ የሚደሰትበትን ዓይነት እምነት አለን ማለት እንችላለን ?

ያዕቆብ ስለ እምነት አስፈላጊነት ሲያወያየን እንዲህ ይላል “ወንድሜ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነጽ ሊያድነው ይቾላልን? ወንድም ወይም እህት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ ከእናንተ አንዱም ፦ በደህና ዒድ እሳት ሙቅ ጥገቡ ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጋቸውን ባትሰጧቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ፦ አንተ እምነት አለህ እኔ ግን ሥራ አለኝ እምነትኝ ከሥራ ለይተህ አሣየኝ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል። አንተ እግዚአብሄር

አንድ እንደሆነ ታምናለህ መልካም ታደርጋለህ፣ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል፣ አንተ ከንቱ ሰው እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብረሃም ልጁን ይስሐቅን በመሰዊያ ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነቱ ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደነበረ፣ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን ? መጽሐፍም አብርሃምም እግዚአብሄርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፣ የእግዚአብሄርም ወዳጅ ተባለ፣ ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ፣ እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልዕክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" (ያዕቆብ 2፡14~26) ያዕቆብ እንደገለጸው እምነት አለህ ማለት አንድ ነገር ነው፣ ይህንንም ማረጋገጥ ሌላ ነገር ነው፣ ለማንኛውም እምነት ምን ማድረግ ይችላል? ምን ዋጋ አለው? ያዕቆብ እንደገለጸው ብቻውን የሞተ ነው። ህያው የሆነ እምነት የሚሰራ እምነት ነው።

እምነት የሚሠራ ከሆነ መዳን በፀጋ አይደለምን? ጳውሎስ እንዲህ ይላል "ፀጋው በእምነት አድኖአችዋልና፣ ይህም የእግዚአብሄር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፣ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌሶን 2፡8~9) ሰው ለመዳን እና ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ከእግዚአብሄር ተለይቶና የተለየ በጎ ሥራ ፈፅሞ ሊሰራ አይችልም፣ ሆኖም ጳውሎስ ብዙዎች የሚቃወሙትን ነገር እየተናገረ ነው፣ እዚህ ላይ ያለው በፀጋው ድነናል ማለት ምን ማለት ነው? ፀጋ ሰውን ይወክላል ማለት ነው። እግዚአብሄር በፀጋው ማዳንን ሰጥቷል፣ ነገር ግን መዳንን በእምነቱ መቀበል የሰው ድርሻ ነው፣ እግዚአብሄር ከሰጠን ግን እንቀበልም ካልን መዳን አንችልም። እግዚአብሄር ከሰጠን ከተቀበልን ያድነናል ። ግን እንዴት እንቀበላለን? የተናገረውን አምነን እንድናደርግ የጠየቀንን በማድረግ ነው። ነገር ግን አንድ ነገር ብናደርግ መዳን በፀጋ አይደለም ማለት አይደለምን? አይደለም፣ መዳናችንን አገኘን እስከማለት ድረስ እግዚአብሄርን መታዘዝ አንችልም፣

የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍን ስናገላብጥ እና በዚያ ስለተመዘገቡት የተለያዩ ተሃድሶ ጉዳዮች ስናነብ እያንዳንዱ ጉዳይ ወንጌል ወይም የጌታ ፈቃድ መዳን የሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንደቀረቡ እንመለከታለን፣ የእግዚአብሄርን ቃል በመስማታቸው አማኞች ሆኑ፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ አልዳኑም። ይልቁንም በእምነታቸው መሰረት ከኃጥያታቸው ንሠሀ ሊገቡ፣ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ሊመሰክሩ፣ ኃጥያታቸውም ይሰረይ ዘንድ ሊጠመቁ ሄዱ። ያን ባደረጉ ጊዜ ጌታ አዳናቸው ወደ ቤተክርስቲያንም ጨመራቸው፣ በተለይ የሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 2፣8፣9፣ 10 እና 16፣ አንብብ ፣ እነዚህ በእምነት ብቻ ነው

የዳኑት? የለም፣ ማንም። ጌታን እንዲታዘዙ የሚመራቸው እምነታቸው ጠንካራ ሲሆን ብቻ ነው የዳኑጥ ዛሬም ተመሣሣይ ነው፣ ክርስቶስ ተናግሯል ለመዳን አምኖ መጠመቅ አለበት (ማርቆስ 16፡16) አንድ ሰው አምኗል እንበል ግን ለመጠመቅ ፈቃደኛ አይደለም፣ እና መዳን ይችላል/? በማርቆስ 16፡16 መሰረት ግን መዳን አይችልም። በዚህ ሁኔታ እርሱ የማያምን ተብሎ ይፈረጃል፣ እና ክርስቶስ አንድ ሰው ካላመነ እሱ እንደሚፈረድበት ተናግሯል፣ በጌታ ስናምን የሚያድነን እምነት እስካለን ድረስ የሚለውን ሁሉ እናደርጋለን

ምን ዓይነት እምነት አለህ ? እምነትህ የሚሠራ እምነት ነው? በእምነትህ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ፈቃደኛ ነህ? ጌታን ብትታዘዝ ያድንሃል ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል።

## ትምህርት 9
## ንሠሀ ለምን አስፈላጊ ሆነ

ንሰሀ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከታዘዘው ውስጥ አንዱ ነው፣ይህም ንሠሀ ማለት የአስተሣሠብ ለውጥ ማምጣት፣ ወደ ህይወት ለውጥ የሚያመራ የአስተሣሠብ ለውጥ ማለት ነው። በተመሣሣይ ጊዜ ንሠሀ ለተፈጸመው በደል ከማዘን በላይ ነው። ሀዘን በንሠሀ ውስጥ ይካተታል ነገር ግን አንዴ ስለተያዘ ለኃጥያቱ ይጸጸት ይሆናል እንደዚያ ከሆነ አሁንም ንሠሀ መግባት ወይም በህይወቱ መጥፎ እና ስህተት የሆነውን ነገር መተው ያስፈልገዋል፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ "እንደእግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሀዘን ጸጸት የሌለበትን፣ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንሠሀ ያደርጋልና፣ የዓለም ሀዘን ግን ሞትን ያመጣል" (2ኛ ቆሮንቶስ 7፡10)

ጌታ ንሠሀን በተመልከተ ስለ አንድ ሰው ሁለት ልጆቹ ስላሉት ሰው ምሣሌ ያነሣል፣ እንዲህ ይላል "ነገር ግን ምን ይመስላችዋል? አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፣ ወደ አንደኛው ቀርቦ፣ ልጄ ሆይ ዛሬ ሂድና በወይኔ አትክልት ሥራ አለው፣ እርሱም መልሶ አልወድም አለ፣ ቦኃላ ግን ተጸጸተና ሄደ፣ ወደ ሁለተኛውም ቀርቦ እንዲሁ አለው እርሱም መልሶ እሺ ጌታየ አለ፣ ነገር ግን አልሄደም፣ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ ያደረገ ማን ነው? ፊተኛው አሉት፣ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፣ እውነት እውነት እላችዋለሁ ቀራጮችና ጋለሞቶች ወደ እግዚአብሄር መንግሥት በመግባት ይቀድሟችዋል፣ ዮሐንስ በጽድቅ መንገድ መጥቶላችሁ ነበርና፣ አላመናችሁበትም፣ ቀራጮችና ጋለሞቶች ግን አመኑበት እናንተም ይህን አይታችሁ ታምኑበት ዘንድ ቦኃላ ንሠሀ አልገባችሁም" አላቸው (ማቴዎስ 21፡28~32) ኢየሱስ እዚህ ጋ ከካህናት አለቆችና በዘመኑ ከነበሩት ሽማግሌዎች ጋር ይነጋገር ነበር፣ በሌላ አነጋገር ኃይማነተኞች ሰዎች ነበሩ፣ እነሱ ግን በኃይማኖት ስህተት ውስጥ ነበሩ፣ ኢየሱስ ንሠሀ

መግባት እንደሚያስፈልጋቸው እየነገራቸው ነው፡፡ ከዚያም ንሠሀ መግባት ምን ማለት እንደሆነ ገልጿል፣ ንሠሀ የገባ ሰው አልፈልግም ብሎ ግን ሀሳቡን ቀይሮ እሠራለሁ ብሎ የወሰነው ነው ብሏል፡፡ ሌላው ልጅ ሄጄ እሰራለሁ ብሏል ግን አልሄደም፣ ክርስቶስ የትኛው ልጅ የአባቱን ፈቃድ እንዳደረገ አድማጮቹን ጠየቀ፣ የመጀመሪያው አልሄድም ያለው ከዚያ በኃላ መሄድን መረጠ አሉ፣ ጌታ የዚያን ቀን ቀራጮችና ጋለሞቶች ካህናትና ሽማግሌዎች ስላልፈቀዱ በጊዜው በነበሩት የኃይማኖት ሰዎች ፊት ወደ እግዚአብሄር መንግሥት እንደሚገቡ ተናግሯል

ነገር ግን ንሠሀ ለምን አስፈለገ? ምክንያቱም ዓለም በክፉ የተሞላች፣ በኃጥያት፣ በሥርዓት አልበኝነት፣ በሥጋ ሥራ የረከሰች ናትና፡፡ የእያንዳንዱ ኃጥያት ጥፋት ነው፣ ጳውሎስ ሲናገር “የኃጥያት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሄር የጸጋ ሥጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ህይወት ነው” (ሮሜ 6፡23) እንደገና “አትሳቱ እግዚአብሄር አይዘበትበትም ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ያጭዳልና፣ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ህይወት ያጭዳል፣ “ ይላል (ገላቲያ 6፡ 7~8)

እንግዲህ ኃጥያት አጥፊ ከሆነ ንሠሀ መግባት ያለባቸው እነማን ናቸው? ንሠሀ መግባት ያለባቸው ለኃጥያቱ ተጠያቂ የሚሆኑት ናቸው ፣ እነዚህም መልካምና ክፉን የለዩ እና ኃጥያተኛ የሆኑ የሠሩ ሰዎች ናቸው፣(ሮሜ 3፡23)፣ እነዚህ የእግዚአብሄርን ህግ የጣሱ የተላለፉ ወይም ለእግዚአብሄር ፈቃድ ታዛዥ ያልሆኑ ናቸው፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን ዓለም በጣም ክፉ ሆነ፣ እግዚአብሄር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ፣ ይህም ማለት ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ ክፉ ስለሆኑ፣ እግዚአብሄር ጻድቅ የሆነውን ኖህን ለሰዎች ንሠሀን እንዲሰብክ እና ንሠሀ ካልገቡ በታላቅ የጥፋት ውኃ እንደሚጠፉ ያስጠንቅቃቸው ዘንድ ላከው፡፡ ቢያዳምጡ ኖሮ ከክፋታቸውም ቢመለሱ በዳኑ ነበር፣ እነርሱ ግን አልሰሙም፣ በዚህም ምክንያት ከኖህና ከሚስቱ ከሦስቱ ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው በቀር ሁሉም በጥፋት ውኃ ጠፉ፡፡(ዘፍጥረት 6_8)

ምናልባት የዮናስን ታሪክክ ታስታውስ ይሆናል ፣ እንዲህ ይላል “የእግዚአብሄርም ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ ፣ ተነስተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነኔዌ ሂድ፣ ክፋታቸውም ወደ ፊቴ ወጥቷልና በእርሷ ላይ ስበክ፡፡ ዮናስ ግን ከእግዚአብሄር ፊት ወደ ቴርሰስ ይኮበልል ዘንድ ተነሣ ወደ ኢዮጴም ወረደ፣ ወደ ቴርሰስም የምታልፍ መርከብ አገኘ፡፡ ከእግዚአብሄርም ፊት ኮብልሎ ከእነርሱ ጋር ወደ ቴርሰስ ይሄድ ዘንድ ዋጋ ሰጥቶ ወደ እርሱዋ ገባ” (ዮናስ 1፡1~3) መዝገቡ በመቀጠል በባህሩ ላይ አውሎ ነፋስ እንዴት እንደሆነ ይነግረናል፣ መርከበኞቹም ለዚህ ተጠያቂው ዮናስ መሆኑን

ሲወስኑ ወስደው ወደ ባህር ጣሉጥ እግዚአብሄርም አንድ ትልቅ ዓሣ አዘጋጀ በዓሣውም ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ተቀመጠ፣ እግዚአብሄርም ዓሣውን ዮናስን በደረቅ ምድር ላይ እንዲተፋው አደረገው ፣ ሲነበብ ዘገባው እንዲህ ይላል "የእግዚአብሄርም ቃል ሁለተኛ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ፦ ተነስተህ ወደዚያቺ ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነኔዌ ሂድ፣ የምነግርህንም ስብከት ስበካት አለው፡፡ ዮናስም ተነስቶ እንደእግዚአብሄር ቃል ወደ ነኔዌ ሄደ፣ ነኔዌም የሦስት ቀን መንገድ ያህል እጅግ ታላቅ ከተማ ነበረች፣ ዮናስም የአንድ ቀን መንገድ ያህል ወደ ከተማዩቱ ውስጥ ሊገባ ጀመረ፣ ጮኾም፦ በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች" አለ፡፡፣ የነነዌም ሰዎች እግዚአብሄርን አመኑ፣ ለጾም አዋጅ ነገሩ፣ ከታላቁም ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ማቅ ለበሱ ወሬውም ወደ ነነዌ ንጉስ ደረሰ እርሱም ከዙፋኑ ተነስቶ መጎናጸፊያውን አወለቀ ማቅም ለበሰ ፣ በአመድም ላይ ተቀመጠ አዋጅም አስነገረ በነነዌም ውስጥየንጉሱንናየመኳንንቱን ትዕዛዝ አሳወጀእንዲህምአለ፦ሰዎችና እንስሳት ላሞችም በጎች አንዳችን አይቅመሱ፣ አይሰማሩም፣ ውኃንም አይጠጡ ሰዎችና እንስሶችም በማቅ ይከደኑ ወደ እግዚአብሄርም በብርቱ ይጩሁ ሰዎችም ሁሉ ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ይመለሱ፣ እኛ እንድንጠፋ እግዚአብሄር ተመልሶ ይጸጸት እንደሆነ ከጽኑ ቁጣውም ይመለስ እንደሆነ ማን ያውቃል? እግዚአብሄርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፣ እግዚአብሄርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም" (ዮናስ 3፡1~10) ዮናስ ከጌታ ለመሸሽና የተሰጠውን ኃላፊነት ፣ በኃላ ላይ ደጋግሞ እንደተናገረ እና ለክፉዋ ነነዌ ለመስበክ በሄደ ጊዜ ታላቂቱ ከተማ ንሠሀ ገብታ ከኃጥያቷ ተመለሰች፣ ነነዌን ስለማጥፋት እና በዚህም ምክንያት ከተማዩቱ ንሠሀ ለመግባት ፈቃደኛ ስለነበረች ከጥፋቱ ተረፈች፣ የእግዚአብሄር ቃል ሲታወጅ እና ንሠሀ ሲገባ፣ ይህም እግዚአብሄር ለሚመለከቷቸው ሁሉ ለሚታዘዙት ሁሉ ሊራራላቸው ፈቃደኛ መሆኑን ያሣያል፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ እግዚአብሄር ከክፋት እንዲርቁ እና እንደፈቃዱ እንዲሄዱ እስራኤልን ደጋግሞ ይማጸን ነበር፣ ይህን ካደረጉ እርሱ አምላካቸው እንደሚሆንላቸው ውጊያቸውንም እንደሚዋጋላቸው እናእንደሌሎች ሰዎች በላይ እንደሚባርካቸው ቃል ነበራቸው፣ እስራኤል ግን መንገዳቸውን፣ በኡሪያቸው ያሉትን አማልክት ተቀብለው በክፍታ ጎዳና መሄዳቸውን ቀጠሉ፣ በዚህም ምክንያት እግዚአብሄር ቀጣቸው ጠላቶቻቸውም ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲማርኳቸው ፈቀደላቸው፣ ይህ ሁሉ የባሪነት ውጤት ንሠሀ ያለመግባት ውጤት ነው፣ አንድ ብልህ ሰው እንዲህ ብሏል "ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች፣ ኃጥያት ግን ሕዝብን ታስነውራለች" ይላል (ምሳሌ 14፡34)

በማቴዎስ 3፡1~3 ላይ መጥመቁ ዮሐንስ እየሰበከ እንደመጣ እናነባለን “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሠሀ ግቡ” ይል ነበር። ክርስቶስ በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች ንሠሀ ካልገቡ እንደሚጠፉ ገልጿል (ሉቃስ 13፡3) ጴጥሮስና ሐዋሪያት በኢየሩሳሌም ከተማ በጴንጤቆስጤ ዕለት ለብዙ ታዳሚዎች ሲሰብኩ፣ ከነዚህም አንዳንዶቹ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ሲሰቀል ተካፍለዋል፣ ዳሩ ግን ስለኃጥያታቸው በሰሙ ጊዜ በሰሙትም ስብከት ልባቸው ተነካ፣ ከዚያም አማኞች ሊሆኑ፣ የቻሉት ምን ማድረግ እንዳለባቸውም ለማወቅ ፈልገው በጠየቁ ጊዜ ነው “ጴጥሮስም፡ ንሠሀ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ” አላቸው፣ (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38) ያም ማለት ከኃጥያታቸው እንዲመለሱ ወይም ኃጥያት መሥራትን ለማቆም ንሠሀ አስፈላጊ ነበር፣ ለኃጥያታቸው ይቅርታ ከፈለጉ ንሠሀ ከመስፈርቶቹ አንዱ ነው ማለት ነው፣ ይሁን እንጂ ንሠሀ መግባት ብቻ ሊያድን አይችልም፣ ንሠሀ አንዱ መስፈርት ይሆንና፣ ማመን ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መመስከር እና መጠመቅን ከፈጸሙ በኃላ ወደ ትክክለኛው መዳን ይመጣሉ ማለት ነው (የሐዋሪያት ሥራ 2፡37፣ 38፣ የሐዋሪያት ሥራ 8፡36~39)

በሐዋሪያት ሥራ 17፡30 “እንግዲህ እግዚአብሄር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንሠሀ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል” ይላል በአንድ ወቅት እግዚአብሄር አንዳንድ ነገሮችን ችላ ብሎ ወይም አንዳንድ ነገሮችን ታግሶ ሊሆን ይችላል እያለ ነው፣ አሁን ግን እግዚአብሄር በሁሉም ቦታ ያሉ ሰዎች ሁሉ ንሠሀ እንዲገቡ አዟል። በሐዋሪያት ሥራ 17፡31፣ ሁሉም ከሙታን በተነሣው በእርሱ የሚፈረድበት ቀን ይመጣል ይላል። ስለዚህ እርሱን ለመገናኘት ንሠሀ መግባት አለብን፣ ወይም ከኃጥያታችን መራቅ አለብን፣ በዚህ ዓለም እና በሚመጣው ዓለም እንድንድን ጌታ ከእኛ የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ አለብን።

ነገር ግን የሚወድቅ ወይም ኃጥያት የሚሠራ ክርስቲያንስ ? ይህም ኃጥያት የጌታን ፊት ከእሱ ሰውሯል ማለት ነው (1ኛ ጴጥሮስ 3፡12) ኃጥያት የሚወገድበት ወይም የሚሰረይበት ብቸኛው መንገድ ስህተት የሠራው በኃጥያቱ ተፀፅቶ ስህተቱን ሲናዘዝ እና አባቱን ይቅርታ ሲጠይቅ ብቻ ነው፣ (የሐዋሪያት ሥራ 8፡14~25፣ ያዕቆብ 5፡16)

አሁን አንተስ? ንሠሀ ገብተሃል ወይስ ወደ ኃጥያትህ ተመለስክ? ይህ ለአንተ ፊላጎት መሆኑን ተገንዘብ በክርስቶስ አምነህ፣ እግዚአብሄርን ስትታዘዝ ከኃጥያትህ ንሠሀ ገብተህ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደህነ ስትመሰክር ኃጥያትህንም ልትታጠብ ስትጠመቅ መልካምና እግዚአብሄርን የምትፈራ ህይወት ስትኖር የተለወጠ ሰው ትሆናለሕ

ህይወትህ የተሻለ፣ የበለጸገ እና ደስተኛ ይሆናል፣ ይህንን ስታደርግ በዙሪያህ ያሉ ነገሮች በተሻለ ሁኔታ መለወጥ ይጀምራሉ፣ እስቲ ሞክርና እንደማይሠራ ተመልከት ።

## ትምህርት 10
## ለምንድነው የምንጠመቀው

ጥምቀት የመጽሐፍ ቅዱስ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ፣ ዓላማውና የእሱን አስፈላጊነት ለማወቅ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መሄድ አለብን።

ወደ ቅዱሣት መጽሐፍት ስንሄድ በመጀመሪያ ዮሐንስ የሚባል ሰው ሊያጠምቅ እንደወጣ እናነባለን። ዮሐንስ ብዙዎችን አጥምቋል። ስሙም መጥመቁ ዮሐንስ ወይም አጥማቂው ዮሐንስ ተብሎ ይጠራ ነበር። በማቴዎስ 3፡1 እንዲህ እናነባለን "በዚያም ወራት መጥመቁ ዮሐንስ፣ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሠሀ ግቡ ብሎ በይሁዳ በምድረ በዳ እየሰበከ መጣ፣ በነቢዩ በኢሳያስ ፦ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና። ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው፣ በወገቡም ጥፍር ይታጠቅ ነበር፣ ምግቡም አንበጣና የበረሀ ማር ነበረ። ያን ጊዜ በኢየሩሣሌም ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፣ ኃጥያታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር" (ማቴዎስ 3፡1~6)፣ እንደገናም "ዮሐንስም ደግሞ በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና ያጠምቅ ነበር፣ እየመጡም ይጠመቁ ነበር" (ዮሐንስ 3፡23)

ጥናታችንን ስንቀጥል ዮሐንስ ክርስቶስን እንዳጠመቀ እናነባለን "ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ዮሐንስ ግን ፤ እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህ? ብሎ ይከለክለው ነበር፣ ኢየሱስም መልሶ፣ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው። ያን ጊዜ ፈቀደለት፣ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኃላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ፣ የእግዚአብሄርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፣ እነሆም፣ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" (ማቴዎስ 3፡13~17)

አሁንስ የዮሐንስ ጥምቀት ምን ትርጉም አለው? የጌታን መንገድ እንዲያዘጋጅ የተላከው የክርስቶስ ቀዳሚ ዮሐንስ ነበር። በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች ጥምቀትን የማስተዋወቅ ሥራ ተሰጥቶት ክርስቶስና ሐዋሪያት አብረው ቀርበው ጥምቀትን እንዲያስተምሩ አመቻችቶላቸዋል። ነገር ግን ዮሐንስ የሰበከው ጥምቀት በንሠሀ የተሰበከ፣ በውኃ ውስጥ የተጠመቀ እና ለኃጥያት ሥርየት የሆነች ናጥ

በክርስቶስስምአልተጿረገም፤የመንፈስቅዱስንምተስፋአልተሸከመም፤ ስለዚህ ጳውሎስ በኤፌሶን በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁ ነገር ግን ስለ መንፈስ ቅዱስ ምንም የማያውቁ ሰዎች በኤፌሶን ባገኛቸው ጊዜ ክርስቶስ የሚፈልገውን እውነት ካስተማሩ በኋላ በክርስቶስ ስም ተጠመቁ። (የሐዋሪያት ሥራ 19፡1~5) ያም ማለት የዮሐንስ ጥምቀት እስከ ክርስቶስ ሞት ድረስ ዘልቋል። ከዚያም ክርስቶስ ባስተማረው ጥምቀት ተተካ።

ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ወደ ሰማይም ከማረጉ በፊት ለሐዋሪያቱ እንዲህ ብሎ ነበር "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ ያመነ የተጠመቀ ሁሉ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈርድበታል" አላቸው (ማርቆስ 16፡15~16)፤ እንዲሁም ታላቁ ትዕዛዝ እንዲህ አላቸው ይለናል ማቴዎስ "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃቸዋቸሁ ያዘዝኋቸሁንም ሁሉ እያስተማራቸሁአቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" አላቸው (ማቴዎስ 28፡19~20)፤ እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ "ታላቁ ትዕዛዝ" ትብለው ይጠራሉ። እነዚህ ትዕዛዞች ዓላማቸው ወንጌልን ወደ ዓለም ማድረስ ነው፤ የክርስቶስን የምሥራች ወደ ዓለም ማድረስ፤ ይህም የምሥራች የክርስቶስ ሞት መቀበር እና ትንሣኤ ነው፤ በዚህም ላይ ሰው አምኖ ንሠሀ ገብቶ በመጠመቅ መዳን እንዳለበት ይሰበካል፤ ከዚህ ውጪ ሌላ የመዳን መንገድ የለምና። አስታውስ ክርስቶስ የተናገረውን "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ 16፡16)

እንግዲህ ጥምቀት አንዱ የመዳን ሁኔታ ነው፤ በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡21፤ ጥምቀት ያድናል፤ ጥምቀት የመጨረሻው የመዳን ውሳኔ የሚፈጸምበት ሁኔታ ነው።

የሐዋሪያት ሥራን ስናነብ ሰዎች ጌታን የታዘዙበትን ደጋግመን እናስተውላለን። በየትኛውም ሁኔታ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል ሰምተው አምነው እንደተጠመቁ በቀጥታ ይናገራል። በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ጌታን የሚታዘዙት ደግሞ ከኃጥያታቸው ንሠሀ እንደገቡ እና ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከራቸውን ይገልጻል፤ ይህንን በተመለከተ በሰፊው ለመረዳት የሐዋሪያት ሥራ 2ን ማንበብ ይቻላል፤ ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋሪያት እንዴት ለሰዎች ሁሉ ወንጌልን እንደሰበኩ እና ሰዎቹ የእግዚአብሄርን እውነት ከሰሙ በኋላ ጌታን እንደ ታዘዙ እንመለከታለን፤ ከዚያም " እድን ዘንድ ምን ማድረግ አለብኝ?" የሚለው ጥያቄ ከቀረበ በኋላ (የሐዋሪያት ሥራ 16፡31) እናነባለን፤ ጳውሎስና ሲላስ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንዳለበት በዚያ ለነበረው የእስር ቤት ጠባቂ ነገሩት፤ ነገር ግን ይህ ሰው በእርሱ ለማመን ስለክርስቶስ አላወቀም ነበር፤ መፍትሄው እርሱንና ቤተሰቡን መስበክ

ነበር፣ ይህም በሆነ ጊዜ በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ፣ በመቀጠል በሐዋሪያት *ሥራ* 2፡38፣ ላይ ሰዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ እንደፈለጉ እናነባለን ፣ ንሠሀ እንዲገቡ ለኃጥያታቸው ሥርየት እንዲጠመቁ በዚያውም የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ እንደሚቀበሉ ተነግሯቸዋል፣ (የሐዋሪያት *ሥራ* 2፡38) እናም እነዚህ ሰዎች አምነው ወንጌልን ታዘዋል። ቀጥሎ በሐዋሪያት *ሥራ* 8፡29~39፣ የኢትዮጵያን ሰው ታሪክ እናገኛለን፣ ዘገባው ፊሊጶስ ክርስቶስን እንዴት እንደገለጸለት ይነግረናል። ሰውዬውም ለመጠመቅ ፈለገ፣ ፊሊጶስ በፊጹም ልቡ ካመነ ማድረግ እንደሚቻል ገለጸለት እንዲህ ይላል "ፊሊጶስም በፊጹም ልብህ ብታምን፣ ተፈቅዶልሃል አለው፣ መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" (የሐዋሪያት *ሥራ* 8፡37) ፊሊጶስም ወደ ውኃ ውስጥ ወሰደው አጠመቀውም፣ እና በመጨረሻም በሐዋሪያት *ሥራ* ውስጥ ባሉት የንሠሀ ጉዳዮች በሁሉም ሁኔታዎች ጌታን ለመታዘዝ የፈለጉ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች መጠመቃቸውን ይገልጻል፣ በሐዋሪያት *ሥራ* 2፡38፣ ላይ ሰዎች የተነገራቸውን እናነባለን "ጴጥሮስም፣ ንሠሀ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ትቀበላላችሁ" አለ (የሐዋሪያት *ሥራ* 2፡38) በሐዋሪያት *ሥራ* 8 ላይ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በፊሊጶስ መጠመቁን፣ በሐዋሪያት *ሥራ* መቶ አለቃ ቆርኔለዎስና ቤተሰቡ መጠመቃቸውን፣ በሐዋሪያት *ሥራ* 9 እና 22 ላይ ቅዱሣት መጽሀፍት የሚነግሩን ሳኦል እንዴት ወንጌልን እንደታዘዘ እንዴት ተነስቶ ኃጥያቱ እንዲታጠብለት መጠመቅ እንዳለበት እንደተነገረውና እሱም አድርጎት እንደታጠበለት እናነባለን፣ በሐዋሪያት *ሥራ* 16 ላይ በሌሊት ድቅድቅ ጨለማ ይወይኒ ቤት ጠባቂውና ቤተሰቡ መጠመቃቸውን እውነተኛ ዘገባዎቹ ያረጋግጡልናል።

በጳውሎስ የተነገረን ጥምቀት በመቀበር መሆኑን ነው "በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፣ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሄር አሠራር በማናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ" (ቆላስያስ 2፡12) በሮሜ 6፡3 ላይ በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅን እናነባለን፣ ፊሊጶስም ኢትዮጲያዊውን ሰው ይዞ ሊያጠምቀው ወደ ውኃ እንደወረዱ እና አጥምቆም ከውኃ ውስጥ እንደወጡ አይተናል (የሐዋሪያት *ሥራ* 8፡29~39) ጥምቀት ሰውን ወደ ክርስቶስ ይጨምራል (ሮሜ 6፡3~5፣ ገላቲያን 3፡26~27)፣ እንዲሁም ጥምቀት ሰውን ወደ ቤተክርስቲያን ይጨምራል (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ከውኃ እና ከመንፈስ መወለድ እንዳለበት ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 3፡3፣5፣ ላይ ተናግሮ እናነባለን፣ እዚያ ያለው ውኃ የሚያመለክተው ጥምቀትን ነው እናም የእግዚአብሄር መንግሥት ስለጌታ ቤተክርስቲያን ነው። በዚያን ጊዜ መንግሥቱ ወይም

ቤተክርስቲያን አልተመሠረተችም ነበር፣ ስለዚህም አንድ ሰው ሊገባ አይችልም፣ ነገር ግን ክርስቶስ በቅርቡ ስለሚሆነው ነገር እየተናገረ ነው፣ ዛሬ በእርግጥ አንድ ሰው ወደ ቤተክርስቲያን ለመግባት ከውኃ እና ከመንፈስ መወለድ አለበት ይህም የወንጌል ትዕዛዙን በመጠበቅ ለመዳን እና ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲቃሉ እንደመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይጨመራል ማለት ነው።

ለምን እንጠመቃለን? ክርስቶስ ስላዘዘን ተጠምቀናል፣ ለመዳን ወደ ክርስቶስ እና ወደ ቤተክርስቲያኑ ለመግባት ተጠምቀናል፣ የጌታ ሞት፣ መቀበርና ትንሣኤ ምልክት የሆነውን ታዛዥነታችንን ፈጸምን፣ (ሮሜ 6 ላይ ተጽፏል። ይህም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቷል እና እኛም ለኃጥያታችን መሞት አለብን፣ ክርስቶስ ተቀብሯል እኛም ለኃጥያታችን ሥርየት በውኃ ውስጥ መቀበር አለብን፣ ክርስቶስ ከመቃብር ውስጥ ተነስቶ ሲኦልን መቃብርን ድል ነስቶ እንደተነሣ እኛም ከውኃ ውስጥ ከመቃብር ተነሣን አዲስ ፍጥረትም ሆነን በአዲስ ህይወት ለመመላለስ ወይም የክርስትናን ህይወት ለመምራት ተነሣን፣ ስለዚህ ጌታን በጥምቀት በመታዘዝ በክርስቶስ ሞት መቀበርና እና ትንሣኤ እናምናለን ማለታችን ነው፣ እናም አንድ ሰው እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲጠመቅ ከክርስቶስ ጋር ሞቶ ከሱ ጋር ተቀብሮ ከእሱ ጋርም ከሞት ተነስቷል ማለት ነው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ተጠምቀሃል? ካልሆነ እነዚህን ጉዳዮች ትምህርት ማጥናትህን እንድትቀጥል እንጸልያለን፣ እናም በቅርቡ ጌታን ለመታዘዝ ውሳኔ እንደምትወስን ተስፋ አደርጋለሁ

## ትምህርት 11
## ለምን በመታዘዝ እናምናለን

መታዘዝ የሚለው ትምህርት በጣም አስፈላጊ እና ጠቃሚ ጉዳይ ነው፣ እናም ስለዚህ የትምህርት ነጥቦች በጣም እንድታስብበት ተስፋ አደርጋለሁ፣ አምናለሁም።

ብዙ ሰዎች ለሥልጣን ክብር በማይሰጡበት እና ብዙ እምብተኛነት ባለበት በዚህ ዘመን እግዚአብሄር መታዘዝን ብቻ ሳይሆን እታዘዙት ዋጋ የከፈለበትን እንዲያውቁ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጠ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ መንፈስን የሚያድስ ነው፣ በኃይማኖቱ ዓለም ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች የፈለጉትን ለማድረግ በግትርነት መንገድ በሚሄዱበት በዚህ ወቅት የሰዎችን ትምህርት ከፍ በማድረግ ባለበት ጊዜ፣ በቅዱሣት መጽሐፍት ውስጥ ያለውን አጽናኦት የሚሰጠው ቃሉን አድራጊዎች በመሆን በመኡአዝ ላይ ያለን ማየት እጅግ ያስገርማል። ወደ መንግሥተ ሰማያት በሚወደው ቀጥተኛ እና ጠባብ መንገድ ላይ በመታዘዝ ለመሄድ ነው።

እግዚአብሄር እርሱን የሚታዘዙትን እንዴት እንደባረካቸው እና እርሱን የማይታዘዙትን እንዴት እንደሚቀጣ ለማየት አሁን ከእኔ ጋር ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንሂድ፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህን በአዕምሮው ይዞ ነው ይህን የጻፈው "እንግዲህ የእግዚአብሄርን ቸረነትና ጭከና ተመልከት፣ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፣ በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሄር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፣ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ" (ሮሜ 11፡22)

በመጀመሪያ ጌታን የታዘዙትን አንዳንድ ምሣሌዎችን እንመለከታለን። በብሉይ ኪዳን ከታወቁት የታዛዢነት ምሣሌዎች አንዱ ምሣሌ ኖህ ነው፣ እግዚአብሄር ክፉዎችን በምድር ላይ ለማጥፋት የጥፋት ውኃ በላከ ጊዜ ራሱንና ቤተሰቡን ለማዳን መርከብ ሠራ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እግዚአብሄርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ፣ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ፣ እግዚአብሄርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፣ በልቡም አዘነ። እግዚአብሄርም የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፣ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ስለፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁናአለ፣ኖህግንበእግዚአብሄርፊትሞገስንአገኘ"(ዘፍጥረት 6፡5~8) መዝገቡ በመቀጠል እግዚአብሄር ኃጥያተኞችን ለማጥፋት የጥፋት ውኃ ለመላክ ያለውን ሀሳብ ለኖህ እንዴት እንደተገለጸ ያሳያል። እናም ሚስቱን ሶስቱን ወንዶች ልጆቹን እና ሚስቶቻቸውን ከተውሰኑ እንስሳት ጋር፣ ከጥፋት ውኃ ይድኑ ሊያድናቸው። ከዚያም ዘገባው ሲቀጥል "ኖህም እንዲሁ አደረገ፣ እግዚአብሄር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ" (ዘፍጥረት 6፡22) ውጤቱም ኖህ እና በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ከጥፋት ውኃ ድነዋል፣ ነገር ግን ክፉዎች እና ያልታዘዙት ሁሉ በጥፋት ውኃ ወድመዋል።

በ2ኛ ነገስት 5 ላይ ደግሞ ስለ አንድ ንዕማን ስለሚባል እናያለን "የሶሪያ ንጉስ ሠራዊት አለቃ ንዕማንም እግዚአብሄር በእርሱ እጅ ለሶሪያ ደህንነትን ስለሰጠ በጌታው ዘንድ ታላቅ ክቡር ሰው ነበረ፣ ደግሞም ጽኑዕ ኃያል ነበረ፣ ነገር ግን ለምጻም ነበረ" (2ኛ ነገስት 5፡1) አዎን ለምጻም ነበር እናም በዚህ ውስጥ እውነተኛ ችግር ነበረበት፣ ሶሪያም እስራኤልን ሊወጋ በወጣቸ ጊዜ አንዲት ታናሽ ገረድ ለንዕማን ሚስት እንዲህ አለቻት "እሜቤቷንም ጌታዬ በሰማርያ ካለው ከነቢዩ ፊት ቢደርስ ኖሮ ከለምጹ በፈወሰው ነበር አለቻት"(2ኛ ነገስት 5፡3)የሆነ ሰው ይህንን መረጃ ወደ ንዕማን ወሰደው ከዚያም ንጉሱ ከሥጦታዎች ጋር ለእስራኤል ንጉስ ደብዳቤ ሊልክለት ተስማማ። የእስራኤል ንጉስ በዚህ ተበሳጨ ፣ ምክንያቱም ሦሪያ ይህን ሰበብ አድርጎ ነው ብሎ በማሰብ ነው፣ የእግዚአብሄር ነቢይ ኤልሳዕ ግን ሰምቶ ንዕማንን እንዲልክለት ወደ እስራኤል ንጉስ ላከ። ንዕማንም ወደ በሩ መጣ፣ ኤልሳዕ ግን ሄዶ

በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ እንዲታጠብ በመልዕክተኛው ላከበት፣ ይህን ቢያደርግ ለምጹ ከሱ ይነሳል፣ ንጹህም ይሆናል አለ። ንዕማን ይህንን ሲሰማ በጣም ተናደደ፣ ኤልሳዕ ወጥቶ እሱን ባለመናገሩ እንደዚሁም ደግሞ የአምላኩን ስም ጠርቶ በለምጹ ቦታ በእጁ ነክቶ የሚፈውሰው ነበር የመሰለው እንጂ በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ማለት የዚህ የዚህ ብዙ ወንዞች አሉ አይደለም፣ በማለት ተበሳጨ ቦኋላ አጠገቡ ያሉት ለምን እንዲህ ትበሳጫለህ ነቢዩኮ ትልቅ ነገር አላዘዘህም ለምን ሂደህ አትሞክረውም በማለት አሳመኑት እሱም ካሰበበት ቦኋላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄዶ እንደተባለው ወንዝ ውስጥ ገብቶ አንድ ጊዜ ትልቅ አለ፣ ሁለት ጊዜ፣ ሦስት ጊዜ እያለ እስከ 6 ጥልቅ አለ ለምጹ አልነጻም መጨረሻ ላይ ሰባተኛውን ጥልቅ ብሎ ሲወጣ ለምጹ ከሱ ላይ ተወግዶ ንጹህ ሆነ፣ ዘገባው ሲናገር "የእግዚአብሄርም ሰው እንደተናገረው በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ አለ፣ *ሥጋውም እንደገና እንደትንሽ ብላቴና ሥጋ ሆኖ* ተመለሰ ንጹህም ሆነ" (2ኛ ነገስት 5፡14) አሁን ንዕማንን ማን ፈወሰው? እግዚአብሄር ፈወሰው፣ ይህም የእግዚአብሄርን ነቢይ የኤልሳዕን መመሪያ ስለተከተለ ተፈወሰ፣ ባይከተል እና ያንን መመሪያ ባይታዘዝ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? አይፈወስም ነበር፣ ስለዚህ የመታዘዝ እና የአለመታዘዝ ውጤት መዳን እና ያለመዳንን ያተርፍልናል።

የእግዚአብሄርን በረከቶች ተከትለው የታዘዙት ታዛዥነት በነበረበት ጊዜ ሌሎች በርካታ ምሣሌዎችን ልንጠቅስ እንችላለን። ነገር ግን እግዚአብሄርን ያልታዘዙ ግለሰቦች እንዴት እንደተቀጡ የሚያሳዩ ምሣሌዎች አሉ። አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ነገር የእባቡን ቃል ሰምተው የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ስለተላለፉ አልተቀጡም ? ከእነሱ መተላለፍ የሥጋ ሞት ለሰው ልጅ ሁሉ ተረፈ፣ እና በሥጋም በመንፈስም ሞት ተቀጡ፣ (ዘፍጥረት 3) እግዚአብሄር በ1ኛ ሳሙኤል 15 ላይ በሳሙኤል በኩል ለሳኦል ለእስራእል ንጉስ ትዕዛዝን ሰጠ፣ ይህም አማሌቃዊያንን እንዲዋጋ ነበር፣ እንዲያጥፋቸው ነበር፣ እስቲ እናንብብ " ነገር ግን ሳኦልና ህዝቡ ለአጋግ፣ ለተመረጡትም በጎችና በሬዎች ለሰቡትም ጥጆችና ጠቦቶች፣ ለመልካሞቹም ሁሉ ራሩላቸው፣ ፈጽሞ ሊያጠፏቸውም አልወደዱም፣ ነገር ግን ምናምንቴንና የተናቀውን ሁሉ ፈጽመው አጠፉት" (1ኛ ሳሙኤል 15፡9) ከዚያ ወደ ቤታቸው ሄዱ፣ ዘገባው ቦኋላ የሆነውን ሲናገር "ሳሙኤልም ወደ ሳኦል መጣ፣ ሳኦልም፣ አንተ ለእግዚአብሄር የተባረክህ ሁን የእግዚአብሄርን ትእዛዝ ፈጽሜአለሁ አለው፣ ሳሙኤልም፣ ይህ በጆሮዬ የምሰማው የበጎች ጩኸትና የበሬዎች ግሣት ምንድነው? አለ" (1ኛ ሳሙኤል 15፡13~14) ሳኦል መግለጽ ጀመረ ሕዝቡ ለእግዚአብሄር ለመስዋዕት ያቀርቡ ዘንድ መልካሙን በጎችና ብሬዎች እንዳስቀሩ ገለፀ፣ ውይይታቸው ቦኋላ እንዲህ ይላል " ሳሙኤልም፦ በውኑ የእግዚአብሄርን ቃል በመስማት

ደስ እንደሚለው እግዚአብሄር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመስዋዕት ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል" አለው (1ኛ ሳሙኤል 15፡22) ከዚያም ሳኦል ኃጥያቱን ተናዘዘ ፣ ቢሆንም በጣም ዘግይቷል፣ ባለመታዘዙ ምክንያት ሳኦል በእስራኤል ላይ ንጉስ ሆኖ አልቀጠለም፣ ተጣለ። ጌታን ቢታዘዝ ቀላል ይሆንለት ነበር፣ የሚያሳዝነው ይህን አለመገንዘቡ ነበር። ሰዎች በጌታ ላይ ባመጹ ጊዜ ውጤቱን መቀበል ነበረባቸው። እኛም እንደምናደርገው ሁሉ፣ ጳውሎስ ወደ ብሉይ ኪዳን ይመልሰንና እግዚአብሄር በዚያን ጊዜ ከነበሩት ሰዎች ጋር እንዴት እንደያዛቸው አንዳንድ ምሣሌዎቸን ይሰጣል፣ እንዲህ ይላል፣ "በመጽናና መጽሐፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎልና" (ሮሜ 15፡4) በእርግጥም ከእነዚህ የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ብዙ ትምህርትን ልንማር ይገባናል።

ወደ ክርስቶስ ራሱ ስንመጣ ሰለርሱ እንዲህ እናነባለን "ምንም ልጅ ቢሆን፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፣ ከተፈጸመም በኃላ በእግዚአብሄርእንደመልከጼዴቅሹመትሊቀካህናትተብሎስለተጠራ፣ ለሚታዘዙት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው" (ዕብራዊያን 5፡8~9) ክርስቶስ በነገር ሁሉ እግዚአብሄርን እንደ ታዘዘ እንዲሁ ከእኛና ከሰዎች ሁሉ መታዘዝን እፈልጋል፣ በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ እና በአዲስ ኪዳን እንደተዘገበው የክርስቶስን ህይወት አንብብ፣ እና ጌታ እንዴት ወደ እርሱ ከሚመጡት ሰዎች ላይ መታዘዝን እንደሚፈልግ ተመልከጥ ይህ በእርሱ ላይ ያላቸውን እምነት፣ ትህትናን፣ የሚፈትኑበት መንገድ ነው፣ ጌታ እሱን መታዘዝ ላልፈለጉት በረከቱን ሲሰጥ የሚገልፅ አንድም ጽሁፍ ወይም ምሣሌ አናገኝም።

ክርስቶስ ሲናገር "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማይ የሚገባ አይደለም" ብሏል (ማቴዎስ 7፡21) እንደገናም "ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል" ይላል (ማቴዎስ 7፡24) ያዕቆብም "ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳቸሁን እያሳታቸሁ የምጸሙ ብቻ አትሁኑ" ይላል (ያዕቆብ 1፡22) ጴጥሮስም "ለእውነት እየታዘዛቸሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማቾ መዋደድ ነፍሳቸሁን አንጽታቸሁ እርስ በእርሳቸሁ ከልባቸሁ አጥቃቸሁ ተዋደዱ" (1ኛ ጴጥሮስ 1፡22)፣ በ2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7~9፣ ላይ ጳውሎስ ሲናገር ወንጌልን ካልታዘዙ የጌታ በቀል እንደሚሆን ይናገራል፤፤ ክርስቶስ እስከመጨረሻ በታማኝት ከታዘዝን የህይወት አክሊልን እንደምናገኝ ተናግሯል (ራዕይ 2፡10፣ ዮሐንስ ራዕይ 22፡14)

ሰዎች የጠፉበት ምክንያት ጌታን ላለመታዘዝ ስለመረጡ ብቻ ነው። ሰው ራሱን ማዳን አይችልም እንዲሁም ነገሮችን በራሱ

መንገድ በማድረግ በታይማኖትም ቢሆን መዳን አይችልም ፣ አንድ ሰው እንዲፈለገው አምኖ፣ የአንዳንድ ሰው ሰራሽ ቤተክርስቲያን አባል መሆን፣ የሰውችን ስም የለበሰውን ቤተጸሎት በራሱ መንገድ ማምለክ ይችላል ነገር ግን መዳን ካለበት በዚያ መንገድ ወደ ሰማይ ሊሄድ አይችልም፣ ጌታ እንዲሠራ የሚፈልገውን ማድረግ አለበጥ ከዚህ ውጪ ምንም የመዳን ሌላ አቋራጭ መንገድ የለም።

ጌታን ታዘሃል? እሱን ትታዘዛለህ? ክርስቶስ ሲናገር “እንግዲህ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል” (ማርቆስ 16፡15~16) ከአዲስ ኪዳን የሐዋሪያ ሥራ መጽሐፍ ብታነብ ንሠሀ በገቡ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ ነገር ሲያደርጉ ታያለህ  ሁሉም ወንጌልን ሰምተዋል፣ በክርስቶስ አመኑ፣ ከኃጥያታቸው ንሠሀ ገቡ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ሊጅ እንደሆነ መሰከሩ፣ ለኃጥያታቸውም ስርየት ተጠመቁ። ያን ባደረጉ ጊዜ ጌታ አዳናቸው፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ጨመራቸው፣ እነሱ የተለዩ አልነበሩም እንደ አንተው ነበሩ፣ ስለዚህ እንድትወስን አበረታታሃለሁ፣

## ትምህርት 12

## ለምን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ሆንን

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል እክሊሺያ ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ይህም “የተጠሩት” ማለትን ይወክላል። በዚህ ሁኔታ ክርስቶስ እርሱን እንድከተሉት ሰዎችን ከዓለም ጠራቸው፣ ክርስቶስ ስለደቀመዛሙርቱ ሲናገር “ እኔ ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፣ እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው” (ዮሐንስ 17፡14)፣ ክርስቶስ ታስሮ በነበረበት ጊዜ  ቦኃላ ለፍርድ ሊቀርብና ሊሰቀል ባለበት ሰዓት በአጠገቡ ለተሰበሰቡት እንዲህ አለ “ኢየሱስም መልሶ፣ መንግሥተ ከዚህ ዓለም አይደለችም፣ መንግሥቴስ ከዚህ ብትሆን፣ ለአይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፣ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም” አላቸው (ዮሐንስ 18፡36) ክርስቶስ መንግሥቴ የሚላት ቤተክርስቲያንን ይወክላል፣ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ አልተመሰረተችም ነበርና (ማቴዎስ 3፡1)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው ቤተክርስቲያን በአጥቢያነት ተነግሯል፣ እንደ ቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡2)፣ የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን (1ኛ ተሰሎንቄ 1፡1) እንዲሁም ብዙ ሌሎች ወዘተ ከዚያም በዓለም አቀፍ ደረጃ ይነገራል። በዚህ ሁኔታ እነዚህ ሁሉ አጥቢያ አቢያተ ክርስቲያናት ወይም ጉባኤዎች አንድ ላይ ሆነው አንዲት ቤተክርስቲያን፣ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን (ማቴዎስ 16፡18፣ ሮሜ 16፡16) ይባላሉ፣ በእርግጥም በአጥቢያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቤተክርስቲያን ናቸው ማለት ነው። የክርስቶስም ስለሆነች

የክርስቶስን ስም ትለብሳለች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ትባላለች

እንደ ቅዱሣት መጽሐፍት አገላለጽ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሄር መንግሥት (ሉቃስ 21፡31)፣ የክርስቶስ መንግሥት (ኤፌሶን 5፡5)፣ የሰማይ መንግሥት (ማቴዎስ 5፡19)፣ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን (ሐዋሪያት ሥራ 20፡28)፣ የክርስቶስ አብያተክርስቲያናት (ሮሜ 16፡16)፣ የክርስቶስ አካል (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡27)፣ የእግዚአብሄር ማደሪያ ቤት (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡15) እና ወዘተ። የጌታ ቃል ከዚህም ውጪ ቤተክርስቲያንን ሲናገር የጌታ ሙሽራ (ዮሐንስ 3፡29)፣ የበጎቹ በረት (ዮሐንስ 10፡1~18)፣ የወይን ግንድ ቅርንጫፍ (ዮሐንስ 15፡1~8)፤ በሌላ መንገድ የክርስቶስ አካል መንፈሳዊ አካል (1 ኛ ቆሮንቶስ 12)፣ የክርስቲያኖች (ሐዋሪያት ሥራ 11፡26)፣እንዲሁም የዳኑት ሰዎች ስብስብ (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47) ተብለዋል።

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ማንበብ የምትችለው ብቸኛዋ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነጭ ብዙ አስመስሎዎች አሉ ሁሉም ሰው ሰራሽ ናቸው፣ ነገር ግን አንዷት እውነተኛ ቤተክርስቲያን አለች።

አሁን እኔ እና ወንድሞቼ ለምን ከሌላ ቤተክርስቲያን ይልቅ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት እንደሆንን ልነግርህ እፈልጋለሁኝ

በትንቢት ስለተነገረ እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ነን። ኢሳያስ ጌታ መንግሥቱን ወይም ቤቱን በኢየሩሣሌም እንደሚመሰርት (ኢሳያስ 2፡1~3) ኢዩኤል በኃይል እንደሚመጣ ተናግሯል (ኢዩኤል 2፡28~29)፣ ዳንኤል ፈጽሞ እንደማይፈርስ ነገር ግን ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖር ተናግሯል (ዳንኤል 2፡44)። እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች የተፈጸሙት በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ መፈጸማቸውን ቅዱሣት መጽሐፍት ያረጋግጣሉ።

እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ነን ምክንያቱም ክርስቶስ እንደሚሠራት ቃል ገብቷል፣ ክርስቶስ በዚያን ጊዜ በነበሩት ሰዎች በህይወት እያሉ በኃይል እንደሚመጣ ተናግሯል (ማርቆስ 9፡1) እንደገና ሐዋሪያት ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ ብለው ከመሰከሩ ቦኃላ እንዲህ ሲል መለሰላቸው "እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ፣ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆች አይችሏትም" አለ (ማቴዎስ 16፡18) ቤተክርስቲያን ገና አልተቋቋም ነበር ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ ቦኃላ ሊመሰረት ነው፣ አንድ ሰው የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ቢፈልግ ክርስቶስ እሠራለሁ ካለው ከአንዲት ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ቤተክርስቲያን የተሻለች ወይም የምትበልጥ እንዴት ማግኘት ይችላል?

እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ነን ምክንያቱም ፣ እሷ በ 33 ዓ/ም በኢየሩሳሌም ከተማ ስለተመሰረተች፣ በትንቢት የተነገረውና ክርስቶስ በራሱ የገባው ቃል መሠረት ነው። ቀኑ የአይሁድ በዓል በሆነው በጴንጤቆስጤ ቀን ነበር፣ አይሁዶች ከሁሉም የዓለም ክፍሎች

በተሰበሰቡበት፣ጌታ ቤተክርስቲያኑን የሚመሰርትበት ቀን አድርጎ መረጠ፣ በዚህቸም ቀን ነበር ሐዋሪያት በሌላ ቋንቋ እንዲናገሩና የእግዚአብሄር ሰዎች መሆናቸውን ለማሳመን ተአምራትን እንዲያደርጉ በሐዋሪያት ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፣ ከዚያም ክርስቶስን ሰበኩላቸው ቦኃላ 3000 የሚያህሉት ነፍሣት በክርስቶስ በማመን፣ ንሠሀ በመግባት፣ ክርስቶስን መስክረው በመጠመቅ የኃጥያትን ሥርየት አግኝተው የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታን ተቀበሉ ጌታንም ታዘዙ፡፡ዘገባው በመቀጠል ጌታ የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያኑ ጨመረ፡፡ ይህ ሁሉ በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ ተጽፏል፡፡ ይህም እውነት ከሆነ በኢየሩሳሌም ያልነበረቸ በ33 ዓ/ም የተመሰረተቸ ናት፣ የምንናገረው ስለቤተክርስቲያናቸን አይደለም፡፡ ይልቁንም እኛ የምንናገረው ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ናት እያልን ነው፣ እሷም በኢየሩሳሌም በ33 ዓ/ም የተመሰረተቸን ነው፣ ያቺም ቤተክርስቲያን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለቸ የምትኖርም ናት፣ አንተም የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ለራስህ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንድትፈትሽ አበረታታሃለሁኝ፡፡

እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት በክርስቶስ ላይ የታነፅን ነን፡፡ ዳግመኛም ጴጥሮስና ሐዋሪያት ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ በመሰከሩበት ጊዜ ቤተክርስቲያኑን በዚያ ዓለት ላይ እሠራለሁ አለ (ማቴዎስ 16፡18)፣ ይህ እውነታ እስከዛሬ ድረስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንዳልሆነ ከተረጋገጠ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ጊዜ በፊት ህልውናዋን ባቆመቸ ነበር፡፡ ጳውሎስ ሲናገር “ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይቸልምና ፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡11) ጴጥሮስም የከበረና የተመረጠ የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ ተጽፏል ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡4~8) ከክርስቶስ ውጪ ያለ መሠረት አይጸናም (ማቴዎስ 7፡24~27) ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ላይ ስልምታርፍ፣ ቤተክርስቲያን የእውነት መሠረትና ዓምድ ናት፣ (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡15)፣ ይሄውም ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ላይ ተሠርታለቸ በዚህም ምክንያት ቤተክርስቲያን እውነትን መደገፍ ወይም እውነትን ለዓለም ማወጅ ቸላለቸ፡፡

እኛየክርስቶስቤተክርስቲያንአባላትነን፣ምክንያቱምቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተገዛቸ ናትና ፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖቸ ሲናገር እንዲህ ይላል “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሣት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳቸሁ ተጠንቀቁ” (የሐዋሪያት ሥራ 20፡28)፣ እንደገና ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን እራሱን አሳልፎ ሰጠ፣ ሞተላት በማለት ጳውሎስ ይነግረናል (ኤፌሶን 5፡25) በማቴዎስ 16፡18፣ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን እሠራለሁ ብሎ ተናግሯል፣ ይህም የእርሱ ነቸ ማለት

ነው፣ ሌላው የማብራሪያ መንገድ፣ ክርስቶስ ሰውን ከኃጥያቱ ለማዳን በመስቀል ላይ ሞተ፣ አንድ ወይም ብዙ ሲታዘዙ ያድናቸዋል እና በደሙ መፍሰስ የነጹትን ቤተክርስቲያኑ ላይ ይጨምራቸዋል፣ በነፍሱ ዋጋ ከፍሏል፣ ስለዚህ እነዚህ የዳኑት ሁሉ ቤተክርስቲያን ይባላሉ በሐዋሪያት ሥራ 2፡47 ላይ የዳኑት ወደ ቤተክርስቲያን እንደሚጨመሩ እናነባለን፣ እንግዲህ ቤተክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ከሆነቾ ክርስቶስ ስለእርሷ ሊሞትላት፣ ደሙን ሊያፈስላት ይገባው ነበር ማለት ነው ይህ መስዋዕት ሁሉ በእርግጥ ቤተክርስቲያንን በጣም አስፈላጊ ያደርጋታል።

እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ነን። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን የሱን ስም ለብሣለች፣ ክርስቶስም ያለው የእኔን ቤተክርስቲያን ነው ያለው (ማቴዎስ 16፡18፣ ኤፌሶን 5፡23) ይህ እውነት ነው፣ ይህ ማለት የባለቤትነት እውቅና የሚያውጅ ነው፣ ማንም ሰው የራሱ በሆነ ነገር ላይ ባለቤት ነው፣ በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ ስለዚህ የሚያወሩ ከቅዱሣት መጽሀፍት እናገኛለን የክርስቶስ አቢያተ ክርስቲያናት ስለአጥቢያ የሚናገሩ (ሮሜ 16፡16፣ የክርስቶስ አካል (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡27) የፍቅሩ ልጅ መንግሥት (ቆላስያስ 1፡13) በሙሉ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መሆኗን የሚያውጁ ናቸው፣ ይህ ብቻ ሳይሆን ሁሉም አባላት የሱን ስም ነው የለበስነው ክርስቲያን (የሐዋሪያት ሥራ 11፡26፣ 1ኛ ጴጥሮስ 4፡ 16) ጴጥሮስም ሲያውጅ ፣ መዳን በክርስቶስ እንጂ በሌላ በምማንም የለም ይለናል (የሐዋሪያት ሥራ 4፡12)

እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ነን ምክንያቱም ክርስቶስ አዳኟ ነው፣ (ኤፌሶን 5፡23) እሱ ራስ ነው (ቆላስያስ 1፡18) ቤተክርስቲያን አንዲት ብቻ ናት (ኤፌሶን 4፡4፣ ኤፌሶን 1፡22~23)

አንተ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነህ? ወይስ የሌላ ቤተክርስቲያን አባል ነህ? ልብ በል ክርስቶስ ያለው ቤተክርስቲያን አንድ ብቻ ነች፣ ያቺም አንተ ልትጨመርባት የሚያስፈልግህ ናጥ በክርስቶስ ብታምን፣ ከኃጥያትህ ንሠሀ ብትገባ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በአፍህ ብትመሰክር፣ ለኃጥያትህ ሥርየት ብትጠመቅ ክርስቶስ ያድንሃል፣ ወደዚህቾ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል (ማርቆስ 16፡16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 47)፣ ቤተክርስቲያን አታድንም ነገር ግን ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ያድናታል፣ ስለዚህ ለመዳን ወደ ቤተክርስቲያንወይም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን አለብን፣ ከዚያም ክርስቲያን መሆንና የክርስትና ህይወት መኖር፣ በመጨረሻም አንድ ቀን ጌታ ሲመጣ እሱ ወደ ሚኖርበት ወደ ሰማይ ይወስደናል (ዮሐንስ 14፡1~3)

## ትምህርት 13
## ክርስቲያን ብቻ የሆንነው ለምንድነው

እንደሚታወቀው በዓለማችን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በክርስቶስ እንደሚያምኑ ያውጃሉ ያወራሉ፣ ነገር ግን ስሙን አልለበሱም፣ ይልቁንም የሰዎችን ስም፣ የጻድቃንን ስም፣ የትምህርታቸውን የዶክትሪን ስም፣የሰዎችን ስም፣ ከቀናቶች ውስጥ የአንዱን ስም ወዘተ የለበሱ ናቸው። እነዚህ ነገሮች ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የሚጻረሩ መሆናቸውን እናምናለን፣በአንጻሩ እኛ በብዙ ሚሊዮኖች የምንቆጠር ደግሞ ይህንን የሰዎችን የነገሮችን የጻድቃንን ስም የለበሱትን አንቀበልም፣ ይህንን ያልተቀበልነው ወይም የተቃወምነው ደግሞ ክርስቶስን አምነን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለወንጌል ታዘን ክርስቲያንና ክርስቲያን ብቻ የሆንን ጊዜ ነው።

ወደ እግዚአብሄር ቃል ስንሄድ መዳን በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ተነግሮናል “መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሠማይ በታችሌላ የለምና” ይላል (የሐዋሪያት *ሥራ* 4፡12) እውነት ነው በዓለማችን ላይ ብዙ ታላላቅ ሰዎች አሉ፣ እነዚህን ሰዎች በማንነታቸውና ስላደረጉት *ሥራም* እናደቃቸዋለን እናከብራቸዋለንም ፣ ይህ ታላላቅ ሰዎች የመኖራቸው ጉዳይ በዘማንት ሁሉ የሚሆን ነውና የሚካድ አይደለም፣ ዳሩ ግን ምንም ታላቅ ቢሆኑ፣ ምንም ቢከበሩ፣ የእነሱን ስም ለመልበስ ብቁ አይደሉም፣ ለዚህም ነው መዳን በክርስቶስ ብቻ መሆኑን እና መልበስ ያለብንም ስም የእሱ ብቻ መሆን ያለበት፣ ስሙን ስንለብስ ለቃሉ ስንታዘዝ ሊያድነን የሚችለው ክርስቶስ ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን በክርስቶስ ስናምን ንሠሀ ስንገባ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክረን ኃጥያታችን እንዲታጠብልን ስንጠመቅ ቃሉን ታዘናልና እንደሚያድነንና ወደ ቤተክርስቲያኑም እንደሚጨምረን ያስተምረናል፣ ይህንን አድርገን ስንታዘዝ ክርስቶስን የለበስን የክርስቶስ ብቻ ቤተሰብ ነን። “ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ይፈርድበታል” (ማርቆስ 16፡16)፣ ከዚያ እነዚህ ወንጌልን ታዘው የዳኑት ደግሞ ጌታ “ጌታ የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር” ይላል (የሐዋሪያት *ሥራ* 2፡47) ነገር ግን በዬትኛው ቤተክርስቲያን ላይ ነው የሚጨምራቸው? በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ላይ። ቤተክርስቲያን እሠራለሁ ብሎ ተናግሯል (ማቴዎስ 16፡18) እና ይህቺ ቤተክርስቲያን ላይ ነው የሚጨምር ፣ በሐዋሪያ *ሥራ* 20፡28፣ ላይ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በደሙ እንደገዛ ይናገራል፣ ስለዚህ ነፍሣት እንዲድኑ አስፈላጊውን ዋጋ ከፍሎ እንዳዳነ አንብበናል። በኤፌሶን 5፡23 ጳውሎስ ክርስቶስ አካል ወይም የቤተክርስቲያን አዳኝ ብሏል። ነገር ግን ይህ ሁሉ የሚያመለክተው እርሱ የቤተክርስቲያን

አዳኝ ስለሆነ የዳኑትና ወደ ቤተክርስቲያኑ የተጨመሩት የክርስቶስ መሆናቸውን ነው። ስለዚህም የራሱ ስለሆንን ስሙን መልበስ አለብን ፤ የእሱ ካልሆንን ግን ስሙን የመልበስ መብት የለንም ማለት ነው። የሌሎችን ስም ብንለብስ የክርስቶስ እንዳልሆንን ያሳያል። አየህ የሆነ የኔ ከሆነ በስሜ ነው የሚጠራው ስለዚህ ስሜን ይለብሳል፤ አንዳንድ ንብረት ወይም ቤት በስሜ ተመዝግቧል። ሚስት ካለኝ ስሜን ለብሣ ታከብረኛለጭ ልጆቸ ካሉኝ ስሜን በመልበስ አባታቸው መሆኔን ያሳያሉ፤ እነዚህ እና ሌሎች ነገሮች በሌሎች ስም ከሆኑ የእኔ መሆናቸውን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? በክርስቶስና በሕዝቡም ዘንድ ተመሣሣይ ነው፤ ለዚህም ነው የክርስቶስን ስም የምንለብሰው፤ ክርስቲያን ብቻ የምንሆነው።

ክርስቲያን የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል። ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው በሐዋሪያት ሥራ 11፡ 26፤ ላይ ይገኛል፤” ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ” ከዚህ ጊዜ በፊት ምን ነበሩ? ክርስቲያኖች ወይም የክርስቶስ ተከታዮች ነበሩ ነገር ግን የጌታ ሰዎች በመጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን መባል ጀመሩ። የምቀጥለው የክርስቲያን ስም በሐዋሪያት ሥራ 26፡ 28 ላይ ይገኛል፤ በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ንጉሥ አግሪጳን ሲያስተምር ነበር፤ እና እምነቱን ሲጠይቅ እናነባለን “አግሪጳም ጳውሎስን በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ አለው” (የሐአዋሪያት ሥራ 26፡28) አንዳንዶች ንጉሱ ክርስቲያን የመሆኑን ሀሳብ እያፊዜበት ነበር ይላሉ፤ ነገር ግን ቅንም ሆነ አልሆነ ስለክርስቲያን ስም አንድ ነገር ያውቅ ነበር፤ ምናልባት ጳውሎስን ከማግኘቱ በፊትም ቢሆን ስለ ክርስትና ብዙ ሰምቶ ሊሆን ይችላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ጳውሎስ በዚህ ጊዜ በእስር ላይ ነበር፤ እናም በቅርቡ ወደ ሮም ይላካል፤ እሱም ክርስቲያን ስለሆነ እና በሄደበት ሁሉ ክርስቶስን ይሰብክ ስለነበር ነው፤ ንጉስ አግሪጳ በዘመኑ ከነበረው ክርስቲያን ጋር ሙሉ በሙሉ ያውቅ ይሆናል፤ ይህ ካልሆነ ግን ጳውሎስ ስለክርስቶስና ክርስቲያን ለመሆን ምን ማድረግ እንዳለበት ነግሮት ይሆናል። በተጨማሪም የክርስቶስ ተከታዮች በዚያን ቀን ሌሎች ስሞችን ለብሰው ቢሆን ኖሮ ንጉሥ አግሪጳም ይህንኑ ይጠቅስ ነበር፤ ነገር ግን ስለክርስቲያን ስም ብቻ ስለተናገረ የክርስቶስ ተከታዮች በክርስቲያኖች ይታወቁ ነበር ብለን መደምደም አለብን በ1ኛ ጴጥሮስ 4፡16 ላይ “ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሄርን ያመስግን እንጂ አይፈር” (1ኛ ጴጥሮስ 4፡16) እዚህ ላይ ጴጥሮስ በኃጥያት ምክንያት መከራን እና ክርስቲያን የሚለውን ሀሳብ እያነፃፀረ ነው ለአንዳንዶች ለመጥፎ ወይም መሰቃየት ውርደት እንደሆነ ያሣያል፤ በተለይም አንድ ሰው ጥፋተኛ ከሆነ፤ ነገር ግን አንድ ሰው ስለክርስቲያን ስም መከራን ቢቀበል በዚህ ጉዳይ

ምንም የሚያሳፍር ነገር እንደሌለ ያሳያል። ክርስቲያን ማንነው? እርሱ ክርስቶስን የሚመስል የክርስቶስ ተከታይ ነው። እርሱ አምላካዊ ሰው ነው፣ ታማኝ እና ሁልጊዜ ትክክል ለማድረግ የሚጥር፣ ይህ ምን ችግር አለው? ስለዚህ አንድ ሰው ስለ ክርስቲያን ስም መከራ ቢቀበል ሊያፍር አይገባውም ነገር ግን አንዳንዶችን ለዚህ ክብር መከራን ለመቀበል ዕድሉን በማግኘቱ ደስ ሊለውና እግዚአብሄርን ሊያከብር ይገበዋል፣ ያዕቆብ ክርስቲያን የሚለውን ስም ባይጠቅስም የክርስቶስን ጠላቶች በተመለከተ ሲናገር ይህን ስም እየጠቀሰ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፣ “የተጠራቸሁበትን መልካሙን ስም የሚሰድቡ እነርሱ አይደሉምን?” (ያዕቆብ 2፡7) ስለዚህ ይህ በመንፈስ አነሣሽነት የተጻፈ ጸሐፊ ስለጥሩ ስም ማለትም የእግዚአብሄር ልጆች ስለተጠሩበት ስም ተናግሯል፣ ከክርስቶስ ስም በላይ ክርስቲያን ከሚለው ስም የበለጠ ምን ሊለብሱ ይችሉ ነበር? ነገር ግን አንድ ሰው ጌታን ሲታዘዝ ክርስቲያን የሚለውን ስም መውሰድ ብቻ አይደለም ነገር ግን ያ ሰው ክርስቲያን መሆኑን በህይወቱ ማሳየት አለበት፣ ማለትም እርሱ ክርስቶስን መምሰሉ እርሱ በሁሉም የክርስቶስ ታማኝ ተከታይ ነው፣ ስለዚህም ጳውሎስ በጊዜው ለነበሩት ክርስቲያኖች ሲጽፍ “እግዚአብሄር አብን በእርሱ እያመሰገናቸሁ፣ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት “ ይላል (ቆላስያስ 3፡17)

እኛ ክርስቲያኖች የሆንነው መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው ነገር ብቻ ነው። ቅዱሣት መጻህፍት አንድ ሰው በክርስቶስ ሲያምን እና ጌታ ክርስቶስን ሲታዘዝ ሲያድነው እና ስለዚህ እርሱ የክርስቶስ እንደሆነ ይነግረናል፣ ስለዚህም የማን እንደሆነ ለማሣየት የክርስቶስን ስም የክርስቲያንን ስም ይለብሣል። አንድ ሰው ሌላ ስም ለብሶ ያንን ባለቤትነት እንዴት ያሳያል? እንዴት ሰው ሰራሽ ስም ለብሶ የክርስቶስን ስም ሊያከብር ይችላል?

እኛ ክርስቲያኖች ነን ምክንያቱም ክርስቶስን ስለምንከተል ብቻ ነው። ክርስቶስ ጌታችንና መምህራችን ነው። ወደ እርሱ እንድንመጣ ተጠርተናል (ማቴዎስ 11፡28~30)፣ እኛም ጥሪውን መለስን ፣ በእርሱ እንድናምንና እንድንታዘዝ ጠየቀን እኛም አደረኝ (ማርቆስ 16፡15~16)

እኛ ክርስቲያኖች ብቻ ነን፣ ምክንያቱም የእግዚአብሄር ቤተሰቦች ነን፣ እንደ ቤተሰብ አባል የእግዚአብሄር ቤተሰብን ስም ለብሰናል (ኤፌሶን 3፡13~14)

እኛክርስቲያኖችነን፣ምክንያቱምየክርስቲያንህይወትስለምንኖርና በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ተሰባስበን ስለምናመልክ (የሐዋሪያት ሥራ 20፡7) ክርስቶስን ለመከተል በየቀኑ እንተጋለን (ሉቃስ 9፡23)

አሁን አንድ ነገር ልጠይቅሕ በክርስቶስ አማኝ ነህ? አንተ ክርስቲያን ነህ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንበብ የማትችለው ወይም ያልተጻፈ

የቤተክርስቲያን አብል ከሆንክ እና ሰው ሰራሽ ስም ከለበስክ፣ ክርስቲያን ነኝ ብትልም ክርስቲያን አይደለህም። ብዙዎች ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስቲያን ነን ይላሉ፣ ክርስቲያን ከሆንክ ለምን ክርስቲያን እንደሆንክ ለማሳየት ወደ እግዚአብሄር ቃል ሄደህ መጽሐፍን፣ ምዕራፉን፣ እና ቁጥሩን መስጠት ትችላለህ

ክርስቲያን ካልሆንክ እንድትሆን ልናበረታታህ እንወዳለን፣ በክርስቶስ ካመንክ ከኃጥያትህ ንሠሀ ከገባህ፣ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ከመሰከርክ፣ ለኃጥያትህም ሥርየት ከተጠመቅክ፣ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል (ማርቆስ 16፡16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 47)፣ ከዚያም የጌታ ቤተሰብ አባል እንደመሆንህ በግልህ የቤተክርስቲያን አባል ትሆናለሕ ይህ ማድረግ በጣም ቀላል ነው እና አንተም ልክ እንደነ ጴጥሮስ፣ እንደነጳውሎስ፣ እና እንደሌሎችም ክርስቲያን መሆንህን ማወቅ በጣም የሚያረካ ነው፣ ጳውሎስ ጴጥሮስና ሌሎቹም በሙሉ የመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ነበሩ ስለዚህ ልክ እንደነሱ እንደእኛ ክርስቲያን ለመሆን ይህ ጥናት በቂህ ነው።

## ትምህርት 14
## ለምን በአንድነት እናምናለን

በኃይማኖት ውስጥ ከአንድነት የበለጠ ጠቃሚ ነገር የለም። በእግዚአብሄር፣ በክርስቶስ እና በመንፈስ ቅዱስ መካከል አንድነት አለ።በቅዱሣት መጽሐፍት ውስጥ አንድነት አለ። ባማኞች፣ በእግዚአብሄር ቤተሰብ፣ በቤተክርስቲያን መካከል አንድነት አለ፣ በሰው እና በጌታ በክርስትና ህይወት ውስጥ አንድነት አለ።

አንድነት ማለት ኅብረት፣ ሙሉነት፣ መስማማት፣ መሰባሰብ፣ መተባበር፣ አብሮ መሥራት መቻል ነው።

እኛ የጌታ ሰዎች ነን የጌታችን ቤተክርስቲያን በአንድነት እናምናለን፣ ምክንያቱም የዚያ ተቃራኒ መለያየት ነው። ስለአንድነት ከማሰብ ከመቀጠላችን በፊት ቅዱሣት መጽሐፍት ስለመለያየት ምን እንደሚሉ እንመልከት፣ መለያየት ምን እንደሆነ፣ ምን እንደሚወክል እና ወደ ምን እንደ ሚመራው ስናይ ያን ጊዜ ታላቅ አማኞች እና የአንድነት አራማጆች እንሆናለን ብዬ አምናለሁ፣ ጠቢቡ ሰለሞን በጥንት ዘመን እግዚአብሄር ከሚጠላቸው ነገሮች አንዱ “በወንድማማቾች መካከል ጠብን የሚዘራ ነው” ይላል (ምሣሌ 6፡19)፣ ያ በቀላሉ መለያየትን የሚፈጥርን ሰው ያመለክታል። ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮም የነበሩትን ክርስቲያኖችን እንዲህ ብሎ ጽፏል “ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችዋለሁ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፣

እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፤ በመልካም የሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ"(ሮሜ 16፡ 17~18) እባክህን መለያየትንና ጥፋትን የሚፈጥሩትን እንዲጠቁሙ ማበረታታቱን አስተውል። በተጨማሪም እነዚህ ሰዎች ምልክት ሊደረግባቸው የሚገቡት ከትምህርቱ ወይም ከተማሩት ነገር ጋር የሚቃረኑ ነገሮችን እያደረጉና እያስተማሩ ስለነበር ነው፤ እነዚህም መለያየትን የፈጠሩ ናቸው ብሏል። ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ ላይ ጌታን ስላላገለገሉ መራቅ እንዳለባቸው ተናግሯል። ይልቁንም ሆዳቸውን ሲያገለግሉ ነበር ማለትም ለግል ጥቅማቸው እንዲህ ይሠሩ እንደነበር ይናገራል፤ በመጨረሻም በመልካም ንግግራቸው ሰዎችን ያታልሉ ነበርና ብሎ ያስጠነቅቃቸዋል። እሱ በጣም የተለየ ነበር አይደል? ነገር ግን እንዳይሣሣቱ ስለእነዚህ ሰዎች ማስጠንቀቅ አስፈላጊ ነበር።

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡11~17፤ ላይ "ወንድሞቼ ሆይ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎኤ ቤተሰዎች አስታውቀውኛልና፤ ይህንም እላለሁ እያንዳንዳችሁ ፤ እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፤ እኔ ኝ የኬፋ ነኝ፤ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለእናንተ ተሰቀልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን? በስሜ እንደተጠመቃችሁ ማንም እንዳይል ከቀርስጶስና ከጋይዮስ በቀር ከእናንተ አንድን እንኳ ስላላጠመቅኩ እግዚአብሄርን አመሰኛለሁ፤ የእስጢፋኖስንም ቤተሰዎች ደግሞ አጥምቄአለሁ፤ ጨምሬ ሌላ አጥምቄ እንደ ሆነ አላውቅም፤ ለማጥመቅ ክርስቶስ አልላከኝምና፤ ወንጌልን ልሰብክ እንጂ፤ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም "
(1ኛ ቆሮንቶስ 1፡11~17)

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል መከፋፈል እንደነበረ ቀደም ሲል እንደተመለከተው እንመለከታለን። ከአባላቱ አንዳንዶች የጳውሎስ ነን፤ አንዳንዶቹ የአጵሎስ ነን፤ ሌሎቹ የጴጥሮስ ነን ሌሎቹ የክርስቶስ ነን ይሉ ነበር፤ ጳውሎስ ይህ ስህተት መሆኑን እንዲገነዘቡ ለመርዳት ሦስት ጥያቄዎችን ጠየቃቸው፤ ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስ አጵሎስ ወይም ጴጥሮስ ስለ እናንተ ተሰቅለዋልን? በመጨረሻ በጳውሎስ ወይም በጴጥሮስ ስም ተጠመቃችሁን? በእርግጥ ክርስቶስ እንዳልተከፋፈለ ፤ ክርስቶስ ስለእነርሱ እንደተሰቀለ እና በክርስቶስ ስም እንደተጠመቁ ያውቃሉ፤ እውነት ነው ጳውሎስንና ሌሎችን መከተል ለእነሱ ሞኝነት ነበር፤ ክርስቶስ ስላልተከፋፈለ ነገር ግን ክርስቶስ ስለእነሱ ተሰቅሎአል እናም በክርስቶስ ስም ተጠመቁ ክርስቶስንና ክርስቶስን ብቻ መከተል አለባቸው፤ ይህን ሲያደርጉ አንድ ይሆናሉ። ነገር ግን በዚያ በቆሮቶስ በነበረው ሁኔታ ምክንያት ጳውሎስ እርሱን ለመከተል እንዳይሞክሩ ከእነርሱ አብዝቶ ባለማጥመቁም

ደስተኛ መሆኑን ተናግሯል። ነገር ግን የእስጥፋኖስን የቀርስጶስን እና የጋይዮስን ቤተሰዎች እንዳጠመቀ ተናግሯል። በመቀጠልም ጌታ እንዲያጥምቅ እንዳልላከው ነገር ግን ወንጌልን እንዲሰብክ እንደላከው ተናግሯል። የተላከበት ዋና ዓላማ ወንጌልን መስበክ መሆኑን እየተናገረ ነው።ለወንጌል መታዘዝ የሚሹ ቢኖሩ ግን ማጥመቅ ግድ ነው፣ ጳውሎስ እዚህ ጋ ጥምቀት አስፈላጊ አይደለም እያለ አይደለም። ቢሆንም ቅድሚያ ጥምቀት ሳይሆን ወንጌልን መስበክ መሆኑን ለማስረዳት ያህል ነው።

የጠቀስናቸው የተለያዩ የቅዱሣት መጻፍት ጥቅሶች ላይ የምናየው አመስለኛል እና በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ላይ ጌታ በመከፋፈላቸው አልተደሰተም ነገር ግን ይቃወመዋል እና ያወግዛል ። እውነት ሆኖ ሳለ ቅዱሣት መጽሀፍት ስለአንድነት ምን እንደሚሉ እንይ ወደ ቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ስንመለስ "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ ሀሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችዋለሁ" (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡10) እንዳየሽው አንድነት ሲበረታታ መለያየት የተወገዘ ይሆናል።

በዮሐንስ 17 ላይ ክርስቶስ ሐዋሪያትንና በእሱ ለምናምነው ሁሉ የጸለየው ጸሎት ነበረ፣ እንዲህ ይላል፣ " ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፣ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለእነዚህ ብቻ አልለምንም፣ አንተ እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ፣ እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ፣ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደላክኸኝ በወደድከኝም መጠን እነርሱን እንደወደድሃቸው ያውቃሉ" (ዮሐንስ 17፡20~23) እባክህን አስተውል ክርስቶስ በእርሱ ለሚያምኑት በቃላቸው ማለትም በወንጌል ስብከት (ማርቆስ 16፡15~16)፣ እንደሚጸልይ ተናግሯል እና ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ነው፣ እንደሚታወቀው ሐዋሪያት አንድ ዓይነት መልዕክት ቢሰብኩና ሁሉም ቢያምኑት ሁሉም አንድ ነገር አምነው ተመሣሣይ ነገር ያደርጋሉ ሁሉም አንድ ይሆናሉ፣ እንደገናም እርሱ እና አብ አንድ እንደነበሩ ክርስቶስ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ ጸለየ፣ ይህ ፊጹም አንድነት ይሆናል፣ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ የጸለየበት ሌላው ምክንያት አብ የላከው ዓለምን ለማሣመን ነው፣ ሁሉም ቢከፋፈሉ እና ቢቃረኑ ግን ጉዳት እንደሆነና ዓለምም እንደሚስቅባቸው ያውቃል። አንድነት ለበጎ ነገር ኃይል መሆኑን አስታውስ መከፋፈል ግን አጥፊ ነው።

በኤፌሶን 4፡1~6፣ ላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለአንድነት መሰረታዊ ነገሮችንያስቀምጣል "እንግዲህበጌታእስርየሆንሁእኔበተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችዋለሁ፣ በትህትና

ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም፣ እርስ በርሳቸሁ በፍቅር ታገሱ፣ በሠላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ፣ በመጠራታቸሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራቸሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ ኃይማኖት አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ" (ኤፌሶን 4፡1~6) ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ አንድነት የሚለምን መሆኑን እባክህን አስተውል፣ አንድ እግዚአብሄር፣ አንድ ጌታ ፣አንድ መንፈስ ፣አንድ እምነት፣አንድ ጥምቀት፣ አንድ አካል፣ ወይም ቤተክርስቲያን አንድ ተስፋ ላይ መመስረቱን ይናገራል ። በሌላ አገላለፅ እዚህ ጋ አንድ አምላክ ወይም አባት አለ እርሱም ፈቃዱን በመንፈስ ቅዱስ በኩል የገለጠልን አንድ ጌታና መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ሁላቸንም አንድ ዓይነት ትምህርት አምነን ለአንድ ጌታ በጥምቀት ስንታዘዝ ይኼውም በውኃ ውስጥ በመቀበር ስንታዘዝ ጌታ ደግሞ ወደዚህቸ አንድ አካል ይጨምረናል፣ በቤተክርስቲያንም ሁላቸን የዘላለም ህይወት ተስፋ አለን ወዳጆቼ ሁላቸንም አምነን ለአንድ ጌታ የምንታዘዝ ከሆነ እንዴት እንለያያለን? አንድ ያደርገናል እንጂ አይከፋፍለንም፣ በጥንት ዘመን መዝሙረኛው ዳዊት " ወንድሞቸ በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው" ብሎኦል (መዝሙር 133፡1)

ወዳጆቼ፣ ክርስቶስን እንከተላለን በሚሉት መካከል ዛሬ በኃይማኖታዊው ዓለም ብዙ መለያየት እንዳለ እንውቃለን፡፡ ይህ አሣዛኝ እናልብየሚሰብርነው፣ነገርግንበዚህምክንያትክርስቶስንናትምህርቱን አይውቀሱ፡፡ ይልቁንም ለዚህ ተጠያቂው ሰው ነው ምክንያቱም ብዙዎቸ ጌታ የጠየቀውን ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው፡፡ እባክህን ይህ እንዲያታልልህ አትፍቀድ፣ ወደ ክርስቶስ እና ወደ ቃሉ ለእውነት ለመታዘዝ ሂዱ፣ እማኑ፣ እና ታዘዘው፣ በማድረግህም ትድናለህ ወደ አንዲቱ ቤተክርስቲያኑም ይጨምረሃል፣ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ ምታነበው ቤተክርስቲያን ማለት ነው፣ በእውነት ከታዘዙት ሁሉ ጋር ትሆናላቸሁ፣ አዎን አሁንም ክርስቶስ የጸለየለት አንድነት እንዲኖር ማድረግ ይቻላል፣ ለመዳን እና ወደ መንግሥተ ሰማያት መሄድን የመሰለ ምንም ነገር የለምና፡፡

አንተ ክርስቲያን ነህ ? የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነህ? ካልሆንክ ከክርስቲያኖቸ ውስጥ አንዱ እንድትሆን እንጸልያለን፣ ይህንን ለማድረግ በክርስቶስ ማመን ከኃጥያትህ ንሠሀ መግባት፣ እምነትህን በአንደበትህ መመስከር፣ እና ኃጥያትህ እንዲታጠብልህ በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ ያስፈልግሃል፣ ከዚያ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ እራሱ ቤተክርስቲያንም ይጨምርሃል፣ ከዚያን ከክርስቲያኖቸ፣ ከክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት አንዱ ትሆናለህ፣

## ትምህርት 15
## ክርስቶስ ለምን በመስቀል ላይ ሞተ

በመጀመሪያ እግዚአብሄር ወንድና ሴትን ሲፈጥር ፊጹማን ነበሩ ኃጥያተኛም አልነበሩም። ነገር ግን በዚያ ንጹህ ሁኔታ ውስጥ ለረጅም ጊዜ አልቆዩም፣ ብዙም ሳይቆይ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ጣሱ ። እናም ከውቢቷ ከኤደን ገነት ተባረው በመንፈስ ሞቱ በኃጥያታቸው መዘዝ ሊሰቃዩ፣ ወንድ በላቡ ለፍቶ ጥሮ ግሮ ኑሮውን እንዲያሸንፍ፣ ሴቷ ደግሞ ልጅ በመውለድ ስቃይ እንዲደርስባት ተረገሙ። እና በመጨረሻም በአካል መሞት (ዘፍጥረት 1~3) ሰው ኃጥያተኛ በመሆኑ የእግዚአብሄር ጠላት ሆነ።

የሰው ልጅ ወደ እውነተኛው ቅድስና እራሱን መመለስ ባለመቻሉ እንደዚሁም የእንስሳት መስዋዕት ለዘላለማዊ ቋሚ የኃጥያት ሥርየት ሊሆን ባለመቻሉ እግዚአብሄር አንዲያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን መስዋዕት አድርጎ ወደ ዓለም ላከው፣ እርሱም በሰው እና በእግዚአብሄር መካከል አስታራቂ አማላጅ ሆኖ መጣ፣ ይህም ሰዎች ሁሉ በእሱ በኩል ወደ እግዚአብሄር እንዲመለሱ ነው፣ (ዕብራዊያን 10፡4፣ ዘፍጥረት 3፡15)፣ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሄር ከድንግል ማርያም እንዲወለድ አድረገ፣ ይህንንም ለማሪያም እጮኛ ለዮሴፍ የእግዚአብሄር መልዓክ ተገልጦ “ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙንም እሱ ለሰው ልጅን ከኃጥያታቸው ያድናቸዋል፣ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ” አለው (ማቴዎስ 1፡21)

ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ከመወለዱ በፊት በትንቢት ተነግሮናል እንግዳ ነገር ቢመስልም እግዚአብሄር ግን እንዲሞት መላኩን እናነባለን “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሄር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፣ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሄር ወደ ዓለም አልላከውምና” (ዮሐንስ 3፡ 16~17)። እንዲሞት የላከው ለኃጥያተኞች ለክፉዎች እንዲሞት ነው የላከው እንዲህ ይላል፣ “ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጥያተኞች ሞቶአልና፣ ስለጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፣ ስለቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል፣ ነገር ግን ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቶአልና እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል፣ ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን” (ሮሜ 5፡6~9)፣ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ሲናገር “እኔ እንደ ወደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትዕዛዜ ይህች ናት፣ ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም” (ዮሐንስ 15፡12~14) ዮሐንስም እንዲህ ብሏል “በዚህ የእግዚአብሄር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፣ በእርሱ በኩል በህይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሄር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፣

ፍቅርም እንደዚህ ነው፣ እግዚአብሄር እርሱ እራሱ እንደወደደን ስለኃጥያታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሄርን እንደወደደነው አይደለም” (1ኛ ዮሐንስ 4፡9~10)

ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ ሲመላለስ በነበረበት ጊዜ ብዙ መልካም ነገሮችን አድርጓል፣ ደዌን ፈውሷል፣ ዕውራንን ዓይኖቻቸውን ከፍቷል፣ ሙታንን አስነስቷል፣ እጅግ በርካታ ተአምራትን አድርጓል ይህም ደግሞ ከእግዚአብሄር መላኩን ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ ነው፣ ዮሐንስ ሲነግረን “ኢየሱስምበዚህመጽሐፍያልተጻፈሌላብዙምልክትበደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ፣ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል” (ዮሐንስ 20፡30~31)

ኢየሱስ መልካም ሰው ነው፣ ፊጹም ሰው ነው፣ ኃጥያት የለበትም፣ ጳውሎስ ይህን ሲናገር “እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሄር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጥያት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ ኃጥያት አደረገው” (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)፣ ጴጥሮስም ሲናገር “እርሱም ኃጥያት አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም” (1ኛ ጴጥሮስ 2፡22)

ነገር ግን ይህ መልካም ሲያደርግ ኃጥያት ያላደረገው የእግዚአብሄር ልጅ ስለዓለም ኃጥያት በመስቀል ላይ እንደሞተ ተነግሯል “በምስሉም እንደሰውተገኝቶራሱንአዋረደ፣ለሞትምይኸውምየመስቀልሞትእንኳ የታዘዘ ሆነ” (ፊልጵስዩስ 2፡8) ጴጥሮስም ሲያውጅ “የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፣ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሣሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሏልና፣ እርሱም ኃጥያት አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተኘበትም፣ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፣ መከራንም ሊቀበል አልዛተም፣ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፣ ለኃጥያት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፣ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጥያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፣ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ” (1ኛ ጴጥሮስ 2፡21~24) ጳውሎስም ሲናገር መጽሐፍም እንዳለው ክርስቶስ ስለኃጥያታችን በመስቀል ላይ ሞተ ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3)

ነገር ግን ክርስቶስ ለምን ተሰቀለ፣ ማለትም ለምንድነው ይህ ደግ ሰው ሊሞት የተፈለገው? ሰውን ለማዳን ቢመጣም፣ ከኃጥያተኛ ሰው ጋር መገናኘቱስ እግዚአብሄርን ይወክላሉ የተባሉት እንደካህናቱ፣ ጸሐፍት ፣ ፈሪሳዊያን፣ ሰዱቃዊያን ወዘተ የሰውን ትምህርትና ትዕዛዝ ተከትለው ሄደዋል፣ ስለዚህም በቅናት እና በክፋት የተሞሉ ነበሩ ፣”የእርሱ ወደ ሆኑት መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም” (ዮሐንስ 1፡11)፣ እንደገና እንዲህ ይላል፣ “ነገር ግን ህይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም” አላቸው፡፡ (ዮሐንስ 5፡40)፣ ለእነዚህ የኃይማኖት ሰዎች በጴንጤቆስጤ ቀን ጴጥሮስ እንዲህ አላቸው “የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ፣ ራሳችሁ እንደምታውቁ

የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሄር በመካከላቸሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆቸ በምልክቶቸም ከእግዚአብሄር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፣ እርሱንም በእግዚአብሄር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በአመጸኞቸ እጅ ሰቅላቸሁ ገደላቸሁት ፣ እግዚአብሄር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፣ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና” (የሐዋሪያት ሥራ 2፡22~24) አልፎ የተሰጠበት ቀን ዘገባው ስለክርስቶስ ሲናገር “የካህናት አለቆቸ አሳልፈው እንደሰጡት ያውቅ ነበርና” ይላል (ማርቆስ 15፡10) ስለዚህም ክርስቶስ የሐሰት ፍርድ ተሰጥቶት በመስቀል ላይ እንዲሞት ተፈርዶበታል፣ በክፉ እጆቸ ተይዞ ተደበደበ፣ ተሣለቁበት፣ ሰደቡት ፣ በጭካኔ በመስቀል ላይ ቸነከሩት

በሁለት ወንበዴዎቸ መካከል ተሰቅለ፣ ነፍሱንም እዚያው ሰጠ ከዚያም ወደ ታቸ ወርዶ ቀበሩት አንድ ትልቅ ድንጋይ በመቃብሩ ላይ አስቀመጡበት ኢየሱስ ግን በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ተናግሮ ቃል ገብቶ ነበር(ዮሐንስ 14፡10) ከሦስት ቀንም ቦኃላ ከሞት የተነሣ ጌታ ሆኖ ወጣ። በሦስተኛው ቀን ጠዋት ሴቶቹ መቃብሩን ሊጎበኙ በመጡ ጊዜ መልዓክ እንዲህ አላቸው፣ “እንደተናገረ ተንሥቶአልና በዚህ የለም፣ የተኛበትን ሥፍራ ኑና እዩ” አላቸው (ማቴዎስ 28፡6) በደቀመዛሙርቱና 500 ለሚያህሉት በአንድ ጊዜ ከተገለጠ ቦኃላ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶቸ ጌታ ሆኖ ሊነግሥ ወደ ሰማይ ወደ አብ ተመለሰ (1 ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~8፣ የሐዋሪያት ሥራ 1፡1~11) እዚያ እስከ ዛሬ ድረስ ይኖራል።

እንደገና አሁንም ክርስቶስ ለምን በመስቀል ላይ ሞተ? ብዙ ምክንያትቸ አሉ። በእርግጥ ዋናው የሞቱ ዓላማ ለሰው ልጆቸ ኃጥያት ሆኖ በእሱ የሚያምኑ ይድኑ ዘንድ ነው። ነገር ግን ሌላው የሞቱ ምክንያት ሞቱን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን የተነገረውን ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው፣ (ኢሳያስ 53፣ ሐዋሪያት ሥራ8) የብሉይ ኪዳንን ህግ ከመንገድ ለማስወጣት ነው፣ (ቆልሳያስ 2፡14፣ ዮሐንስ 1፡17፣ ማቴዎስ 26፡28) የሚፈሰው ደሙ የሰውን ልጅ ኃጥያት እንዲያነፃ ነው (ኤፌሶን 1፡7፣ ሐዋሪያት ሥራ 22፡16) ቤተክርስቲያኑ እንዲመሰረት ነው (ኤፌሶን 5፡25)፣ ለሚድኑት የዘላለም ህይወት ተስፋ። ሊሰጥ ነው (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡16)

በትክክል የክርስቶስ ሞት ምክንያት እውነታው ዓለምን ሊያድን ነው፣ አብዛኛው የዓለም ህዝቦቸ ጥፍተዋልና፣ ለምን? ብዙ ምክንያቶቸ አሉ። አብዛኛው የእግዚአብሄርን ፈቃድ አለማወቅ ነው፣ ጳውሎስ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ቤተክርስቲያንን ያሳድድ በነበረበት ጊዜ ያንን ያደረገው ካለማወቅ እንደሆነ ይናገራል (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡13) ሌሎቹ በራሳቸው ጽድቅ መልካምነት እንድናለን ብለው ስለሚተማመኑ ነው፣ ነገር ግን ቆርኔለዎስና ቤተሰቡ መልካምና አስተዋይ ሰዎቸ ነበሩና የክርስቶስን ወንጌል ታዘው መዳናቸው አስፈላጊ ሆኖላቸዋል

(የሐዋሪያት ሥራ 10)ሌሎቹ ደግሞ የእግዚአብሄርን ክብር ትተው የሰውን ክብር አስበልጠዋልና ክርስቶስ “ከእግዚአብሄር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና” ይላል (ዮሐንስ 12፡43) ሌሎቹ በሐሰት ትምህርት ተወስደው በኃይማኖት ስም ተታለዋል ዮሐንስ ይህንን እንዲህ ይላል “ወዳጆቸ ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሄር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፣ ብዙዎቸ ሐሰተኞቸ ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና” ይላል (1ኛ ዮሐንስ 4፡1) እንግዲህ ዛሬም ብዙ የሐሰት አስትማሪዎቸ በመኖራቸው ብዙዎቸ በእነዚህ እየተመሩ ዓለምን ወደው ጠፍተዋል፣ ዓለምን አትውደዱ ይላልና ቃሉ (1ኛ ዮሐንስ 2፡15) ይህም የሥጋ ሥራ ሲሆን የሥጋ ሥራ ደግሞ ወደ ሞት ይመራል (ገላቲያ 5፣ ሮሜ 6፡23)

ወዳጆቼ ! ክርስቶስ እናንተን ለማዳን በመስቀል ላይ መሞቱን ታውቃላቸሁ? እባካቸሁን ይህንን አትጣሉ፣ አትካዱ፣ ይህንን ብቸኛ የዘላለም ህይወት ተስፋ ሰጪ የሆነውን ጌታ አትጠራጠር፡፡ በእሱ ካመናቸሁ፣ ከኃጥያታቸሁ ንሠሀ ከገባቸሁ፣ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ከመሰከራቸሁ፣ ለኃጥያታቸሁ ሥርየት ከተጠመቃቸሁ፣ እሱ ያድናቸዋል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምራቸዋል፣ እስከ መጨረሻም ታማኝ ሆነህ ከኖርክ አንድ ቀን ይመጣል ወደ ሰማይ ወደ አባቱም ይወስድሃል (ማርቆስ 16፡16፣ ማቴዎስ 10፡32፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 47፣ ዮሐንስ ራዕይ 2፡10)፡፡

## ትምህርት 16

## ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን ለምን እናምናለን

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የኖረና የሞተው ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት አከባቢ መሆኑን በእርግጠኘት እናውቃለን፡፡ ያ መጨረሻ ቢሆን ኖሮ ከጥንት ጀምሮ ይረሣ ነበር፡፡ ግን አሁንም በሺዎቸ እና በሚሊዮኖቸ በሚቆጠሩ ሰዎቸ አዕምሮ እና ህይወት ውስጥ ይኖራል፣ ለምን ? ለምሣሌ በጭካኔ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ተቀበረ እና ከሦስት ቀን ቦኃላ ከመቃብር ተነስቷል፣ እኛ ስለዚህ ክርስቶስ መሞቱን ብቻ ሳይሆን ከሙታንም መነሣቱን በዚህ ቀን እንሰብካለን፣ ስለዚህም የዕብራዊያን ጸሐፊ እንዲ ይላል “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነው” ይለናል (ዕብራዊያን 13፡8)

ክርስቶስ በህይወት እያለ እንኳን ከሞት እንደሚነሣ ተስፋ ሰጥቶአል፡፡ “ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦሥት ቀንም አነሣዋለሁ” ብሏል፡፡ በእርግጥ አይሁድ በኢየሩሳሌም ስላለው እውነተኛው ቤተመቅደስ እየተናገረ መሰላቸውና እንዲህ ተባባሉ “ኢየሱስም መልሶ፦ ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት፣ በሦስት ቀንም አነሰዋለሁ አላቸው፣ ስለዚህ አይሁድ፣ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፣

አንተስ በሦስት ቀን ታነሳዋለህ? አሉት እርሱ ግን ስለሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበር" (ዮሐንስ 2፡19~21) ከዚያም እንዲህ እናነባለን "ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ነበር" ማቴዎስ 16፡21) በዚያን ጊዜ ኢየሱስ የሚላቸውን ደቀመዛሙርቱ አላስተዋሉም ነበር ቦኃላ ላይ ግን ያላቸው ሁሉ ሆነው ሲያዩና የትንሣኤው ጌታ መሆኑን ምስክርም በሆኑ ጊዜ እያንዳንዱን ያሳውሱ ጀመር፡፡

ክርስቶስ በሐሰት ተላልፎ ከተሰጠ በመስቀል ላይ ከተሰቀለ እና በአሰቃቂ ሞት ከሞተ ቦኃላ ዘገባው እንደሚለው "በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፣ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ነበረ፣ ይኼውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው፡፡ ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ፣ ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹህ በፍታ ከፈነው፣ ከዓለት በወቀረው ባዲሱ መቃብርም አኖረው፣ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ፣ መግደላዊት ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው በዚያ ነበሩ" (ማቴዎስ 27፡57~61)፣ በዚህ ጊዜ ይህ የኢየሱስ መጨረሻ ይመስላል፣ ደቀመዛሙርቱ እንኳን ምንም እንኳን በድንጋጤ ውስጥ ቢሆኑም ይህንን የተቀበሉ ይመስሉ ነበር እና ወደ ቀድሞ ህይወታቸው ለመመለስ ማሰብ ጀመሩ፣ ይህ ሆኖ ሳለ የኢየሱስ ጠላቶች ከመቃብር ስለመውጣት የተናገረውን አልረሱም ነበር ስለዚህም እንዲህ አሉ "በማግስቱም ከመዘጋጀት ቦኃላ በሚሆነው ቀን የካህናት አለቆችና ፈሪሳዊያን ወደ ጲላጦስ ተሰበሰቡና፣ ጌታ ሆኚ ያ አሳች በህይወቱ ገና ሳለ፣ ከሦስት ቀን ቦኃላ እነሣለሁ እንዳለ ዕ አለን፣ እንግዲህ ደቀመዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ለሕዝቡም፣ ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ የኋለኛይቱ ስህተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩ እስከ ሦስተኛ ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት፣ ጲላጦስም ጠባቆች አሏችሁ፣ ሄዳችሁ እንዳወቃችሁ አስጠብቁ አላቸው፣ እነርሱም ሄደው ከጠባቆች ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አስጠበቁ" (ማቴዎስ 27፡62~66)

እባክህን ከላይ በተጠቀሰው ነገር ላይ ክርስቶስ በእርግጥ ከመቃብር ይወጣል ብለው አላመኑም ነበር፣ ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ሊሰርቁት ይችላሉ ብለው ፈሩ እና በዚህም ምክንያት የእሱ ተወዳጅነት ቀድሞ ከነበረው የበለጠ ሊስፋፋ ቻለ፣ በትክክል መቃብሩ ታሽጎ ታተመበትና እርግጠኛ ለመሆን እና እንዲጠብቁት ሁለት ሰዎችን እዚያ ትተው ሄዱ፡፡

ማንበባችንን ስንቀጥል እንዲህ ይላል "በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያ ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ፣ እነሆም የጌታ መልዓክ ከሰማይ ስለወረደ ታላቅ

የምድር መናወጥ ሆነ ቀርቦም ዲንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ ፣መልኩም እንደመብረቅ ልብሱም እንደበረዶ ነጭ ነበር። ከጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደሞቱም ሆኑ። መልዓኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፦ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና እንደተናገረ ተነሥቷልና በዚህ የለም የተኛበትን ሥፍራ ኑና እዩ፣ ፈጥናችሁም ሂዱና፦ ከሙታን ተነሣ እነሆም ወደ ገሊላ ይቀድማችዋል፣ በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሯቸው፣ እነሆም ነገርኋችሁ፣ በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፣ ለደቀመዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ እነሆም ኢየሱስ አገኛቸውና ፦ ደስ ይበላችሁ አላቸው እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት፣ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ አትፍሩ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሯቸው በዚያም ያዩኛል አላቸው” (ማቴዎስ 28፡1~10) እንግዲህ ይህ ለደቀ መዛሙርቱ ቀደም ብለው የኢየሱስን አስክሬን ለመስረቅ ያሰቡ አይመስልም፣ አይደል? ይልቁንም ልክ እንደጠባቂዎቹ የተገረሙ ይመስላል። አንዳንድ ሐዋሪያት ይህን ነገር በመጀመሪያ ይጠራጠሩ ነበር።

ንባባችንን እንቀጥል ጠባቂዎቹ ከትንሣኤው ጋር እንዴት እንደሆኑ እናያእን “ሲሄዱም ሳሉ እነሆ ከጥባቆቹ አንዳንድ ወደ ከተማ መጥተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ፣ ከሽማግሌዎቹ ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው፣ እኛ ተኝተን ሳለን ደቀመዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደሆነ፣ እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ ሥጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሏቸው፣ እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ አስተማሯቸው አደረጉ ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል” (ማቴዎስ 28፡11~15) አሁን እዚህ ላይ ስለተፈጠረው አስብ ከቀደሙት ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹን እንደምናነበው፣ መቃብሩን ለማየት የሄዱት ሰዎች ምን እንደተፈጠረ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ጥባቂዎቹ ተቀጠቀጡና የሞቱ መስሏቸው፣ ከዚህ ሁሉ ቦኃላ የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች ለመንገር ወደ ከተማይቱ ገቡ። እውነት ከመናገር እና ኢየሱስ በእውነት ከመቃብር እንደወጣ ለራሳቸው ከማመን ይልቅ ከሽማግሌዎች ጋር ተሰብስበው በጉዳዩ ላይ ተወያይተው ብዙ ገንዘብ ተሰጣቸው ። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መጥተው ተኝተው ወሰዱት የሚለው ቃል ይዋሹ ነበር ማለት ነው። ያ በእርግጥ ቢሆን ኖሮ ገንዘብ መስጠት አስፈላጊ አይሆንም ነበር እና ጠባቂዎቹ መዋሸት ባላስፈለጋቸውም ነበር፣ ነገር ግን በዚያን ጊዜም ቢሆን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ተኝተው ሳለ አስከረኑን እንደሰረቁት ወታደሮች እንዴት ይሰማቸዋል? በብዙ እንሰዚህ ባሉ ጉዳዮች ላይ በሥራ ላይ በመተኛታቸው ጥፋተኛ የሆኑ ወታደሮች ህይወታቸውን

ይከፍሉ ነበር፣ እርግጥ ነው ሽማግሌዎቹ እነዚህ ሰዎች ይህ ወዲ ገዢው ጆሮ ቢመጣ ከደህንነታቸው ጋር የተያያዘ እንደሚሆን እንደሚያስረዱት አረጋግጠውላቸዋል።

እንግዳ ቢሆንም፣ ግን እስከዛሬ ድረስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም የሚሉትም ቢሆኑ፣ ዷቀመዛሙርቱ ሰረቁት የሚሉት ሁሉ የዘበት ነው። የማቴዎስ፣የማርቆስ፣ የሉቃስ፣እና የዮሐንስ ዘገባዎች እንዲሁም መላው መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ከመቃብር መነሣቱን ይመሰክራሉ። ይህም ብቻ ሣይሆን ደህንነት፣ጥምቀት፣ ቤተክርስቲያን፣ የጌታ እራት፣ እና በአጠቃላይ ክርስትና ሁሉም ህልውናና የህይወት ፋይዳ ሁሉ በክርስቶስ ትንሣኤ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት የሆነውን የእግዚአብሄርን ቃል ይወክላል፣ እናም በእርግጠኝነት ክርስቶስ ከመቃብር እንደተነሣ ያስተምራል፣ እኛም እናምናለን

ሐዋሪያው ጳውሎስ ሲጽፍ እንዲህ ይለናል “ወንድሞች ሆይ የሰበኩላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግም የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ፣ በከንቱ ካላመናችሁ በቀር፣ ብታስቡት በምን ቃል እንደሰበኩላችሁ አሳስባችኋለሁ። እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ፣ እንዲህ ብዬ ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጥያታችን ሞተ፣ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፣ ለኬፋም ታየ፣ ቦኃላም ለአሥራ ሁለቱ ከዚያም ቦኃላ ከአምሥት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፣ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከአሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፣ ከዚያም ቦኃላ ለያዕቆብ ኃላም ለሐዋሪያት ሁሉ ታየ፣ ከሁሉም ቦኃላ እንዲ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየ፣ እኔ ከሐዋሪያት ሁሉ የማንስ ነኝና” ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~8)

አሁን ጳውሎስ ማን ነበር? ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ሳኦል በመባል ይታወቅ ነበር። እርሱ አይሁዳዊ፣ በገማልያል እግር ሥር ቁጭ ብሎ የተማረ፣ ፈሪሳዊ፣ ለኃይማኖቱም በጣም የሚቀና ነበር (ፍልጵስዩስ 3፡4~7)፣ ስለዚህ ቤተክርስቲያንን አሳዳጅ ነበር፣ ማለትም ጌታ እስኪገለጥለትና ወደ ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ (የሐዋሪያት ሥራ 9፡22)፣ ከዚያም ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ትንሣኤም እንደሆነ ሊሰብክ ወጣ (የሐዋሪያት ሥራ 9፡20፣ 17፡18) በድንገት ከአለማመን ወደ ማመን የመጣ፣ በድንገት የጌታ ለእርሱ መገለጥ ከእራሱ የተረዳ ሰው ነው።

አንተስ ? ክርስቶስ ከመቃብር መነሣቱን ታምናለህ? አሁንስ ህያው እንደሆነና አንድ ቀን የራሱ የሆኑትን ቤተክርስቲያንን ሊወስድ እንደሚመጣ ታምናለህ ? ካላመንክ ከአማኞች ውስጥ አንዱ እንድትሆን እንጸልይለሃለን፣ በክርስቶስ ብታምን፣ንሰሀ ብትገባ፣

ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ብትመሰክር፣ ለኃጥያትህ ሥርየት ብትጠመቅ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል፣(ማርቆስ 16፡16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 2፡47)

## ትምህርት 17

## ክርስቶስ ተመልሶ እንደሚመጣ ለምን እናምናለን

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን፣ ከሞትም እንደተነሣ እናምናለን፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 ላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንን የክርስቶስን ሞት፣ መቀበር እና ትንሣኤን በተለያዩ የሰዎችን ቁጥር ጥቅሶ የዓይን ምስክሮችን እማኝ በማድረግ ይገልጻል፣ “ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ፦ ትንሣኤ የለም እንዴት ይላሉ? ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ፣ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው። እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፣ ደግሞም ክርስቶስን አሥነስቶታል ብለን በእግዚአብሄር ላይ ስለመሰከርን ሐሰተኞች የእግዚአብሄር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፣ ሙታን ግን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ፣ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፣ እስካሁን ድረስ በኃጥያታችሁ አላችሁ እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋላ። በዚህች ህይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን፣ አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷል” (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡12~20)

እኛ በክርስቶስ ትንሣኤ እናምናለን እንደዚሁም በዳግም ምጽዓቱ ተመልሶ እንደሚመጣ እናምናለን፣ ክርስቶስ እራሱ እንዲህ ብሏልና “ልባችሁ አይታወክ፣ በእግዚአብሄር እመኑ፣ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ እንዲህስ ባይሆን ባልኳችሁ ነበር፣ ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፣ ሄጄም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እውስዳችኋለሁ” ብሏል (ዮሐንስ 14፡1~3)

ጌታ ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ባረገበት ጊዜ ዘገባው እንደሚለው “ይህንም ከተናገረ ቦኃላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው፣ እርሱም ሲሄድ ወደ ሰአምይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፣ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ ደግሞም የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁትእንዲሁ ይመጣል” አሏቸው (የሐዋሪያት ሥራ 1፡9~11) አንዳንዶች ኢየሱስ አንድ ቀን ይመጣል መንግሥቱንም በኢየሩሳሌም ይመሰርታል በዚያም ከጻድቃን ጋር አንድ ሽህ ዓመት ይነግሣል ብለው የሚከራከሩ አሉ፣ ነገር ግን ሁለቱ

ነጫጭ ልብስ የለበሱ መላእክቶች ሲሆኑ ክርስቶስ ወደ ሰማይ እንደሄደ ዳግመኛም እንደሚመጣ መናገራቸውን እንዳነበብን እናስታውሳለን ከዚያ ውጪ እንደገና ወደዚህች ምድር መጥቶ ምዕመናንን አቋቁሞ አንድ ሺህ ዓመት ይነግሣል የሚለውም አልተናገሩም፡፡ በመጀመሪያ ጌታ በደቀመዛሙርቱ ዘመን ማለትም በህይወት እያሉ መንግሥቱ እንደሚቋቋም ተናግሯል (ማርቆስ 9፡1)፣ ሁለተኛ ኢየሱስን ሞት እንኳን መንግሥቱን ከመመስረት እንደማያግደው ተናግሯል (ማቴዎስ 16፡ 18፣19)፣ ሦስተኛ  በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ የእግዚአብሄር መንግሥት ወይም የክርስቶስ መንግሥት መገኘቱን እናነባለን፡፡ (ሐዋሪያት ሥራ 8፡12፣ ቆላስያስ 1፡13፣ ዕብራዊያን 12፡28) ጸሐፊው የእግዚአብሄርን መንግሥት ተቀብለናል ይላል፡፡  በመጨረሻም ቅዱሣት መጽሐፍት ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ (1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡15፣  ይህ ሁሉ ማለት መንግሥቱ እና ቤተክርስቲያኑ አንድ ናቸው፣ መሠረቷም ክርስቶስ ነው፣ አሁንም በዚህች መንግሥቱ ቤተክርስቲያን ላይ እየገዛ ነው፣ እውነት ከሆነ ክርስቶስም ተመልሶ መንግሥት ሊመሰርትና በላዩ ላይ አንድ ሺህ ዓመት ሊነግስ አይመጣም ማለት ነው፣ ይህን ካላድረገ ምን ያደርጋል?

የጌታን ተመልሶ መምጣትን አስመልክቶ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ሲናገር እንዲህ ይላል “የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፣ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፣ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሣት ይቀልጣል፣ ምድርም በእርሷም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል፣ ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ የእግዚአብሄርን ቀን መምጣት እየ፣ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሄርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሣት ይፈታል፣ ነገር ግን ጻድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደተስፋ ቃል እንጠብቃለን፣ ስለዚህ ወዳጆች ሆይ ይህን እየጠበቃችሁ ያለ ነውርና ያለነቀፋ ሆናችሁ በሠላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ” ይላል (2ኛ ጴጥሮስ 3፡10~14)

ጳውሎስም ሲጽፍ እንዲህ አለ “ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን፡፡ ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና፡፡ በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፡፡ እኛ ህያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፣ ጌታ እራሱ በትዕዛዝ በመላዕክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሄርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፡፡ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፣ ከዚያም በኋላ እኛ ህያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፣ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን፣ ስለዚህ

እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተፅናኑ” (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13~18)

ጳውሎስ ሲቀጥል ጽሁፉን እንዲህ ይላል “ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላዕክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን፣ መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሄር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና፡፡ እግዚአብሄርን የማያውቁትን፣ ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፣ በዚያም ቀን በቅዱሣኑ ሊከብር ፣ ምስክርነታችንን አምናችኋልና “ ይላል (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7~9)

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ ብሏል “ቦኃላም መንግሥቱን ለእግዚአብሄር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፊጻሜ ይሆናል” (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡24)

አሁን ካነበብናቸው ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች ላይ ያለውን ነገር ጠቅለል አድርገን እንመልከት፦ አንደኛ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቶአል፣ ሁለተኛ እንደ ሄደ ይመጣል በደመና ይመጣል፣ ሦስተኛ በሌሊት እንደሌባ ይመጣል ማለትም ሳያውቋ ድንገት ይመጣል፣ አራተኛ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉም ነገር ይሆናል፣ ሰማይና ምድር በውስጣቸውም ያሉት ሁሉ ይጠፋሉ፣ አምስተኛ በክርስቶስ መምጣት ጊዜ ጻድቃን ሙታን ይነሣሉ፣ እነርሱና ህያዋን ሆነው በአየር ላይ ሊገናኙት በዚያም ከጌታ ጋር ለዘላለም ለመሆን በአንድነት ይነጠቃሉ፡፡ ስድስተኛ በመምጣቱ ጊዜ እግዚአብሄርን የማያውቁትን እና ወንጌል ያልታዘዙትን ይበቀላል፡፡ ክርስቶስ አለማወቅን ለወንጌል አለመታዘዝ ሰበብ አድርጎ አይቀበልም፣ ተናግሯልና “እንዲህም አላቸው ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈርድበታል” (ማርቆስ 16፡15~16) ወንጌል የሚታዘዙ ይድናሉ፣ በምንም መልኩ ቢሆን ለወንጌል መታዘዝ ያልቻሉ ያልፈቀዱ ይጠፋሉ፣ ጌታ በፍርድ ቀን ሌላ እርምጃ እንደሚወስድ ከቅዱሣት መጻህፍት ምንም ፊጭ የለንም፣ ክርስቶስ ሲናገር “የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፣ እኔ የተናገርኩት ቃል እርሱ በመጨረሻ ቀን ይፈርድበታል” ብሏል (ዮሐንስ 12፡48) የዕብራዊያን ጸሐፊም “ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ ቦኃላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው” ይላል (ዕብራዊያን 9፡27)ክርስቶስ በፍርድ ቀን በፊቱ ለሚቀርቡት ኃጥያተኞችና ጻድቃን እንዲ ይላቸዋል “እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ” ብሏል (ማቴዎስ 25፡46)

ሰባተኛ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ክፉዎች ከመንግሥት ወይም ከቤተክርስቲያን ተሰብስበው ወደ ገሃነም ይጣላሉ (ማቴዎስ 13፡41) እና ጻድቃን እና ታማኙን የሚወክል መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሄር ተላልፈዋል፣ ከጌታ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ፣ ክርስቶስ

እንዲህ ብሏልና “በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካምም ያደረጉ ለህይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ” አላቸው (ዮሐንስ 5፡28~29)

ስለዚህ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት እናምናለን፣ ጌታ አስጠንቅቆናል፣ፈቃዱን አሳውቆናል፣ ደህንነትን ሰጥቶናል፣ እንደዚሁም እሱን የምንቀበልበትን እድሎች ፈጥሮልናል፣ ስለዚህ ቃሉን ሰምተን እድሉን ተጠቅመን፣ ለእርሱ ዳግም ምጽዓት መዘጋጀት የኛ ፋንታ ነው።

በክርስቶስ ታምናለህ? እሱን ታዘሃል? በዳግም ምጽዓቱ ከእሱ ጋር ለመገናኘት ትፈልጋለህ? ታዘህ ከሆነ መልካም ነው፣ ካልሆነ ግን እና እሱን ለመገናኘት ካልተዘጋጀህ፣ በክርስቶስ እመን፣ ከኃጥያትህ ንሠሀ ግባ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክር፣ ከዚያም ለኃጥያትህ ሥርየት በውኃ ውስጥ በመቀበር ተጠመቅ፣ ይህንን ስታደርግ ጌታ ያድንሃል፣ ቢቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምርሃል፣(ማርቆስ 16፡16፣ ሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 47)፣ እስከ መጨረሻው ታማኝ ክርስቲያን ሆነህ ከኖርክ ጌታ የህይወት አክሊልን ይሰጥሃል (ዮሐንስ ራዕይ 2፡10)

## ትምህርት 18
## ዛሬ ክርስትና ለምን አስፈለገ

ዛሬ በዓለም ዙሪያ የተለያዩ ኃይማኖቶችን የሚወክሉ ብዙ ኃይማኖቶች አሉ። ያም ሆኖ እንደ ክርስትና ኃይማኖት ያለ የለም። እንደ ክርስትናም አስፈላጊ የሆነ ኃይማኖት የለም።

ክርስትና ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ  በመሆኑ ላይ የተመሰረተ ነው። ክርስትና የክርስቶስን ትምህርት በሚታዘዙ ሰዎች ይተገበራል፣

እኛ በክርስትና እናምናለን፣ ወይም የክርስቶስን ኃይማኖት እንሰብካለን፣ ነገር ግን ከሁሉም በላይ አስፈላጊው የአምልኮ ሥርዓቱ ነው፣ ያዕቆብ ሲናገር እንዲህ ይላል “ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምጸሙ ብቻ አትሁኑ” ይላል (ያዕቆብ 1፡22) ቀጥሎም እንዲህ ይላል “ነገር ግን ነጻ የሚያወጣ ፊጹሙን ተመልክቶ የሚጸናበት ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሣ ያልሆነ ነው በሥራው የተባረከ ይሆናል” (ያዕቆብ 1፡25) አሁንም እንዲህ ይላል “አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሄርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው። ንጹህ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሄር አብ  ዘንድ ይህ ነው፣ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው” (ያዕቆብ 1፡26~27)

በዛሬው ጊዜ ዓለም ምን ያህል ክፉ እንደሆነ ሁላችንም

እናውቃለን። የሥነ ምግባር እሴቶች ወደ አዲስ ዝቅተኛ ደረጃ ወድቀዋል። ለሥልጣን ክብር ማጣት ብየቦታው ይታያል። ጉቦና ሐቀኝነት የጎደለው ሥርዓትውስጥ ናት፣ ነገሮች እየሄዱ ባለበት ሁኔታ ዓለም ወደ ምን እየመጣች ነው? በእርግጠኝነት አንዳንድ ለውጦች ያስፈልጉናል ግን ዓለምን በተሻለ ሁኔታ ሊለውጠው የሚችለው ምንድነው? ዓለም ከምንም ነገር በላይ የሚፈልገው ንጹህ የሆነ የአዲስ ኪዳን ክርስትና፣ የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ኃይማኖት እንደሆነ አምናለሁ ስልህ ሊገርምህ ይችላል፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የሰው ልጅ ብቸኛ ተስፋ ነው፣ እኔ የምለው ወንዶቹም ሴቶቹም የተለያዩ ኃይማኖቶችን ሞክረዋል በሚለው መሰረት ነው፣ ወታደራዊ ኃይልን ሞክረዋል ከደስታ ቦኃላ ሄደዋል ለቁሳዊ ነገሮች አጽናኦት ሰጥተዋል፣ ዓለም ሁሉንም ሞክረዋል ግን ይህ ዓለምን የተሻለ አድርጎታል? ሰው የበለጠ ደስተኛ ነው? አይ ! በጭራሽ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የቀረው እግዚአብሄር፣ ክርስቶስ እና ክርስትና ብቻ ነው፣

በመንፈሳዊጉዳዮችክርስትናለሰውየሚያስፈልገውነው፣በሁሉም ኃይማኖታዊቡድኖችአስተሳሰብክርስትናብቻሳይሆንበመጽሐፍቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው የክርስትቶስ አንድ ሃይማኖት ነው፣ በክርስቶስ ማመን፣ ለአንድ ወንጌል መታዘዝ፣ የአንድ ቤተክርስቲያን አባላት መሆን፣ አንድ ስም ለብሶ፣ አንድ ዓይነት ነገር ማስተማር፣ በአንድነት በመሥራት፣ በአንድ ተስፋ ላይ የተመሰረተ ነው፣ ክርስቶስ ሁላችንም በእርሱ አንድ እንድንሆን ጸለየ (ዮሐንስ 17)፣ መለያየት በመጽሐፍ ቅዱስ ተውግዟል (ሮሜ 16፡17~18) ይህም ብቻ ሳይሆን የሰዎች ትምህርት መለያየትን ስለሚያስከትል ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ይቃረናል፣(ማቴዎስ 7፡ 21~23)

ክርስትናን የሚከተሉ ሰዎች ጥሩ ዜጋ ይሆናሉ፣ የሀገራቸውን ህግ በማክበር ያምናሉ፣ ይህን አስመልክቶ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሲናገር “ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሄር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፣ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች፣ በእግዚአብሄር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሄርን ሥርዓት ይቃወማል፣የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ።ገዢዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና፣ ባለሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ፣ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፣ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሄር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና፣ ክፉ ብታደርግ ፍራ፣ ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሄር አገልጋይ ነውና ስለዚህ ስለቁጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስል ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው” (ሮሜ 13፡1~5)። ክርስቲያኖች ለመንግሥት ግብር መክፈል ልክ መሆኑን ያምናሉ፣ ምክንያቱም የእግዚአብሄርን ቃል ጳውሎስ

እንዲህ ይነግረናል “ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁና፣ በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሄር አገልጋዮች ናቸውና፣ ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፣ ግብር ለሚገባው ግብርን ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን መፈራት ለሚገባው መፍራትን ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ” ይላል (ሮሜ 13፡6~7) ክርስቲያን መሪዎቻቸውን በማክበር ያምናሉ ጴጥሮስ ሲናገር “ሁሉን አክብሩ፣ ወንድሞችን ውደዱ እግዚአብሄርን ፍሩ፣ንጉሥን አክብሩ” ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡17) እንደዚሁ ሀገራችንን መውደድ አለብን ። የምናየውን የተለማመድነውን ሁሉ ካልወደድን ነገሮችን በተሻለ ሁኔታ ለመለወጥ መሞከር አለብን። በእርግጠኝነት መሪዎቻችን ላይ በተቃዋሚነት መሥራት ሥልጣንን አለማክበር፣ ግብር አለመክፈል ወዘተ ክርስቲያናዊ ባህሪይ አይደለም። አንዳንዶች ከሀገራቸው ወይም ከመንግሥታቸው የሚያገኙትን ሁሉ ይፈልጋሉ ነገር ግን በምላሹ መስጠትን በፊጹም አይፈልጉም። ክርስትና በአንዲት ሀገር እያደገ ሲሄድ ለሥልጣን ማክበር፣ የሀገሪቱን ህግጋት ማክበር እና ህዝባችን እድገት እንድታደግ መርዳት ይሆናል።

ክርስትናን የሚለማመዱ ሰዎች ማህበራዊ ጥፋቶችን ይቃወማሉ፣ ይህም ጽንስ ማስወረድ፣ የአልኮል መጠጦችን መጠጣት፣ ፊቺ፣ እና በማንኛውም ምክንያት ዳግም ጋብቻ፣ ቁማር፣ ግብረ ሰዶም ጉቦ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። ጳውሎስ እንዲህ ይላል “ወይስ አመጸኞች የእግዚአብሄርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሣቱ ሴሰኞች፣ ቢሆኑ፣ ወይም ጣኦትን የሚያመልኩ፣ ወይም አመንዝሮች፣ ወይም ቀራጮች፣ ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ፣ ወይም ሌቦች፣ ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች፣ ወይም ተሳዳቢዎች፣ ወይም ነጣቂዎችየእግዚአብሄርንመንግሥትአይወርሱም”ይላል(1ኛቆሮንቶስ 6፡9~10)፣ ከላይ የተጠቀሱትን እና መሰል ነገሮችን የማይተገብሩትን ኃይማኖት መገመት ትችላለህ ? ሌሎች ኃይማኖቶች ብዙ ኃጥያተኛ እና ሥርዓትየጎደላቸው ልማዶችንያበረታታሉ ወይምይደግፋሉ። ኘክርስትና አይደሉም።ክርስትናበሰዎችውስጥምርጥባህሪይይፈጥራልክርስቲያን ነን የሚሉ ነገር ግን በመጥፎ ነገር የተጠመዱ ካሉ ክርስትና ስህተት ነው ማለት አይደለም ነገር ግን እንዲህ ያሉ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ሰዎች ተሳስተዋል እንጂ። ስለዚህም በኃጥያት ውስጥ ናቸው ማለት ነው፣ አሁንም ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣ “የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፣ርኩሰት፣መዳራት፣ጣኦትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ጥል፣ክርክር፣ቅ ንዓት፣ቁጣ፣አድመኝነት፣መለያየት፣መናፍቅነት፣ምቀኝነት፣መግደል፣ስ ካር፣ዘፋኝነት፣ይህንም የሚመስሉ ነው፣አስቀድሜ እንዳልሁ፣ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሄርን መግሥት አይወርሱም” (ገላቲያ 5፡19~21) እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሄርን መንግሥት አይወርሱም ሲል በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከቀጠሉ አይድኑም፣

የእግዚአብሄር መንግሥት ወይም በቤተክርስቲያን አይሆኑም ማለቱ ነው፣ ነገር ግን ከዚህ ሥራቸው አምነው፣ ንሠሀ ገብተው፣ ክርስቶስን አምነው ጌታን ከታዘዙ፣ ጌታ ያድናቸዋል፣ ቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምራቸዋል፣(ማርቆስ 16፡16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡47)፣ ከዚያ እንደ ክርስቲያን ከዚያ ክፉ ሥራ ተመልሰው በአዲስ ህይወት በመመላለስ ትክክለኛውን የክርስትና ህይወት ይለማምዳሉ ማለት ነው።

ክርስትናን የሚለማመዱ ሰዎች ህይወታቸውን ለማሻሻል ይሞክራሉ ፣ ንጹህ አካል፣ እና ንጹህ ልብስ እና ንጹህ ቤት እንዳላቸው ያምናሉ፣ ለልጆቻቸው ትምህርት ለመስጠት ይሞክራሉ፣ እነስይ ታታሪ ሠራተኞች ናቸው እና ለሰዎችም ታማኝ ለመሆን ይጥራሉ፣ ጳኡሎስ እንዲህ ይላል "እርስ በእርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፣ ሌላውን የሚወድ ሕኝ ፈጽሞታልና" (ሮሜ 13፡8) እንደገና እንዲህም ይላል "ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፣ክፉውን ነገር ተጸየፉት፣ከበጎ ጋር ተባበሩ፣ በወንድማማች መዋደድ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ፣ እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ፣ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፣ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፣ ለጌታ ተገዙ፣ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፣ በመከራ ታገሱ፣ በጸሎት ጽኑ፣ ቅዱሣንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፣እንግዶችን ለመቀበል ትጉ፣የሚያሳድዷችሁን መርቁ፣ መርቁ እንጂ አትርገሙ። ደስ ከሚለው ጋር ደስ ይበላችሁ፣ ከሚያለቅሱ ጋር አልቅሱ፣ እርስ በእርሳችሁ በአንድ ሀሳብ ተስማሙ፣ የትዕቢትን ነገር አታስቡ፣ ነገር ግን የትህትናን ነገር ለመሥራት ትጉ ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ፣ ለማንም ስለክፉ ፋንታ ክፉን አትመልሱ፣ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ፣ ቢቻላችሁስ ከእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሠላም ኑሩ። ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ፣ ለቁጣው ፋንታ ስጡ እንጂ ፣ በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሣለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎልና፣ ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሣት ፍም ትከምራለህና። ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ" (ሮሜ 12፡9~21)።

ይህንን የክርስትና ህይወት የተለማመዱ ክርስቲያኖች በሰዎች መካከል መልካም በማድረግ ይታወቃሉ፣ ይህም ደሆችን መርዳት ወላጅ አልባዎችን ማሰብ የመሣሠሉትን ነው፣ ጌታ እንዲህ ይላል "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" ይላል (ማቴዎስ 5፡16)

አሁን በዚህ ሀገር ወይም በየትኛውም ሀገር እና በዓለም ላይ ባሉ ሀገራት ሁሉ የዚህ ዓይነት ክርስትና ሲተገበር የሰው ልጅ ሁሉ ተጠቃሚ ይሆናል። ከዚህም በላይ ክርስትናን እየተቀበሉ እና ክርስትናን እየተለማመዱ ሲሄዱ ዓለም ቀስ በቀስ እድገት እያሳየች ነው፣ ክርስትና ነጎሮችን ሊለውጥ ይችላል ነገሮችንም ይለውጣል፣ ማለትም እንደ

መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲተገበር ማለት ነው። ይህን የሚያደርጉ ሁሉ ወደ መልካም ነገር ተለውጠዋል።

ግን ከዬት ይጀመር ነው ጥያቄው፣ ከራስህ ጀምር፣ ክርስቲያን ካልሆንክ እንግዲያውስ ከክርስቲያኖች አንዱ ሁን፣ ከዚያም ክርስቲናን ስትለማመድ ሌሎቸም እንዳደረግክ እንዲያደርጉ ማበረታታት ትቸላለህ።

በኢየሱስ ክርስቶስ እምነህ፣ ከኃጥያትህ ንሠሃ ገብተህ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክረህ ለኃጥያትህ ሥርየት ተጠምቀህ ክርስቲያን ትህናለህ፣ ይህንን በተመለከተ የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍን አንብብ አጥና፣ ይህንን ስታድርግ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል፣ክርስቲያን ነህ ማለት ነው።እነዝህን አንብባቸው(ማርቆስ 16፡16፣ ማቴዎስ 10፡32፣ሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ ሐዋሪያት ሥራ 2፡47)

## ትምህርት 19

## በክርስቶስ ደም ውስጥ ኃይል ለምን ኖረ

ደም ለአንዳንድ ሰዎች አስደሳች ህሣብ ላይሆን ይቸላል ምክንያቱም መቆረጥ፣ መቁሰል ወይም ሞትንም ሊያመለክት ይቸላል። በኃይማኖታዊው ዓለም ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ይህን ከቃላቶቻቸው ውስጥ ለማጥፋት ሞክረዋል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሄር የሰውን ኃጥያት ለማስተሰረይ የእንስሳት መስዋዕቶቸ ወይም የደም መስዋዕቶቸን ይፈልጋል። ደም በጣም አስፈላጊ ነበር ምክን ያቱም ህይወትን ይወክላል ምክንያቱም ህይወት ነፍስ ያለው በደም ውስጥ ነበር በዚህም ምክንያት ደም መብላት የተከለከለ ነው፣ ይህንን እንዲህ እናነባለን “የሥጋ ህይወት በደሙ ውስጥ ነውና ደሙም ከህይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሰዊያው ላይ ለነፍሣቸሁ ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት፣ ስለዚህ የእስራኤል ልጆቸ፦ ከእናንተ ማንም ደምን አይበላም፣ በመካከላቸሁም ከሚኖሩ እንግዶቸ ማንም ደምን አይበላም አልሁ” (ዘሌዋዊያን 17፡ 11~12)

ብሉይ ኪዳን እራሱ በደም ተወስኗል፣ የዕብራዊያን ፀሐፊ ሲነግረን “ሙሴም ትዕዛዛትን ሁሉ እንደሕጉ ለሕዝቡ ሁሉ ከተናገረ ቦኃላ፣ የጥጆቹንና የፍየሎቸን ደም ከውኃና ከቀይ የበግ ጠጉር ከሂሶጵም ጋር ይዞ እግዚአብሄር ያዘዘላቸሁ የኪዳን ደም ይህ ነው ብሎ በመፅሐፉና በሕዝቡ ሁሉ ላይ ረጨው እንዲሁም በድንኳኒቱና በማገልገያው ዕቃ ሁሉ ደምን ረጨ፣ እንደ ሕጉም ከጢቂቶቸ በቀር ነገር ሁሉ በደም እነፃል፣ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም” (ዕብራዊያን 9፡19~22) እንደገና ይኼው ፀሐፊ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በደም እንደሚገባ ነግሮናል “በሁለተኛይቱ ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ

ይገባበታል፣ እርሱም ስለራሱና ስለሕዝቡ ስህተት የሚያቀርበውን ደም ሳይይዝ አይገባም" (ዕብራዊያን 9፡7)፣ " የኮርማዎቸና የፍየሎቸ ደም ኃጥያትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና" (ዕብራዊያን 10፡4)

ምንም እንኳን የሚሠውት እንስሶቸ ከመንጋው ውስጥ የተሻሉ ሊሆኑ ቢቸሉም ነውርና እድፍ ባይኖርባቸውም እንስሳት ብቻ ነበሩ። ስለዚህ ፊፁም መስዋዕት ያስፈልግ ነበር፣ የእንስሳት ደም የዚያን ፊፁም መስዋዕት ደም ብቻ ያመለክታል። ነገር ግን እንስሶቸ ኃጥያትን ሊያስወግዱ ስላልቻሉ፣ ሰውም ራሱ ኃጥያተኛ ስለ ነበረ ራሱንም ሆነ ሌሎቸን ማዳን ስላልቻለ ፊፁም መስዋዕት ሆኖ የሚያገለግለው ማን ነው? አንድ ብቻ ነበር እርሱም የሕያው እግዚአብሄር ሊጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ያለ ኃጥያት ኖረ፣ ጴጥሮስ ኃጥያት እንዳልሠራ ተናግሮአል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡22) ከኃጥያት ውጪ ስለኖረ ሕጉን ፊፁም አድርጎ ስለኖረ ለፈተናም ባለመሸነፍ ስለዓለም ኃጥያት በመስቀል ላይ መሞት ቻለ።

እኛ የክርስቶስን ደም አፅናኦት የሚያሳዩ አንዳንድ መዝሙሮቸን እንዘምራለን፣ "በደሙ ውስጥ ኃይል አለ" የተባለውን እና ሌላኛው ደግሞ "ኃጥያቴን ምን ያጥበዋል? ከኢየሱስ ደም በቀር ሌላ አይደለም" ይላል፣ እነዚህ ቃላቶቸ ምን ያህል እውነት ናቸው

ማዳን የማይቸሉ ብዙ ነገሮቸ አሉ፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው የእንስሳት ደም ሊያድን አልቻለም፣ ሕጉም ሊያድን አልቻለም፣ ሰዎቸን ወደ ክርስቶስ ብቻ አመጣ፣ ጳውሎስ ይህን ሲናገር "ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መፅሐፍ ከኃጥያት በታቸ ሁሉን ዘግቶታል፣ እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታቸ እንጠብቅ ነበር፣ እንደዚህ በእምነት እንፀድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታቸን ሆኖአል፣ እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታቸ አይደለንም" (ገላቲያ 3፡22~25) በሕግ *ሥራ* አለመዳናቸን ብቻ ሣይሆን በራሳቸን መልካም *ሥራም* መዳን አንቸልም፣ ጳውሎስ ይህንንም እንዲህ ይላል "እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፣ የማንታዘዝ፣ የምንስት፣ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደባሪያዎቸ የምንገዛ፣ በክፋትና ምቀኝነት የምንኖር፣ የምንጣላ ነበርን፣ ነገር ግን የመድኃኒታቸን የእግዚአብሄር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፣ እኛ ስላደረኘው በፅድቅ ስለነበረው *ሥራ* አይደለም ያን መንፈስም፣ በፀጋው ፀድቀን በዘላለም ህይወት ተስፋ ወራሾቸ እንድንሆን በመድኃኒታቸን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው" (ቲቶ 3፡3~7)

ጴጥሮስም በብር ወይም በወርቅ አይደለም የዳንነው ይላል

"ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በውርቅ ሳይሆን፣ ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደበግ ደም በበኩር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ" (1ኛ ጴጥሮስ 1፡18~19) ሰው በህይወት ዘመን ውስጥ ማንኛውንም ነገር ሊገዛ ወይ ሊሰጥ ይችላል ነገር ግን ደህንነትን ሊገዛ አይችልም፣ ማዳንን ከዬትም አይገዛም፣ እንጊድያውስ በቁሳዊ ነገሮች ላይ አለመታመን ጥበብ ይሆናል፣ በመጨረሻም የሰው ኃይማኖተኞች እና የሰዎች ትምህርት እና ትዕዛዛት ሁሉ ወደ መግሥተ ሰማያት አይወስዱም፣ ክርስቶስም እንዲህ ብሏል "የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ" (ማቴዎስ 15፡9) ዮሃንስም እነዚህን የሐሰት አስተማሪዎችን ሠላም ማለት ራሱ ከእነሱ ጋር እንደመተባበር ነው ይላል (2ኛ ዮሃንስ 11)፣ ጳውሎስም እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን ሳይሆን መከፋፈልን የሚያመጡ እንደሆነ ይናገራል (ሮሜ 16፡17~18)

ኃጥያተኞች በመሆናችን ለመዳን አንድ መንገድ ብቻ አለን እርሱም በክርስቶስ መሥዋዕት እና በደሙ መፍሰስ ነው። በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ የክርስቶስን ደም አስፈላጊነት የሚያጎሉ ብዙ መግለጫዎች አሉ፣ ጳውሎስ ከእግዚአብሄር ጋር እንደታረቅን ወይም በክርስቶስ ደም የእግዚአብሄር ወዳጆች ለመሆን እንደቻልን ተናግሯል። እንዲሀ ሲል " እግዚአብሄር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፣ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሠላም አድርጎ በምድር ወይም በሠማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷል" (ቆላሲያ 1፡19~20) ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በአንድ ወቅት ከእግዚአብሄር ርቀው እንደነበሩ ነገር ግን በክርስቶስ ደም ወደ እግዚአብሄር እንዲቀረቡ ፅፏል። ይህም አይሁድም ሆኑ አህዛብ በክርስቶስ አንድ እንደሆኑ ገልፆአል። የከፍልፍል መካከለኛ ግድግዳ ተሰብሯል። ማለትም አሮጌው ሕግ ተወግዷል ይህም የሚለያቸው ግድግዳ (ኤፌሶን 2፡13~17)

ጳውሎስ ስለክርስቶስና ስለደሙ ሲናገር ለኤፌሶን ክርስቲያኖች እንዲህ ይላል "በውድ ልጁም፣ እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን፣ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ሥርየት" ይላል (ኤፌሶን 1፡7)፣ ለቆላስያስ ክርስቲያኖች ሲናገር ደግሞ "እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፣ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጥያታችን ሥርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን" ይላል (ቆላስያስ 1፡14)፣ ክርስቶስም የጌታ እራት የወሰዱ ጊዜ እንዲህ አለ "ስለብዙዎች ለኃጥያት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴዎስ 26፡28) እነዚህ በክርስቶስ ደም የዳኑት ወደ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ይጨመራሉ (ሐዋሪያት ሥራ 2፡47)፣ ጳውሎስም በኤፌሶን ላሉት ሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት

ለመንጋው ሁሉና ለራሳቸሁ ተጠንቀቁ" (ሐዋሥራ 20፡28) በኤፌሶን 5፡25 ላይም ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ወይም ለአካሉ ደሙን እንዳፈሰሰ በዚህ ደም እንደዋጇት ይነግረናል፣ በሌላ አነጋገር ለቤተክርስቲያን መገኘት ክርስቶስ ታላቅ ዋጋ መክፈሉን ነው፣ እኛም እንደክርስቲያን በክርስቶስ ደም የነፃን ነን "ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳቸን ኅብረት አለን፣ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጥያት ሁሉ ያነፃናል" (1ኛ ዮሐንስ 1፡7)፣ በመጨረሻ ፣ እንደ እግዚአብሄር ህዝብ ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የምንሰበሰበውና የምንወስደው የጌታ እራት የክርስቶስ ደም ተምሣሊት ነው (ሐዋሥራ 20፡7)፣ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎቸ ሲናገር ይህን ከጌታ እንደተቀበለና ይህን የጌታ እራትን መካፈል እንዳለባቸው እንጀራ እና የወይን ጭማቂ መውሰድን ተናግሯል፣ "እንደዚሁም ከእራት ቦኃላ ፅዋውን ደግሞ አንስቶ፦ ይህ ፅዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፣ በጠጣቸሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፣ ይህን እንጀራ በበላቸሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ፅዋ በጠጣቸሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላቸሁና፣ ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ፅዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት ሰው ግን ራሱን የፈትን፣ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከፅዋውም ይጠጣ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና" (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23~29)

ስለክርስቶስ ደም ብዙ የተባሉ ነገሮቸ አሉ፡፡ ለምን እንደፈሰሰ፣ እናም በውስጡ ስለአለው ኃይል ብዙ ተብሏል፡፡ እስቲ ስለዚህ ትክክለኛ መልስ ለማግኘት ወደ ቅዱሳን መፅሐፍት እንሂድ፦

1.ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ ስለ ሰው ኃጥያት ደሙን አፍስሶ ፍፁም መስዋዕት ነበር

2.በክርስቶስ ደም መፍሰስ አሮጌው ሕግ ተወግዶ አዲስ ኪዳን በደሙ ታትሟል፡፡

3.የዳንነው በክርስቶስ ደም ነው፡፡ በደሙ የምንድነው በመታዘዝ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ክርስቶስ ሰው እንዲድን በእርሱ ማመን፣ ከኃጥያቱ ተፀፅቶ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክሮ እና መጠመቅ ( በውኃ ውስጥ በመቀበር) እንዲድን ወይም የኃጥያቱ ስርየት እንዲያገኝ ተናግሯል፣(ማርቆስ16፡16፣ ሐዋሥራ2፡38)፣አንድ ሰውጌታን በመታዘዝ በጥምቀት ውኃ ከክርስቶስ ደም ጋር ሲገናኝ የጌታን ሞት ጥቅም ያገኛል፡፡ ይኼውም በክርስቶስ ደም ኃጥያትን ማጠብ ነው፣ ይህንንም በሮሜ6 ላይ እናነባለን፣ እንደዚሁም ለሳኦል የተነገረው ተነስና ተጠመቅ ከኃጥያትህም ታጠብ ሲባል ከኃጥያቱ እንደሚታጠብ እርግጠኛ ሆነ፣ አምኖ ንሰሐ ገብቶ ተጠምቆ ኃጥያቱ ከእሱ ላይ ተወገደ፡፡ እነዚህን ስናነብ "አሁንስ ለምን ትዘገያለህ ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ

ከኃጥያትህም ታጠብ” (ሐዋሥራ 22፡16)፣ እንዲሁም ክርስቶስ ደሙ ለሰው ልጅ የኃጥያት ሥርየት እንደሚፈስ ተናግሯል (ማቴዎስ 26፡28፣ ኤፌሶን 1፡7)፣ በሐዋሥራ 2፡38፣ ላይ ጴጥሮስም ለተሰበሰቡት ብዙ ሕዝቦች የተናገረው እያንዳንዳቸው ንሰሐ ገብተው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከተጠመቁ የኃጥያት ሥርየትን እንደሚያገኙ ነገራቸው እነሱም አደረጉጥ ከዚያም ጌታ ወደ ቤተክርስቲያን የሚድኑትን ይጨምር ነበር (ሐዋሥራ 2፡47)፣ ስለዚህ አንድ ሰው ለመዳን ከፈለገ ማመን አለበት፣ ንሠሐ መግባት አለበት፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መመስከር አለበት፣ ከዚያ መጠመቅ አለበት፣ ይህንን በማድረጉ ከክርስቶስ ደም ጋር ይገናኛል፣ ኃጥያቱም ይሰረይለታል።

4.የጌታ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተዋጀች ናት፣ ስለዚህ በደም የተገዛች እና በጣም አስፈላጊ ናት ። እኛም የዚህ ቤተክርስቲያን አባል ሆነን የክርስቶስ መሆን አለብን።

5.የክርስቶስ ደም ክርስቲያንን በክርስቶስ ብርሃን ሲመላለስ ወይም እንዲፈቃዱ ማፅዳት ይቀጥላል፣ ይህም ለእርሱ ታማኝ ሲሆን ማለት ነው።

6.የጌታ ሰዎች እንደመሆናችን መጠን የክርስቶስን ደም በማሰብ የክርስቶስን ሥጋ በማሰብ ኅብስቱን በመመገብ በየሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የጌታን እራት እንካፈላለን። ይህም እንድንበት ዘንድ ክርስቶስ የከፈለውን መስዋዕት እንድናስታውስ ይረዳናል።

ወዳጆቼ ! ክርስቶስ ሞቶልሃል። ኃጥያትህ ይሰረይ ዘንድ ደሙን አፍስሶልሃል። በእሱ ታምናለህ ? ወንጌልን ታዘሃል? ካልታዘዝክ፣ እንድትታዘዝ እናበረታታሃለን፣ ጌታ ያደረገልህን ማዳን አለመቀበል ምንኛ አሳፋሪ ነው።

## ትምህርት 20
## መሰረቱ ለምን አስፈላጊ ሆነ

እንደምናውቀው በዚህ ግዑዝ ዓለም ቤትን፣ አፓርታማ፣ ሕንፃን፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ለመሥራት ሲታሰብ በትክክለኛ መሠረት ላይ መገንባት አስፈላጊ ነው፣ በሥራም ሆነ በሙያችን ውጤታማ ልንሆን ብንሄድ እንኳን በቂ ትምህርት ወይም ሥልጠና በማግኘት በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልግ እንገነዘባለን። የዚህን መሰረት አስፈላጊነት ወይም ለወደፊት የመዘጋጀት አስፈላጊነትን ስናስተውል አንዳንድ መጥፎ ጊዜያት ውስጥ እንገኛለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለቱ ኝበኞች አንዱን በዓለት ላይ የሠሩትን እና ሌላውን በአሸዋ ላይ የሠሩትን በመጥቀስ ጥሩ መንፈሳዊ መሠረት እንደሚያስፈልግ ገልፆአል። “ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።

ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፣ በዓለት ላይም ስለተመሰረተ አልወደቀም። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል፣ ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፣ ወደቀም አወዳደቁም ታላቅ ሆነ" (ማቴዎስ 7፡24~27)

ኢየሱስ ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ ላይ ጥበበኛና ሞኝ የሆኑትን ሁለቱን ምድራዊ ኻበኞች በማነፃፀር አሳይቷል። ጥበበኛ መንፈሳዊ ገንቢ ቃሉን ከክርስቶስ በመሆኑ ሰምቶ የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል፣ ጌታን በመታዘዝ በክርስቶስ ላይ ስለሚገነባ ጥበበኛ ግንበኛ ነው፣ ክርስቶስና ትምህርቱ መንገዱ እስኪመጣ ድረስ ባሕሉንና ትውፊቱን፣ ዓለማዊውን፣ የሰውን ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎችን ሳይቀር ይቆፍራል፣ በዚያም ይገነባል፣ እሱ እውነት አለው፣ ክርስቶስ አለው፣ እሱ ክርስቲያን ነው፣ የጌታ ቤተክርስቲያን አባል ነው፣ ምንም ሊያንቀሳቅሰው አይችልም፣ የሚይዘው ነገር አለው፣ የዘላለም ህይወት ተስፋ አለው።

ኢየሱስ የተናገረው ሌላው ሰው ሞኝ ግንበኛ ነው፣ የክርስቶስን ቃል ሰምቷል፣ ነገር ግን እርሱን መታዘዝ ተስኖታል፣ አያምንም፣ ምናልባት ብዙ ጊዜ እንዳለው ያስባል፣ እሱ በቂ ነው ብሎ ሊያስብ ይችላል፣ ወይም የሰዎችን ትምህርት ተከትሎ ሂዶ ሊሆን ይችላል ችግሩ ምንም ይሁን ምን እውነታው ግን ጌታን አለመታዘዝ ነው፣ እና ስለዚህ በመጨረሻ የሚገነባው ነገር ይፈርሳል፣ ጥፍቷል እናም ከዘላለም ህይወትም ይጠፋል።

በጥንት ዘመን ነቢዩ ኢሳያስ መሰረት በፅዮን የሚመሰረትበትን ቀን አመልክቷል፣ ያ መሰረት ክርስቶስ ሲሆን መሰረቱ በኢየሩሣሌም ይጣላል።ትንቢቱን እናንብብ "ስለዚህ ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል ፦ እነሆ በፅዮን ድንጋይን ለመሰረት አስቀምጣለሁ፣ የተፈተነውን፣ የከበረውን፣ የሚያምን አያፍርም" (ኢሳያስ 28፡16) እባክህን ስለመሰረቱ ገለፃ አስተውል፣ ድንጋይ ነው፣ የተፈተነ ድንጋይ፣ የከበረ የማዕዘን ድንጋይ እና አስተማማኝ መሰረት ይሆናል። እነዚህን ገላጭ ቃላቶች በኃላ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እናስተውላለን፣ እነዚህም ሁሉ አየሱስ ክርስቶስን ያመለክታሉ። ነገር ግን መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙሩ 118፡23 ላይ ይህንን መሰረት አመልክቷል "ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፣ ይህቺ ከእግዚአብሄር ዘንድ ሆነች ለዓይናችንም ድንቅ ናት" (መዝሙረ ዳዊት 118፡22~23) በተጨማሪ ይህ ትንቢት በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ መፈፀሙን እናያለን።

ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን ስንመለስ የምናነበው "ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ ለዓይኖቻችንም ድንቅ ነው የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን? (ማቴዎስ 21፡42)፣ በሉቃስ 20፡17~18 ላይ ለካህናት

አለቆቸና ሽማግሌዎቸ እንዲህ አላቸው "እርሱ ግን ወደ እነርሱ ተመልክቶ እንግዲህ ፦ ግንበኞቸ የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ ተብሎ እንደተፃፈው ይህ ምንድርነው? በዚያም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይቀጠቀጣል፣ የሚወድቅበትን ሁሉ ግን ይፈጫቸዋል" አለ (ሉቃስ 20፡17~18) ቃል በቃል ድንጋይ ወይም የማዕዘን ድንጋይ ለመሰረት ሊያገለግል ይቸላል ነገር ግን አንድ ሰው በላዩ ላይ ቢሰናከል ወይም ቢወድቅ ሊሰበር ወይም ሊገደል ይቸላል። በተመሣሣይም አንድ ሰው ላይ ቢወድቅ ያንን ሰው ሊያጠፋው ይቸላል፣ በሌላ አነጋገር ንብረቱ ጥቅም ላይ ሲውል በረከት ሊሆን ይቸላል ነገር ግን ቸላ ከተባለ ወይም አላግባብ ጥቅም ላይ ሲውል አጥፊ ኃይል ሊሆን ይቸላል በመንፈሳዊ ዓለት ክርስቶስም እንዲሁ ነው

ወደ ሐዋሪያት ሥራ መፅሐፍ ስንሄድ ጴጥሮስ ስለተፈወሰ ሰው ለካህናትና አለቆቸ ለፀሯቸም ሲናገር እንዲህ አላቸው "እናንተ በሰቀላቸሁት እግዚአብሄርም ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደህና ሆኖ በፊታቸሁ እንደቆመ፣ ለእናንተ ለሁላቸሁ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ ያታወቀ ይሁን፣ እናንተ ግንበኞቸ የናቃቸሁት፣ የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው፣ መዳኝም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎቸ የተሰጠ ስም ከሠማይ በታቸ ሌላ የለምና" (የሐዋሪያት ሥራ 4፡10~12)፣ ጳውሎስም እስራኤሎቸንና አይሁድን በተመለከተ እንዲህ አለ "እስራኤል ግን የፅድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም፣ ይህስ ስለምንድርነው? በሥራ እንጂ በእምነት ፅድቅን ስላልተከተሉ ነው፣ እነሆ በፅዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ ዓለት አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ እንደተፃፈ በእንቅፋቱ ድንጋይ ተሰናከሉ" (ሮሜ 9፡31~33)፣ እዚህ ጋ ጳውሎስ በትክክል ከ ኢሳያስ 28፡16 ነው ይህን ጥቅስ የጠቀሰው።

ግን መሰረት ወይም ዓለት ማን ነው? ጳውሎስ ሲናገር "ከተመሰረተው በቀር ማንም ሌላ መሰረት ሊመሰርት አይቸልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡11)። በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡3~4፣ ላይ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፣ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ" ይለናል።

ለኤፌሶን ክርስቲያኖቸ ሲፅፍ ጳውሎስ "እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮቸና የእግዚአብሄር ቤተ ሰዎቸ ናቸሁ እንጂ መፃተኞቸ አይደላቸሁም፣ በሐዋሪያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንፃቸዋል፣ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው በርሱም ሕንፃ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፣ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሄር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራቸሁ ትሠራላቸሁ" (ኤፌሶን 2፡19~22) እዚህ ላይ ሐዋሪያው ስለ

እነዚህ ክርስቲያኖቹ የእግዚአብሄር ቤት ወይም የእግዚአብሄር ቤተሰብ እንዴሆኑ ይናገራል ይህም ቤተክርስቲያን ነበረች እና እንዴት በሐዋሪያት ትምህርት ላይ እንዴታነፀ ነው፣ አየሱስ ክርስቶስ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ብቻ አይደለም አጠቃላይ ዋና አስፈላጊ መሰረትም ነው፣ መሰረቱ በጣም አስፈላጊ ነው የመሰረቱ አካል ቤተክርስቲያን ያለዚያ መሰረት ምድራዊም ሆነ መንፈሳዊ ቤት መቆም አይችልም፣ ጳውሎስ ሲናገር "ብዘገይ ግን፣ በእግዚአብሄር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እፅፍልሃለሁ፣ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት፣ የሕያው እግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ነው" ይላል (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡15)ክርስቶስ መሰረት፣ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ሆኖ፣ የእግዚአብሄር ቤት ወይም ቤተክርስቲያን በላዩ ላይ ሲታነፅ፣ ቤተክርስቲያን የእውነት መሰረት ሆና ታገለግላለጭ ይኼውም በፅኑ መሰረት ላይ እየተገነባች ያለችው ቤተክርስቲያን ለጠፋች ዓለም እውነትን የምታውጅ ናት፣

ሐዋሪያው ጴጥሮስ በዘመኑ ላሉት ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏል "እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኮልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሐሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ ፣ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጒ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ፣ በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሄር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡር ወደ ሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ፣ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሄር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሣን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ፦ በመፅሐፍ እነሆ የተመረጠና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በፅዮን አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ ተፅፏልና። እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፣ ለማያምኑ ግን አናጢዎቾ የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ ማሰናከያ ዓለት ሆነ፣ የማያምኑ ስለሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፣ ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው" (1ኛ ጴጥሮስ 2፡1~8)

አሁንም ፀሐፊው ክርስቶስ በኢሳያስ 28፡16፣ ላይ የተነገረው ትንቢት ፊፃሜውን ያገኘው እንዴት እንደሆነ ሲገልፅ፣ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ሆኖ፣ አይሁዶች የናቁትና የተሰናከሉበት የመሰረት ድንጋይ ብቻ ሳይሆን የማዕዘን ራስ ድንጋይ የሆነው የመሰረቱ የቤቱ ዋነኛ ክፍል መሆኑን ልብ እንድንል ያደርጋል። ጴጥሮስ ክርስቶስን በመቀበል ለእነዚያ ግን በረከት እንደሚሆን አሳይቷል፣ የናቁትም ጠፍተዋል

በማቴዎስ 16፡13~19፣ ክርስቶስ ዓለም ስለእርሱ ምን እንደሚያስብ ለሐዋሪያት ጠይቋል፣ ሐዋሪያቱ አንዳንዶች እሱ ከነቢያት አንዱ ነብይ እንደሆነ አድርገው እንደሚያስቡ ነበር የገለፁት፣ ክርስቶስ ግን የሚፈልገው ይህን አልነበረም በዚህ ቃል ላይ ቤተክርስቲያን መምስረት

አልፈለገም፣ ከዚያም ወደ ሐዋሪያት ዘወር ብሎ ስለእርሱ ምን እንዷሚያስቡ ጠየቃቸው፣የእግዚአብሄር ልጅ ነው ብለው እንዷሚያምኑ ገለፁ። በውጤቱም ጌታ በዚያን ምስክርነት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ ሲል መለሰ፣ ያም እነዚህ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ያመኑት ሐዋሪያት ኃይል ሲመጣ በሐዋሪያት ሥራ 2 የክርስቶስን ወንጌል ሰብከዋል እናም 3000 የሚያህሉ ነፍሳት ጌታን ታዘዙ እና አዳናቸው ወደ ቤተክርስቲያንም ጨመራቸው፣ ግን ቤተክርስቲያን በምን ላይ ተሠራ?/ ቤተክርስቲያን የታነፀቸው በክርስቶስ ላይ ነው። የእግዚአብሄር ልጅ ስለነበር ነው።ይህም ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያንም እስከ ዘመናችን ድረስ በዚሁ ሁኔታ ትገኛለች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ አለመሆኑ ባለፉት ዓመታት ማረጋገጥ ቢቻል ኖሮ ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ ወድቃ ወይም ከሕልውና ውጪ በሆነች ነበር። ቤተክርስቲያን ግን አሁንም አለች እና የምትቆምበት ብቸኛው መንገድ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ ነው በሚለው ላይ ነው፣ እሱ ዓለት፣ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ነው በሚለው እውነታ ላይ የተመሰረተ ነው፣ ጳውሎስ እንዷተናገረው እርሱ የተረጋገጠ መሰረት ነው።

ውድ ወዳጆቼ ! በምን ላይ ነው የምትገነቡት? ቃሉን ሰምታሁ ካደረጋችሁ በክርስቶስ ላይ መገንባት ትችላላችሁ። በክርስቶስ አምነህ በኃጥያታችሁ ንሠሃ ከገባህ በክርስቶስ ላይ ያለህን እምነት ብትናዘዝ ለኃጥያትህም ስርየት ከተጠመቅክ ጌታ ያድንሃል። በክርስቶስ ላይ ወደምታነፀው ቤተክርስቲያን ይጨምራሃል፣ (የሐዋሪያት ሥራ 2) ጥበበኛ ከሆንክ ይህን ታደርጋለህ፣ እኛም ይህንን እንድታደርግ እንፀልያለን።

## ትምህርት 21

## አዲስ ልደት ለምን እንሰብካለን

አዲስ ልደት ምንድነው? ይኼ ጥሩ ጥያቄ ነው፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ያ ጥያቄ ብዙ ጊዜ ተጠይቆ ብዙ ጊዜ የተለያዩ መልሶች ተሰጥተዋል፣ አሁንም አብዛኛው ሰው ምን እንደሆነ አያውቅም፣

አንዳንድ የኃይማኖት ድርጅት ኳደኞቻችን አዲስ ልደትን አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ ሲቀበል በሰው ህይወት ውስጥ የሚፈጠር ተአምራዊ ለውጥ ነው ብለው ይገልፁታል

ወደ ዮሐንስ 3 ስንሄድ ክርስቶስ ስለ አዲስ ልደት ሲናገር እንሰማለን ወይም አንድ ሰው እንዷገና መወለድ አለበት፣ ይህን ትምህርት ክርስቶስ ያስተማረው ከመሞቱ በፊት መሆኑን እና እንደ ሕግም አስገዳጅ ባልሆነበት ጊዜ መሆኑን አስታውስ፣ ይህን ያስተማረው ግን የክርስቶስ ወይም የክርስትና ሕግ ከፀና ቦኃላ እንዷሚያስፈልግ በመጠበቅ ነው፣ መንግሥቱ ወይም ቤተክርስቲያን ከመስረቱ በፊት ም ያስተምር ነበር ነገር

ግን ጌታ ሲናገር የነበረው መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን ከተመሰረተ በኃላ ወደ እርሷ ለመግባት ዳግመኛ መወለድ አስፈላጊ እንደሆነ ነው፣

ነገር ግን ስለ አዲስ ልደት ከቃሉ እናንብብ፣ ዘገባው እንደሚለው “ከፈሪሳዊያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆድሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፦ መምህር ሆይ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ካልሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው፣ ኢየሱስም መልሶ ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሄርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆድሞስም ፦ ሰው ከሸመገለ በኃላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማህፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው። ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ሊገባ አይችልም ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፣ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፣ ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋቸዋል፣ ስላልሁህ አታድንቅ ፣ ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፣ ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወደ ዬትም እንደሚሄድ አታውቅም፣ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲህ ነው፣ ኒቆዲሞስም መልሶ ፦ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው፣ አየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እውነት እውነት እልሃለሁ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን ምስክራችንንም አትቀበሉትም። ስለምድራዊ ነገር በነገርኳችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፣ ስለሰማያዊው ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፣ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው” (ዮሐንስ 3፣1~13)

ከላይ ከተዘረዘሩት እባክህን ቅንብሩን አስተውል ፣ ኒቆዲሞስ የሚሉት አንድ ሰው በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጣ፣ አንዳንዶች ፈሪሳዊና የአይሁድ ገዢ ስለነበረ ጉብኝቱን እንዲሰውር በዚህ ጊዜ እንደመጣ መሰላቸው። ፈሪሳዊያን የአይሁድ ኃይማኖታዊ ክፍል ነበሩ። በትንሳኤ እና በመላዕክት ያምኑ ነበር የአይሁድ ገዢ ስለነበር ሽማጊሌና ክብር ያለው ሰው ነበር ማለት ነው። ወደ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ እንደ ረቢ ወይም አስተማሪ ስለእርሱ እስከተናገረ ድረስ በእርሱ እንደሚያምን ገለፀ። ተአምራትን ማድረጉን አይቶ እግዚአብሄር እንዳላከው የተገለጠ ነው ብሎ ተናግሯል። ኢየሱስ አንድ ሰው የእግዚአብሄርን መንግሥት ለማየት ከፈለገ ዳግመኛ መወለድ አስፈላጊ እንደሆነ በመግለፅ የመለሰው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው። ኒቆዲሞስ ግን ክርስቶስ የተናገረውን ስላልተረዳው ግራ ተጋባ። ከዚያም ሰው በሸመገለ ጊዜ እንዴት ዳግመኛ ሊወለድ እንደሚችል ማወቅ ፈለገ። ቀጠለና ይህ ማለት አንድ ሰው ወደ እናቱ

ማህፀን ሁለተኛ ገብቶ ይወለዳል ማለት እንደሆነ ጠየቀ፣ በርግጥ እርሱ ያንን ማድረግ አይችልም ነበር፣ እና ኢየሱስም እንደዚህ አላስተማረም። ክርስቶስ ስለ መንፈሳዊ ልደት እየተናገረ ነበር፣ ኒቆድሞስ ግን ስለሥጋዊ ልደት እያሰበ ነበር፣ ምክንያቱም ምንም የማያውቀው ይህ ብቸኛ ልደት ስለሆነ ነው።

በመቀጠልም ኢየሱስ ተመልሶ መጥቶ ስለአዲስ መወለድ በሰፊው ገለፀ፣ ብዙ ቃል ሲናገር አንድ ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ መወለድ ወደ እግዚአብሄር መንግሥት መግባት እንደሚያስፈልግ እየነገረው ነበር፣ ከዚህም ሌላ ወደ እርሷ የሚገባ ሌላ መንገድ ከዚህ ውጪ የለም

ግን እነዚህን ቃላት በጥቂቱ እንመርምር ፦ በመጀመሪያ ከውኃ መወለድ አስፈላጊ እንደሆነ መናገሩን አስተውል ። መወለድ ማለት መውጣት ማለት ነው፣ መወለድ አዲስ ህይወትን ይጠቁማል። ግን እዚህ ያለው ውኃስ ? ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ይህ ልደት ሁለተኛ ጊዜ ወደ እናቱ ማኅፀን ዳግመኛ ገብቶ ከመወለድ የተለየ እንደሆነ ስለገለፀ ከሥጋ ልደት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ ይህንን ውኃ የሚለውን ቃል ስናስብ ልብ ልንለው የሚገባን ሌላው ደንብ በሌሎቹ በሁሉም በታዎቹ ጥቅም ላይ የሚውሉባቸው በታዎች ሁሉ መንፈሳዊ ውኃ ከሆነ የሚያመለክት የህይወት ውኃ እንደሆነ ይነገራል። ቃል በቃል ውኃ እንደሆነ በሌላ በኩል በተለያዩ ጥቅሶች ላይ ውኃ የሚለው ቃል ብቻ በተገለፀበት ጊዜ ትርጉሙ ቀጥተኛ ወይም ትክክለኛ ውኃ ማለት ነው። ግን እዚህ አጠቃቀሙ ላይስ ? ውኃ የሚለው ቃል ብቻ ስለሚታይ እሱ ስለእውነተኛ ውኃ እየተናገረ ነው ብለን መደምደም አለብን፣ አሁን ወደ ቀጣዩ ጥያቄ፣ በቅዱሳት መፅሐፍት ውስጥ በውኃ የተያያዘ የትኛውን ትዕዛዝ እናነባለን ? የጌታን ቃል ጠንቅቀህ የምታውቀው ከሆነ ከውኃ ጋር የተያያዘ አንድ ትዕዛዝ ወይም ድርጊት አንድ ብቻ እንዳለ ታውቃለህ እርሱም ጥምቀት ነው፣ በሐዋሪያት ሥራ 8፡26~39 ከኢትዮጵያ አንድ ሰው ክርስቶስን ተምሮ መጠመቁን እናነባለን። ከዚህም በተጨማሪ ክርስቶስ አንድ ሰው ከውኃ መወለድ አለበት ብሏል፣ ሰው እንዴት ከውኃ ሊወለድ ይችላል? እንግዲህ እዚህ ላይ ውኃ ስለጥምቀት የሚጠቅስ ከሆነ በውኃ ውስጥ መጠመቅ መቀበር መሆኑን አስታውስ (ቆላስያስ 2፡12) በውኃ ውስጥ መቅበር ካለ አንድ ሰው ከዚያ ውኃ መውጣትም ይኖራል ማለት ነው፣ መቀበር መወለድ፣ ሐዋሪያው ጳውሎስም በጥምቀት የሚከናወነው ይህ እንደሆነ ገልፆአል (ሮሜ 6፡3~4)

ከውኃ መወለድ ወይም መጠመቅን በተመለከተ ማሰባችንን ስንቀጥል፣ አንድ ሰው ዳግመኛ ሲወለድ እንደሚወጣ ወም አዲስ ህይወት እንደሚለማመድ እናስታውሳለን። ዳግመኛም ይህ ከጥምቀት ጋር የሚስማማ ነው፣ ምክንያቱም ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ 6፡3 እና ገላቲያ 3፡26~27 ላይ ጥምቀት አንድን ሰው በክርስቶስ እንደሚያደርኛ

በክርስቶስ ያሉት ደግሞ አዲስ ፍጥረት እንደሆኑ ስለሚነግረን ጳውሎስ ሲናገር "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል" (1ኛ ቆሮንቶስ 5፡ 17)፤ ጴጥሮስም ለክርስቲያኖች ሲናገር እንዲህ አለ "ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ፤ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ" ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 2፡3)

ሁለተኛ ፦ ክርስቶስ ሲናገር አንድ ሰው ከመንፈስ መወለድ አለበት ብሏል። እዚህ ጋ ይህ መንፈስ ማን ነው? ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡4 ላይ አንድ መንፈስ ይላል። እና ያ መንፈስ ምን ይሆን? መንፈስ ቅዱስ ነው ወይስ የመንፈስ ኃይል በርግጥ (ዮሐንስ 14፡26፤ ሐዋሪያ ሥራ 1፡ 8፤የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡8)፤ ግን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን ነበር? አንደኛ ነገር የጌታን ቃል እንዲፅፉ ሐዋሪያትንና ሌሎችንም አዘዛቸው። ከዚያ በፊት የቀደሙትን ቅዱሣን ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል እንዲፅፉ መርቷቸዋል (2ኛ ጴጥሮስ 1፡21) ጳውሎስ በእግዚአብሄር መንፈስ የተፃፉ እንደሆነ ነግሮናል (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16~17) ነገር ግን በመንፈስ ቃል ወይም በጌታ ቃል የተገለጠው ምንድነው? እውነት ነው የተገለጠው (ዮሐንስ 17፡17)፤ የክርስቶስ ወንጌል ነው (ሮሜ 1፡16) ወይም አንድ ሰው ሰምቶ የሚድንበት ነው (ሐዋሪያት ሥራ 2፡37~38)። አንድ ሰው የመንፈስን ቃል ቢያምን አይታዘዝምን? ጴጥሮስ በዘመኑ ለነበሩት ክርስቲያኖች ሲፅፍ እንዲህ አለ "ለእውነት እየታዘዛችሁ፤ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ፤ ነፍሳችሁን አንፅታችሁ፤ እርስበእርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ። ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም። በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሄር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ፤ ሥጋ ሁሉ እንደሣር ክብሩም ሁሉ እንደሣር አበባ ነውና፤ ሣሩ ይጠወልጋል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው" (1ኛ ጴጥሮስ 1፡22~25)፤ በዮሐንስ 3፡5 ላይ ክርስቶስ አንድ ሰው ከመንፈስ መወለድ አለበት ያለውን አስታውስ፤ ግን በ1ኛ ጴጥሮስ 1፡23 ላይ ደግሞ በእግዚአብሄር መንፈስ ተመርቶ ከእግዚአብሄር ቃል መወለድ አለ። ግን ቃሉን የሰጠው ማንነው? መንፈስ ነው። ስለዚህ ከመንፈስ መወለድ እና ከእግዚአብሄር ቃል መወለድ ሁለቱም አንድ ናቸው፤ ልዩነት የላቸውም። ነገር ግን እምነት እንዴት ይመጣል ? የእግዚአብሄርን ቃል በመስማት (ሮሜ 10፡17)፤ እንግዲህ ሰው እየግዚአብሄርን ቃል ከሰማ ያምናል፤ሰው ቃሉን ካመነ ይታዘዛል፤ ከታዘዘ ይጠመቃል ወይም በጥምቀት ውኃ ውስጥ ይቀበርና ከዚያ ይነሣል፤ ከዚያ ዳነ ማለት ነው (ቆላስያስ 2፡12 ፤ ማርቆስ 16፡ 16)፤ እንግዲህ ጴጥሮስ በ1ጋን መልዕክቱ 1፡23 ላይ የሚነግረን ይህንን

ነው፣ ዳግመኛ የተወለድነው በመንፈስ ለእውነት በመታዘዝ ነው፣ ወይም መንፈስ አንድ ሰው በእግዚአብሄር ቃል ምን ማድረግ እንዳለበት በሚመራው መሰረት ነው፡፡ ከውኃ እና ከመንፈስ መወለድ ማለት የእግዚአብሄርን ቃል ትምህርት ሲታዘዝ በክርስቶስ አምኖ በኃጥያቱ ተፀፀቶ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ሲመሰክር እና ኃጥያቱ የሰረይ ዘንድ በውኃ ሲጠመቅ ማለት ነው፡፡ ጌታ ያንን ሰው ያድነዋል እናም ወደ መንግሥቱ ወይም ወደ ቤተክርስቲያን እጨምረዋል፣ የሐዋሪያት ሥራ 2 ን አንብብ እና ሕዝቡ በዚያ በኢየሩሳሌም ያደረጉትን ይህንኑ ታያለሕ ስለዳግመኛ መወለድ ምንም አልተነገረም፣ ነገር ግን ዳግመኛ መወለዳቸውን እናውቃለን ምክንያቱም ክርስቶስ አንድ ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ በተወለደ ጊዜ ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ይገባል ብሎ ስለተናገረ የሐዋሪያ ሥራም ሰዎች የወንጌልን ስብከት ሰምተው አመኑ፣ ከኃጥያታቸው ንሠሀ ገብተው ለኃጥያታቸው ሥርየት ተጠመቁ፣ ጌታ አዳናቸው እና ወደ ቤተክርስቲያን ጨምሯቸዋል፣ ግን መንግሥትና ቤተክርስቲያንስ? የተለያዩ ተቋማት አይደሉም? በፊፁም አይደለም፣ መንግሥትና ቤተክርስቲያን በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ አንድ ዓይነት ተቋም ወም ድርጅት ተለይተው አይታወቁም፣ በቆላስያስ 1፡14 ላይ ለምሣሌ ጳውሎስ እዚያ ላለቹ ቤተክርስቲያን ሲፅፍ እነዚያ ራሳቸው አባላቱ ከጨለማ ሥልጣን ነፃ ወጥተው ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት እንደፈለሱ ተናግሯል፡፡ (ቆላስያስ 1፡13) በሐዋሪያት ሥራ 2 ሰዎች ካመኑ ቦኃላ ተጠመቁ፣ ዳኑ እናም ወደ ቤተክርስቲያን ተጨመሩ፣ ግን ፣ በሰማሪያ ምዕራፍ 8 ላይ ካመኑ ቦኃላ ወንድም ሰቶቸም ተጠመቁ (ሐዋሪያ 8፡12)፣ ይህ ማለት የሐዋሪያ 2 የቤተክርስቲያን አባል ሆነው የሐዋሪያ 8 የእግዚአብሄር መንግሥት አባል ሆኑ ካለ በሁለቱ መካከል ልዩነት አለ ማለት ነው? አይደለም ሁለቱም ተመሳሳይ እና አንድ ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ ሲወለድ የጌታን ቃል ሰምቶ አምኖ ንሠሃ ገብቶ በክርስቶስ ማመኑ ተናግሮ ሊድን ከዚያም ቦኃላ በውኃ ተጠመቀ ማለት ነው፡፡ ጌታ ወደ ቤተክርስቲያን ይጨምረዋል ማለትም ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ይገባል፣ እንደ የጌታ በተሰብ አባል፣ እንደ አዲስ ፍጥረት፣ እንደአዲስ ክርስቲያን፣ እሱ ማደግ እና ሙሉ ክርስቲያን ሊሆን ይቸላል ይህ ሰው በእምነቱ እያደገ መሄድ አለበት ይህንን ማድረግ አለብን እናም ይህንን መስበክ አለብን፣ ጌታን ደስ ለማሰኘት ከሆነ ለዓለም ሁሉ ይህንን ማድረግ አለብን፡፡

ዳግመኛ ተወልደሃል ? ክርስቲያን ነህ ? ካልሆንክ ግን ጠፍተሃል እና እስከታደርግ ድረስ ጠፍተዋል፣ ዳግመኛ ለመወለድ ከዚህ ዓለም እና ከሚመጣው ለመዳን ሌላ መንገድ የለም፡፡ በነዚህ ጉዳዮቹ ላይ የአምላክን ፈቃድ ሙሉ በሙሉ እስክትገነዘብ ድረስ እና እሱ እንዳዘዘው እንድታደርግ ጥናትህን እንድትቀጥል እንፀልያለን

## ትምህርት 22
## ለምን አንዲት ጥምቀት

ስለዚህ ርዕስ ግንዛቤው ይኑርህ አይኑርህ አላውቅም፣ ነገር ግን ይህንን በክርስቶስ እናምናለን ከሚሉ መካከል ስለጥምቀት የተለያየ ነገር የሚያስተምሩ አሉ። አንዳንዶቹ ጥምቀት ውኃ ውስጥ በመቀበር ይከናወናል የሚሉ ፣ ሌሎቹ በራስ ላይ በመርጨት እከናወናል የሚሉ፣ ሌሎቹም በራስ ላይ በማፍሰስ ይከናወናል የሚሉ፣ ሌሎቹም በመንፈስ ማጥመቅ የሚሉ እና ወዘተ ናቸው፣ በዚህ ላይ እነዚህ ለተለያየ ዓላማ ያላቸው የጥምቀት ዓይነት ናቸው፣ አንዳንዶቹ ጥምቀት የደህንነት ምልክት ነው ይላሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ ጥምቀት ለኃጥያት ሥርየት እና ወደ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን መግቢያ ነው ይላሉ።

መፅሐፍ ቅዱስ ግን አንዲት ጥምቀት ብሎ ያስተምራል፣ ጳውሎስ እንዲህ ይላል “በመጣራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፣ አንድ ጌታ አንድ ኃይማኖት ፣ አንዲት ጥምቀት ፣ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ” ይላል (ኤፌሶን 4፡4~6)፣ እባክህን አስተውል ይህ የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት ሰው የሚለው አንድ አምላክ፣ አንድ ጌታ ወይም ክርስቶስ፣ አንድ መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ፣ አንድ ኃይማኖት አንድ ጥምቀት፣ አንድ አካል፣ እና አንድ ተስፋ አለ ይላል ከነዚህም መካከል አንድ ጥምቀት ይላል፣ አንድ እግዚአብሄር፣ ክርስቶስ ወዘተ ካለ አንዲት ጥምቀት ማለት አንዲት ጥምቀት አለ ማለት ነው።

ነገር ግን ይህ ጥምቀት ዬትኛው መሆን አለበት ? በዛሬው ጊዜ ሰዎች ከሚናገሩት ጥምቀት በተጨማሪ፣ በቅዱስ ቃሉ ውስጥ ስለ ልዩ ልዩ ጥምቀቶች እናነባለን። ለምሣሌ በሉቃስ 7፡29፣ ሰዎቹ በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁበትን እናነባለን። ክርስቶስ ሊፈትኑት የሚሞክሩ ሰዎችን “የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረች ወይስ ከሰው?” መልሱልኝ” ሲል ጠየቀ(ማርቆስ 11፡30) ክርስቶስ የተጠመቀው ፅድቅን ሁሉ ለመፈፀም ነው፣(ማቴውስ 3፡13~17) ሕዝቡ በአጠቃላይ ለጌታ መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን መምጣት ለመዘጋጀት ተጠመቁ፣ ስለዚህ እሱ የንሠሀ ጥምቀት ተብሎ ተጠርቷል (ሉቃስ 3፡3) ጳውሎስ በኤፌሶን አንዳንድ ሰዎችን በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁ ነገር ግን ስለመንፈስ ቅዱስ ያልሰሙትን ተገናኝቶ ነበር፣ ስለዚህም ስለዮሐንስ ጥምቀት ዓላማ አስተማራቸው “አጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው ሀገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፣ አንዳንድ ደቀመዛሙርትንም አገኘ ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው። እነርሱም፦ አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳ አልሰማንም አሉት፣ እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ ? አላቸው፣ እነርሱም በዮሐንስ ጥምቀት አሉጥ ጳውሎስም የዮሐንስስ ከእርሱ ቦኃላ በሚመጣው

በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንሠሀ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው፡፡ ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ" (የሐዋሪያት ሥራ 19፡1~5)፣ በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ጥምቀት ለዘላለም እንዲቀጥል ታስቦ አልነበረም፡፡ ዓላማውን ያከናወነ ሲሆን ከዚያም ላይቀጥል ቆመ፡፡

በማቴዎስ 3፡11~12፣ መጥመቁ ዮሐንስ ወይም አጥማቂው ዮሐንስ ክርስቶስ ስለሚያደርጋቸው ሁለት ጥምቀቶች ተናግሯል፣ "እኔስ ለንሰሀ በውኃ አጥምቃችዋለሁ፣ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ ቦኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፣ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፣ መንሹም በእጁ ነው፣ አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል፣ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፣ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል" (ማቴዎስ 3፡11~12) እዚህ ላይ ዮሐንስ ክርስቶስ አጫጁን በሥዕላዊ መግለጫው መሠረት ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ያሳያል፡፡ የዚያን ቀን ሰዎች የስንዴ አዝመራን ያውቁ ነበር፡፡ ስንዴው ይወቃ ነበር እና በነፋስ ወይም በማራገቢያ እርዳታ ገለባው እና ስንዴው ይለያያሉ ስንዴው ተሰብስቦ ለምግብ ይቀመጣል፣ ገለባው ወይም የማይረባው ይቃጠላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ዮሐንስ ክርስቶስ ከዚያ ቦኋላ በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት እነደሚያጠምቅ ተናግሯል፣ ቦኋላ ኢየሱስ አፅናኙን ወይም መንፈስ ቅዱስን በእነርሱ ላይ እንደሚልክ ለሐዋሪያቱ ቃል ገባላቸው (ዮሐንስ 15፡26፣ ዮሐንስ 16፡ 7፣13)፣ በሐዋሪያት ሥራ 1፡8 ላይም እንደሚልክ እንደገና ቃል ገባላቸው፣ በተጨማሪም ሉቃስ 24፡49ን አንብብ፡፡ በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ መንፈስ ቅዱስ በሐዋሪያት ላይ እንደፈሰሰ እናነባለን፣ ይህም ክርስቶስ ያስተማራቸውን ሁሉ እንዲያስታውሱ በሌሎች ቋንቋዎች እንዲናገሩ እና ተአምራት እንዲያደርጉ ኃይል ሰጣቸው ፡፡ በእነሱ አማካይነት ሁሉም ተባረኩ፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ ደግሞ በእሳት እንደሚያጠምቅ ተናግሯል፣ ይህ ምንን ያመለክታል? ስንዴው ፃድቃንን የሚያመለክት ከሆነ፣ የሚቃጠለው ገለባ ኃጥያተኞችን ያመለክታል፣ ክርስቶስ ሐዋሪያትን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃቸው ነበር፣ ኃጥያተኞችን በእሳት ያጠምቃቸዋል፣ ጥምቀት ማለት ጥምቀት ማለት መሆኑን ከተረዳን ሐዋሪያት በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ ወይም ተዋጡ ከተባለ ክፉዎች ደግሞ በእሳት ይጠመቃሉ ይዋጣሉ ማለት መሆኑን መረዳት አለብን፡፡ በቅዱሳት መፅሐፍት ውስጥ በክፉዎች ላይ እንዲህ ዓይነት ድርጊት እንደሚፈፀምባቸው የሚናገረው ዬት ነው? በመጀመሪያ ድደረጃ ክርስቶስ አንድ ቀን በዓለም ላይ እንደሚፈርድ እና ክፉዎች ወደ ገሃነም እንደሚጣሉ (2ኛ ጴጥሮስ 2፡4) ወይም ወደ ዘላለም ጥፋት እንደሚሄዱ (ማቴዎስ 25፡46) እንደገናም ሲኦል እንደ እሳት ባህር ተገልፆአል፣ (2ኛ ጴጥሮስ 3፡7፣ ይሁዳ 7፣ ዮሐንስ ራዕይ 20፡10፣14፣ ዮሐንስ ራዕይ 21፡

8)። ያም ማለት ከፉዎች፣ ኃጥያተኞች ወይም የጠፉት በእሳት ባህር ይጠመቃሉ ወይም ይገባሉ ማለት ነው ይህም የዘላለም ፍርድ ነው ማለት ነው።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1~4፣ ላይ ጳውሎስ ሲፅፍ "ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እውዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባህር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባህር ተጠመቁ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፣ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ" ምንም እንኳን በዚያን ጊዜ እንደጥምቀት ባይታሰብም ጳውሎስ የእስራኤል ልጆች በባህር ውስጥ ሲያልፉ በሁለቱም በኩል ውኃ ይዘው በደመና ላይ ሲያልፉ ሲመለከት ጥምቀት መሆኑን ገልፆአል። በሌላ አነጋገር፣ የተቀበሩት ወይም በደመና እና በባህር ውስጥ ይጠመቁ ነበር ማለት ነው።

የዘብዴዎስ ልጆች እናት ክርስቶስ ልጆቿ በመንግሥት ከእርሱ በሁለቱም ወገን እንዲቀመጡ እንዲፈቅድላቸው ስትለምን ምን እንዳለ ስናነብ ፦ "ኢየሱስ ግን መልሶ የምትለምኑትን አታዉቁም፣ እኔ ልጠጣው ያልውን ፅዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን ? አለ። እንችላለን አሉጥ እርሱም ፦ ፅዋዬንስ ትጠጣላችሁ፣ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው" (ማቴዎስ 20፡22~23) እንደገናም ኢየሱስ እንዲህ አለ "ነገር ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ፣ እስክትፈፀም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ" አለ (ሉቃስ 12፡50) እዚህ ጋ ክርስቶስ የሚናገረው ጥምቀት በመስቀል በስቃይ የሚጠመቀውን ነው። ይህንንም አንድ ጊዜ የሚያደርገው መሆኑ ይታወቃል።

በመጨረሻ ቅዱሣት መፅሐፍት የሚናገሩት የአማኞች ጥምቀት ነው፣ ይህ ጥምቀት በውኃ ውስጥ ነው (ሐዋሪያ ሥራ 8፡26~39)፣ በመቀበር ጥምቀት (ቆላሲያስ 2፡12፣ ሮሜ 6፡3፣4)፣ ይህም ለኃጥያት ሥርየት ነው (ሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ ከኃጥያት ለመታጠብ ነው፣ (የሐዋሪያት ሥራ 22፡16)፣ ለመዳን ነው (1ኛ ጴጥሮስ 3፡21)፣ አንድን ሰው በክርስቶስ እንዲሆን ነው (ገላቲያ 3፡26~27)፣ አንድን ሰው በቤተክርስቲያን ላይ ለመጨመር ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)።፣ ያም በክርስቶስ ስም የሚሆነው ነው (የሐዋሪያ ሥራ 2፡38)፣ ይህ ነው በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም (ማቴዎስ 28፡19~20)፣ ክርስቶስም አለ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ 16፡15~16)

ወደ ኤፌሶን ስንመለስ ጳውሎስ አንዲት ጥምቀት ብሎ 4፡4~6፣ የተናገረው ወይም የፃፈው በግምት በ 64 ዓም ነው። ነገር ግን በቅዱሣት

መፅሐፍት ውስጥ ከምናነበው ጥምቀት ሁሉ የትኛው ጥምቀት ነው አንድ ጥምቀት የተባለው? መከበር ያለበት በማንኛውም ጊዜ የአማኞች ጥምቀት የውኃ ጥምቀት ነው፣ በሌላ አነጋገር ቅዱሣት መፃሕፍት ስለመንፈስ ቅዱስና ስለእሳት ጥምቀት፣ ስለዮሐንስ ጥምቀት፣ ስለስቃይ ጥምቀት እና ስለዳመና ጥምቀትና የባህር ጥምቀት ይናገራሉ። ስለዚህ በኤፌሶን 4፡4~6 ስለአንድ ጥምቀት ስናነብ፣ ይህ የሚያመለክተው የአማኞችን ጥምቀት ነው ብለን መደምደም አለብን።የኛ ኮርስ ዛሬ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለዘመናችን ሰዎችም እንደሆነ ሲናገሩ እንሰማለን ነገር ግን ጥምቀት በክርስቶስ ለሐዋሪያት ቃል እንዲተገባ እና እርሱንም ጥምቀት ያካሄደው እርሱ እንደሆነ ነው፣ ያ ጥምቀት የራሱ ዓላም ነበረው እናም ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀም ያጠመቀም የለም። የውኃ ጥምቀትን የሚያስተምሩ ሌሎችም አሉ ነገር ግን ያ አማኝ ከመጠመቁ በፊት ድኗል ይሉና ከዚያም እርሱ እንደዳነ ለማሳየት ይጠመቃል ይላሉ። እነዚህ ትክክል ከሆኑ ያ ከክርስቶስ ውጪ እና ከቤተክርስቲያኑ ውጪ ይድናል ማለታቸው ነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሄር ቃል ወደ ክርስቶስ እና ቤተክርስቲያኑ ለመግባት መጠመቅ እንዳለበት ስለሚናገር (ገላቲያ 3፡26~27፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)፣ በዚህ ነጥብ ላይ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ስህተት ውስጥ እንዳሉ እናውቃለን፣ አንድ ሰው ጌታን እስካልታዘዘ ድረስ መዳን አይችልም እና ትዕዛዝ ደግሞ የውኃ ጥምቀትን ያካትታል።

ጥምቀትን በመርጨት እና በግንባር ላይ ማፍሰስ የሚል ሰው ከእግዚአብሄር ቃል ትምህርት እጅግ በጣም የራቀ ነው፣ በምንም መልኩ ውኃን በጭንቅላት ላይ በመርጨት ወይም በማፍሰስ ጥምቀት ነው ማለት አይቻልም። ጥምቀት በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ ነው፣ መርጨት ግን መርጨት ነው፣ ማፍሰስም ያው ማፍሰስ ነው እንጂ ጥምቀት አይደለም።

አሁን ጥያቄው የመፅሐፍ ቅዱስን አንድ ጥምቀት ተቀብለሃል ወይ ?የሚለው ነው፣ ከልተቀበልክ እና እና ካልዳንክ አሁኑኑ ማድረግ አለብህ፣ የሐዋሪያት ሥራን በአዲስ ኪዳን ብታነብ ለጌታ የታዘዙ ሁሉ ወንጌልን ወይም ክርስቶስን ወንጌል ሰምተው በእግዚአብሄር እና በክርስቶስ አምነው ከኃጥያታቸው ንሠሀ ገብተው ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክረው እንደሆነ ትገነዘባለህ፣ እናም ለኃጥያታቸው ሥርየት ተጠመቁ፣ ከዚያም ጌታ አዳናቸው ወደ ቤተክርስቲያንም ጨመራቸው (ሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣41፣47) እነርሱ ያደረጉትን ካደረግክ ጌታ አንተንም ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምርሃል።

በማፍሰስ ወም በመርጨት ወይም ለትክክለኛ ዓላማ ሳትጠመቅ የተጠመቅክ እና የዳንክ አርገህ የምታስብ ከሆነ እንደቅዱሳት መፅሐፍት ትዕዛዝ አልተጠመቅምና አልዳንክም። አሁን ከመፅሐፍ ቅዱስ

እንዲተማርክ እንዲዚሁ መጠመቅ አለብህ ምናልባት ጥምቀት አንድ ናትና ሁለት ጊዜ አልጠመቅም ትል ይሆናል፣ አይ ጥምቀት አንድ ናት ያቺ አንዲቷን ነው ያለተጠመቅከው እና መጠመቅም የኢያስፈልግሕ ይህም ደግሞ የእግዚአብሄር ቃል እንደሚያስተምረው ማለት ነው፣ ስለዚህ እነሆ በዚህ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በተማርከው መሰረት መጠመቅ እንዳለብህ አበረታታሃለሁ

## ትምህርት 23

### ለምን ህሊናን እንደ አስተማማኝ መመሪያ አንቀበልም

ህሊና የሚለው ቃል ከሰው ልብ፣ አዕምሮ እና ነፍስ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንድ ሰው የተወሰንር መጠን ያለ መረጃ እና እውቀት ሰብስቧል ማለት ነው፣ ይህም ትክክል ወይም ስህተት መሆናቸውን ለመወሰን ከሌሎቾ ነገሮች ጋር ለማነፃፀር ያገለግላል፣ መረጃው በእውነታው ላይ የተመሰረተ ወይም በውሸት ዘገባዎች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል እውነትም ሆነ ሐሰት ምንም ይሁን ምን እንደእውነት ተቀብሎ እንደ መመሪያ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ህሊና አስተማማኝ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል የሚሰማቸው ሰዎች አሉ፡፡ ሌሎች ስለበጎ ሕሊና ይናገሩና በጎ ሕሊና ስለአላቸው ይህ በራሱ ትክክል እንደሚያደርጋቸው ይሰማቸዋል፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ተታልሎ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን እውነትን እንደተቀበለ በማሰብ መጨረሻው በጎ ሕሊና ይኖረዋል፡፡ እንግዲህ የእሱ በጎ ሕሊና በእውነት ላይ የተመሰረተ ሣይሆን በስህተት ላይ ነው፡፡ አንድ ሰው ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን ለመወሰን ሕሊናው የመጨረሻው ባለሥልጣን ሆኖ እንዲያገለግል መፍቀድ የማይችለው ለዚህ ነው፡፡

ሕሊና እንዴት እንደሚሠራ ተበለጠ ለማብራራት ስለአንድ ትንሽ ልጅ አስብ፡፡ መስረቅ ወይም የእሱ ያልሆነውን ነገር መውሰድ ስህተት እንደሆነ ወላጆቹ ያስተምራሉ፣ ከወላጆቹ ጋር በነበረባቸው ዓመታት ሁሉ ይህንን ማስተማሩን ቀጥለዋል፡፡ እሱ ስለሚያከብራቸው፣ ይህ ደግሞ ሌሎች ሐቀኛ ሰዎች ከሚያስተምሩት ጋር የሚስማማ ነው፣ እና ሕጉ እንደሚለው፣ ይህ አንድ እውነት ተቀብሎ ያደገ ነው፣ ግን አንድ ቀን በጓደኛው ቤት ማግኘት የሚፈልገውን ነገር አየ እንበል፣ የእሱ ያልሆነውን ለመውሰድ ይፈተናል፣ እናም ያደርጋል፣ ምክን ያቱም እሱ የተማረውን ነገር ስለሚቃረን ከህሊናው ያለፈ ፋይዳ የለውም፣ ሕሊናው ይረብሸው ነበር፣ በመጨረሻም የወሰደውን ለመመለስ ተገዷል፣ ስህተትን የተማሩ ስህተት ቢሆንም ወይም ሐሰት ቢሆንም፣ እውነት ነው ተብሎ ተምሮ፣ እውነት ሆኖ ከተቀበለ እውነት ነው ተብሎ የተማረውን ቢቃወም ሕሊናው ረበሸው፡፡

ከዚያም የአንድ ሰው ሕሊና አስተማማኝ እንዲሆን በእውነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፣ በሌላ አነጋገር፣ እውነት የእግዚአብሄር ቃል

ሕሊናን መግዛት አለበጥ አንድ ሰው ሕሊናው በውሸት ወይም በስህተት ላይ የተመሰረተ ከሆነ ሕሊና አስተማማኝ መመሪያ እንደሆነ ሊታወቅ አይችልም፡፡

ወደ እግዚአብሄር ቃል ስንመለስ ሳኦል ጥሩ ሆኖ እናገኘዋለን፣ ይህ ማለት አሁን ከምንናገረው ጋር የሚስማማ ምሣሌ ነው፡፡ በመጀመሪያ ሳኦል አይሁዳዊ መሆኑን አስታውስ፣ የአይሁድ እነት ተከታይም ነው፣ እናም ክርስትና የዚህ እምነቱ ጠላት እንደሆነ የተማረ የተነገረው ስለሆነ ለኃይማኖቱ በጣም ቀናተኛ ሆነ፣ በዚህም ምክንያት ክርስትያኖችን ሊያሳድድ ወጣ፣ ስለእርሱ ስናነብ “ሳኦል ግን ቤተክርስትያንን ያፈርስ ነበር፣ ወደ ሁሉም ቤት እየገባ ወንዶችንም ሴቶችንም እየጎተተ ወደ ወይኒ አሳልፎ ይሰጥ ነበር” (ሐዋሪያ *ሥራ* 8፡3) ስለእሱ ማንበቡን ስንቀጥል “ሳኦል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀካህናት ሄደ፣ በዚህ መንገድ ያሉትንም ሰዎች ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ፣ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኩራቦች ደብዳቤ ከእርሱ ለመነ” (የሐዋሪያት *ሥራ* 9፡1~2) ታሪኩ ሲቀጥል ሳኦል እና ባልደረቦቹ ጌታ በተገለጠልርት ጊዜ ወደ ደማስቆ በሚወደው መንገድ ላይ ነበሩ ፣ እንዲህ ይነበባል “በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ ፦ ሳኦል ሳኦል ስለምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ፣ ጌታ ሆይ አንተ ማንነህ? አለው ? እርሱም አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው፣ እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ፦ ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው ጌታም ተነስተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው?” (የሐዋሪያ *ሥራ* 9፡4~6) ዘገባው እንደሚነግረን ሐናኒያ የሚባል አንድ የወንጌል ሰባኪ ወደ እርሱ መጥቶ ተነስቶ እንዲጠመቅ እንደነገረው ኀጥያቱ ይታጠብ ዘንድ ዘግቧል (የሐዋሪያት *ሥራ* 22፡16) አሁን ሳኦል ምን አደረገ? በክርስቶስ አመነ፣ ከኃጥያቱ ተፀፀተ፣ ክርስቶስን ጌታ እንደሆነ አምኖ ተጠመቀ፣ ይህንንም ሲያደርግ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ወዲያው እንደሰበከ ይናገራል (የሐዋሪያ *ሥራ* 9፡20)

አሁን ስለዚህ ሰው አስቡት እሱ በጣም ቅን፣ ለአይሁድ እምነት ቀናተኛ ሰው ነበር፡፡ ክርስቲያኖችን ወንዶችንም ሴቶችንም እስከ ማሳደድ ድረስ ክርስትናን ይቃወም ነበር፡፡ ነገር ግን በድንገት በክርስቶስ አመነ እና ጌታን ሲታዘዝ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ ብሎ ሰበከ፡፡ ይህም ብቻ ሣይሆን ቀሪ ህይወቱን ጌታን በማገልገል እና ዓላማውን በማስፋፋት አሳልፏል፡፡

ግን ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ስለነበሩት ዓመታትስ ምን ማለት ይቻላል ? እሱ ባደረገው ነገር ሐቀኛ እና ቅን ነበር? ለምን ይህን ሁሉ እንዳደረገ ሲገልፅ ፦ “እኔም ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን ስም የሚቃወም

እጅግ ነገር አደርግ ዘንድ እንዲገባኝ ይመስለኝ ነበር፣ ይህንም ደግሞ በኢየሩሳሌም አደረግኩት ከካህናት አለቆቹም ሥልጣን ተቀብዬ እኔ ከቅዱሣን ብዙዎቹን በወይኒ አሳሰርኳቸው ሲገድሏቸውም አብሬ ነበርኩ፣ በምኩራብም ሁሉ ብዙ ጊዜ እየቀጣሁ ይሰድቡት ዘንድ ግድ አልኳቸው፣ ያለልክ ስቆጣባቸውም እስከ ውጭ አገር ከተማዎች ድረስ እንኳን አሳድድ ነበር"

እነዚህ ሁሉ የሚነግሩን ሳኦል እነዚህን ሁሉ በሚያደርግበት፣ ቤተክርስቲያንን በሚያሳድድበት ጊዜ በጥሩ ህሊና ሆኖ እንደሆነ ነው፣ ለሚሠራው ሥራ በታማኝነት እና አክብሮት ነበረው። ለሚሠራቸው እና ለሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ስለትክክለኛነቱ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ አልነበረውም፣ ነገር ግን የእሱ ጥሩ ሕሊና እግዚአብሄር በሚፈልገው መሰረት ላይ አልነበረም የሳኦል ሕሊና የሳኦል አስተሳሰብ ጥሩነት ለእሱና የሱ ለሆኑት ነበር፣ የእሱ ሕሊና ጥሩነት የአስተሳሰቡ ትክክለኛነት በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያወቀው እና የተረዳው እውነትን ሰምቶ አምኖ ከታዘዘ ቦኃላ ነው፣ በመጨረሻ ሳኦል ስሙ ተቀይሮ ጳውሎስ ከተባለ ስለራሱ የፃፈውን እንዲህ ያስነብበናል "ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረኝ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰኛለሁ። አስቀድሞ ተሳዳቢና፣ አሳዳጅ፣ አንገላቺም፣ ምንም ብሆን፣ ይህን አደረገልኝ፣ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግኩት ምህረትን አገኘሁ፣ የጌታችንም ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ካሉ ከእምነትና ከፍቅር ጋር አብልጦ በዛ። ኃጥያተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ፣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው። ከኃጥያተኞቹም ዋና እኔ ነኝ፣ ስለዚህ ግን የዘላለምን ህይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሣሌ እንድሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በሚሆን በእኔ ላይ ትዕግሥቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ ምህረትን አገኘሁ፣ ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው፣ ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከዘላለም ድረስ ይሁን አሜን" (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡12~17)።

ከላይ በተመለከትኩት እኔ እንደማስበው ጳውሎስ በእግዚአብሄር ፊት በፍፁም ሕሊና የኖረበትን ጊዜ ያሳውሰዋል (የሐዋሪያት ሥራ 23፡ 1) ሆኖም ግን የቀድሞ ዘመኖቹን ከእግዚአብሄርና ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመታገል እና የጌታን ሕዝብ ሲያሳድድ አሳልፏል። እውነትን ሲማር እና እራሱን ክርስቲያን ለመሆን እግዚአብሄርን በመታዘዝ፣ የኃጥያተኞች አለቃ ከሆነ፣ መዳን እንደሚቻል የእግዚአብሄር ምህረት እና ፀጋ ታላቅ እንደሆነ ተገነዘበ። ያለፈውን ጊዜ አልረሳውም ነገር ግን ወደ ፊት ለመራመድ የበለጠ ማበረታቻ እንዲሰጠው እና ያለፈውን ለመካካስ የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ የፈቀደለት ሲሆን ቀሪ ህይወቱን የክርስቶስን ጉዳይ በማስፋፋት ነው።

ወዳጆቼ እግዚአብሄር ከሰዎች የሚፈልገው በጎ ሕሊና ያሚፈልግ ከሆነ ይህ ማለት ሁሉም ኃይማኖተኛ ሰዎች ሁሉ ይድናሉ ወይም ድነዋል ማለት ነው፣ የሁሉም ቤተክርስቲያን ሰዎች እንዲነርሱ መዳን ይችላሉ ማለት ነው፣ ሰዎች በእግዚአብሄር አመኑም አላመኑም በጎ ሕሊና ካላቸው ይድናሉ ማለት ነው፣ አንድ ሰው በጥሩ ሥነ ምግባራዊ ህይወት ላይ በመመስረት ወይም መልካም ሥራዎችን በማድረግ ብቻ መዳን ይችላል ማለት ነው፣ በእርግጥ አንድ ሰው ክርስቲያን መሆን አለመሆኑ የቤተክርስቲያን አባል መሆን አለመሆኑ ወይም አንድ ሰው ለእግዚአብሄር ታማኝ ቢሆን ወይም ባይሆን ምንም ችግር የለውም ማለት ነው፣ ሁሉም ሰዎች ውሎ አድሮ የራሳቸውን አስተሳሰብ፣ ድርጊት፣ ኃይማኖት፣ ወዘተ የማጽዲቅ ዝንባሌ አላቸው። ሕሊናቸው እስከማይወቅሳቸው ድረስ ሕሊናቸውን ሊኮርጁ ወይም የአምላክን ፈቃድ ሊቃወሙ ይችላሉ፣ እንደነዚህ ዓይነቶችን (1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1~5)።

መልካም ሕሊና ብቻውን እንግዲያውስ መልስ አይደለም፣ ወይም አይሆንም፣ ይህም የመዳንን መንገድ አያረጋግጥም፣ አንድ ሰው ሕሊናው ትክክል እንዲሆነ ሊቆጥረው የሚችለው በእግዚአብሄር ፈቃድ እውቀት ላይ ሲመሰረት ብቻ ነው፣ ስለዚህም አንድ ሰው አስተሳሰቡን፣ ተግባሩን እና ሕይወቱን የሚመራው በእግዚአብሄር ቃል ነው። ሕሊና አስተማማኝ መመሪያ ሊሆን የሚችለው በእግዚአብሄር ቃል ሲመራ ወይም በሌላ መንገድ ሲገለፅ፣ ሳሊናው ሲያስጨንቀው፣ የእግዚአብሄርን ትምህርት ሲፃረር ወይም ጌታ የሚፈልገውን ሳያደርግ ሲቀር ብቻ ነው፣ ሳሊናው ሕያውና ደህና ነው ማለት ነው።

መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄርን ቃል ይዟል፣ እሱ እውነት ነው፣ ትክክልም ነው። አሁን ስንኖር፣ በመንፈስ እንደተሰጠን፣ ያ ማለት ትክክል ነን ማለት ነው። መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር ሲመሰክር፣ ማለትም የመንፈስ ቃል የጌታን ትምህርት እንደፈፀምን ሲስማማ፣ ያኔ እኛ የእግዚአብሄር ልጆች መሆናችንን እናውቃለን፣ ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚለውን አድምጥ “የእግዚአብሄር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል” ይላል (ሮሜ 8፡16) በሌላ በኩል የመንፈስ ቃል የእግዚአብሄር ቃል አንድ ነገር ሲናገር ወይም አንዳንድ ነገሮችን ሲያስተምር እኛ ሳንታዘዘው ወይም ጌታ ከእኛ የሚፈልገውን ጠብቀን እንዳለብን ሲጠይቀን ይህ በቃሉ በኩል መንፈሱ ተናገረን ማለት ነው፣ ይህ እኛ የእግዚአብሄር ልጆች አለመሆናችንን እየመሰከረ ወይም እያወጀ ነው፣ወይም ጌታ እንደሚፈልገው እየታዘዝን አይደለም ማለት ነው።

ይህ ማለት ጥሩ ስሜት ወይም በጎ ሕሊና ብቻ መኖር መዳናችንን የሚያሳይ ማረጋገጫ አይደለም፣ እባክህን ጌታ በቃሉ ከደነገገው በተለየ መንገድ መዳን እንደሚችሉ በማሰብ እናዳትታለሉ። በእርግጥ

የእግዚአብሄርን ፈቃድ ካወቅን እና እሱን መታዘዝ ከቻልን፣ ይህ ማለት ሕሊናችን ሕያው ከሆነ፣ እግዚአብሄር የተናገረው ለእኛ አስፈላጊ ከሆነ ሕሊናችን ይረብሸናል፣ እናም ይህ ጥሩ ማሳሰቢያ ነው። እኛ በእግዚአብሄር ፊት ነገሮችን ማስተካከል አለብን። ያን ስናደርግ ፈቃዱን እንደፈፀምን ስንገነዘብ ጥሩ ስሜትን፣ በጎ ሕሊናን ያስገኛል፣ ነገር ግን የአምላክን ፈቃድ አውቀን እሱን በመታዘዝ ላይ ብቻ ስንሆን ሕሊናችን በትክክለኛው ቦታ ሆኗል አስቧል ማለት ነው።

ጥሩ ሕሊና አለህ? የእግዚአብሄርን ፈቃድ ታውቃለህ? ፈቃዱን ታዘሃል? ባይሆን ሕሊናህ እንደሚያስቸግርህ እና ጌታን እስክትታዘዝ ድረስ እንደሚቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ። በክርስቶስ ካመንክ፣ ከኃጥያትህ ንሠሀ ገብተህ፣ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ከመሰከርክ እና ለኃጥያትህ ሥርየት ከተጠመቅክ ጌታ ያድንሃል እናም የእሱ ልጅ እና ቤተሰቡ አባል፣ የቤተክርስቲያን አባል ያደርግሃል። (ማርቆስ 16፡ 16፣ሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ ገላቲያ 3፡26~27፣ ሐዋሪያ ሥራ 2፡47) ይህን ብታደርግ የጌታ ፈቃድ ላንተ እንደሆነ ታውቅ ዘንድ በጎ ሕሊና ሊኖርህ ይችላል፣ ለእግዚአብሄርም ታዘሃል እሱም አድኖሃል ማለት ነው።

## ትምህርት 24
## የጌታን ስም ለምን እንጠራለን

ቅዱሳት መፅሐፍት የጌታን ስም ስለመጥራት ይናገራል፣ ከረጅም ዘመናት በፊት ነቢዩ እዩኤል በትንቢት የተናገረውን ስንመለከት እንዲህ ይላል “ከዚህም ቦኃላ እንዲህ ይሆናል መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፣ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ። ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፣በላይ በሰማይ ድንቆችን አሳያለሁ፣ በታች በምድርም ደምና እሳት የጢስም ጭጋግ፣ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሄር ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ። ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣል። እንዲህም ይሆናል፣ የእግዚአብሄር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፣ እግዚአብሄርም እንደተናገረ፣ በፅዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሄር የጠራቸው፣ የምሥራች የሚሰበክላቸው ይገኛሉ” (ኢዩኤል 2፡28~32)

የእግዚአብሄር መንፈስ በሐዋሪያቶቹ ላይ ከፈሰሰ እና ሐዋሪያቶቹ በአዲስ እና በሌላ ቋንቋ በመናገራቸው በዚያ የተሰበሰቡት ማለትም ለጴንጤቆስጤበአልየመጡትከተለያየሀገርየመጡሲሆንከሐዋሪያቶቹ በራሳቸው ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተው እነዚህ ጉሽ ጠላ ጠጥተው ነው ባሉበት ጊዜ መፅሐፍ ሲናገር “ ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፣ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፣ አይሁድ

በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፤ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ ቃሎቼንም አድምጡ። እናንተ እንደመሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፤ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፤ ነገር ግን ይህ በነቢዩ ኢዩኤል የተባለው ነው፤ ‵እግዚአብሄር ይላል፤ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ፤ ድንቆችን በላይ በሰማይ፤ ምልክቶችንም በታች በምድር እሰጣለሁ ደምም እሳትም የጢስ ጭጋግም ይሆናል፤ ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ፤ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል” (የሐዋሪያት ሥራ 2፡14~21)

ኢዩኤል በጥንት ዘመን በተናገረው ትንቢት በኢየሩሳሌም ከተማ በጴንጤቆስጤ ቀን ፊፃሜው ላይ ከክርስቶስ ሞት፣ከመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ እና ከደህንነት መምጣት ጋር የተያያዘ መሆኑ ግልፅ ነው። ይህ ሁሉ የሆነው በመጨረሻው ዘመን ማለትም ከክርስቶስ ሞት በኃላ ባሉት ቀናት ነው። የዕብራዊያን ፀሐፊ እግዚአብሄር በመጨረሻው ዘመን ሰውን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንደሚናገር ያስነብበናል (ዕብራዊያን 2፡1~2) ክርስቶስም በዚያ መጀመሪያ ዘመን በሐዋሪያት በኩል ተናግሯል፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም በቃሉ ተናገረን። በአዲስ ኪዳን እንደተገለፀውም ጳውሎስ ሲናገር “ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልኩትም፤ አልተማርኩትምም” ይላል (ገላቲያ 1፡ 12) ዮሐንስ በራዕይ ስለ ክርስቶስ ያየውን የተመለከተውን አስመልክቶ ደግሞ እንዲህ ይላል “ዘመኑ ቀርቧልና የሚያነበው፤ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተፃፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው” ይላል (ዮሐንስ ራዕይ 1፡3)

ስለዚህም በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ መንፈስ ቅዱስ በሐዋሪያት ላይ ከፈሰሰ በኃላ የክርስቶስን መምጣት አስመልክቶ የሰበከውን ተአምራትን በእግዚአብሄር ዘንድ እንደሰበከ የሚነግረን ዘገባ አለን። ስለሞቱ፤ መቀበሩና ትንሳኤው፤ እናም በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀምጦ የነገሥታት ንጉስ የጌቶች ጌታ ሆኖ ሊነግስ ወደ አባቱ ወደ ሰማይ ስለመመለሱ፤ እነዚህን ነገሮች ሲሰሙ ወደ 3000 የሚያህሉ ልባቸው ተነካና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ ፈልገው ጠይቀው የሆነውን ዘገባው እንደሚከተለው ይገልፀዋል “ ጴጥሮስም ንሠሀ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፤ የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው፤ በብዙ ሌላ ቃልም መሰከረና፦ ከዚህ ጠማማ ትውልድ

ዳኑ ብሎ መከራቸው ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፣ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፣ በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር" (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38~42)

በመጀመሪያ ፦ አሁን እዚህ ብዙ ነገሮችን እናስተውል፣ ጴጥሮስ የጌታን ጥሪ ጥቅሶአል። ይህን የሚያደርገው እንዴት ነው? ጳውሎስ በተሰሎንቄ ላሉ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏቸዋል "ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ" ይላል (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡14)፣ በሌላ አነጋገር፣ የተጠሩት ጳውሎስ በሰበከው ወንጌል ነው፣ ወንጌል ምን ነበር? በሮሜ 10፡15፣ በጌታ ሞት፣ መቀበር እና ትንሳኤ መዳን ወይም የምሥራች ዜና ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~4) በተጨማሪም፣ አንድ ሰው እንዲድን መሟላት ያለባቸው የወንጌል ሁኔታዎች ነበሩ። ከነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ በክርስቶስ ማመን ነው። ሌላው ደግሞ አንዱ ከኃጥያቱ ንሰሃ መግባት ነው። በመጨረሻም አንድ ሰው ለኃጥያቱ ስርየት መጠመቅ ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነበር። እንግዲህ ይህ ሁሉ በሐዋሪያት ሥራ 2 ተሰብኳል። ሐዋሪያት የክርስቶስን ሞት፣ መቀበር እና ትንሣኤ ሰብከዋል፣ እናም ሦስት ሺህ የሚያህሉ አማኞች ሆነው ከኃጥያታቸው ሥርየት እንዲጠመቁ ተነገራቸው። በወንጌል ስብከት ጌታ እንዲታዘዙት እየጠራቸው ነበር እንደተገለፀው ወደ ሦስት ሺህ የሚያህሉት ያን ጥሪ ተቀብለው ጌታን ታዘዙ፣ እርሱም በተራው አዳናቸው እና ወደ ቤተክርስቲያኑ ጨመራቸው .

ሁለተኛ ፦ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል የሚል ትንቢት በኢዩኤል ተተንብዮአል፣ ጴጥሮስና ሐዋሪያቶቹም ለሕዝቡ ይህ ትንቢት በዚይ ቀን በጴንጤቆስጤው በዓል ላይ እንደተፈተፈፀመ ሰብከዋል፣ ታዲያ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል ማለት ምን ማለት ነው? ብዙዎች የጌታን ስም የሚጠራ ማለት ደህንነትን መለመን ወይም ለዚያ መፀለይ ማለት ነው፣ በሌላ አነጋገር የጌታን ስም መጥራትን ከፀሎት ጋር ያመሳስሉታል፣ ነገር ግን ፀሎት ከመዳን ጋር በተያያዘ የተጠቀሰው ዬት ጋ ነው? በእርግጥ፣ ክርስቶስ ከተሰበከ ቦኃላ፣ እና በልባቸው ከተሰማቸው ወይም በክርስቶስ ካመኑ ቦኃላ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለማወቅ ፈለጉና ጠየቁ፣ ጴጥሮስም ንሰሐ እንዲገቡና ለኃጥያት ሥርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ እንዳለባቸው ነገራቸው። ዘገባው በመቀጠል ሦስት ሺህ የሚያህሉ ነፍሳት ይህንን እንዳደረጉና ጌታ የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያኑ እንደጨመረ ይናገራል፣ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ የጌታን ስም መጥራት ማለት የጌታን መታዘዝ ማለት ነው፣ በሌላ መንገድ ፣ ክርስቶስ አንድ ወይም ብዙ ሲታዘዝ እንደሚያድናቸው ቃል ገብቷል፣ (ማርቆስ 16፡15~16) ስለዚህ ጌታን በመታዘዝ ላይ፣ እርሱን ለማዳን የገባውን ቃል እንዲጠብቅ በመጥራት ብቻ ጌታን መጥራት ነው።

ሦስተኛ ፦ ጌታ መንፈሱን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ የሚያፈስበት ቀን እንደሚመጣ በትንቢት ተነግሯል። ያን የተስፋ ቃል ጠብቆአል፣ እናም እጨምራለሁ ብሎ የገባውን ቃል መፈፀሙንም ቀጥሏል፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ መመሪያ መሰረት የጌታን ቃል በስብከታቸው ምክን ያት ጌታን የታዘዙ ሁሉ መዳን ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስም ተሰጥቷቸዋል፣ ይህ በበዓለ ሀምሣ ቀን ላሉት ብቻ ሳይሆን ለልጆቻቸው ወይም ለወደፊት ትውልዶች እና በሩቅ ላሉት ማለትም ለአህዛብም በእግዚአብሄርም ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ሆነዋል። ሐዋሪያት እና ቆርኔሊዎስ ከነ ቤተሰቡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ከመቀበላቸው በተጨማሪ ሐዋሪያት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲኖራቸው በተመረጡት ላይ እጃቸውን እንዲጭኑና ኃይል እንዲያስተላልፉ ጌታ ሥልጣንን ሰጥቶአቸዋል። ሌሎቹ ሁሉ ተራውን የመንፈስ ቅዱስ መለኪያ ወይም ተአምራዊ ያልሆነውን የመንፈስ ቅዱስ መለኪያ ተቀብለዋል። ይህም እስከ ዘመናችን ድረስ ቀጥሏል፣ ስለዚህ ጌታ እነዚህን ትንቢቶች ፈፅሞአል፣ እናም ቃሉ በሁሉም ሁኔታዎች ተጠብቆ ቆይቶአል።

በሆነ ጊዜ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች እንዲህ ብሎ ፅፏል “ነገር ኝ ምን ይላል? በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፣ ይህም የምንሰብከው የእምነት የእምነት ቃል ነው። ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሄርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፣ ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃልና፣ በአፉም መስክሮ ይድናልና። መፅሐፍ ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና። በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፣ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፣ ለሚጠሩትም ሁሉ ጌታ ባለጠጋ ነው፣ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፣ እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙጽ እንዴት ያምናሉ? ያለሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው? ተብሎ እንደተፃፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙምኢሳያስ፦ጌታ ሆይምስክክርነታችንን ማን አመነ? ብሎአልና፣ እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው” **(ሮሜ 10፡8~17)**

በቅዱሣትመፅሐፍትእባክህንፀሐፊውእያለያለውንበማስተዋል አንብብ፣ ፀሐፊው በድጋሚ የጌታን ስም መጥራትን ያመለክታል፣ እና ምንድነውየሚካተተው?ከአውዱፅሑፉእንደምንረዳውየእግዚአብሄር ቃል መሰበክ መሰማት ማመን፣ ክርስቶስን መመስከር አለበት ይላል፣ እና ምንም እንኳን ንሠሐ እዚህ ላይ ባይገለፅም ጥምቀትም በይገለፅም ነገር ግን ቃሉን የመስበክ አካል እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። በእግዚአብሄር እና በጌታ በማመን በሐዋርያት ሥራ እና ሌሎች በርካታ ከደህንነት ጋር በተያያዙ ቅዱሳት መፅሸሐፍት ውስጥ የተዘረዘሩት

ስለጻህንነት ስለመለወጥ የተፃፉ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ዋናው ነገር ግን አንድ ሰው ጌታን ሲታዘዝ እንደገና ጌታ የገባውን ቃል እንዲፈፅም እንጠራዋለን ማለት መሆኑን ማወቅ ነው፡፡ “ለአንዳንዶቹ የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንሠሀ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለእናንተ ይታገሳል” (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)

ለመዳን የጌታን ስም ጠርተሃል? የለም እዚህ ስለፀሎት ማውራት አስፈላጊአይደለም፣ጌታንመታዘዝላይእናስባለን፣ለፈቃዱበመታዘዛቸሁ ብትጠሩት እርሱ እናንተን በማዳን እና ወደ ቤተክርስቲያኑ በመጨመር ምላሽ ይሰጣል፡፡ ለመዳን ሌላ መንገድ የለም፡፡

## ትምህርት 25

## ጥሩ ስነምግባር መኖር ለጻህንነት ብቻውን ለምን በቂ አይሆንም

ብታውቅም ባታውቅም፣ ምናልባት የብዙ ሰዎች ሰዎች መጥፋት ምክንያቱ ጻህንነትን በመልካምነታቸው ለማግኘት ስለሚጥሩ ነው፣ ይህንን በተመለከተ ወደ ኢየሱስ ሰማያዊውን የዘላለም ህይወት ፍለጋ የመጣውን ወጣት ያስታውሰናል እንዲህ ይነበባል “እነሆም አንድ ሰው ቀርቦ ፦ መምህር ሆይ የዘላለምን ህይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ አለው፡፡ እርሱም ስለመልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ መልካም የሆነ አንድ ነው ወደ ህይወት መግባት ብትወድ ግን ትዕዛዛትን ጠብቅ አለው፣ እርሱም ዬትኞቹን ? አለው፣ ኢየሱስም አትግደል አታመንዝር፣ አጽረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አባትህንና እናትህን አክብር፣ ባለንጀራህን እንደራስህ ውደድ አለው፡፡ ጎበዙም፦ ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጃብሬ ጠብቄአለሁ፣ ደግሞስ የሚጎድለኝ ምንድርነው? አለው፣ ኢየሱስም፦ ፌፁም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆቸ ስሸ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ አለው፡፡ ጎበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ” (ማቴዎስ 19፡16~22)

የቀደመው ታሪክ የተከናወነው በብሉይ ኪዳን ነው፡፡ ኢየሱስ ዘላለማዊ ህይወት እንዲኖረው ከፈለገ አሥርቱን ትዕዛዛት በመጥቀስ ትዕዛዛቱን እንዲጠብቅ ሲገልፅ ከታናሽነቴ ጃምሬ ጠብቀያለሁ በማለት ምላሽ ሰጠ። ይህ ሰው በርግጥ ጥሩ ሥነምግባር ያለው ሰው ነበር፣ ወይም በሌላ መንገድ፣ እሱ በምንም ዓይነት መንገድ ምንም ዓይነት ክፉም ያለሆነ እና ይህ ባህሪው ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደው አድርጎ ነበር ያሰበው፣ ለዚህም ይህን ሐሳቡን ጌታ እንዲያፀድቅለት ነበር የፈለገው፣በዚህ ሁኔታ ግን ብቻ በቂ አልነበረም፡፡ ሂዶ ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድሆቸ እንዲሰጥ ነገረው፣ ከዚያም አሳዛኝ መግለጫ የሆነው ይህን በሰማ ጊዜ ብዙ ባለጠግነት ስለነበረው እያዘነ ሄደ ይላል፡፡ መልካም ሥነምግባር ባለቤት መሆን አንድን ሰው ሊያድነው በቂ አይደለም፡፡

ስለዚህ ታሪክ ጥሩ ምሣሌ የሚሆነን ሌላው ቆርኔለዎስና ቤተሰቡ ናቸው፣ ቆርኔለዎስ አህዛብ ነው፣ እሱ በ ውትድርና ዓለም ውስጥ ባለሥልጣንና ትልቅ ቦታ ያለው ሰው ነው። የመቶ አለቃም ነበር፤ ዘገባውም እንደሚለው "እርሱም ከቤተሰቦቹ ጋር እግዚአብሄርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምፅዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሄርም ሁልጊዜ የሚፀልይ ነበረ" (የሐዋሪያት ሥራ 10፡2)፣ ሆኖም የጠፋ ሰው ነበር። በጌታ ጣልቃ ገብነት ቆርኔሌዎስ እና ቤተሰቡ እና ጴጥሮስ እና ወንድሞቹ አንድ ላይ ተሰበሰቡ። በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ሰበከላቸው እና ዘገባው እንደሚለው ወንጌል ለአይሁድ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ አህዛቦቸም ላይ ወረደ ይላል፣ ከዚያ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ጠየቀ "በልሳኖቸ ሲናገሩ እግዚአብሄርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና፣ በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ ፦ እነዚህ እንደእኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚቸል ማነው? አለ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው፣ ከዚህ ቦኃላ ጥቂት ቀን እንዲቀመጥ ለመኑት" (ሐዋሪያት ሥራ 10፡47~48)፣ ቆርኔሌዎስ የኖረበትን ዘይቤ ደግመህ ብታስብ፣ ዛሬም እንደሱ  ዓይነት እግዚአብሄርን የሚፈሩ፣ ምፅዋት የሚሰጡ፣ እግዚአብሄርን የሚያመልኩ ለድሆቸም የሚመፀውቱ እንዳሉ ታያለህ፣ ስለዚህ ሁልጊዜ መፀለይ፣ መልካም ሰው መሆን እንደጥሩ ሰው ሆኖ ይመደባል፣ ሆኖም ግን ቆርኔሌዎስ የጠፋ ሰው ነበር፣ ስለዚህም ወንጌልን መስማት፣ ማመን፣ እና መታዘዝ ነበረበት፣ እንዲድን እና ወደ ጌታ ቤተክርስቲያን መጨመር ነበረበት፣ እናም ከነቤተሰቡ ታዘዘ አደረገ፣ ይህን ፈቃደኛ ሆኖ ባያደርጋቸው ኖሮ የሚያደርጋቸው መልካም ነገሮቸ ሁሉ ጠፍተው እሱም ይጠፋ ነበር።

እውነት ነው አንድ ሰው ለመዳን ጥሩ የሞራል ህይወት መኖር አለበት። ያ ማለት አንድ ሰው መጥፎ እና ስህተት የሆኑትን ወንጀለኞቸ ከማድረግ መቆጠብ አለበት ማለት ነው። ከዚህም በላይ አንድ ሰው የሥጋን ሥራ መሥራት አይቸልም ማለት ነው ጳውሎስ ይህንን አስመልክቶ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖቸ ሲፅፍ "ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይቸሉ ያግቡ፣ ሚስትም ከባሏ አትለያይ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባሏ ትታረቅ ባልም ሚስቱን አይተዋት ብዬ የተጋቡትን አዛቸዋለሁ እኔ ግን አላዝም ጌታ እንጂ" (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡9~10) እንደዚሁም ለነዚህ ወንድሞቸ ከአለም ጋር ስላላቸው ግንኙነት እንዲህ ይላል "ከሴሰኞቸ ጋር እንዳትተባበሩ በመልዕክቴ ፃፍሁላቸሁ። በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞቸን ወይም ገንዘብን የሚመኙትን ነጣቂዎቸንም ወይም ጣኦትን የሚያመልኩትን አላልሁም፣ ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባቸሁ ነበር። አሁን ግን ወንድሞቸ ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም

ጣኦትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆኑ ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እፅፍላቸዋለሁ፣ ከንደነዚህ ካሉ ጋር መብልን እንኳን አትብሉ" (1ኛ ቆሮንቶስ 5፡9~11) እዚህ ላይ ጳውሎስ ከዓለማዊ ሰዎች ጋር ሳንገናኝ በዚህ ህይወት መመላለስ አይቻልም እያለ ነው፣ ነገር ግን በክርስቶስ ከዳተኛ ወንድም ጋር በተያያዘ ፈርሀ አምላክ የሌለበት ህይወት እየመራ ከሆነ እንዲህ ካለው ሰው ጋር መተባበር ወይም መቅረብ የለብንም እያለ ነው።

ጳውሎስ ለገላቲያ ወንድሞች ሲፅፍ እንዲህ ብሏል " የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው፣ አስቀድሜም እንዳልሁ፣ እንደነዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሄርን መንግሥት አይወርሱም" ይላል (ገላቲያ 5፡19~21)። ጳውሎስ በእነዚህ የተለያዩ ቅዱሳት መፅሐፍት ውስጥ አንድ ሰው በእነዚህ ኃጥያት ተግብራት ውስጥ ገብቶ ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ወይም ወደ ጌታ ቤተክርስቲያን መግባት እንደማይችል እየተናገረ ነው፣ እንደክርስቲያኖችም አንድ ሰው በእንደዚህ ዓይነት ኃጥያተኛ ድርጊቶች ቢሳተፍ እግዚአብሄርን ማስደሰት አይችልም። አንድ ሰው እንደነዚህ ያሉትን ባለማድረግ ብቻ መዳን ባይቻልም ነገር ግን አሁንም ደግ ክርስቲያን ለመሆን ጌታ የሚፈልገው ከክፉ መምሰል መራቅ እንዳለበት ነው፣ (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡22)።

አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያን ከሌሎች ኃይማኖቶች የበለጠ የሞራል ነፃነት ይፈቀድለታል የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ አላቸው፣ ክርስቲያን የሚያጨስ፣ የሚጠጣ፣ የሚሰክር፣ ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት የሚፈፅም፣መጥፎ ቋንቋ የሚናገር፣ ጨዋነት የጎደለውልብስ የሚለብስ ወዘተ የመሳሰሉትን ያስባሉ፣ በእነዚህ እና በሌሎች ልማዶች ውስጥ ክርስቲያን ነን የሚሉ የሚያደርጉ አንዳንዶች አሉ፣ይህን ማድረጋቸው ግን አምላክን ያሳዝናል። ንሰሀ ካልገቡ በቀር ይጠፋሉ፣ አንድ ሰው ለመዳን እና ክርስቲያን ለመሆን በእግዚአብሄር ማመን ብቻ ሳይሆን በክርስቶስም የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ከኃጥያቱ ሁሉ ንሰሀ መግባት ወይም ከኃጥያቱ መራቅ አለበት እና ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን አምኖ መቀበል ወይም መመስከር እና በመጨረሻም መጠመቅ ኃጥያቱን መታጠብ አለበት፣ አንድ ሰው ይህን ሲያደርግ ብቻ ነው ጌታ እሱን ለማዳን እና ወደ ቤተክርስቲያኑ ለመጨመር የሚፈልገው፣ እንደ ክርስቲያን የህይወትን አክሊል የሚቀበል ከሆነ እስከ ሞት ድረስ ለጌታ ታማኝ መሆን አለበጥ እነዚህን ሁሉ የምናነበው (ማርቆስ 16፡15~16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ ማቴዎስ 10፡32፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡47፣ ዮሐንስ ራዕይ 2፡10)

አሁን አንድ ሰው ጥሩ ሥነ ምግባራዊ ሰው መሆን እና በመልካም ኑሮው እንደሚድን ማመን ይቻላል፣ ነገር ግን እንደ ኃጥያተኞች ለመዳን ከፈለገ ጌታን መታዘዝ አለበት፣ ቸርነቱ ብቻውን አያድነውም፣ የራስን የፅድቅ ሥራ መሥራት አያድነውም፣ (ኤፌሶን 2፡8~9፣ ቲቶ 3፡ 5)፡፡ አንድ ሰው በመልካምነቱ መዳንን ከማሰብ ይልቅ ንሠሐ መግባት እና ከኃጥያቱ መመለስ አለበት፣ ምክን ያቱም ጳውሎስ ሲናገር "ሁሉም ኃጥያት ሠርተዋል" ይላልና (ሮሜ 3፡23)፣ ከዚያም የምናነበው ክርስቶስ የጠፉትን ፍለጋ መምጣቱን ነው (ሉቃስ 19፡10) አይደለም ክርስቶስ የሞተው ሰው አስቀድሞ ስለዳነ አይደለም፣ ነገር ግን ሰው ስለጠፋ እና መዳን ስላስፈለገው ነው፣ ጴጥሮስ ሲናገር "ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሄር እንዲያቀርበን እርሱ ፃድቅ ሆኖ ስለአመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጥያት ምክንያት ሞቶአልና፣ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ህያው ሆነ" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)

ወዳጄ ድነሃል ? ከሆነስ እንዴት ነው የዳንከው? ጥሩ የሞራል ህይወት በመምራት ወደ ሰማይ ለመሄድ ከሚጥሩት አንዱ ነህ? እምነትህ በራስህ ፣ በዓለማዊ፣ በሀብት፣ በሰው ልጅ ላይ፣ በሰው ሰራሽ ሥርዓት፣ ወይስ በሌላ የዚህ ዓለም ነገር ትተማመናለህ? ወይስ ወደ ሰማይ ለመሄድ የራስህን ፈጠራ ይዘሃል? እነዚህ ከሆነ ይህንን ማድረግ እንደማይቻሉ መገንዘብ ያስፈልግዎታል፣ ከክርስቶስ በቀር ማንም ሊያድን አይቻልም፡፡ እርሱን ስትታዘዙ እና እስከሞት ድረስ ንፁህ እና እግዚአብሄርን በመምሰል ስትኖሩ እርሱ ሊያድንህ ብቻ ሳይሆን በመንግሥተ ሰማያትም መኖሪያ ይሰጥሃል፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ክርስትና ማለት ያ ነው፣

ከብዙ ዘመናት በፊት የእግዚአብሄር ነቢይ ያኔ እውነት የሆነውን መርህ አውጥቶአል፣ ዛሬም ያ መርህ እውነት ነው፣ እንዲህ ይላል፣ "አቤቱ የሰው መንገድ ከራሱ እንዳይደለ አውቃለሁ፣ አካሄዱንም ለማቅናት ከሚራመድ ሰው አይደለም" (ኤርሚያስ 10፡23)፣ ይህንን ለመቀበል ትህትናን ይጠይቃል ነገር ግን አንድ ሰው ይህንን ሲያደርግ ጥበበኛ ይሆናል፡፡

እንደገና ማን እንደሆንክ፣ የምትኖረው ዓይነት ህይወት፣ ጥሩም ሆነ መጥፎ፣ እንድትድኑ እግዚአብሄርን እንድትታዘዙ እመክርሃለሁ፣ በዚያን ጊዜ ብቻ መዳን ትቻላለህ፣ (ማርቆስ 16፡16) ከዚያም በኃላ ብቻ ነው ጌታ ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምርሃል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47)

## ትምህርት 26
## ለምን ለአምልኮ እንሰበሰባለን

እኛ እንደክርስቲያን፣ እና እንደ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ማህበር፣ ሁልጊዜ ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን ለማምለክ ዓላማ እንሰበሰባለን፣ ይህን የምናደርግበት ምክንያቶቹ ደግሞ፦

በመጀመሪያ አንድ እግዚአብሄር አባት ጌታ እና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ መኖሩን መረዳት አለብን፣ እሱ ፈጣሪያችን ነው። እሱ ያለንን ሁሉንም በረከቶቹ የሰጠን ነው፣ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ልጁን ኢየሱስን ልኮ ለዓለም ኃጥያት በመስቀል ላይ እንዲሞትልን አደረገ። በእሱ ፀጋ እና ምህረት እኛን ለማዳን እንዲቻል አደረገ፣ ልጆቹ ስለሆንን እንደሱ ፍላጎት እንኖራለን  እንደ ቃሉ ምሪት እናመልከዋለን ። ልጆቹ  በመሆናችን ለእርሱ ልንኖርና እሱን ልናመልከው እንወዳለን። ክርስቶስም እንደተናገረ "እግዚአብሄር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና  በመንፈስና በእውነት  ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" (ዮሐንስ 4፡24) እግዚአብሄር ሰው አይደለም ወይም እንስሳ ወይም ግቅዝ ነገር  በከዋክብት በወንዝ በተራራ በጨረቃ፣ ወይም በሰው የተሠራ ምስልን አይወክልም ። እርሱ መንፈስ  ነው፣ የሁሉ ነገር ፈጣሪ፣ ወንዝን እና ህይወት ና የህይወት ጠባቂ አምላክ ነው። ሞኝ ብቻ ነው የሚክደው (መዝሙር 14፡1)

የምንሣተፍበት  አምልኮ  ለሰማዩ  አምላክ   የሚሰጠውን አገልግሎት፣ ምስጋና እና ክብርን ያካትታል። አምልኳችን የሚቀርበው በመንፈስ  ነው።  ይህም  ማለት  የምናደርገውን  ነገር  በተመለከተ በቅንነት፣ በትህትና እናደርጋለን።

አምልኳችን  ን የምናቀርበው በእውነት   ነው። ይህም ማለት እግዚአብሄርን የምናመልከው በእውነት ወይም እግዚአብሄር በቃሉ በተናገረው መሰረት ነው። እኛ የምናመልከው እግዚአብሄርን ነው እና ራሳችንን ለማስደሰት ከመገኘት ይልቅ እሱን ማስደሰት እንፈልጋለን።
ይህም ማለት እግዚአብሄርን እንደሰዎቹ ትምህርትና ትዕዛዝ ማምለክ የለብንም ማለት ነው.። እንደፈለግን ብናመልከው ኖሮ እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ ላይ አይናገርም ነበር።

እንደ መፅሐፍ ቅዱስ  ትምህርት እኛ ክርስቲያኖች በእያንዳንዱ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለአምልኮ እንሰበሰባለን፣ ለዚህ ምሣሌ አለን በሐዋሪያት ሥራ 20፡7 ላይ "ከሣምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን፣ ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ሳለሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፣ እስከመንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስርረዘመ" ይላል። በብሉይ ኪዳን ህግ ሰንበት የአምልኮ ቀን ነበር ነገር ግን ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ያን ሕግ ከመንገድ አውጥቷል፣ በራሱ ሕግ ተካ (ቆላስያስ 2፡14) ሕግን  በማንሣት የሰንበት ቀንም እንዲሁ የአምልኮ ቀን መሆኑ ተወግዷል። ክርስቶስ ከመቃብር በሣምንቱ

የመጀመሪያ ቀን እንደተነሣ እናነባለን (ማቴዎስ 28፡1~6)፣ እንዲሁም ወንጌል በመጀመሪያ የተሰበከው በሣምንቱ መጀመሪያ ቀን ነበር፣ ቤተክርስቲያንም የተጀመረችው በዚያው ቀን ነበር (ሐዋሥራ 2)፣ በመጨረሻ ጳውሎስ በቆሮንቶስ የነበሩትን ክርስቲያኖች ካገኙት ገንዘባቸው በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንዲሰጡ ፅፏል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ክርስቲያኖች በእያንዳንዱ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንዲሰበሰቡ ዬትም አይልም ሊል ይችላል፣ እውነታው ግን በያንዳንዱ ሣምንት የመጀመሪያው ቀን አለ፣ እና የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የጌታ ቀን ነው፣ የአምልኮ ቀን ነው፣ ከዚያም ክርስቲያኖች በእያንዳንዱ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለዚሁ ዓላም መገናኘት አለባቸው፡፡

የዕብራዊያን ፀሐፊ ሲነግረን መሰባሰባችንን መተው እንደሌለብን ይነግረናል፣ስሙት “የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና፣ እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፡፡ ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፣ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው፣ እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ፣ የእውነትን እውቀት ከተቀበልን ቦኃላ ወዷን ኃጥያት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለኃጥያት መሥዋዕት አይቀርልንምና፣ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ” ይላል (ዕብራዊያን 10፡23~27)፣ እባክዎትን ምን እያለ እንደሆነ አስተውሉ መሰብሰባችንን መተው የለብንም፣ ስለምን ያወራል? መልካም ፣ ልንተወው የማይገባ ምን ጉባኤ አለን ? አንዳንዶች ትተውት ነበር ነገር ግን እነሱ እንዳደረጉት ማድረግ የለብንም ብሏል፡፡ ይልቁንም ቀኑ እየቀረበ እንዳለ ስናይ በጉባኤው ላይ እንገኝ፣ እርስ በእርሳችን መመካከር ወይም እርስ በርሳችን መበረታታት እንዳለብን ተናግሯል፣ ነገር ግን የአምላክን ፈቃድ ብናውቅም ሆን ብለን ኃጥያት ብንሰራ ጌታ ሊታገሰን እንደማይችል ተናገረ፣ ስለዚህ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማወቃችን ብቻ ሳይሆን ለፈቃዱ መታዘዛችን አስፈላጊ ነው ይህም በቤተክርስቲያኑ ትላልቅ ስብሰባዎች ላይ መገኘትን ይጨምራል፡፡

አሁን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን በማምለክ ምንድነው የምናደርገው? በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ የተዘረዘሩት ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ በሐዋሪያት ሥራ 20፡7 ላይ እንደተገለፀው ክርስቲያኖች ዳቦ ለመቁረስ ወይም የጌታን እራት ለመካፈል ይሰበሰቡ ነበር፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲፅፍ “ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ደግሞ ከጌታ ተቀብዬ አለሁና፣ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ቆርሶም እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፣ ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፣ እንደዚሁም ከእራት ቦኃላ ፅዋውን ደግሞ አንስቶ፦ ይህ

ፅዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፣ በጠጣቻሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላቸሁና፣ ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ፅዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፣ ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከፅዋውም ይጠጣ፣ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፣ ይጠጣልምና። “ (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23~29) እባክህን ይህን አስተውል ጳውሎስ ኅብስቱ የክርስቶስን ሥጋ ለማክበርና ፅዋውም የክርስቶስን ደም በማሰብ መካፈል እንዳለበት ተናግሯል። በሌላ አነጋገር ጌታ ሕዝቡ እንዲድኑ የተከፈለውን ዋጋ በማስታወስ እንዲቀጥሉ ይፈልጋል። ክርስቲያኖቹ የጌታን እራት ሲበሉ ወደ መስቀል ይመለከታሉ። በዚህም ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበትን ጊዜ ያመለክታሉ። ስለዚህ የጌታ እራት በጣም አስፈላጊ ነው። አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሁኔታ በጌታ ፊት የቆመበትን ለማየት የራሱን ህይወት የሚመለከትበት ጊዜ ነው። በተመሳሳይም ክርስቲያኖቹ ስለ ክርስቶስ አንዳንድ ጠቃሚ ትምህርቶችን ለዓለም እንዲያስተምሩ ዕድል ይሰጣቸዋል።

በመቀጠልምክርስቲያኖቹበሣምንቱየመጀመሪያቀንተሰብስበው ማምለክ አለባቸው። በአምልኮአቸውም ከሚያገኙት ስጦታ በዚህ ቀን ሊሰጡ እንደሚገባቸው ጳውሎስ ይናገራል እንዲህ ሲል “ለቅዱሣንም ገንዘብን ስለማዋጣት ለገላቲያ አብያተክርስቲያናት እንደደነገግኩ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፣ እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን ከእናንተ እያንዳንዱ በየሣምንቱ የመጀመሪያ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ፣ “ (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2) በ2ኛ ቆሮንቶስ 9፡6፣7 ላይ ጳውሎስ አሁንም እንዲህ ይላል “ይህንም እላለሁ ፦ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፣ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል እግዚአብሄር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በሀዘን ወይም በግድ አይደለም” ይላል፣ እንደዚሁም ኢየሱስም እንዲህ ብሏል “ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው” (የሐዋሪያት ሥራ 20፡35)፣ በአሮጌው ሕግ የእግዚአብሄር ሰዎቹ አሥራት እንዲያወጡ ወይም ከሚያገኙት ገቢ አንድ አሥረኛውን እንዲሰጡ ታዝዘዋል፣ ነገር ግን ያ ሕግ አሁን አይሰራም፣ ምን ያህል ነው በአዲስ ኪዳን የምንሰጠው? ከአሥር በላይ መሆኑ ጥርጥር የለውም፣ ከክርስቶስ ዘመን በፊት ከነበሩት የበለጠ በረከቶቹ እና ተስፋዎቹ አለንና።

ለእግዚአብሄር የውዳሴ መዝሙር ለመዘመር በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን መሰብሰብ አለብን፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን ለነበሩት ክርስቲያኖቹ ተናግሯል። “በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳቸሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባቸሁ ተቀኙና ዘምሩ” ብሏል (ኤፌሶን 5፡19)፣ ጳውሎስ ቆላስያስ ክርስቲያኖቹም ሲያውጅ እንዲህ

አላቸው “የእግዚአብሄር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገስፁ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳችውም ቅኔ በፀጋው በልባችሁ ለእግዚአብሄር ዘምሩ፣ እግዚአብሄር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት” ይላል (ቆሎስያስ 3፡16~17)። በእነዚህ ጥቅሶች እና ሌሎች ምንባቦች ላይ እንደምታዩት አፅናኦቱ በመዘመር ላይ ነው፣ ዕብራዊ መፅሐፍ ፀሐፊ በከንፈራችን ፊሬ ጌታን ማመስገን እንዳለብን ተናግሯል፣ (ዕብራዊያን 13፡15) እንደ የጌታ ሕዝብ እነሆ በአምልኮ ውስጥ ሜካኒካል ሙዚቃን አንጠቀምም፣ ግን በአምልኮ ውስጥ ሜካኒካል ሙዚቃን መጠቀም ምን ችግር አለው? በመዝሙር ብቻ እግዚአብሄርን ማምለክ አንችልም ? እንደሚቻል ታውቃላችሁ፣ ስለዚህ ቅዱሳት መፅሐፍት በግልፅ እንደሚያስተምሩ እንዘምር፣ ከዚያ ወዲያ መሄድ ጌታን አለማስደሰት ሊህን ነው። በአምልኮው እኛን ደስ እንዲለን ሳይሆን ጌታን ደስ ለማሰኘት እስከሆነ ድረስ ያለሙዚቃ መሣሪያ ማምለክ አለብን። በአምልኳችን መደሰት ያለበት እኛ ሳንሆን ሊመለክ የተገባው እግዚአብሄር ነው።

በመጨረሻም እንደክርስቲያን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ልንሰበሰብ ይገባናል፣ እግዚአብሄርን በመፍቀድ በቃሉ እንዲናገረን እኛ ደግሞ በፀሎት ለእግዚአብሄር በመናገር ቃሉንም በማጥናት እንበረታታለን።(2ኛ ጢሞተዎስ 2፡15)። ክርስቶስ ቅዱሳት መፃሐፍትን እንድንመረምር ጠይቋል (ዮሐንስ 5፡39)፣ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች “በሐዋሪያት ትምህርትና በኅብረት እንጀራንም በመቁረስ በፀሎትም ፀንተው ይተጉ ነበር “ (ሐዋሪያ ሥራ 2፡42)፣ ያለመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ያለፀሎት እንዴት ማምለክ እንችላለን?

እግዚአብሄርን ታመልካለህ ? በመደበኛነት ታደርጋለህ ? ክርስቲያን ነህ? ካልሆንክ እርሱን ተቀባይነት ባለው መንገድ እንድታመልከው ከርሱ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት የለህም። ክርስቲያን እንድትሆን ላበረታታህ እወዳለሁ፣ ክርስቶስ እንዲህ አለ “ያመነ የተጠመቀም ይድናል “ ብሏል (ማርቆስ 16፡16) ይህን ስታደርግ ክርስቶስ በቤተክርስቲያኑ ላይ ይጨምርሃል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47) ከዚያም ማምለክ ትችላለህ።

## ትምህርት 27
## በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለምን እናመልካለን

መፅሐፍ ቅዱስ እኛ ክርስቲያኖች የጌታ ቤተክርስቲያን አባላት እግዚአብሄርን በመንፈስ እና በእውነት ማምለክ እንዳለብን ያስተምራል (ዮሐንስ 4፡24) ይህም ማለት የምንሰራውን በማስተዋል እና በቅንነት ማምለክ አለብን ማለት ነው፣ እና እኛ እንደጌታ ቃል ትምህርት ልናመልክ ይገባናል። ግን መነሣት ያለበት ጥያቄ ያንን የምናደርገው መቼ ነው

የሚል ነው፡፡ እና ምን ያህልስ ማድረግ አለብን ዓርብ ላይ መሆን አለበት? ቅዳሜ እሁድ ወይስ ሌላ የሣምንቱ ቀናት ? ለአምልኮ እስከተገናኘን ድረስ በርግጥ ይህን ማወቅ አስፈላጊ ነውን ?

የብሉይ ኪዳንን በምናነብበት ጊዜ የምንመለከተው እግዚአብሄር ሕዝቡን እስራኤልን ሰንበትን በመቀደስ እንዲያስታውሱ እንዳሚፈልግባቸው እናያለን፡፡ ይህ ደግሞ ከአሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ ነው፣ (ዘፀአት 20፡8~11)፣ ወደዚህ ወደ ክርስቶስ ስንመጣ ደግሞ የምንማረው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተ ቦኋላ ይህንን የብሉይ ኪዳንን ህግ እንዳስወገደና የሰንበትን ቀን አምልኮ እንደቀረ እናያለን (ዮሐንስ 1፡17፣ ቆላስያስ 2፡14፣ ዕብራዊያን 9፡15~17) ስለዚህ የአሮጌው ኪዳን ሲወገድ አዲሱ ኪዳን ተተካ፡፡ ያ እውነት ነው፣ የሰንበት ቀን መታሰብ አቆመ እና ያ ነጥብ ጌታ ለሕዝቡ ለአምልኮ ዓላማ የሚሰበሰቡትን አዲስ ቀን አዲስ ኪዳን አስተዋወቀ፣ ያ ቀን የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነበር፡፡ ያ ሰንበት ወይም ቅዳሜ የሣምንቱ በሰባተኛው ቀን ነበር ፣ አሁን ግን ክርስቶስን በአምልኮ ውስጥ ለማስገባት እናም አምልኮ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹ ነገሮች ሁሉ እሱን እንድናስቀድም የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ሆነ፡፡

የአዲስ ኪዳን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ብዙ የሚናገረው ነገር አለው፣ ይህ ቀን ለምን አስፈላጊ እንደሆነ እና ለምን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደምንሰበሰብ እና እንደምናመልክ አንዳንድ ምክንያቶችን ለመጥቀስ ጊዜ ወስደን እናያለን፡፡

በመጀመሪያ፦ ክርስቶስ ከሞት የተነሣው በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው፣ ሰንበት ገና የሣምንቱ ቅዱስ ቀን ከሆነ ወይም የእግዚአብሄር ሕዝብ ለአምልኮ የሚሰበሰብበት ቀን ከሆነ ክርስቶስ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ወይም እሁድ ለምን ተነሣ? በርግጥ ምክንያቱ ቅዱስ ቀን እንደሆነ ሊከራከር ይችላል፣ ግን ምን ያህል ቅዱስ ሊሆን ቻለ፡፡ ሰንበት ገና ሳይቆይ ወይም ቅዱስ ከሆነ በዚህ ቀን ክርስቶስ ከመቃብር ቢወጣ ኖሮ የአምልኮ ቀን አይሆንምን ? በእውነት ክርስቶስ በዚህ ቀን የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን አፅናኦት ለመስጠት በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከመቃር ተነሣ፡፡፣ ወደ ማቴዎስ 28፡1 ስንመጣ "በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ" ይላል፣ ከዚያም ጌታ በዚህ ቀን ከመቃብር መነሣቱን በማርቆስ 16፡1፣2 እና በተመሳሳይ በሉቃስ 24፡1 ፣ 2፣ እና በመጨረሻ አሁንም በዮሐንስ 20፡1 እናያለን

ሁለተኛው ፦ ክርስቶስ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከመቃብር ከተነሣ ቦኋላ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በሁለት አጋጣሚዎች መገናኘት ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፣ ሁለቱም በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን መሆናቸውን እናነባለን "ከስምንት ቀን ቦኋላም ደቀመዛሙርቱ ደግመው በውስጥ

ነበሩ፣ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፣ በመካከላቸውም ቆሞ፣ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፣ ከዚያም በኋላ ቶማስን ጣትህን ወዲዚህ አምጣና እጆቼን እይ፣ እጅህምንም አምጣና በጎኔ አግባው፣ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው፣ ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት፣ ኢየሱስም ፣ ስለአየኸኝ አምነሃል፣ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው አለው" (ዮሐንስ 20፡26~29) ኢየሱስም ከሣምንቱ በመጀመሪያው ቀን ከመቃብር ወጥቶ በዚያች ምሽት ለደቀመዛሙርቱ ታይቶ ከስምንት ቀን በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ቢገለጥ ኖሮ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከእነርሱ ጋር ተገናኘ ማለት አይደለምን? ቅዱሳት መፅሐፍት እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተፈፀሙት በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደሆነ አፅናኦት መስጠቱ እንግዳ አይመስልም፣ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ምንም ትርጉም ባይኖረው ነው? ነገር ግን ኢየሱስ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከመቃብር መውጣቱ እና በሌሎች ሁለት አጋጣሚዎች ከደቀመዛሙርቱ ጋር መገናኘቱ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ትልቅ ትርጉም እንዳለው እንድናውቅ እመክራችኋለሁ።

ሶስተኛ ፦ጴንጤቆስጤ ሁልጊዜ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከፋሲካ በኋላ በሃምሳኛው ቀናት ውስጥ ትመጣለች ፣ ይህ ማለት በሐዋሪያት ሥራ 2 መሠረት ጌታ መንፈስ ቅዱስን በሐአዋሪያት ላይ ለመላክ ይህን ቀን የመረጠው ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌል እንዲሰበክ ነው፣ ለወንዶቹም ለሴቶቹም ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመንገር በዚያም ቀን ቤተክርስቲያን እንድትመሠረት ነው። አሁን ይህ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ላይ ልዩ ትኩረት ካልተሰጠ ምን ሊሆን ይችላል? ይህ ቀን ከሌሎቹ የሣምንቱ ቀናት በላይ መመረጡ ልዩ ምክንያት ሊኖርበት ይገባል ማለት ነው። ለምሣሌ የሰንበት ቀን አሁንም ፀንቶ ከነበረ ለምን ጌታ ያንን ቀን ሊጠቀምበት አልመረጠም? በሚቀጥለው ቀን ለምን አልሆነም? የሰንበት ቀን በክርስቶስ ሕኛ በክርስትና ጊዜ የአምልኮ ቀን ተብሎ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ይተካ ነበር

አራተኛ ፦ የጥንት ክርስቲያኖች በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን ለማምለክ ሲሰበሰቡ የሚያሳይ ምሣሌ አለን፣ እናነባለን "ከሣምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፣ እስከመንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ" (የሐዋሪያት ሥራ 20፡7) አውዱን ስንመለከት ጳውሎስና ሌሎች በመርከብ ከፍሊጵስዩስ ወደ ጢሮአዳ እንደደረሱ እና በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን በቤተክርስቲያን ጋር ይገናኙ ዘንድ ከሰባት ቀናት በላይ እንደቆዩ ተነግሮናል፡፡ የሰንበት ቀን ወይም ሌላ ቀን ከአከባቢው ክርስቲያኖች ጋር ለአምልኮ መሰብሰብ እና ጉዟቸውን መቀጠል ይችሉ እንደነበር በእርግጥኝነት ማየት ይችሉ

ነበር። ታዲያ በዚያ ቀን ምን ሆነ ? በመጀመሪያ ደረጃ ደቀመዛሙርቱ በዚህ ቀን ተሰበሰቡ እና ለምን ተሰበሰቡ? ዘገባው እንደሚናገር እንጀራ ለመቁረስ አንድ ላይ እንደተሰበሰቡ ይናገራል ይህ ደግሞ የክርስቶስን ሥጋና ደም ለማሰብ ለመካፈል የጌታን እራት ለመውሰድ መሰብሰባቸውን የሚያመለክት ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23~29)፣ ይህም ማለት በመፈሳዊ ምሣሌ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ክርስቲያኖች እንጀራ የሚቆርሱበት ቀን እንደሆነ ተምረናል። የሳምንቱ የመጀመሪያ ዬትኛው ቀን ነው? በርግጥ በየሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን፣ በብሉይ ኪዳን የሰንበት ቀን የአምልኮ ቀን በነበረበት ጊዜ እግዚአብሄር ሁሉንም ወይም እያንዳንዱን የሰንበት ቀን እንዲያስታውሱ አላለም፣ የጌታ እራት መካፈልን በተመለከተ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀንም ተመሣሣይ ነው። በዚያ ስብሰባ ላይ የተወሰነ ስብከት ነበራቸው ዘጋባው ጳውሎስ እንደሰበከና እስከ እኩሌ ሌሊት ድረስ ንግግሩን እንደቀጠለ ይናገራል። ምንም እንኳን ፀሎቶች ነበራቸው ወይም በመዘመር ላይ ተሰማርተው እንደነበር ባይናገርም በትክክል እንዳደረጉት ጥርጥር የለውም፣ ነገር ግን ጳውሎስና በዚያ ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች እንጀራ ለመቁረስና እግዚአብሄርን ለማምለክ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከተሰበሰቡ እኛም ክርስቲያኖች ከሆንን ዛሬም እንዲሁ እናድረጋለን ማለት ነው።

አምስተኛው፦ ሐዋሪያው ጳውሎስ በዘመኑ ያሉትን ክርስቲያኖችን ከሚያገኙት ገንዘብ ለእግዚአብሄር ቤት በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንዲሰጡ አስተምሯቸዋል፣ እንዲህ ይላል “ ለቅዱሣንም ገንዘብን ስለማዋጣት ለገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደነገግሁት እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ። እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን ከእናንተ እያንዳንዱ በየሣምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ” (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1፣2)። ጳውሎስ በገላቲያ ላሉ አቢያተ ክርስቲያናትም ሆነ በዚያ በቆሮንቶስ ላለች ቤተክርስቲያን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንዲሰጡ ወይም እንዲያስቀምጡ እንዳዘዛቸው አስተውል። በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ስለ መስጠት አመለካከት ምን ያህል መሰጠት እንዳለበት፣ የመስጠት ዓላማ እና የመሰሳሉትን በተመለከተ ብዙ ማለት ይቻል ነበር፣ ከሌላ ቀን ለምን ተደረገ ? ይህ ቀን ክርስቲያኖች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት መንፈሳዊ ቀን ስለሆነ እና አብረው በሚሆኑበት ጊዜ ይህ ቀን የአቅማቸውን ለመለገስ ጥሩ ነው።

ለማጠቃለል ያህል የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደሰንበት የዕረፍት ቀን አይደለም፣ እና በእርግጥ ሰንበት አይደለም፣ ግን በጌታ ትንሣኤ የተከበረ ቀን ነው፣ እና ለመንፈስ ቅዱስ መምጣት የተመረጠች ቀን፣ በእውነት ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሰበክ እና ቤተክርስቲያን እንዲትመሰረት የሆነች ቀን ናት፣ ይህም ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ እንዲሰበሰቡ

ጌታ የመረጠበት ቀን ነው፣ በአዲስ ኪዳን የተገለፀው ምሣሌ በመከተል በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን ለማምለክ ዓላም ሳንዘነጋ መሰብሰብ ነው ስህተት የሚሆንብን ይህን ቀን ቸላ ስንል እና ስንዘነጋ ነው፣ የዕብራዊው ፀሐፊ መሰብሰባቸንን እንኳ ቸል እንዳንል ይመክረናል (ዕብራዊያን 10፡25) እኛ ክርስቲያኖቸ የሆንን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የመገናኘት የመሰብሰብ መብት አግኘተን ጌታቸንን ለዚያ ባዘጋጀው ቀን እርሱን በማምለክ ማመስገን እንዴት ያለ ታላቅ ደስታ ነው፣ እንዴት ያለ አስደናቂ ነገር ነው።

ክርስቲያን ነህ? ከክርስቲያኖቸ ጋር በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን ለማምለክ ጸበሰባለህ? ካልሆንክ ካላደርግክ የእግዚአብሄርን ቃል እንድታጠና እና በክርስቶስ አምነህ ከኃጥያትህ ንሠሃ ገብተህ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መስክረህ ለኃጥያትህ ስርየት ኃጥያትህ እንዲታጠብልህ እንድትጠመቅ እንፀልይልሃለን፣ ይህንን ካደረግክ ጌታ አድኖህ ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምርሃል።የሐአውሪያት ሥራ 2 አንብብ፣ በዚያ ጊዜ የነበሩት ይህንን ማድረጋቸውን ተመልከት፣ አንተም እንድታደርግ እንፀልይልሃለን።

## ትምህርት 28

## የጌታን እራት የምንካፈለው ለምንድነው?

ዘገባው ሲናገር እንዲህ ይላል “ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና እንካቸሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፣ ፅዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው፣ እንዲህም አለ `ሁላቸሁ ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎቸ ለኃጥያት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፣ ነገር ግን እላቸዋለሁ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከውይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣውም፣ “ አለ (ማቴዎስ 26፡26~29)

በማርቆስ ወንጌል ደግሞ እንዲህ ተዘግቧል “ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንስቶ ባረከ ቆርሶም ሰጣቸውና ፦ እንካቸሁ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፣ ፅዋውንም አንሥቶ አመስኞም ሰጣቸው ሁሉም ከእርሱ ጠጡ። እርሱም ይህ ስለብዙዎቸ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው። እውነት እላቸዋለሁ፦ በእግዚአብሄር መንግሥት ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ደግሞ አልጠጣውም አላቸው መዝሙርም ከዘመሩ በኃላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ፣” (ማርቆስ 14፡22~26)

መጨረሻ ላይ ሉቃስ እንደዚህ ዘግቧል “ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ጋር በማዕድ ተቀመጠ፣ እርሱም ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር እላቸዋለሁና በእግዚአብሄር መንግሥት እስኪፈፀም ድረስ ወደ ፊት ከዚህ አልበላም አላቸው፣ ፅዋንም ተቀበለ አመስግኖም ይህን እንካቸሁ በመካከላቸሁም

ተካፈሉት እላቸዋለሁ የእግዚብሄር መንግሥት እስኪትመጣ ድረስ ከአሁን ጀምሮ ከወይኑ ፍሬ አልጠጣም አለ፣ እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው” አለ (ሉቃስ 22፡14~19) እርግጥ ነው እኛ ስለነዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተናገረው እንጀራ፣ በዚህ እራት ስንካፈል እንኳ፣ የክርስቶስ ሥጋዊ አካል እንዳልሆነ እናውቃለን። ፅዋው ፣ የወይኑ ፍሬ ወይም የወይኑ ጭማቂ የክርስቶስ እውነተኛ ደም አይደለም። ያፋሲካ በዓል ያልቦካቂጣእናየወይኑፍሬምተመሣይመሆኑወይምእንጀራውያልቦካ ኅብስት የክርስቶስ ሥጋን ለመወከል የወይን ጭማቂውም የክርስቶስ ደም ለመወከል መሆኑን ለመጠቆም ነው። ክርስቶስና ሐዋሪያቱ ፋሲካን በልተዋልና እንጀራውንና ፅዋውንም ሰርተው የእራሱን እራት አዘጋጅተዋልና እስከ ዛሬ ድረስ የጌታን እራት ስንበላ ያልቦካ ቂጣና የወይኑ ፍሬ ወይም የወይን ጭማቂ እንጠቀማለን፣ ጭማቂ የጌታን ደም ለማስታወስ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በእግዚአብሄር መንግሥት ከእነርሱ ጋር አዲስ እስካደርገው ድረስ ዳግመኛ ይህን እራት አልበላም ብሎ ነገራቸው። ይህም ማለት ክርስቶስ በቅርቡ ተላልፎ ይሰጣል ይሰቀላል እና ደሙን በመስቀል ላይ ስለዓለም ኃጥያት ያፈሳል ማለት ነው። ከሞት ከተነሣ በኃላ ለደቀመዛሙርቱ እና ለሌሎቸም ጥቂት ሰዎቸ ለጥቂት ቀናት ታየ፣ ከዚያም ወደ ሰማይ ወደ አብ ይመለሣል፣ የእግዚአብሄር መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም ይመሰረታል፣ እና ከዚያ በመላው ዓለም ይስፋፋል፣ ከተመሰረተ በኃላ ስናነብ ፦ “በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር” ይላል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42) እዚህ የቅጣው መቁረስ የጌታ እራትን ይመለከታል ። ነገር ግን ክርስቶስ ከጌታ እራት ሲበሉ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በመንግሥቱ ወይም በቤተክርስቲያን መምጣት ቃል ገብቶ ነበር። በእርግጥ እርሱ ከእነርሱ ጋር ይሆናል ማለቱ በአካል አይደለም ነገር ግን ከእነርሱ ጋር ነበር እና ዛሬም በመንፈስ ከሕዝቡ ሁሉ ጋር ነው። ኢየሱስ ሲናገር “በስሜ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በተሰበሰቡበት እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ” ብሏል (ማቴዎስ 18፡20)፣ እንደገና እስከዓለም ፍዛሜ ድረስ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ተስፋ ሰጥቷል፣ (ማቴዎስ 28፡20) ስለዚህ ቤተክርስቲያን እንደ እግዚአብሄር ሕዝብ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የጌታ እራትን እንወስዳለን ሁሌም ጌታ በመካከላቸን ነውና።

አሁን ከኔ ጋር ወደ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23~29፣ እንሂድ እናም ሐዋሪያው ጳውሎስ የፃፈውን እናንብብ “ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትንእኔከጌታተቀብያለሁና፣ጌታኢየሱስአልፎበተሰጠባትሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፣ ቆርሶም፦ እንካቸሁ ብሎ፣ ይህ ስለእናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፣ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፣ እንዲሁም

ከእራት በኃላ ፅዋውን ደግሞ አንሥቶ ይህ ፅዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፣ በጠጣቸሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፣ ይህን እንጀራ በበላቸሁ ጊዜ ሁሉ ይህን ፅዋ በጠጣቸሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስከመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላቸሁ፣ ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታ ፅዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፣ ሰው ግን ራሱን ይፈትን፣ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከፅዋውም ይጠጣ፣ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና” (

ከላይ በተመለከትነው ልዩ ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ ጳውሎስ የጌታ እራትን በተመለከተ ከጌታ የተቀበለውን መረጃ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዳደረሳቸው ተነግሯል። ሁለተኛ ፦ የክርስቶስን ሥጋና የፅዋውን የክርስቶስን ደም ለማሰብ ኅብስቱን መብላት አለባቸው ሲል የፈሰሰውን ደም የአዲስ ኪዳን ወይም የክርስቶስን ሕግ ለማፅደቅ ነው። ሦስተኛ፦ ይህን እራት በበሉ ቁጥር ይህ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን የሚናገሩበት መንገድ ነው ተብሏል። ግን ምን ያህል ጊዜ ነው የሚወስዱት ? በሐዋሪያት ሥራ 20፡7 ጳውሎስ በጢሮአዳ ከክርስቲያኖች ጋር እንጀራ ለመቁረስ የተሰበሰበበትን ምሣሌ አለን። የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ስንት ጊዜ ይመጣል? በሣምንት አንድ ጊዜ ነው፣ እናም ክርስቲያኖች የጌታን እራት ለመክካፈል ይሰበሰቡ ነበር በዛሬው ጊዜ ያለን ክርስቲያኖችም በተመሣሣይ ሁኔታ ነው፣ እኛ ሐሙስ ቀን ወይም በየሦስት ወር ወይም በዓመት አንድ ጊዜ የመገናኘት ስልጣን የለንም፣ ይልቁንስ የመጀመሪያው ክፍለዘመን ክርስቲያን የጌታን እራት ለመካፈል በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ይሰበሰቡ እንደነበር ተናግሯል፣ ክርስቶስን የማስታወስ ዓላም የእነርሱን አርአያነት መከተል ከፈለግን እንዲሁ ማድረግ አለብን።

በመቀጠል እና አራተኛው የጌታን እራት በመካፈል ለመዳን እና የዘላለም ህይወት ተስፋ እንዲኖረን ክርስቶስ የከፈለውን መስዋዕትነት ለማስታወስ ወደ መስቀል መለስ ብለን እንመለከታለን። እንጀራ ስንቆርስ በክርስቶስ እናምናለን እንላለን፣ ስለዚህ እንዴገና የሚመጣበትን እናስባለን።

አምስተኛ ይህንን እራት ያለአግባብ መካፈላችንን ማለትም ለጌታ ታማኝ አለመሆናችንና ለምናደርገው ነገር ቅን ባለመሆናችን የክርስቶስን ደም በመበደል ጥፋተኞች መሆናችንን ማስታወስ አለብን፣ የጌታን እራት በማይገባው መንገድ መካፈል ማለት በራሳችን ላይ እርግማን እየበላን እና እየጠጣን ነው ማለት ነው። አሁን ያ ማለት ከመካፈላችን በፊት ፊፁም መሆን አለብን ማለት አይደለም ፣ ነገር ግን የጌታ እራት ለእኛ እና ለጌታ ምንም ማለት ከሆነ ለጌታ ታማኝ መሆን አለብን ማለት ነው።

እና በመጨረሻ እና ስድስተኛው የጌታ እራት ከመብላታችን በፊት ራሳችንን እንድንመረምር እናበረታታለን፣ ስለዚህም ልባችንን እና ህይወታችን በእግዚአብሄር ፊት ትክክል መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የምንችለውን ያህል እየሠራን መሆናችንን ስናውቅ ብቻ ነው መካፈል ያለብን፣ በልባችን ውስጥ ጌታ ከእኛ የሚፈልገውን መሰረት በማድረግ ለእርሱ ታማኝ መሆናችንን መናገር ከቻልን፣ ከሣምንት እስከሣምንት እንጀራ ለመቁረስ ከመቀጠላችን በፊት ከኃጥያታችን ንሠሀ በመግባት ጌታ ይቅር እንዲለን ልንጠይቀው ይገባል

ወዳጆቼ ፦ የጌታ እራት ለክርስትያን፣ የጌታ ቤተክርስቲያን አባል ለሆነው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም ክርስቶስን ለማስታወስ እና ለእርሱ ታማኝ ለመሆን ነው፡፡ ለዕይታ እንዲሙብል ወይም ዓላማውን ሳይረዱ መካፈል አይደለም፡፡ ክርስቲያንን ለማጠናከር እና በተመሳሳይ ጊዜ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለመጠቆም በጌታ እራት በኩል ዕድል ለመስጠት ነው፡፡

ክርስቲያን ነህ? የጌታ እራት ላንተ ምን ማለት ነው? በየሣምንቱ የመጀመሪያው ቀን ከጌታ ሕዝብ ጋር እንጀራ ትቆርሳለህ ? ክርስቲያን ካልሆንክ እንድትሆን ልናበረታታህ እንወዳለን ። ያንን ለማድረግ በክርስቶስ ማመን ለኃጥያትህ ንሠሀ መግባት በክርስቶስ ላይ ያለህን እምነት በመመስከር እና በውኃ ውስጥ ለኃጥያትህ ሥርየት በመቀበር በመጠመቅ (ማርቆስ 16፡16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፡፡ እንደ ክርስቲያን እናየጌታ ቤተሰብ አባል በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የጌታን እራት መብላት ትችላለህ፣ ክርስትያናዊ ህይወት ሲኖርህ በዚህ በክርስቶስ ያለህን እምነት ለማረጋገጥ ክርስቶስን እምነትህን ለዓለም ማወጅ ትጀምራለህ

## ትምህርት 29

## በአምልኮ ጊዜ ለምን በድምፃችን ብቻ እንዘምራለን

እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በአምልኮ ጊዜ ስንዘምር ከሌሎች የሐይማኖት ድርጅት አዘማመር ልዩ ነን፣ ልዩ የሆነው እንደሌሎቹ በሙዚቃ መሣሪያ አለመዘመራችን ሲሆን ይህንንም ልዩ ለመሆን ፈልገን ሳይሆን እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ቃል በመታዘዝ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች በሚዘምሩት መሰረት ስለሆነ ነው፡፡

ሁለት ዓይነት ሙዚቃዎች አሉ፡፡ አንዱ ቮካል (የሰው ድምፅ ) ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሜካኒካል የሰው ድምፅ ከሰው ብቻ የሚመጣ ውጤት ነው፣ ይህ ሰዎች በአንድ ላይ በራሳቸው ድምፅ ብቻ ሲዘምሩ ነው፣ ይህ በዓለም ላይ በጣም ቆንጆ ሙዚቃ ነው፣ ይህ ዓይነቱ ሙዚቃ የመጣው ከእግዚአብሄር ፍጥረት ነው፣ ከነፍስ የተገኘ ነው፣ ለእግዚአብሄር ወይም ለፈጣሪያችን ምስጋና የሚቀርብበት ነው፣ በመንፈስ በእውነት እና በህይወት የተሞላ ነው፡፡ ሜካኒካል ሙዚቃ የሚመጣው በሰው ከተሠሩ

መሣሪያው፡ ነው። እነዚያ መሣሪያዎች ህይወት አልባ ናቸው። ነፍስም መንፈስም የላቸውም። ድምፅ የሚያሰሙት ብቸኛው ምክንያት ሰው ስለሚደበድባቸው፣ ስለሚመታቸው ወይም ስለሚጫወትባቸው ነው። አሁን ጥያቄው ይህ ነው፣ እግዚአብሄር ይህን ይፈልጋል ወይም ይህ መሣሪያ እግዚአብሄርን ያወድሰዋል ወይ ? የሚለው ነው። በእውነት ለእግዚአብሄር ትርጉም የሚሰጠው ዬትኛው ነው? የዕብራዊያን ፀሐፊ እንዲህ ይላል "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሄር የምስጋናን መሥዋዕት፣ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት" ይላል (ዕብራዊያን 13፡15) እባክህን በከንፈራችን ፍሬ እግዚአብሄርን እናመስግን እንዳለ አስተውል። የከንፈራችን ፍሬ ምን ይሆን? ንግግራችን ቃላችን፣ ዝማሬያችን ፣ ፀሎታችን፣ የምስጋና ቃላችን ይሆናል። ይህ ምስጋና ወደ ዬት የሚደርስ ነው? በእርግጥ ወደ እግዚአብሄር የሚደርስ ነው።

በከንፈራችን ፍሬ እግዚአብሄርን ማመስገን በሚለው ሀሳብ በመቀጠል ጳውሎስ ሲናገር "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በእርሳችሁ ተነጋገሩ፣ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፣ ሁልጊዜ ስለሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለሁሉ አመስግኑ" ይላል (ኤፌሶን 5፡19፣20) እባክህን እርስ በእርስ ስለመነጋገር ወይም ስለመዘመር ሲናገር የራስን ድምፅ ማለቱን አስተውል። በተጨማሪም መንፈሳዊና ዝማሬውን በዜማው በልብ እንጂ በሜካኒካል መሣሪያ መሆን እንደሌለበት ነው የሚገልፀው፣ አሁን ክርስቲያኖች ብቻ ቢዘምሩ እግዚአብሄርን ማምለክ ይችላሉ? ምናልባት አዎን ትል ይሆናል፣ ግን በሙዚቃ መሣሪያ መዘመርስ? ቅዱስ መፅሐፍት ይህን አያስተምሩም፣ ያስተምራሉ የሚል ካለ ዬቱ ጋ ያስተምራሉ? ታዲያ በሙዚቃ መዘመርን ቃሉ ካላስተማረ እኛ ብንጨምር የጌታን ፈቃድ እያደርግን ነው?

እንደገና ጳውሎስ እንዲህ ይላል "የእግዚአብሄር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥፁ፣ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሄር ዘምሩ" ይላል (ቆላስያስ 3፡16) አሁን ጳውሎስ እዚህ ጋ ምን እያለ ነው? የክርስቶስን ቃል አፅናኦት በመስጠት በመንፈሳዊ እና ቅዱስ ፅሑፋዊ መዝሙሮች እያስተማረ እና እየገሰፀ እና ጌታን በመዘመር እንዲያመሰግኑት እያደረገ ነው። እውነት ከሆነ በጳውሎስ መግለጫ ውስጥ ሜካኒካል ሙዚቃን መጠቀምን የሚጨምር ነገር ታያለህ? ካልሆነ በአምልኮ ውስጥ እግዚአብሄርን ለማወደስ ሜካኒካል ሙዚቃን ብትጨምር በእግዚአብሄር ቃል ላይ መጨመር አይሆንም?

ነገር ግን በእሱ ላይ ምንም ስህተት እንዳልተመለከትክ ልትከራከር ትችላለህ፣ ከዚያ ሌላ ሰው በሌላ ነገር ላይ ምንም ስህተት አይመለከትም

ይሆናል፣ እና በእሱ ላይ ሊቀጥል ይችላል፣ ዋናው ነገር እኛ በእግዚአብሄር ቃል ትምህርት መገዛት አለብን  በቃሉ ላይ ካላደርግን ታዲያ ምን ያስቸግረናል?

ስለምትወደው ነገር ክርክር ይዘህ ትመላለሣለህ ወይስ መሣሪያውን የመጫወት ችሎታ ስለአላቸው ሰዎች ጉዳይ የማምልኪያ ስጦታቸው ትላለህ? ብዙ ለጌታ ክብር የማይሆኑ ችሎታዎች አሉ፣ ታዲያ ችሎታ ስላላቸው ብቻ ይህን እግዚአብሄርን ልናመሰግንበት ይገባል ማለት እንችላለን?  እነዚህ በቀዳምቷ ክርስቲያኖች ዘንድ የልተለመደውን ነገር ለእግዚአብሄር ክብር ብለን ለአምልኮ ማበረታታት አለብን ?፣ እስቲ እየተነሣ ያሉትን ጥያቄዎች በደንብ እንድታሰላስለው እፈልጋለሁ፡፡

አሁንም በቤት ውስጥ ሜካኒካል ሙዚቃን ማግኘት ከቻልክ ይህን ለአምልኮ መጠቀም እንደምትችል ተከራክረህ ይሆናል ዳሩ ግን እውነታው ግን የምንወደውን ወይም በቤታችን የምንጠቀመውን ወደ አምልኮ ልንወስድ አንችልም ፣ ለምሣሌ እኔ እና ቤተሰቤ ሙዚቃን እንወዳለን፣ እኛ ብዙውን ጊዜ ሙዚቃን በራዲዮ  እንሰማለን በካሴት መቅረጫላይእንጫወታለን፣ግንወደአምልኮሲመጣእጋንየሚያስደስቱ ነገሮችን መጠቀማችንን እናቆማለን እና ጌታን ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ እንጀምራለን፣ እቤት ውስጥ አይስክሬም እና ሻይ እንጠጣለን ነገር ግን  በአምልኮ ውስጥ እነዚህን ነገሮች ለማድረግ መሞከር ከቦታ ውጪ እንደሚሆን እንገነዘባለን፡፡

በአምልኮ ውስጥጥ ለሜካኒካል ሙዚቃ ከሚቀርቡት ዋና ዋና ክርክሮችአንዱዳዊትናሌሎቹበብሉይኪዳንይጠቀሙትያስተምሩትም ነበር የሚለው ነው፣ ይህ ሆነም አልሆነም ብሉይ ኪዳን እንደሕግ አስገዳጅነት የለውም፡፡ ክርስቶስ  በመስቀል ላይ ከመንገድ  ለማስወገድ እና አዲስ ሕግን ለመስጠት በመስቀል በመስቀል ላይ መሞቱን እናነባለን "ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፣ ፀጋና እውነት ኻ በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ" (ዮሐንስ 1፡17)፣ ክርስቶስ ሕጉ ሁሉ እስኪፈፀም ድረስ አያልፍም ብሏል፡፡ "እኔ ሕግን እና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፣ ልፈፅም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም፣ እውነት እውነት እላችዋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም" አለ (ማቴዎስ 5፡17~18) ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ አሮጌውን ሕግ ለማጥፋት ፈፀመው (ቆላስያስ 2፡14) ጉዳዩ ይህ ከሆነ ዛሬ በአምልኮ ውስጥ ሜካኒካል ሙዚቃን ለማፅደቅ መዝሙረ ዳዊትን ወይም ሌላ የብሉይ ኪዳንን ክፍል መጠቀም አንችልም፡፡ በእነዚያ ጊዜያት እኛ  አሁን ባለንበት ዘመን የማንሠራቸው እና የማንችላቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ፡፡

የሜካኒካል ሙዚቃን በአምልኮ ውስጥ መጠቀምን ለማስረዳት በሚደረገው ጥረት የሚቀርበው ሌላው ዋና  ሙግት በሰማይ ውስጥ

ሙዚቃ ይኖራል የሚል ነው፡፡ በሰማይ ሙዚቃ ካለ እኛ እዚህ ምድር ላይ ሙዚቃን ማምለክ መቻል አለብን ብለው ይደመድማሉ ፡፡ በርግጥ ስለ ሜካኒካል የሚያወሩት በራዕይ ውስጥ ወይም በሌላ ውስጥ ሰው ሰራሽ ሙዚቃን በተመለከተ የተፃፈ ዬት ጋ አንብበውት ነው? ነገር ግን በገነት ውስጥ ሜካኒካል ሙዚቃ ቢኖር እንኳን ይህ ማለት ጌታ እኛም እንዲኖረን ፈቅዷል ማለት አይደለም፣ እንደ እውነቱ ከሆነ እዚህ ምድር ላይ የማናገኛቸው ብዙ ነገሮች በሰማይ ይኖራሉ፣ እግዚአብሄር ዛሬ የሚፈልገው በተለይ በአምልኮ እና በመጨረሻ በሰማይ ሊገለጥ የሚችለው ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡

የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራንና ታላላቅ የኃይማኖት መሪዎች በመጀመሪያ መቶ ክፍለዘመኖች የነበሩት ክርስቲያኖች በአምልኳቸው ውስጥ ሜካኒካል ሙዚቃን ይጠቀሙ እንደነበር ከቅዱሳት መፃሕፍትም ሆነ ከሌሎች የመረጃ ምንጮች ምንም ዓይነት ፍንጭ እንደሌለ አምነዋል፡፡ በጊዜው ያሉ ሰዎችም ሆነ እስከዘመናችን ድረስ ሜካኒካል ሙዚቃን ለእግዚአብሄር አምልኮ አልተጠቀሙም፡፡ ለምሣሌ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በስተመጨረሻ ተከፋፈለች እና ለዚህ ክፍፍል ካመጡት ነገሮች አንዱ ሜካኒካል ሙዚቃ እግዚአብሄርን ለማመስገን ከዘፈናቸው ጋር አብሮ መሆን አለበት ወይ የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ የተሰማው ቡድን መካተት አለበት ተብሎ የሚጠራው የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በመባል ይታወቅ ነበር፣ እና እስከዛሬ ድረስ ይጠቀማሉ፣ ሌላው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የግሪክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በመባል መጠራት ጀመሩ፣ ቦኃላ በተሃድሶ እና በፕሮተስታንታዊ እንቅስቃሴዎች እንደነ ማርቲን ሉተር እና ጆን ዊስሊ ያሉ ሰዎች በቅዱስ ቃሉ ውስጥ በተገለፀው የእግዚአብሄር መለኮታዊ እቅድ ላይ ተጨማሪዎች መጠቀማቸውን ተቃውሞአቸውን በግልፅ አወጁ፡፡

ወደ ቅዱሳት መፅሐፍት ስንመለስ ብዙ ልናነባቸው የሚገቡን ጥቅሶች አሉን ስለጌታ እና ሐዋሪያት እናነባለን እንዲህ ይላል "መዝሙርም ከዘመሩ ቦኃላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ " ይላል (ማቴዎስ 26፡30) ጳውሎስና ሲላስ ከተገረፉ ቦኃላ ወደ ውስጠኛው ወይኒ ከገቡም ቦኃላ እግራቸው በኻድ ታስሮ ነበር ይህ ሁሉ የሆነው ለጌታ ባደረጉት ሥራ ነው፣ እንዲህ ይላል "በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየፀለዩ እግዚአብሄርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፣ እስረኞቹም ያደምጧቸው ነበር" ይላል (የሐዋሪያት ሥራ 16፡26)፣ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሎ ፅፎ ነበር "በልሣን ብፀልይ መንፈሴ ይፀልያል፣ አዕምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው፣ እንግዲህ ምንድነው ? በመንፈስ እፀልያለሁ በአዕምሮም ደግሞ እፀልያለሁ በመንፈስ እዘምራለሁ፣ በአዕምሮም እዘምራለሁ" ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡

14~15)። ያዕቆብም ሲናገር እንዲህ ይላል “ ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እሱ ይፀልይ፣ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር” ይላል (ያዕቆብ 5፡13) በዮሐንስ ራዕይ መፅሐፍ ስለመዝሙር የተፃፉ አሉ ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ፅፏል “መፅሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሀል፣ ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሄር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገኑም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት የሆኑ ዘንድ አድረግካቸው፣ በምድርም ላይ ይነግሳሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ” ይላል (ዮሐንስ ራዕይ 5፡9)፣ “ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፣ የአህዛብ ንጉሥ ሆይ መንገድህ ፅድቅና እውነተኛ ነው፣ ጌታ ሆይ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና የፅድቅም ሥራህ ስለተገለጠ አህዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሄርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ” (ዮሐንስ ራዕይ 15፡3)፣ “እንደብዙ ውኃም ድምፅና እንደታላቅ ነጎድጓድ ድምፅ የለ ከሠማይ ድምፅን ሰማሁ”(ዮሐንስ ራዕይ 14፡2)፣ ነገር ግን የብዙ ውኖችን ድምፅ እና ታላቅ ነጎድጓድ ድምፅ እንደ ሰማና ስለአራት አራዊት ሲናገር “ በዙፋኑም ፊት በአራቱም እንስሶችና በሽማግሌዎች ፊት አዲስ ቅኔ ዘመሩ፣” ይላል (ዮሐንስ ራዕይ 14፡2፣3) እና እዚህ በራዕይ መፅሐፍ ውስጥ ፣ ዮሐንስ በሰማይ ያየውንና የሰማውን ለሰው ለማስተላለፍ ብዙ ምሣሌያዊ ቋንቋዎችን ተጠቅሟል። ስለዚህም እንደ ብዙ ውኃ የሚመስል ድምፅ፣ ነጎድጓድም የሚመስል ፣ በበገናም የተሳለ ድምፅ ሰማ፣ ነገር ግን ቀጥተኛ ምድራዊ፣ መካኒካል ዕቃዎች በሰማይ አሉ ማለቱ አይደለም።

እናም በመዝሙር ጉዳይ በመካኒካል የሙዚቃ መሣሪያ ታጅቦ አምልኮ እንዲቀርብ ለማድረግ ሥልጣን የማነው? መፅሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንናገራለን ዝም ሲል ደግሞ ዝም እንላለን ወይስ እሱ ዝም ካለ እኛ እንቀጥላለን? እግዚአብሄር የተናገረውን ምንም ይሁን ምን ማድረግ እንፈልጋለን፣ መፅሐፍ ቅዱስ ሲናገር ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ተሰጠው ይላል ስለዚህ እኛ እሱን እና ቃሉን እናከብራለን እና ከተናገረው በላይ መሄድ የለብንም ፣ ስለዚህ ሙዚቃችንን በአምልኮ ውስጥ በድምፅ ዜማ ወይም በመዘመር ብቻ መወሰን አለብን፣ ከዚያ እና ከዚያ ቦኃላ ብቻ እግዚአብሄር እንደሚደሰት እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

እግዚአብሄርን እንዴት ታመልካለህ ? አስፈላጊ መሆኑን ታውቃለሕ ክርስቲያን ነህ? ካልሆንክ አንድ እንድትሆን እንፈልጋለን፣ ክርስቶስ “ያመነ የተጠመቀም ይድናል” (ማርቆስ 16፡16) ብሏል። ከዚያም እኛ ጌታ የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያን እንደሚጨምር እናነባለን (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47) እንደዳነ ሰው እንደክርስቲያን እና ከዚያ ቦኃላ የጌታ

ቤተክርስቲያን አባል እንደመሆንህ  በእውነት እና በመንፈስ ማምለክ ትችላለህ ።

## ትምህርት 30
## በጸሎት ለምን እናምናለን

ፀሎት የመፅሐፍ ቅዱስ ጭብጥ ነው፣ ትርጉሙም ለእግዚአብሄር መናገር ለእግዚአብሄር መንገር፣ እግዚአብሄርን መጠየቅ ወይም መለመን ማለት ነው።ሐዋሪያው ጳውሎስ ሲናገር “ጌታ ቅርብ ነው፣ በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሄር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ” ይላል (ፊልጵስዩስ 4፡6)

ከእግዚአብሄር ጋር ባለን ግንኙነት እርሱ አባታችን ነው እኛ ደግሞ እንደ ክርስቲያኖች ልጆቹ ነን፣ እግዚአብሄር ምንም አያስፈልገውም፣ እርሱ ዘላለማዊ ነው ፣ ሁሉን ቻይ ነው፣ እናም በረከቶች ሁሉ የሚመጡት ከእርሱ ነው፣ ያዕቆብ ሲናገር “በጎ ስጦታ ሁሉ ፊፁምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ “ ይላል (ያዕቆብ 1፡17) ልጆቹ ሆነን እግዚአብሄርን እንፈልጋለን  እርሱ አባታችን ነው እና እኛ ለፍላጎታችን ሁሉ፣ ፈተናን ለማሸነፍ እንዲረዳን  እና ኃጥያት በምንሠራበት ጊዜ ይቅርታን ለማግኘት ወደ እርሱ መሄድ አለብን።

እስቲ አሁን ስለፀሎት፣ ጌታን እንድንለምን እና እጋን እንዲሚሰማንና ፀሎታችንን እንደሚመልስ ማረጋገጫ የሚናገሩትን የቅዱሣት መፅሐፍት ጥቅሶችን እንመልከት ኢየሱስ ለሐዋሪያቶቹ ያለውን “እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና ፣ አብም ስለወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፣ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለኑ እኔ አደርገዋለሁ “ አላቸው (ዮሐንስ 14፡13~14) እንደገናም “በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል፣ ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀመዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል” አላቸው (ዮሐንስ 15፡7፣8) ከዚያም “እኔ መርጥኳችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም ፣ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬያችሁም ሊኖር ሾምኳችሁ” አለ። (ዮሐንስ 15፡16)

በተራራው ስብከት ላይም ኢየሱስ እንዲህ አለ “ለምኑ ይሰጣችሁማል፣ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፣ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል፣ የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፣ የሚፈልገውም ሁሉ ያገኛልና፣ መዝጊያንም ለሚያንኳካ ይከፈትለታል” ነው ያለው (ማቴዎስ 7፡7~8)፣

ሐዋሪያው ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ፅፏል “በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል፣ የምንለምነውንም

ሁሉ እንዲሰማን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን" (1ኛ ዮሐንስ 5፡14~15)

ከላይ ከተጠቀሱት ቅዱሳት መፅሐፍት ሁሉ ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ሳያስቀምጥ ጌታ እያንዳድንዱን ፀሎታችንን እንደሚመልስ መደምደም እንችላለን፣ ነገር ግን ቅዱሣት መፅሐፍት በጥልቀት ስንመረምር የተለየ ነገር መኖራቸውን እንገነዘባለን ፣ ተቀባይነት ያለውን ፀሎት ከመፀለይ ጋር የተያያዙ ብዙ ነገሮችን ነው ጌታ ሰምቶ የሚመልሳቸው።

በመጀመሪያ ቅዱሣት መፅሐፍት እንደሚያስተምሩት አንድ ሰው ፀሎቱ እንዲመለስለት ክርስቲያን /የእግዚአብሄር ልጅ/ መሆን አለበት፣ ይህንንም ዮሐንስ 9፡31 ላይ ስናይ እግዚአብሄር የኃጥያተኞችን ፀሎት እንደማይሰማ ነው። እግዚአብሄር ኃጥያተኛውን የማይሰማው ለምንድነው? መልሱ በኃጥያት ምክንያት ነው፣ ኃጥያት በእግዚአብሄርና ወደ እርሱ ለመፀለይ በሚሞክር ግለሰብ መካከል ይመጣል ወንጌል ይህንን በጥንት ዘመን ተናግሯል "እነሆ የእግዚአብሄር እጅ ከማዳን አላጠረችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፣ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተ እና በአምላካችሁ መካከል ለታለች፣ እንዳይሰማም ኃጥያታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል" ይላል (ኢሳያስ 59፡1~2) እንደገና ኃጥያተኛው የእግዚአብሄር ልጅ ሳይሆን እግዚአብሄርም አባቱ ሳይሆን እንዴት ወደ እግዚአብሄር ሊቀርብ ይችላል? አንድ ኃጥያተኛ ወደ እግዚአብሄር መፀለይ ከቻለ፣ እና እግዚአብሄር እግዚአብሄር እንዲሰማውና ፀሎቱን እንዲመልስለት የሚጠብቅ ከሆነ ፣ ክርስቲያን ለሆኑት ይልቅ ምን ጥቅም ይኖረዋል? አንዳንዶች የሚያስቡት በተቃራኒ ክርስቲያን አለመሆንና ክርስቲያን በመሆን ወደ እግዚአብሄር መፀለይ ሲመጣ እና ጌታ የአንድን ሰው ፀሎት እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ በመተማመን ላይ ትልቅ ልዩነት አለ።

ሁለተኛው ፦ የእግዚአብሄር ልጅ ፀሎቱ ከተሰማ ፃድቅና ጌታ ታማኝ ሆኖ መቆየት እንዳለበት የእግዚአብሄር ቃል ያስተምራል ጴጥሮስ በዘመኑ ላሉት ክርስቲያኖች ሲፅፍ እንዲህ ብሏል "የጌታ ዓይኖች ወደ ፃድቃኖች ናቸውና ጆሮዎቹም ለፀሎታቸው ተከፍተዋል፣ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡12) ክርስቲያን ኃጥያት ቢሠራ ወይም ከእግዚአብሄር ርቆ ከሆነ፣ ንሠሃ መግባት፣ ስህተቱን መናዘዝ እና ይቅር እንዲለው ወደ ጌታ መፀለይ አለበት፣ ያዕቆብ እንዲህ ይላል "እርስ በእርሳችሁ በኃጥያታችሁ ተናዘዙ፣ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይፀልይ፣ የፃድቅ ሰው ፀሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" (ያዕቆብ 5፡16) ጠንቋዩ ሲሞን ጌታን ታዞ የእግዚአብሄር ልጅ ከሆነ ቦኃላ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጅ ጭነው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ለሳማራዊያን ክርስቲያኖች ሲሰጡ ባየ ጊዜ

ዘገባው እንደሚናገር ያንን ፀጋ በገንዘብ ለመግዛት ጠየቀ፣ ከዚያ ምን እንደተከተለ እናንብብ “ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው ፦ የእግዚአብሄርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ካንተ ጋር ይጥፋ፡፡ ልብህ በእግዚአብሄር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፋንታ የለህም፣ እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንሰሀ ግባ ምናልባትም የልብህን ሀሳብ ይቅር ይልህ እንደሆነ ወደ እግዚአብሄር ለምን በመራራ መርዝና በዓመፅ እስራት እንዳለህ አይሃለሁና፡፡ ሲሞንም መልሶ፦ ካላቸሁት አንዳች እንዳይደርስብኝ እናንተው ወደ ጌታ ለምኑልኝ አላቸው” (የሐዋሪያት ሥራ 8፡20~24፡፡ ሲሞን ተፀፀቶ ይቅርታ ካልጠየቀ ወደ አምላክ መፀለይና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው ይችል ነበር ብለን ለአንድ ደቂቃ ያህል መገመት እንችላለን? በፍፁም አይደለም፡፡

ሶስተኛ ፦ ፀሎታቸው እንዲመለስ ሁሉም ደቀመዛሙርት ማድረግ እንዳለባቸው የሚጠቁሙ በሚመስሉ ጥቅሶች ላይ አንዳንድ ልመናን ለማቅረብ ብቻ መሆኑን ልብ በል፡፡ ጌታ የገባውን ቃል የገባው አንዳንድ ሁኔታዎች መሟላታቸውን መሰረት በማድረግ ነው፣ ለምሣሌ ዮሐንስ 14፡14 ላይ “ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ” አለ ነገር ግን በቀጣዩ ጥቅስ 14፡15 “ ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ” ነው ያለው፡፡ ጌታ ትዕዛዙን ካልጠበቀ ጌታን ካልወደደ የእግዚአብሄር ልጅም ቢሆን ከአብ የለመነውን ነገር ይሰጣል ብለን መገመት እንችላለን? በዮሐንስ 15፡7 ላይ እንዲህ ይላል “በኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል” ይላል፣ እዚህ ጋ ቁልፉ ቃል “እናንተ በእኔ ብትሆኑ ቃሎቼ በእናንተ ቢኖሩ” የሚል ነው፣ በጌታ የሆነ እና የጌታ ቃልም በእሱ የሆነ ሰው ምን ዓይነት ሰው ሊሆን ይችላል? በእርግጥ ታማኝ የእግዚአብሄር ልጅ ይሆናል፣ ነገር ግን አንድ ሰው በጌታ ባይኖር ቃሉም በእሱ ባይኖር፣ ጌታ የዚያን ሰው ልመና አሁንም ይፈፅማልን? በእርግጠኝነት አይደለም፡፡

ክርስቶስ ሲናገር “ _____ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣቸሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬያቸሁም ሊኖር ሾምኋቸሁ” አላቸው (ዮሐንስ 15፡16) ነገር ግን በዚያ ጥቅስ የመጀመሪያ ክፍል እርሱ እንደመረጣቸው ተናግሮ ፍሬ እንዲያፈሩም ሾመ፡፡ እዚህ ላይ ለሐዋሪያቱ እየተናገረ ነው፣ ነገር ግን ጌታ እነዚህን ልመናዎች ሲሰጣቸው ጥሩ ፍሬ ማፍራት ተስኗቸው ነበር ብለህ መገመት ትችላለህ ? እንደገና ክርስቶስ የሚለምኑት ሁሉ እንደሚቀበሉ ቃል ገብቷል (ማቴዎስ 7፡7~8፣ ክርስቶስ በመቀጠልም እንዲህ በማለት ተናግሯል “ወይስ ከእናንተ ልጁ እንጀራ ቢለምነው ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን ? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻቸሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፣ በሰማያት ያለ አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?

“ (ማቴዎስ 7፡9~11) በእርግጥ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በአባት ና ልጅ ግንኙነት አላቸው እንዲአገባቡ ቅዱሣት መፃሕፍት ስታጠና የጌታ በረከቶች እርሱን ለሚታዘዙና ለእርሱ ታማኝ ሆነው ለመቀጠል ፈቃደኛ ለሆኑት ብቻ እንደሆነ ሁልጊዜ ትገነዘባለህ፣ እንዴት አመፀኛና የማታዘዙትን ይባርካል?

በመጨረሻ በ1ኛ ዮሐንስ 5፡14፣15፣ ላይ ዮሐንስ እንደፈቃዱ ከሆነ ፀሎታችንን እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ ዮሐንስ በግልፅ ተናግሯል። ልጆቹን የሚወድ አባት የሚጎዳውን ወይም የሚያጠፋውን ነገር አይሰጣቸውም፣ ነገር ግን የሚቻል ከሆነ አባት የልጆቹን ጥያቄ ይፈፅማል ። በአባታችንም ዘንድ እንዲሁ ነው፣ እኛም እንደዚያ እናስብ ይሆናል፣ ለእኛ የሚጠቅመን ነገር አለ፣ ነገር ግን ጥበበኛ የሆነ አባታችን የሚጠቅመንን ሊያይ ይችላል፣ ይሁን እንጂ አንድ አፍቃሪ አባት የሚጠቅመንን ነገር እንደሚመልስ እርግጠኞች መሆን እንችላለን፣ ከዚያም ጳውሎስ እግዚአብሄርን ከልብ የምንወደው ከሆነ ሁሉም ነገር ለጥቅማችን ለበጎ እንደሚሠራ መናገሩን እናስታውሳለን (ሮሜ 8፡28) እንደ ክርስቲያኖች ሁልጊዜ ወደ እሱ የምንሄድ አባት በማግኘታችን በጣም ተባርከናል፣ ክርስቶስ ሰዎች ሁልጊዜ መፀለይ እንዳለባቸው ተናግሯል (ሉቃስ 8፡1) ሐዋሪያው ጳውሎስ ሳታቋርጡ ፀልዩ ብሏል (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡17) የጥንቶቹ ክርስቲያኖች በሐዋሪያት ትምህርትና በፀሎት ፀንተው እንደቀጠሉ ተነግሮናል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42) ዳግመኛ ያዕቆብ የተጨነቁ ካሉ እንዲፀልዩ ብሏል (ያዕቆብ 5፡13) ከዚያም የፃድቅ ሰው ፀሎት ኃይልን ታደርጋለች ብሉል (ያዕቆብ 5፡16) ምንም እንኳን ጌታ ለሕሙማን ፀሎታችንን በተአምር ሊመልስልን ቃል ባይገባም ፀሎቶች ግን ለውጥ ያመጣሉ። አምላክ የታመሙትን ለመፈወስ በተፈጥሮ በመድኃኒት፣ በዶክተሮች፣ በነርሶች የህክምና ሕግ አማካኘት እንዲሠራ እንፀልያለን። አንዳንድ ጊዜ ኃይሉን ለማሣየት የሚችልበት ወይም አንድን ነገር የሚያደርግበት ብቸኛው መንገድ ተአምር ነው ብለን እናስባለን፣ ጉዳዩ እንደዚያ አይደለም። እምነታችን ዬት ነው ? የሚል ውስጥ አብግባ ፣ ከዚህ በተጨማሪ ኢየሱስ በሽተኞች ባለ መድኃኒት ይስፈልጋቸዋል ስለአለ ጌታን አንፈታተነው (ማtቴዎስ 9፡ 12፣ ማቴዎስ 4፡7)

ፀሎታችን ከአባታችን ተሰሚነት እንዲኖረው በክርስቶስ ስም መለመን አለብን እሱ ጠበቃ አማላጅ እና ሊቀ ካህናችን ነውና (2 ዮሐንስ 2፡1፣ 1 ጢሞተዎስ 2፡5፣ ዕብራዊያን 3፡1)

በፀሎት ታምናለህ ?አባትህ እንደሚሰማህ እና ልመናህን እንደሚፈፅም በማስተማር መፀለይ ትችላለህ ? ክርስቲያን ካልሆንክ ወደ አባት መፀለይ ላይ አይደለህም ይህን ለመሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፣ ስለኃጥያትህ ንሠሃ በመግባት ክርስቶስ የእግዚአብሄር

ልጅ መሆኑን መመስከር እና ለኃጥያትህ ሥርየት መጠመቅ አለብህ (ዕብራዊያን 11፡6 ዮሐንስ 14፡1 ፣ ማቴዎስ 10፡32፣ ሐዋሪያት ሥራ 2፡ 38) በመፈፀም ከአባት ጋር መገናኘት አለብህ ያንን ስታደርግ ጌታ ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምርሓል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47) ከዚያ እንደ ጌታ ልጅ ታማኝ ከሆንክ ጌታ ፀሎትህን እንደሚሰማ እና እንደሚመልስልህ ቃል አለህ ማለት ነው።

ትምህርት 31

*ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስድ አንድ መንገድ ብቻ ለምን ሆነ*

በኃይማኖቱ ዓለም ብዙ ጊዜ “ወደ መንግሥተ ሰማያት ብዙ መንገዶች አሉ” “ሁላችንም በተለያየ መንገድ እየተጓዝን ነው ነገር ግን ሁላችንም ወደ አንድ ቦታ ለመሄድ እየሞከርን ነው” እና የመሳሰሉትን መግለጫዎች እንሰማለን፣ ይህ ላዩን ስናይ ጥሩ ይመስላል፣ በተለይም ስለሱ ለማሰብ ካላቆምክ፣ ነገር ግን ያ በእርግጥ ለመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንግዳ ነው።

መፅሐፍ ቅዱስ ስለመንግሥተ ሰማያት የሚነግረን ውበቱን እግዚአብሄር ኢየሱስን ለታዘዙት ሕዝቡ ማዘጋጀቱን እንዴት እንደተዘጋጀም ይነግረናል ኢየሱስ ሲናገር “ልባችሁ አይታወክ፣ በእግዚአብሄር እመኑ፣ በእኔም ደግሞ እማኑ፣ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ እንዲህስ ባይሆን ባልኳችሁ ነበር፣ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት ቦታ እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችዋለሁ “ አለ (ዮሐንስ 14፡1~3)፣ ስለዚህ በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ፣ እና በመንግሥተ ሰማያት የሚያምኑ ሁሉ በእርግጥ እዚያ መገኘት ይፈልጋሉ። ግን ጥያቄው እንዴት እዚያ መሆን ይቻላል የሚለው ነው። የሚሄድበት አንድ መንገድ ነው ወይስ ብዙ መንገዶች ናቸው ?

ኢየሱስ “እኔ መንገድ፣ እውነትም ህይወትም ነኝበእኔ በቀር ማንም ወደ አብ ሊመጣ አይችልም “ ብሏል (ዮሐንስ 14፡6)፣ እንግዲህ አስተውል ኢየሱስ መንገድ ነው፣ ብቸኛ መንገድ ወደ አብ የሚወድ ነው፣ ስለዚህ አንድ ሰው ወደ አብ ለመሄድ በክርስቶስ በኩል ብቻ መሄድ አለበት፣ ወደ አብ የሚወስዱ ብዙ መንገዶች ቢኖሩ ኖሮ ክርስቶስ ብቸኛ አንድ መንገድ ባልሆነ ነበር።

ኢየሱስ እራሱን እንደ መልካም እረኛ፣ ክርስቲያኖችን እንደ በጎች፣ ቤተክርስቲያንን ደግሞ እንደ በረት ገልፆአል፤፤ አሁን ኢየሱስ ስለበሩ የተናገረውን ስማ “ኢየሱስም ደግሞ አላቸው፣ እውነት እውነት እላችዋለሁ፣ እኔ የበጎች በር ነኝ” አለ (ዮሐንስ 10፡7) በመቀጠልም እንዲህ እያለ ይገልፃል “በሩ እኔ ነኝ፣ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል። ይገባልም ይወጣልም መሰማርያም ያገኛል” ይላል (ዮሐንስ 10፡9)

ከዚያም “እውነት እውነት እላችዋለሁ፣ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው” ይለናል (ዮሐንስ 10፡1) በሌላ አገላለፅ ኢየሱስ የሚናገረው እርሱ የበጎች በረት በር እንደሆነ፣ ወደ ቤተክርስቲያን የሚገቡበት አንዱ መንገድ እና ወደ ራሱ መንግሥት ወይም መንግሥተ ሰማያት የሚገባ መሆኑን ነው። ከዚያም አንድ ሰው በበሩ ሳይሆን በሌላ መንገድ ለመውጣት ቢሞክር እንደ ሌባና ዘራፊ እንደሚቆጠር ያስረዳል። ግን በመጨረሻ ሌቦችና ዘራፊዎች ምን ይሆናሉ? ሐዋሪያው ጳውሎስ ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ወይም ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት እንደማይችሉ ይነግረናል፣ ይህም ማለት ከኃጥያታቸው ንሠሀ ካልገቡ እና እግዚአብሄርን ካልታዘዙ በቀር ማለት ነው፣ በእርግጥም አንድ ሰው ጌታ ከሰጠው መንገድ ውጪ በሆነ መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለምሄድ የሚሞክር ያ ሰው ወደ ሲኦል ይጣላል።

አንድ ጊዜ ኢየሱስ በተራራው ስብከት ላይ በዙሪያው ለተሰበሰቡ ሰዎችእንዲህነበርያለው“በጠበበውደጅግቡወደጥፋትየሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና፣ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፣ ወደ ህይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና ፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው” (ማቴዎስ 7፡13፣14)፣ ኢየሱስ አንድ እና ሁሉም ወደ ጠበበው በር በኩል እንዲገቡ እያበረታታ እንደሆነ አስተውል። ይህ ጠባብ በር ክርስቶስን ይወክላል፣ ወደ ቤተክርስቲያን የመግባት መንገድ እና ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚከድበት፣ በዚህ በጠባብ በር የሚገቡት ወደ መንግሥተ ሰማያት በምትወስደው ጠባብ መንገድ ላይ እንደሚገኙ ተናግሯል፣ በዚህ ሁኔታ አንድ ደጅ አለ፣ አንድ መንድ መንገድም አለ፣ እሱ መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚመራ ነው፣ እሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፣ በዚያ መንገድ የሚገባ ማንነው? ጌታን የታዘዙት የዳኑት ክርስቲያኖች፣ የጌታ ቤተክርስቲያን አባላት፣ ፅድቃን ቅዱሣን እና ለክርስቶስ ታማኝ የሆኑት፣ ከጠባቡ መንገድ ውጪ የሚሄዱ በሌላ መንገድ የሚሄዱ ምን እንደሚሆኑ መገመት እንችላለን? ክርስቶስ ስለእነዚህ ወገን ይናገራል፣ ወደ ሰፊው በር የሚገቡትንና ወደ ጥፋት የምጓዙትን ይናገራል፣ ለዚህ የተዘጋጁት ለጥፋቱ የተዘጋጁት ማናቸው? አብዛኞቹ ሃይማነተኞች፣ የእግዚአብሄር ፍርሓት የሌላቸው የክርስቶስን ሥልጣን ለማክበር ፈቃደኛ ያልሆኑ፣ ወንጌልን የማይታዘዙ፣ በራሳቸው መንገድ ለመዳን የሚያስቡት ናቸው፣ እነዚህ በሰፊው መንገድ ላይ ያሉት ፣ ሰው ሰአራሽ ቤተክርስቲያንን የሚቀላቀሉ፣ የክርስቶስን ሳይሆን የሰው ስም የለበሱ፣ እንደፈለጉ የሚያመልኩ ወዘተ ናቸው፣ ለራሳቸው ተታለው ሌሎችንም የሚያታልሉ ናቸው፣ ታማኝ ያልሆኑት ክርስቲያኖችም በዚህ ቡድን ውስጥ ይሆናሉ፣ ግን ይህ መንገድ ወደ ዬት ያመራል? ወደ ዘላለማዊ ጥፋት ያመራል፣ ኦው ብዙዎቹ ሐቀኞች

ቅኖች ሊሆኑ ይችላሉ፣ በጣም ኃይማኖተኞችም ሊሆኑ ይችላሉ ምንም ይሁን ምን ወንጌልን እስካልታዘዙ ድረስ በሰፊው መንገድ ላይ ናቸውና ዘላለማዊ ጥፋት ይጠፋሉ፡፡

ወዳጆቼ፦ ወደ ዋና ከተማ የሚወስዱ ብዙ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን አንድ ሰው ከእርስዎ ጋር በአንድ መንገድ ብቻ እንዲጓዙ ስምምነት ካደረጋችሁ፣ ሌላ መንገድ ከመረጡ ይሆናል? እንዳትቸገሩ እፈራለሁ፣ እንዲሁም ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ አለው፣ (ማቴዎስ 20፡18)፣ ስለዚህ ይህ ባለሥልጣን ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉ በእርሱ የሆነው "መንገድ እኔ ነኝ" ካለ ሌላ ነገር ትተን እሱ ባለው መንገድ መጓዝ አለብን፡፡

ስለመንግሥተ ሰማያት መንገድ የመናገር ችግራችን በሰው አስተሳሰብ ደረጃ ላይ ማስቀመጥ መፈለጉ ነው፡፡ ወደ ከተማ የሚወስዱት ብዙ መንገዶች ካሉ እና ሁሉም ወደዚያች ከተማ የሚወዱ ከሆነ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ በእርግጥ ተመሳሳይ ይሆናል ብለን እናስባለን፣ ከጌታና ከመንገዱ ጋር ግን አንድ ብቻ ነው እንደሰዎች በእምነት፣ በሰው ሰራሽ ቤተክርስቲያን እና በመሳሰሉት ሌሎች መንገዶች ሁሉ የሚወዱ ሊመስሉ ይችላሉ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስዱ መንገዶች አይደሉም ማንም ሰው በሠራቸው መንገዶችና ድርጅቶች ወደ መንግሥተ ሰማያት መሄድ አይችልም፣ ይህንን ለመገንዘብ ማድረግ ያለብን መፅሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብ ብቻ ነው፡፡ ክርስቶስ እንዲህ ይላል "የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ተናገረ" ይላል (ማቴዎስ 15፡9) እንደገና ክርስቶስ እንዲህ አለ " በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፣ በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን ? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፣ የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኳችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ " ብሏል (ማቴዎስ 7፡21~23) በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ በደርዘንና ደርዘኖች የሚቆጠሩ ተመሳሳይ መግለጫዎች አሉ፡፡ አሁን እግዚአብሄርን እንዳንታዘዝ በእኛ መንገድ ነገሮችን እንድንሠራ ሰው ሰራሽ ቤተክርስቲያን እንድንቀላቀል ሰው ሰራሽ ስሞችን እንድንለብስ፣ እንደምንፈልገው ማምለክ፣ በፈለኘው መንገድ መጓዝ ለአንድ ደቂቃ እናስብ፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ እንዲህ እያደረግክ አሁንም ወደ ገነት ትሄዳለህ ? እንዲህ የምናስብ ከሆነ በእርግጥ ተሳስተናል፣ ሳኦልን እንመልከት እርሱ በጣም ኃይማኖተኛ ሰው ነበር፣ ለኃይማኖቱ ቀናተኛ ነበር፣ የጌታን ቤተክርስቲያን ቢያሳድድም በጎ ሕሊና ነበረው፣ ነገር ግን ስህተቱን አወቀ፣ ከኃጥያቱ ተፀፀቶ ጌታን ሲታዘዝ ብቻ ነው የዳነው እና ወደ ትክክለኛ የተመለሰው (የሐዋሪያት ሥራ 9 እና

22)፣ ስለቆርኔሌዎስና ቤተሰቡስ ? ጥሩ ሰዎች ነበሩ፣ ያላቸውን ለድሆች ይሰጣሉ፣ ወደ ሰማይ አምላክ አዘወትረው ይፀልያሉ ሆኖም ጴጥሮስ ከሰበከ ቦኃላ ተጠምቀው እንዲድኑ ታዘዋል (የሐዋሪያት ሥራ 10) ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደው መንገድ አንድ ብቻ መሆኑን የሚገልፁ ሌሎች በርካታ ምሣሌዎችም በቅዱሣት ፅሁፎች ውስጥ አሉ።

ወዳጆቼ ይህንን አስቡ ቅዱሳት መፅሐፍት አንድ አምላክ አለ፣ አንድ ጌታ ወይም አንድ አዳኝ፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ አካል ወይም ቤተክርስቲያን፣ አንዲት እምነት፣ አንዲት ጥምቀት፣ አንድ ተስፋ እንዳለ ያስተምራል። (ኤፌሶን 4:1~6)። መፅሐፍ ቅዱስ አንድ ወንጌል ብቻ እንዳለ ይነግረናል ወይም ለመዳን አንድ መንገድ ብቻ፣ እግዚአብሄርም ጌታ አዳኝ እንደሆነ እርሱን ብቻ እንዲሰሙት አዘዘ፣(ማቴዎስ 17:5) በእርሱ እናምን ዘንድ (ዮሐንስ 8:24) ከኃጥያት ንሠህ በግባት (ሉቃስ 13:3) ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከር (ማቴዎስ 10:32) ለኃጥያት ሥርየት መጠመቅ (ማርቆስ 16:16፣ የሐዋሪያት ሥራ 2:38) ክርስቶስ ደግሞ እራስይ ወደ መሰረታት፣ እራሱ ወደ ሞተላት ፣ በደሙም ወደ ዋጃት፣ እርሱ ራስ ወደ ሆናት አንድ ቀንም ተመልሶ መጥቶ ወደ ሚወስዳት ቤተክርስቲያኑ ይጨምራል (የሐዋሪያት ሥራ 2:47፣ ማቴዎስ 16:16~18፣ ኤፌሶን 5፣ የሐዋሪያት ሥራ 20:28)፣ መፅሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ሁሉም ሰው በመንፈስ እና በእውነት እንዲሰግዱለት እንደሚፈልግ ያስተምራል (ዮሐንስ 4:24) ስለዚህ ሁሉም በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ተገናኝተው የጌታን እራት ለመካፈል፣ የእግዚአብሄርን ቃል ለማጥናት ፣ ለመፀለይ፣ የአቅማቸውን ካላቸው ላይ ለመስጠት እና እግዚአብሄርን ለማመስገን (የሐዋሪያት ሥራ 20:7፣ 2 ጢሞቴዎስ 2:15፣ የሐዋሪያት ሥራ 2:45፣ ኤፌሶን 5:19፣) እግዚአብሄር ሰዎች ሁሉ የሚያደርጉትን ሁሉ በክርስቶስ ስም እንዲያደርጉ ይፈልጋል (ቆላስያስ 3:17) ይህ ማለት ደግሞ ሁሉም የክርስቶስን ስም መልበስ አለባቸው ማለት ነው (የሐዋሪያት ሥራ 11:26) እና ሁሉም ታማኝ ክርስቲያናዊ ህይወት መምራት አለባቸው (ዮሐንስ ራዕይ 2:10)

ሁላችንም ልናነበው፣ ልናምንበት እና ልንታዘዘው የተሰጠን አንድ መፅሐፍ ቅዱስ ብቻ አለ። ለጌታ ብንታዘዝ ለእርሱም ታማኝ ሆነን ብንኖር የምንሄድበት አንድ ሰማይ ብቻ አለ፣ ለኃጥያተኛና ለከዳተኞችም አንድ ሲኦል አለ (ማቴዎስ 25:46)።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሰው ሁሉ እውነት ከሆነ እና አንተ ራስህ ቅዱሣት መፃሕፍትን ማንበብና ማጥናት ከቻልክ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከአንድ በላይ መንገድ እንዴት ሊኖር ይችላል? አዎን ወደ መንግሥተ ሰማያት መንገድ አንድ ብቻ ነው እርሱም የጌታ መንገድ ነው፣ ያንን መንገድ ተቀብለን ወደ መንግሥተ ሰማያት በሚወስደው መንገድ እንድንጓዝ ጌታ የሚፈልገውን ብናደርግ ብልህነት ይሆናል። በሌላ መንገድ መሄድ

አንቸልም፣ አንድ ጥበበኛ ሰው እንዲህ አለ “ ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፣ ፍፃሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው፣ “ አለ (ምሣሌ 14፡12)።
በምን መንገድ ነው እየተጓዝክ ያለኸው ? በሰፊው መንገድ ወይስ በጠባቡ መንገድ? ወደ ጥፋት የሚወስደው መንግድ ወይስ ወደ ገነት? በሁለቱም መንገዶች ላይ ተመሣሣይ ጊዜ መጓዝ አይቾሉም። ክርስቶስ ማንም ሰው ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቸልም ብሎ ተናግሯል (ማቴዎስ 6፡24)፣ ወይ ከእርሱ ጋር መሆን ወይም እርሱን መቃወም አለብህ (ማቴዎስ 12፡30)። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው በየትኛው መንገድ እንደሚሄድ ይወስናል። ክርስቶስን እና የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ እንድትመርጥ እንለምንሃለን።

## ትምህርት 32
## ሠይጣን መኖሩን ለምን እናምናለን

በተለይ አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን ማንም ሰው በሰይጣን ለምን ያምናሉ ብለው የሚገረሙ ሊኖሩ ይቾላሉ፣ ሰዎች ወደ ጠፈር በሚወጡበት ጊዜ ሰይጣንን የመሰለ ገፀ ባህሪ ጊዜው ያለፈበት ይሆናል ብለው ያስባሉ። ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች እራሳቸውን እያታለሉ ነው። አዎን ሰይጣን አለ። እርሱ እንደእግዚአብሄር እና እንደክርስቶስ መኖሩ እርግጥ ነው። እሱ በመላው ዓለም ይኖራል፣ የእሱ ሥራዎች በሁሉም ቦታዎች ይታያሉ፣ የእሱ ተፅዕኖ በሁሉም ውስጥ ይታያል፣ እሱ ብቻ ሳይሆን መፅሐፍ ቅዱስ በዓለም እንዳለ ያስተምራል። እሱ ሰው ሳይሆን መንፈስ ነው፣ እርኩስ መንፈስ ነው፣ እርሱ እግዚአብሄር እና ክርስቶስን ከሚወክሉት ጋር ተቃራኒ ነው። ሁልጊዜ ከመጥፎ እና ከስህተት ጀርባ አለ፣ እርሱ ዲያብሎስ፣ ክፉው፣ የሐሰተኞች አባት፣ የዚህ ዓለም አምላክ ይባላል። እሱ ጨለማን፣ ኃጥያትን እና ሀዘንን ይወክላል ፣ እርሱ ሞትን ያመጣል እርሱ ጠላታችን ስለሆነ ከእርሱ ጋር መተዋወቅ አለብን፣ እሱን ለመገናኘት እራሳችንን በተሻለ ሁኔታ ማዘጋጀት እንቾላለን፣ ያለ እውቀትና ትክክለኛ የጦር ትጥቅ ሊያታልለን፣ ሊያሸንፈን እና ሊያጠፋን ይቾላል፣

አሁን ወደ እግዚአብሄር ቃል እንሂድና ስለርሱና ስለሥራው የሚናገሩ የቅዱሣት መፃሐፍት ጥቅሶቾን እናንብብ፣ ኢየሱስ የእንክርዳዱን ምሣሌ ሲያብራራ እንክርዳዱ የክፉው ልጆች እንደሆኑ ተናግሯል “መላክሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፣ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፣ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፣ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፣ አጫጆቾም ምላዕክት ናቸው” አለ (ማቴዎስ 13፡38~39)፣ ጴጥሮስም በዘመኑ ላሉት ክርስቲያኖች ፅፎል “በመጠን ኑሩ ንቁም፣ ባላጋራቸሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሣ ይዞራልና” ብሏል (1ኛ ጴጥሮስ 5፡8)፣ ጳውሎስም ለተሰሎንቄ

ክርስቲያኖች ሲፅፍ "ስለዚህ እኔ ደግሞ ወደፊት እታገስ ዘንድ ባልተቻለኝ ጊዜ፣ ፈታኝ ምናልባት ፈትኗቸዋል ድካማችንም ከንቱ ሆኗል ብዬ እምነታችሁን ለማወቅ ላክሁ" ይላል (1ኛ ተሰሎንቄ 3፡5)። በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ኃይማኖታዊ ቡድኖች በባኤልዘቡል ኃይል አጋንንትን ያወጣል ብለው ይከሱት ነበር "ከዚያም በኃላ ጋኔን ያደረበትን ዕውር ዲዳም ወደ እርሱ አመጡ፣ እውሩም ዲዳውም እስኪያይና እስኪናገር ድረስ ፈወሰው፣ ሕዝቡም ሁሉ ተገረሙና፣ እንጃ ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን? አሉ፣ ፈሪሣዊያን ግን ሰምተው ይህ በብዔልዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም አሉ፣ ኢየሱስ ግን አሳባቸውን አውቆ እንዲህ አላቸው፣ እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ ትጠፋለች፣ እርስ በእርሡ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም፣ ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣ ከሆነ እርስ በእርሱ ተለያየ እንግዲህ መንግሥቱ እንዴት ትቆማለች?፣ እኔስ በብኤልዜቡል አጋንንትን የማወጣ ከሆንኩ ልጆቻችሁ ባማን ያወጣቸዋል? ስለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባቸዋል፣ እኔ ግን በእግዚአብሄር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆኑ፣ እንግዲህ የእግዚአብሄር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለጭ ወስ ሰው አስቀድሞ ኃእለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል፣ ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፣ ከእኔ ጋርም የማያከማች ይበትናል" አላቸው (ማቴዎስ 13፡22~30) እንደዚሁም ሐዋሪያው ዮሐንስ ሲፅፍ እንዲህ ይላል "አባቶች ሆይ፣ ከመጀመሪያ የነበረውን አውቃችዋልና እፅፍላችዋለሁ፣ ጎበዞች ሆይ ብርቱዎች ስለሆናችሁ የእግዚአብሄርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉውንም ስለአሸነፋችሁ እፅፍላችዋለሁ" ይላል (1ኛ ዮሐንስ 2፡14) ዮሐንስ ይቀጥልና "በመጀመሪያ የሰማችሁዋት መልዕክት እርስ በእርሳችን እንዋደድ የምትል ይህቺ ናትና፣ ከክፉው እንደነበረ ወንድሙንም እንደገደለ እንደቃዬል አይደለም፣ ስለምንስ ገደለው? የገዛ ሥራው ክፉ የወንድሙም ሥራ ፅድቅ ስለነበረ ነው፣ " (1ኛ ዮሐንስ 3"11~12) ይቀጥልና አሁንም "ከእግዚአብሄር የተወለደ ሁሉ ኃጥያትን እንዳያደርግ፣ ነገር ግን ከእግዚአብሄር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን፣ ከእግዚአብሄር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን" ይላል (1ኛ ዮሐንስ 5፡18~19) በኃላ ላይ ዮሐንስ በራዕይ መፅሐፍ ላይ እንዲህ ይላል "ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፣ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ ወደ ምድር ተጣለ መላዕክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ" ይላል (ዮሐንስ ራእይ 12፡9) የበለጠ ሲብራራ ዮሐንስ በሰይጣን የተከሰተውን ሲነግረን "የጥልቁም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልዓክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፣ የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና

ሰይጣን የተባለውን ያዘው ሺ ዓመትም አሰረው፣ ወደ ጥልቅም ጣለው አህዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺ ዓመት እስኪፈፀም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማህተም አደረገበት፣ ከዚያም በኃላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገበዋል" ይላል (ዮሐንስ ራዕይ 20፡1~3)

ኢየሱስ በጊዜው ለነበሩት ሲናገር እንዲህ አላቸው "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፣ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም፣ ሐስተን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፣ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና፣ እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለሆንኩ አታምኑኝም" አላቸው (ዮሐንስ 8፡44~45)፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቶቹ እንዲህ አላቸው "ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልኖርም ፣ የዚህ ዓለም ገዢ ይመጣልና በእኔ ላይም አንዳች የለውም" (ዮሐንስ 14፡30)፣ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏል "ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳን የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው፣ ለእነርሱም የእግዚአብሄር ምሣሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ" (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡3~4)።

ግን ሰይጣን ከዬት መጣ? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። እግዚአብሄር ሁሉንም ነገር ፈጠረ (ዘፍጥረት 1፡1) ከዚያም በተፈጥሮ እግዚአብሄር እርሱንና ከእርሱ ጋር የተገናኙትን መላዕክቶች ሁሉ ፈጠረ፣ ራሱን ከፍ አድርጎ በፈጣሪው ላይ አምፆ የእግዚአብሄር ጠላት ሆነ ይህንንም ጴጥሮስ በቅዱስ ቃሉ ሲናገር እንዲህ ይላል "እግዚአብሄር ኃጥያትን ላደረጉ መላዕክት ሳይራራላቸው ወደ ገሀነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ሊጠበቁ ለፍርድ አሳልፎ ሰጣቸው" ይላል (2ኛ ጴጥሮስ 2፡4) በዚሁ ምሣሌ እኛም የእግዚአብሄርን ፈቃድ ከተቃወምን የሚደርስብንን ውጤት ይሁዳ እንዲህ ሲል ያስነብበናል "መኖሪያቸውንም የተውትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላዕክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከታላቁ ቀን ድረስ ጠብቋቸዋል" (ይሁዳ 6)፣ በመጨረሻው ቀን ኢየሱስ እንዲህ ይላቸዋል "በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፣ እናንተ ርጉማን፣ ለሰይጣንና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ" ይላቸዋል (ማቴዎስ 25፡41)።

ወደ መጀመሪያው ስንመለስ እግዚአብሄር አዳምና ሔዋንን ከፈጠረ በኃላ በኤደን ገነት ካስቀመጣቸውም በኃላ ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዲበሉ ነገር ግን አንዷቷን ከፉና ደጉን እውቀት የምጸጠውን እንዳይበሉ ከበሉ ግን እንደሚሞቱ ነገራቸው፣ እስቲ እናንብብ " እባብም እግዚአብሄር አምላክ ከፈጠራቸው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነበረ፣ ሴቲቱንም ፦ በውኑ እግዚአብሄር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት ፣ ሴቲቱም ለእባቡ አለችው በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ

እንበላለን ፣ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ እግዚአብሄር አለ ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት ፦ ሞትን አትሞቱም ከእርሷ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሄርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሄር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች፣ ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባሏም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርሷ ጋር በላ፣ የሁለትም ዓይኖቸ ተከፈቱ፣ እነርሱም ራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ፣ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ። እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሄርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፣ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሄር ከአምላክ ፊት ከገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ፣ እግዚአብሄር አምላክም አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፣ ዕራቁቴንም ስለሆንኩ ፈራሁ፣ ተሸሸግኩም። እግዚአብሄርም አለው፣ ራቁትህን እንደሆንክ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ከዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን? አዳምም አለ፦ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርሷ ከዛፉ ሰጠቸኝና በላሁ። እግዚአብሄር አምላክም፣ ሴቲቱን ፦ ይህ ያደረግሺው ምንድርነው? አላት፣ ሴቲቱም አለች፦ እባብ አሳተኝና በላሁ" (ዘፍጥረት 3፡1~13)፣ በእርግጥ በዚያ ቀን ወንድና ሴት በመንፈስ ሞቱ፣ ነገር ግን እግዚአብሄር በወንድ በሴት በእባቡ እና በፍጥረት ሁሉ ላይ እርግማን ተናገረ። በማቴዎስ 4 ፈታኙ ሰይጣን ራሱ ወደ ክርስቶስ መጣ፣ በፊቱ እንዲሰግድ ለማድረግ ሦስት የተለያዩ ፈተናዎችን አቀርቧል፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ ፈተናውክርስቶስ የእግዚአብሄር ቃል እንዲህ ይላል በማለት ሲመልስለት ሰይጣን ዲያብሎስ በመሸነፍ ተወው።

ክርስቶስ በሰይጣን ላይ ያገኘው ትልቁ ድል ከመቃብር በወጣ ጊዜ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ የሰው ልጅ መዳን እንዲቻል ለማድረግ እና ወደፊት ስለሚመጣው ትንሣኤ ማረጋገጡ ነው፣ ክርስቶስን የሚታዘዙና ለጌታ ታማኝ ሆነው የሚፀኑትን ሁሉ እንደሚያድናቸው፣ ሁሉንም ፈተናዎችን እንዲያሸንፉ እንደሚረዳቸው እና በመጨረሻም ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚወስዳቸው ቃል ከዳን ገብቶላቸዋል።

ወዳጆቼ፦ ሰይጣንአሮጌውዲያብሎስህይወታችሁንእንዲቆጣጠር አትፍቀዱለት ፣ በዚህ ዓለም ቁሳዊ ነገሮች ወደ አንተ እንዲደርስ አትፍቀድለት፣ የዚህን ዓለም ነገር የሥጋ ምኞትን የዓይን አምሮትን የዚህ ዓለም ትዕቢት በአንተ ላይ ተፅዕኖ እንዲያደርግ አትፍቀድለት፣ በሐሰት ኃይማኖትንና በሐሰት ትምህርት እንዲያሳስትህና እንዲያታልልህ አትፍቀድለት፣ ክርስቶስ ሰይጣንን እስከሞት ድረስ እንዳንከተል ይፈልጋል፣ የእግዚአብሄር ቃል መፅሐፍ ቅዱስ የእውነትን ውበት እና

ወደ ዘላለማዊ ህይወት የሚወደውን መንገድ ይገልፃል፣ በዚያውም ልክ ወደ ሞት ከሚወስዱ ከሰይጣን ተንኮልና ማታለያ መንገዶች ያስጠነቅቀናል፡፡

ስለዚህ ከሰይጣን እንጠንቀቅ፣ በእርሱ አትታለሉ፣ የእግዚአብሄርን ቃል አንብቡና አጥኑ ስለጌታ እና መንገዶቹ ተማሩ፣ ነገር ግን ከጠላትህ ከሰይጣን ጋር ለመለያየት መፅሐፍ ቅዱስን ተማሩ፣ በእግዚአብሄር አብና በሕያው የእግዚአብሄር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ እመኑ፣ ያለእምነት እግዚአብሄርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና (ዕብራዊያን 11፡6) በእግዚአብሄርእናበክርስቶስምእንድናምንክርስቶስተናግሯል(ዮሐንስ 14፡1~3) ክርስቶስን እንድንከተል ሰይጣንን ግን እንድንርቅ እንዲሁም ከፉናስህተትየሆነውንሁሉእናዳንከትልይፈልጋል፣እግዚአብሄርሁሉም ንሠሃ እንዲገቡ አዟል (የሐዋሪያት ሥራ 17፡30) ክርስቶስ ደግሞ ንሠሀ ካልገባን እንደምንጠፋ ነግሮናል (ሉቃስ 13፡3)፣ ከዚያም ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን እንድንመሰክር ተጠይቀናል (ማቴዎስ 10፡ 32) በሰው ፊት ብንመሰክርለት በሰማያት ባለው አብ ፊት ይመሰክርልናል የሚል ቃል ኪዳን መሰረጥ  እና በመጨረሻም ለኃጥያታችን ሥርየት እንድንጠመቅ ወይም በውኃ ውስጥ ተቀብረን እንድንጠመቅ ታዘናል፣ ክርስቶስ አምነን ከተጠመቅን ትድናላችሁ ብሏልና (ማርቆስ 16፡ 16) ጴጥሮስ ንሠሀ ብንገባና ብንጠመቅ የኃጥያታችንን ሥርየት እንደምንቀበል ተናግሯል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38) ይህንን ስናደርግ ጌታ ደግሞ ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምረናል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47) በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት እንሆናለን (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17) ስለዚህ እኛ የሰይጣን አንሆንም የክርስቶስ እንጂ ፣ የክርስቶስ የሆን ክርስቲያኖች ነን (1ኛ ጴጥሮስ 4፡16)፣ እናም እስከ መጨረሻው ለጌታ ታምነን ስንኖር በሰማይ መኖሪያ አለን (ዮሐንስ ራዕይ 2፡10፣ 22፡14)፡፡

## ትምህርት 33
## በሰማያት ለምን እናምናለን

ስለ ሰማያት ስናገር  ስለሰማይ፣ ደመና ወይም ድባቡ ማለቴ አይደለም፣ እኔ የምናገረው  ስለውጫዊ ጠፈርም አይደለም፣ አንዳንድ ጊዜ  እነዚህን እንደሰማይ እንጠራቸዋለንና፣ ነገር ግን የማስበው ሰማያት እግዚአብሄር የሚኖርበት ነው፣ እግዚአብሄርን የሚፈሩ ነፍሳት ለዘላለም የሞኖሩባት የፃድቃን ቤት ያማረች ሥፍራ ስለሆነች ሰማያት ነው፣ ይህቺ መንግሥተ ሰማያት በእግዚአብሄር ቃል አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ተብላም ተገልፃለች ፡፡

ቅዱሳት መፅሐፍት በአጠቃላይ ስለመንግሥተ ሰማያት ይናገራሉ ፣ ክርስቶስ ለፅድቅ ሲሉ ስለሚሰደዱ ሰዎች እንዲህ ብሏል “ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ፣ ከእናንተ በፊት

የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና" (ማቴዎስ 5፡12)፣ ኢየሱስ ለሐዋሪያቶቹ እንዲህ ብሎአቸዋል " አላቸውም ስትፀልዩ እንዲህ በሉ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መምግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር ትሁን" አላቸው (ሉቃስ 11፡2) እንዲሁም እንዲህ ብሎ መመሪያ ሰጣቸው "ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፣ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና" አላቸው (ማቴዎስ 6፡20~21) ክርስቶስ ለሐዋሪያቶቹ እሱ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ከመሰከሩ ቦኃላ እንዲህ አላቸው "የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፣ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈታው በሰማያት የተፈታ ይሆናል" አለ (ማቴዎስ 16፡19) ሰባውን ሲልካቸው እንዲህ ነበርያላቸው "እነሆ፣ እባቡንና ጊጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፣ የሚጎዳችሁም ምንም የለም፣ ነገር ግን መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፣ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተፃፈ ደስ ይበላችሁ" አላቸው (ሉቃስ 10፡19~20)

በመቀጠል ንሠሀ በሚገባ በአንድ ኃጥያተኛ በሰማይ ደስታ እንደሚሆን ተነግሮናል (ሉቃስ 15፡7)፣ ክርስቶስ ከሰማይ እንደወረደ ይናገራል (ዮሐንስ 3፡13) ኢየሱስ አብ ከሠማይ እንጀራ እንደሚሰጣቸው ተናግሯል፣ (ዮሐንስ 6፡32) ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲናገር "ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፣ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሄር የተሠራ ህንፃ እንዳለን እናውቃለንና" (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡1) ለገላቲያ ክርስቲያኖችም ሲናገር "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሠማይ መልዓክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን" ይላል (ገላቲያ 1፡8) ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖችም " ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላዕክት ጋር ከሠማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ፣ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን፣ መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሄርፊትበእርግጥፅድቅነውና፣እግዚአብሄርንየማያውቁትን ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፣ በዚያም ቀን በቅዱሣኑ ሊከብር ምስክርነታችንን አምናችኋልና በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ፣ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣል" (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7~9)። ጴጥሮስም "ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፣ እድፈትም ለሌለበት፣ ለማያልፍም ርስት እንደምህረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፣ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሄር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችዋል"

ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 1፡3~5)። ሐዋሪያው ዮሐንስም ሲናገር እንዲህ አለ "አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ፣ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፣ ባህርም ወደፊት የለም፣ ቅዲስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሣሌም በባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሄር ዘንድ ስትወርድ አየሁ" ይለናል (ዮሐንስ ራዕይ 21፡ 1~2)፣ እናም ስለመንግሥተ ሰማያት፣ የእግዚአብሄር ዘላለማዊ መኖሪያ እና የነፍሳት መኖሪያ በሆነው በማናቸውም ተመሣሣይ የቅዱሳት መፅሐፍት ምንባቦች ማግኘት እንችላለን።

ወደዚህ ሰማያት ማንነው የሚሄደው ? ኢየሱስ ሲናገር "እውነት እውነት እላቸዋለሁ ካልተመለሳችሁ፣ እንደ ህፃናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም" (ማቴዎስ 18፡3)። ያም ማለት ጨቅላ ህፃናት እና ትናንሽ ህፃናቶች ወይም ተጠያቂነት ዕድሜ ላይ ያልደረሱ ፣ በድርጊታቸው የማይጠቁ፣ ትክክልና ስህተት የሆነውን ስለማያውቁ፣ ሲሞቱ ወደ ሰማይ ይሄዳሉ፣ የጌታ መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን በሰማይ መሆኑን ነው፣ ጳውሎስ ሲናገር "ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፣ በዚያን ጊዜ፣ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተፃፈው ቃል ይፈፀማል" (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡54)፣ እንዲሁም ለኤፌሶን የተፃፈውን ስናነብ "ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና" (ኤፌሶን 5፡23) እንደዚሁም (ቆላስያስ 1፡18፣ የሐዋሪያት ሥራ 20፡28) ተመሣሣይ ያስነብቡናል። እንደዚሁም ይህቺን መንግሥት ጌታ ወደ ራሱ እንደሚያቀርባት " እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ" (ኤፌሶን 5፡27) በማቴዎስ 13፡41 ጌታ መላዕክቱን እንደሚልክ ከመንግሥቱ ወይም ከቤተክርስቲያን የሚያሰናክሉትን ነገሮች ሁሉ እንደሚሰበስቡና እንደሚጠፉ ወደ እሳቱም ይጣላሉ ብሏል፣ በሰማይ ላለው ለእግዚአብሄር ታዘን ወደ ዚላለም መዳን ወደ ቤተክርስቲያን ውስጥ መሆን ወይም መጨመር አለብን ማለት ነው ቅዱሣት መፅሐፍት በተጨማሪም ታማኝ ወይም የጌታን ትዕዛዛት የሚጠብቁ ወደ ሰማይ ይሄዳሉ ሲል ክርስቶስ ይናፈራል፣ "ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ፣ እነሆ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወይኒ ሊያገባችሁ አለው፣ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ እስከሞት ድረስ የታመንክ ሁን፣ የህይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ" (ዮሐንስ ራዕይ 2፡10)፣ ያዕቆብም እንዲህ ይላል "በፈተና የሚፀና ሰው የተባረከ ነው፣ ከተፈተነ ቦኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለእርሱ የሰጣቸውን የህይወትን አክሊል ይቀበላልና" ይላል (ያዕቆብ 1፡12)፣ ዮሐንስም "ወደ ህይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው፣

በደጆቿም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው” (ዮሐንስ ራዕይ 22፡14)

በተመሣሣይ ጊዜ አንዳንድ ሌሎች በሠማይ ሊሆኑ እንደማይችሉ መጠቆም አለበት እነዚህም ሠይጣንና መላእክቶቹ ናቸው (ማቴዎስ 25፡41) ታማኝ ያልሆኑ ክርስቲያኖች (ማቴዎስ 13፡41)፣ ክፉዎች (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡9~10፣ ገላቲያ 5፡19~21) በዮሐንስ 21፡8 ላይ የምናነበው “ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሣን የነፍስ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኞችም ጣኦትንም የሚያመልኩ፣ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባህር ነው፣ ይኼውም ሁለተኛው ሞት ነው” (ዮሐንስ ራዕይ 21፡8) ደግሞም አስታውስ ግብዞች ወደ ሰማይ እንደማይሄዱ (ማቴዎስ 24፡51) በመጨረሻም የተታለሉ እና በኃይማኖት የተሣሣቱ ሁሉ ይጠፋሉ (2ኛ ጢሞተዎስ 3፡13፣ ሮሜ 16፡ 17~18)፡፡

በሰማይ ያለው ማን ነው? እግዚአብሄር እዚያ ነው፣ መንግሥተ ሰማያት እራሷ የሕያው እግዚአብሄር ከተማ እንደሆነች ተገልፁአል (ዕብራዊያን 12፡22) ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ አለ (ሐዋሪያት ሥራ 2፡ 32~33)፣ የእግዚአብሄር መላዕክት በዚያ አሉ (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7~9)

መንግሥተ ሰማይ ምን ይመስላል? ዮሐንስ ሲፅፍ ይላል “አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን አየሁ፣ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፣ ባህርም ወደ ፊት የለም ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሊም ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሠማይ ከእግዚአብሄር ዘንድ ስትወርድ አየሁ፡፡ ታላቅም ድምፅ ከሠማይ እነሆ የእግዚአብሄር ድንኳን በስዎች መካከል ነው፣ ከእነርሱም ጋር ያድራል እነሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሄርም እርሱ እራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፣ እባዎቸንም ከዓይኖቻቸው ያብሳል፣ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ሳዘንም ቢሆን ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ፣ በዙፋኑም የተቀመጠው፦ እነሆ ሁሉን አዲስ አድረጋለሁ አለ፡፡ ለእኔም ፦ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸው ናቸውና ጻፍ አለኝ፡፡ አለኝም፦ ተፈፅሟል አልፋና ኦሜጋ ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ፣ ለተጠማ ከህይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ፡፡ ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል፣ አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል” ብሎ ያየውን ፅፏል (ዮሐንስ ራዕይ 21፡1~7) አሁንም የዮሐንስን ፅሁፍ ማንበብ ስንቀጥል “በአደባባይም መካከል ከእግዚአብሄርና ከበጉ ዙፋን፣ የሚወጣውን ፣ እንደ ብርሌ የሚያንፀባርቀውን የህይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ፡፡ በወንዙም እዲያና ወዲህ በየውሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የህይወት ዛፍ ነበረ፣ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ፣ ከእንግድህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም፣ የእግዚአብሄርና

የበጕም ዙፋን በእርሷ ውስጥ ይሆናሉ፣ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፣ ፊቱንም ያያሉ፣ ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል፣ ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፣ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ። እርሱም ፦ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞዎች ናቸው፣ የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ በቶሎ ሊሆን የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ እንዲያሳይ መልዓኩን ሰደደ። እነሆም በቶሎ እመጣለሁ፣ የዚህን መፅሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁህ ነው አለኝ" (ዮሐንስ ራዕይ 22፡1~7)

እርግጥ ነው መላውን የዮሐንስ ራዕይ ስናነብ ፣ በመንፈስ አነሣሽነት ዮሐንስ ሰማይ የውርቅ ጎዳናዎች ይኖሯታል፣ የከተማይቱም ቅጥርመሰረቶችሁሉምዓይነትየከበሩድንጋዮችይኖሩታልወዘተይላል። ዮሐንስ የራዕን መፀሐፍ የጀመረው በእነዚህ ቃላቶች ነው "ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪይዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሄር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው፣ በእርሱም በመልዓኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፣ እርሱም ለእግዚአብሄር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ። ዘመኑ ቅርቧልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተፃፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው" ብሎ ነው የጀመረው (ዮሐንስ ራዕይ 1፡1~3)። ስለዚህ ዮሐንስ ሰው እንደመሆኑ መጠን ማንም ሰው ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀውን ነገር ማየት ችሏል። ስለመንግሥተ ሰማያትና ስለክብሯ ሁሉ ለመፃፍ ሰው ሊረዳው በሚችል ቃላቶች ውስጥ ማስቀመጥ ነበረበት፣ ለዚህም ያያቸውን አብዛኞቹን በምሣሌያዊ አነጋገር ገልፆታል፣ በዚህ ምድር ላይ ካሉት እንደወርቅ የከበሩ ድንጋዮች ጋር በማነፃፀር እጅግ ውብና ድንቅ ከመሆኑ የተነሣ በትክክል ሊገለፅ የማይችል ነበር፣ አስደናቂ ነው፣

አንድ ሰው ሰማይ ለተዘጋጀ ሕዝብ የተዘጋጀ ቦታ ነው፣ አለ፣ እግዚአብሄርና ሕዝቡ ለዘላለም የሚኖሩበት ቦታ ነው። ስለዚህ ሰው ከዚህ ህይወት በእውነት አይሞትም በሥጋ ይሞታል ነፍሱ ግን ለዘላለም ትኖራለች ጌታን የታዘዙ እና ለእርሱ ታማኝ የሆኑ አንድ ቀን ሰማይ ይወሰዳሉ ምቼም አይሞቱም፣ ይህ ሁሉ በትክክል ከኻዛቤ በላይ ሲሆን ሙሉ በሙሉ መረዳትን ስንፈልግ ነው። ስለዚህ በእምነት ተቀብለን እውን የሚሆንበትን ጊዜ እንጠብቃለን፣ እግዚአብሄር አያሣዝንም ነገር ግን ካለምነው ወይም ካሰብነው ሁሉ በላይ እንደሚሰጠን ሙሉ እምነት አለን፣

ወደ ሰማይ መሄድ አይፈልግም? አንድ ቀን ከእግዚአብሄር ጋር መኖር አትፈልግም? ይህ ህይወት ብቻ ቢሆን ኖሮ ምንኛ አስከፊ በሆነ ነበር። እዚህ ብዙ ችግሮች እና ፣ ህመሞች ብዙ ስቃዮች አሉ፣ ነገር ግን ከዚህ ህይወት አልፈን ወደ ተሻለ ዓለም ስንመለከት በሆነ መንገድ

ይህንን ህይወት ማለፍ እንችላለን፡፡
ክርስቲያን ካልሆንክ ጥፍተሃል እናም ከመቃብር በላይ ምንም ተስፋ የለህም፣ ይህንን እንድትገነዘብ እና ለማስተካከል እርምጃዎችን እንድትወስድ እፀልያለሁ፡፡ በኢየሱስ ካመንክ፣ ከኃጥያትህ ንሠህ ከገባህ፣ በክርስቶስ ያለውን እምነትህን ከመሰከርክ እንድትድን ከተጠመቅክ ትድናለህ እናም አንድ ቀን ወደ መንግሥተ ሰማይ የመሄድ ተስፋ ይኖርሃል (ማርቆስ 16፡16) ይህን ካደረግክ ጌታ ያድነሃል ብቻ ሳይሆን ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጨምረሃል (የሐዋሪያት ሥራ 2፡47) አሁንም ጊዜ እና ዕድሉ ስላለህ እንዲያደርጉ እናበረታታለን እንፀልያለንም፡፡

## ትምህርት 34
## ገሀነም መኖሩን ለምን እናምናለን

በገሃነም ስለምናምን ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ገሃነም እና ዲን ድንጋይ እሳትን በመስበካችን እንከሰሳለን፣ ለሰዎች ለኃጥያታቸው ቅጣት ወደ እሳቱ ባህር እንደሚጣሉ ስንነግራቸው እንደሰታለን ማለት ነው፡፡ እውነት ነው መፅሐፍ ቅዱስ በሚናገረው በገሃነም እናምናለን እናም ግፉዎች አንድ ቀን ወደዚያ እላካሉ ነገር ግን ማንም ሰው ወደዚህ አስከፊ ቦታ እንዲሄድ አንፈልግም እናም ሰዎች በግትርነት ወደ አንድ ፍርድ ሲሄዱ በማየታችን ምንም ደስታ አናገኝም፡፡

ጥናታችንን ከመቀጠላችን በፊት ጊዜ ወስደን ገሃነምን ለመግለፅ እንሞክር፡፡እየተነጋገርንያለነውንሙሉበሙሉላትረዱትትችሉይሆናል፣ አንዳንድ ጊዜ በቅዱሣት መፅሐፍት ውስጥ ሲኦል የሚለው ቃል ሞት በሚል ጥቅም ላይም ይውላል፣ ለምሣሌ በማቴዎስ 16፡18 ላይ ክርስቶስ እንዴት እንደሚሞት ሲናገር ነገር ግን ሞቱ እንኳን ቤተክርስቲያኑን ከመምስረት እንደማይከለክለው ሲናገር እዚያ ያለ ነጥብ "የገሃነም ደጆችም አይችሏትም" ይላል፣ ማለትም የሞት ደጆች አይከለክሉትም ማለት ነው፣ ሲኦል ግን በአጠቃላይ የሥቃይ ቦታ ፣ የእሳትና የዲን ሀይቅ፣ ክፉዎች ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖሩበት የዘላለም ቅጣት ተብሎ ይገለፃል፣ የጠፉ ነፍሳት ቋሚ መኖሪያ ይሆናል፡፡

ግን ለምንድነው ማንም ሰው ወደዚህ አስከፊ ቦታ የሚሄደው? ወይስ አፍቃሪ አምላክ ማንንም ሰው ወደ ገሃነም ይልካል? እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ሲኦል ስለምን እንደሆነ የበለጠ እንድናብራራ ያግዛል፣ ሲኦል በመጀመሪያ የተዘጋጀው ለዲያብሎስና ለመላዕክቶቹ ነው ስለክፉዎች ክርስቶስ ሲናገር "እናንተ እርጉማን ለሠይጣንና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ" ሲል በማቴዎስ 25፡41) ላይ ይገልፃል፡፡ስለዚህ ዲያብሎስ ኃጥያትን ኃጥያተኝነትን፣ ክፉትን ይወክላል፣ እርሱ የመልካምና የፅድቅ ተቃራኒ ነው፡፡ የእግዚአብሄር ጠላት ነው፣ ከእርሱም ጋር የቆሙ መላዕክቶች አሉት፣ ስለዚህ ገሃነም

የተዘጋጁላቸው ናቸው፣ በተመሣሣይም ሲኦል ለሰው ልጆች ነፍስ እንዳልተዘጋጀ ሊታወቅ ይገባል፣ ሰው ኀጥያተጋ ቢሆንም እግዚአብሄር ግን ሰው ከገሃነም የሚያመጥበትን መንገድ አዘጋጅቶለታል፣ ሰው የጠፋው እና የገሀነም ፍርድ የተፈረደበት አምላክን ሲክድ እና በልጁ በኢየሱስ በኩል የሚሰጠውን ማዳን ሲያጣ ነው፣ ያንንም ያደረገው እግዚአብሄር ሳይሆን ሰው እራሱ በራሱ ምርጫ የሚያደርገው ነው፣ ስለዚህ እግዚአብሄርን በመካዱ የመጣለትን የመዳን መንገድ ባለመቀበሉ ከራሱ በቀር ማንንም ሊወቅስ አይገባውም፡፡

ሲኦል ብዙውን ጊዜ ከታች እንደሆነ መንግሥተ ሰማያት በሰማይ እየተባለ ነው፣ መፅሐፍ ቅዱስ የትኛውንም ቦታ የት እንዳለ በትክክል አይገልፅም ነገር ግን ሁእቱም ቦታዎች እንዳሉና ወደ ሁለቱም በፍርድ ቀን ፃድቃን ወደ ተዘጋጀው ገነት ኀጥያኑ ወደ ሲኦል እንደሚሄዱ ነው መዘጋጀቱን ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሲኦል የቅጣት ቦታ ነው ክርስቶስ ወንድሙን ጨርቃም የሚለው ሁሉ የጀሃነም ፍርድ ይገባዋል በማለት እንዲህ የሚሉት በአደጋ ውስጥ መሆናቸውን አስጠንቅቋል፡፡ (ማቴዎስ 5፡22)ክፉዎቹን ሁሉ እንደሚሰበስቡ መላዕክቱን ስለመላክ ሲናገር ክርስቶስ እንዲህ ይላል “የሰው ልጅ መላዕክቱን ይልካል፣ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሏቸዋል “ አለ (ማቴዎስ 13፡41~42) ሐዋሪያው ዮሐንስም እንዲህ ብሎ ፅፏል “ሞትና ሲኦልም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ፣ ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው፣ በህይወትም መፅሐፍ ተፅፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሣት ባሕር ውስጥ ተጣለ” (ዮሐንስ ራዕይ 20፡14~15) እንደዚህም ብሏል “ዱሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የእርኩሳንም የነፍሳ ገዳዮቹም፣ የሴሰኛዎቹም የአስማተኞቹም ጣኦትንም የሚያመልኩ፣ የሐሰተኞቹም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው ይኼውም ሁለተኛ ሞት ነው” (ዮሐንስ ራዕይ 21፡8) ሥጋዊ ሞት እንዳለ ጠቁሟል፣ እና ከላይ ባሉት ጥቅሶች ላይ የተናገረው ሁለተኛው ሞት ከእግዚአብሄር መለየቱን የሚያመለክት ነው፡፡ የዘላለም ቅጣት ቦታ ወደ ሆነው ወደ ገሀነም መጣል ማለት ከእግዚአብሄር ተለይቷል ማለት ነው እና እንደዚህ ላለ ሰው ምንም ተስፋ የለውም፡፡

መጥመቁ ዮሐንስ ስለኢየሱስ መምጣት ሲናገር እንዲህ ነበር ያለው “እኔስ ለንሠሀ በውኃ አጠምቃቸዋለሁ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ ቦኃላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃቸዋል መሹም በእጁ ነው አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፣ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል” አለ (ማቴዎስ 3፡11~12)፣ እዚህ ላይ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ለማጥመቅ ኃይል እንዳለው

ተጠቁሟል። እናም ይህ ለሐዋሪያት የገባውን ቃል በማጣቀስ አፅናኙን ወይም መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ነው፣ ከዚያም በኃላ መጠመቃቸውን እናነባለን (ዮሐንስ 16፡13፣ የሐዋሪያት ሥራ 2) ግን ክርስቶስ ደግሞ በእሳት የማጠመቅ ኃይል ይኖረዋል፣ ይህም ክፉዎች ወደ እሳቱ ባሕር መጣላቸውን የሚያመለክት ነው። ከዚያም አውድማውን አፅድቶ ስንዴውን ወይም ፃድቁን ወደ ጎተራ እሰበስባል፣ ገለባው ደግሞ ወይም ኃጣን ግን በማይጠፋ እሳት ይቃጠላሉ በማለት በምሣሌ ያስረዳል።

ክፉዎችን አስመልክቶ ዮሐንስ ሲናገር "እርሱ ደግሞ በቁጣው ፅዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሄር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፣ በቅዱሣንም መላዕክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሰቃያል፣ የስቃያቸው ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፣ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም።

ኢየሱስ ሲናገር "ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፣ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ" አለ (ማቴዎስ 10፡28) ቀጥሎም "እናንተ እባቦች የእፉኚት ልጆች ከገሀነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ? " አላቸው (ማቴዎስ 23፡33) ኢየሱስ በዘመኑ ለነበሩት ኃይማኖተኛ ፈሪሳዊያንና ግብዞች ይህን ጠቅሷል።

የዕብራዊያን ፀሐፊ "የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፣ የእግዚአብሄርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደእርኩስ ነገር የቆጠረ የፀጋውንም መንፈስ ያከፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችዋል" (ዕብራዊያን 10፡28~29) ጳውሎስም "ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላዕክት ጋር ከሠማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ መከራን የሚያሳዩአችሁን መከራን፣ መከራን ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሄር ፊት በእርግጥ ፅድቅ ነውና " (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7~9)፣ ስለክፉዎችና ፃድቃን ኢየሱስ ሲናገር "እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ፃድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ" አለ (ማቴዎስ 25፡46) "የመንግሥትም ልጆች ግን በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ፣ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል" (ማቴዎስ 8፡12) ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች "የኃጥያት ደመወዝ ሞት ነውና፣ የእግዚአብሄር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ህይወት ነው" (ሮሜ 6፡23) ሐዋሪያው ዮሐንስ "ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፣ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ" ይላል (ዮሐንስ ራዕይ 20፡10)

ኢየሱስ ስለአንድ ሀብታም እና ደሀ የተናገረው ታሪክ በመንግሥተ ሰማያት ያለውን ልዩነት የበለጠ እንድንረዳ ያደርገናል “ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለፀጋ ሰው ነበር፣ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር፣ አላዓዛርም የሚባል አንድ ደሀ በቁስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፣ ከባለጠጋውም ማዕድ ከምወርደው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፣ ውሾች እንኳን መጥተው ቁስሎቹን ይልሱ ነበር፣ ድሀውም ሞተ፣ መልዓክትም ወደ አብረሃም እቅፍ ወሰዱት፣ ባለጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብረሃምን ከሩቅ አየ አልዓዛርም በእቅፉ፣ እርሱም እየጮኸ አብረሃም አባት ሆይ ማረኝ በዚህ ነበልባል እሰቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ፣ አብረሃም ግን ልጄ ሆይ አንተ በህይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልክ አስብ፣ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፣ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይፅናናል አንተም ጸቃያለህ፣ ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ አናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል አለ፣ እርሱም እንኪያስ አባት ሆይ ወደ አባቴ ቤት እንድጸደው እለምንሃለሁ አምስት ወንድሞች አሉኝና እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ሥፍራ እንዳይመጡ ይመሰክርላቸው አለ፣ አብረሃም ግን ሙሴና ነቢያት አሏቸው እነርሱን ይስሙ አለው እርሱም አይደለም አብረሃም አባት ሆይ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንሠሃ ይገባሉ አለ፣ ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፣ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው” (ሉቃስ 16፡19~31) ስለዚህ ገሃነም እውነት ነው እናም እኛ ወደዚያ እንዳንሄድ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፣

ነፍስ ወደ ገሃነም ስትጣል ወዲያው ትጠፋለች እና መጨረሻው ነው ለማለት የሚሞክሩ አሉ፣ ነገር ግን እንደተመለከትነው አንድ ሰው ወደ ሲኦል ሲሄድ እስከዘላለም ድረስ ይቀጣል እና ይሰቃያል፣ ሁለቱም ዘላለማዊ ናቸው፣

አሁን ካነበብናቸው ቅዱሣት መፅሐፍት አንዳንድ የመጨረሻ መደምደሚያዎችን እናድርግ፣ ዲያብሎስና መላዕክቱ በገሃነም ውስጥ ይሆናሉ፣ ክፉዎች ኃጥያተኞች፣ ግብዞች በኃይማኖት የተታለሉ፣ በሥርዓት የተጠመዱ ታማኝ ያልሆኑ ወዘተ ሁሉም በገሀነም ውስጥ የመኖር ድርሻ አላቸው።

ወዳጆቼ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል፣ ክርስቶስ ስለሚሰጠው መዳን ተነግሮናል፣ እናም ወደ ሲኦል እንዳንሄድ እና ለመንግሥተ ሰማያት ለማዘጋጀት የሚረዳ ጥሪት ተደርጓል፣ ነገር ግን ጌታ እንድትታዘዙት አያስገድድዎትም፣ ውሳኔው ያንተ ነው፣ ፀሎታችን ክርስቶስ የሚያቀርበውን ደህንነት እንድትቀበል ነው፣ ጳውሎስ ሲናገር “በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፣ እነሆ የተወደደው ሰዓት

አሁን ነው፣ የመዳን ቀን አሁን ነው" (2ኛ ቆሮንቶስ 6፡2)፣ ክርስቶስ እስከነሸክማችን ወደ እሱ እንድንመጣ እየጋበዘን ነው (ማቴዎስ 11፡ 28)፣ የእብራዊያን ፀሐፊም መዳናችንን ቸል እንዳንል ያበረታታናል (ዕብራዊያን 2፡3)

ድነሃል? ወደ ሰማይ ለመሄድ እየተዘጋጀህ ነው? ካልሆነ ጠፍተሃል እናም ገሃነም ይጠብቅሃል። ወዳጄ ሆይ ጊዜህ አሁን ነውና ጌታን ስማ በእርሱ እማን ከኃጥያትህ ንሰሀ ግባ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክር ከኃጥያትህም ትታጠብ ዘንድ ተጠመቅ ክርስቶስ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሀል (ማርቆስ 16፡16 ሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ 47) እባክህን ገሃነም አትግባ !

## ትምህርት 35
## በፍርድ ቀን ለምን እናምናለን

መፅሐፍ ቅዱስ የፍርድ ቀን እንደሚኖር በግልፅ ያስተምራል። ያ ማለት ስለራሳችን መልስ የምንሰጥበት ማለት ነው፣ በዚህ ዓለም ውስጥለተናገርነውና ላደረኘው ሁሉ ተጠያቂ እንሆናለን ማለት ነው፣ ብዙ ሰዎች ላደረጉት ነገር ለማንም ተጠያቂ መሆን እንዳለባቸው ማሰብ አይወዱም ሲሳሳቱ ለፖሊስ መልስ መስጠት እና ግብር ታክስ ተጠያቂ መሆንን አይወዱም ነገር ግን ይህ የህይወት እውነታ ነው፣ ኑሮን የሚያገኙ ከአሰሪያቸው ጋር በሚሰሩት ነው እና ለሚጠየቁት ለአሰሪያቸው መልስ መስጠት አለባቸው ትምህርት ቤት ወይም ኮሌጅ የሚማሩ የፈተና ቀን ሊገጥማቸው ይገባል፣ በውታደራዊ አገልግሎት ውስጥ ያሉ ለበላይ ባለሥልጣናቸው ሪፖኦርት ማድረግ አለባቸው ወዘተ ህይወት እኛ አለቃ ካልሆንን ወይም ከሞትን በቀር ከእነዚህ ኃላፊነቶች ለማምለጥ ምንም መንገድ የለም። ነገር ግን ባለጠጎች፣ የአህዛብ አለቆች ሕያዋንና ሙታንም ሁሉ አንድ ቀን በእግዚአብሄር ፍርድ ወንበር ፊት ይገለጣሉ።

የዕብራዊያን ፀሐፊ "ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ ቦኃላም ፍርድ እንደተመደበባቸው" ይላል (ዕብራዊያን 9፡27) በዚያ ቦታ ማን ይገኛል ? ጳውሎስ ሲናገር "መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ልንገለጥ ይገባናል" ይላል (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡ 10) ፍርድ ብቻ ሳይሆን ሁሉም በዚያ ይሆናሉ እናም ሁሉም በፃድቁ ዳኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ይቀርባሉ እና ሁሉም መልካምም ይሁኑ መጥፎ እንደስራቸው ይፈረድባቸዋል።

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሲፅፍ " ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና ለራሱም የሚሞት የለም፣ በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና ምንሞትም ለጌታ እንሞታለን፣ እንግዲህ በህይወት ሆነን

ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን፤ ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞታልና ሕያውም ሆኖአልና፤ አንተም በወንድምህ ላይ ስለምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና፤ እኔ ሕያው ነኝ ይላል ጌታ ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል ምላስም ሁሉ እግዚአብሄርን ያመሰኛል ተብሎ ተፅፎልና እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስል ራሳችን ለእግዚአብሄር መልስ እንሰጣለን" (ሮሜ 14፡7~12)

ጳውሎስ ለአቴንስ ሰውቸ ሲናገር እንዲህ ይላል "እንግዲህ እግዚአብሄር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንሰሀ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ ቀን ቀጥሯልና፤ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ ሊፈርድ አለው፤" (የሐዋሪያት ሥራ 17፡30~31) እግዚአብሄር ዓለምን በፅድቅ የሚፈርድበት ቀን እንደሾመ አስተውል፡፡ ያም ማለት እግዚአብሄር ሁሉንም ይፈርዳል ፍርዱም ትክክል ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመጥፎ መንገድ አያደርግም አያዳላምም፤ ወይም እርስ በእርሳቸው አያጣላም፤ ያ ቀን መቼ እንደሚሆን አናውቅም ግን እግዚአብሄር ያውቃል፡፡ የጌታ መመለሻም እንዲሁ ነው፡፡ ክርስቶስ ስለዚያ ቀን የሰማይ አባት ብቻ እንጂ መላእክቱ እንደማያውቁ ነግሮናል፤ መላዕክቱ ካላወቁ አባቱ ብቻ የሚያውቅ ከሆነ ሰው እንዴት ያውቃል? በእርግጥ ሰው ክርስቶስ መቼ እንደሚመጣ አያውቅም እናም ፍርጉ መቼ እንደሚፈፀም አያውቅም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሄር በዓለም ላይ እንደሚፈርድ ተነግሮናል ይህም ሰው የሾመውን አስቦ ነበር እናም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ሁሉ ማረጋገጫውን ሰጥቶአል፡፡

ጳውሎስ በፍልክስ ፊት በቆመ ጊዜ እንደሰበከው አልተነገርንም ፊልክስናድሩሲላበምንዝርይኖሩእንደነበርዘገባውይናገራል፤"እርሱም ስለፅድቅ እና ራስን ስለመግዛት ስለሚመጣውም ኩነኔ ሲነጋገር ሳለ ፊሊክስ ፈርቶ አሁንስ ሂድ በተመቸኝም ጊዜ ልኬ አስጠራሃለሁ ብሎ መለሰለት"(የሐዋሪያትሥራ24፡25)ጳውሎስፊልክስእየኖረበትያለውን ህይወት ስላወቀ፤ ስለ ሥራው ሁሉ ለእግዚአብሄር መልስ እንዲሰጥ ስለሚከፍለው ዋጋ ሊያስጠነቅቀው ድፍረት ነበረው፡፡ አፈራራው፤ ነገር ግን ልብ ባለማለቱ ጳውሎስን የበለጠ አመቺ ጊዜ ሲያገኝ እንደሚጠራው ቃል በመግባት አሰናበተው፤ እስካሁን እስከምናውቀው ድረስ ፈፅሞ አልጠራም ስለዚህም በዚያ መሃል ሞተ፤ እንዴት ያሳዝናል !

ኢየሱስ በዘመኑ ለነበሩት ኃይማኖተኞቸ ሲናገር "እናንተ የእፉኝት ልጆቸ ክፉዎቸ ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትቸላላቸሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና፡፡ መልካም ሰው ከልቡ መልካም ነገርን ያወጣል፤ክፉሰውምከክፉመዝገብክፉነገርንያወጣል፤እኔእላቸኋለሁ፤ ሰዎቸ ስለሚናገሩት ስለከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትፀድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኮነናለህ" ብሏቸዋል

(ማቴዎስ 12፡34~37) ያም ማለታንድ ሰው ስለሚያስበውና ስለሚናገረው ማወቅ አለበት፣ አንድ ሰው ስለሚያስበው ወይም ስለሚናገረው ምንም ይሁን ምን አንድ ለዚያ ነገር ተጠያቂ እንደሚሆን መዘንጋት የለበትም፣ ያንን ማወቁ ብቻ አንድን ሰው ከመናገሩና ከመተግበሩ በፊት በጥልቀት እንዲያስብበት ያደርገዋል፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ 2፡16፣ ላይ በፍርድ ቀን በሰው ዘንድ የተሰወረውን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚገልጥ ተናግሯል፡፡ የዕብራዊያን ጸሐፊም የሚያስታውሰን "የእግዚአብሄር ቃል ህያው ነውና፣ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሣለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ስሜትና ሀሳብ ይመረምራል፣ እኛን በሚቆጣጠርበእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም" ይላል (ዕብራዊያን 4፡12፣13) ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች "ነገር ግን በእናንተ ዘንድ ወይም በሌላ ሰው ዘንድ ብፈርድ ለእኔ ምንም አይደለም፣ እኔም በራሴ እንኳ አልፈርድም፣ በራሴ ላይ ምንም አላውቅምና፣ ነገር ግን በዚህ አልፀድቅም፣ እኔን የሚፈርድ ግን ጌታ ነው" (1ኛ ቆሮንቶስ 4፡3~5) እንደገና ጳውሎስ እንዲህ ይላል "በእግዚአብሄር ፊት በህያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ" (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1) ጳውሎስ እራሱንም በተመለከተ "ወደፊት የፅድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም" ይላል (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡8)፣ ጳውሎስ ጌታ ጻድቅ ፈራጅ እንደሆነና  በዚያም ቀን የጽድቅን አክሊል እንደሚሰጠው ሲናገር የፍርድ ቀን ማለቱ ሲሆን እንዲህ ያለውን ዋጋ የሚሰጠው ለእሱ ብቻ ሳይሆን ጌታን ለሚወዱት መገለጡን ለሚጠባበቁት ሁሉ መሆኑን ይገልፃል፡፡

የዕብራዊያን ጸሐፊ እግዚአብሄር የሁሉም ዳኛ መሆኑን ይገልጻል (ዕብራዊያን 12፡23)፣ እንደዚሁም በ 13፡4፣ ላይ ጋብቻ ክቡር መኝታውም ንፁህ እንደሆነና በአመንዝሮቹም ላይ እንደሚፈርድ ይናገራል፡፡

ኢየሱስ በማቴዎስ 25 ላይ እንዲህ ይላል "የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሣን መላዕክት ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፣ አህዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል፣ በጎቹን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል" (ማቴዎስ 25፡31~33) እዚህ ላይ ጌታ ፍርዱን አንድ ቀን  እንደሚፈፅም ያሳያል፡፡ በመምጣቱም ቀን ይሆናል፣ አህዛብም ሁሉ ህዝብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፡፡ በዚያን ቀን እረኛ በጎቹን ከፍየሎች እንደሚከፍል መልካሙን ከክፉው ይለያል፡፡

በቀኝ እጁ ያሉት በጎች ጻድቃንን፣ ክርስቲያንን፣ ቤተክርስቲያንን ይወክላሉ። በግራ ያሉት ፍየሎች ክፉዎችን፣ የተታለሉትን እና ታማኝ ያልሆኑ ክርስቲያኖችን ይወክላሉ፣ እናም ፍርዱ ከተፈፀመ በኃላ ክፉዎች ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ (ማቴዎስ 25፡46)።

አሁን እነዚህን ሁሉ በማጠቃለል እባክህን ይህን አስተውል፦

1 የእግዚአብሄር ፍርድ አንድ ቀን ይመጣል፣ ነገር ግን ከሞት በኃላ ወይም በጌታ ዳግም ምፅዓት ላይ ይሆናል

2 በዚያ ታላቅ ቀን ሁሉም በዚያ ይሆናሉ፣ በህይወት ያሉም የሌሉም ሰዎች ሁሉ በዚያ እንደሚሆኑ አስብ፣ ማንም ሊሸሸግ ወይም ሊያመልጥ አይችልም፣ ወጣት አዛውንት፣ ጥሩ መጥፎ፣ ሀብታም ደሀ ፣ ንጉስ አገልጋይ ባሪያ ሁሉ በፊቱ ይሆናሉ።

3 እግዚአብሄር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ይፈርዳል

4 ሁሉም ሰው በጎም ይሁን መጥፎ በሥራው እንዲፈረድበት የማያዳላ ፍርድ ይሆናል

5. ማንኛውም ከቱ ቃል፣ እያንዳንዱ ተጋባር እና እያንዳንዱ ምስጢራዊ ሀሳብ በዚያ ታላቅ ቀን ይፈረድበታል

6. ይህ ፍርድ የመጨረሻ ይሆናል፣ ሁለተኛ ዕድል አይኖርም፣ የፅድቅ ፍርድ ይሆናል

7 በዚያም ቀን ጻድቃን የዘላለም ህይወትን ያገኛሉ፣ ኃጥአን ደኅም ከዲያብሎስ ጋር የዘላለም ጥፋት ፍርድ ያገኛሉ

ለዚያ የፍርድ ቀን ተዘጋጅተሃል? ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን አስታውስ “የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፣ እኔ የተናገርኩት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል” ብሏል (ዮሐንስ 12፡48) እንደገና እንዲህ ብሏል “ እውነት እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሄርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፣ የሚሰሙትም በህይወት ይኖራሉ፣ አብ በራሱ ህይወት እንዳለው እንዲሁ ለወልድ በራሱ ህይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካምም ያደረጉ ለህይወት ትንሳኤ ፣ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና አታድንቁ፣ እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም እንደሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና (ዮሐንስ 5፡ 25~30)

ወዳጆቼ ፦ ለዚህ ፍርድ ቀን መዘጋጀት ትችላላችሁ፣ በኢየሱስ እመን፣ ንሠሀ ግባ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክር ለኃጥያትህ ሥርየት በውኃ ውስጥ በመቀበር ተጠመቅ፣ ይህንን ስታደርግ ጌታ ያድንሃል፣ ቤተክርስቲያኑም ላይ ይጨምርሃል፣ እስከ ሞት

ድረስ ለርሱ ታማኝ ከሆንክ አንድ ቀን በፊቱ ስትቆም እንዲህ የሚል ድምፅ ትሰማለህ "አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ መልካም ታማኝ ሆይ ና ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" የሚል ትሰማለህ፣ የጌታ ደስታዎቹ ድንቅ አይደሉም? እስቲ አሁን ጊዜው አለህና አስቡበት ተዘጋጅበት፣ ጌታ እንዲረዳህ እንፀልያለን።

## ትምህርት 36
## ክርስትና ለምን ልዩ ሆነ

ክርስትና በዓለም ዙሪያ ይገኛል። በክርስቶስ ያመኑት በሚሊዮንና በሚሊዮንስ የሚቆጠሩ ናቸው። አባላቱ መዕዕክቱን ሲያስተላልፉ ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል።

ክርስትና በክርስቶስ በማመን ላይ የተመሰረተ ነው፣ በሌላ በሰው ላይ ፣ በሌላ ቅዱስ ሰው ላይ ወይም በነቢይ ላይ የተመሰረተ አይደለም። የእግዚአብሄር ልጅ የሆነው ለዓለም ኃጥያት የሞተው ከመቃብር ተነስቶ ለዘላለም የሚኖረው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሰረተ ነው። ጴጥሮስና ሐዋሪያት ይህንን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መሰከሩ (ማቴዎስ 16፡ 16~18) እግዚአብሄርም ከሰማይ ኢየሱስ የእሱ ልጅ መሆኑን በእውቅና አውጇል (ማቴዎስ 17፡5)

ክርስትና ዛሬ በዓለም ላይ በህያው መሪ ያለው ብቸኛ ኃይማኖት ነው። የሁሉም ኃይማኖት መሪዎች ሞተዋል ግን አልተነሱም፣ ክርስቶስ እንደገና ከሞት እንደሚነሣ ተናሯል አድርጎታልም (ዮሐንስ 11፡35፣ ማቴዎስ 28፡1~6) የገባውን ቃል ባጠብቅ ኖሮ ውሸታም አታላይ በሆነ ነበር፣ እርሱ ከመቃብር ባይወጣ ኖሮ ክርስትና በፊፁም አይዳብርም አይኖርም ነበር፣ ነገር ግን ክርስትና ይኖራል፣ ቤተክርስቲያንም፣ ህይወት የትንሣኤ ተስፋም ሁሉም የሚኖሩት ክርስቶስ ህያው ስለሆነ ነው።

ክርስትና በጣም ተወዳጅ ኃይማኖት ነው፣ ከዬትኛውም ኃይማኖት ወይም እምነት የበለጠ ዓለምን ለበጎ ለመለወጥ ብዙ አድርጓል። ዓለም ዓቀፋዊየቀን መቁጠሪያዎቹየፍቅርግንኙነትሥርዓታቸውን በክርስቶስ ህይወትእናሞትላይይመሰርታሉ፣የብሔራት ሕጎቹበዋነኝነትየሚነኩት በክርስቶስ የሥነ ምግባር ትምህርቶቹ ነው። አብዛኞቹ ሀገሮቹ ቅዳሜና እሁድን እንደ ልዩ ቀን የሚመለከቱት እና የምገነዘቡት ከክርስትና ነው፣ ማለትም ክርስቶስ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከመቃብር መውጣቱን እናጌታ ሕዝቡን በመጀመሪያው ቀን እንዲገናኙ በማዘዙ ላይ የተመሰረተ ነው፣እሱን ለማሰብ እናእግዚአብሄርን ለማምለክ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እሁድ ነው (ማቴዎስ 28፡1~6፣ የሐዋሪያት ሥራ 20:7)፣

ክርስትና በሰው ዘንድ የሚታወቁትን ከፍተኛውን የሞራል መርሆቹን ይደግፋል፣ ሀቀኝነትን ያስተምራል፣ እዳ መክፈል፣ የቀን ሥራን ለቀን ደመወዝ መስጠት እና እርስ በእርስ መከባበርን ያስተምራል። እሱ

ለሥና ምግባራዊ ንፅህና ይቆማል፣ የቤተሰብን ሥርዓት ያበረታታል፣ ከአንድ ባልና ከአንድ ሚስት ብቻ ጋር ጋብቻን ይደግፋል፣ እና ከእነሱ ጋር እስከ ሞት ድረስ ታማኝ መሆንን ያስተምራል፣ እግዚአብሄርን የሁሉም ራስ አድርጎ ይገነዘባል፣ ወንድ የሚስቱ ራስ ሲሆን ነገር ግን ወንድና ሴት ሁለቱም የየራሳቸው ኃላፊነት አለባቸው፣ እና ልጆቻቸውን በጌታ አስተዳደግ እንዲያሳድጉ ያስተምራል ክርስትና።

ክርስትና ኃይማኖት ሲሆን ኃይማኖት ማለት ደግሞ ለእግዚአብሄርና ለሰው የሚሰጥ አገልግሎት ማለት ነው፣ ያዕቆብ እንዲህ አለ "ንፁህ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሄር አብ ዘንድ ይህ ነው፣ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶቸንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው" ይላል (ያዕቆብ 1:27) አባት የሌላቸውን እና መበለቶቸን ማለት ማህበራዊ ጉብኝት ከማድረግ የበለጠ ነገር ነው፣ የእነዚህን ሰዎቸ ፍላጎት መንከባከብ ማለት ነው፣ ክርስቲያኖቸም በቻሉት መጠን የሌሎቸን ፍላጎት የመመልከት ግዴታ አለባቸው፣ ጳውሎስ እንዲህ ይላል "ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም፣ እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈፅሙ" (ገላቲያ 6:2)

ክርስትናን የሚወክሉት የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሄር እንደሆነ ያምናሉ (ዘፍጥረት 1:1) ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም የላከው በሰው መካከል እንዲኖርና ለዓለም ኃጥያት በመስቀል ላይ እንዲሞት የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ያምናሉ፣ክርስቶስ እንዲህ ይላል "እንግዲህ ፦ በኃጥያታቸሁ ትሞታላቸሁ አልኋቸሁ፣ እኔ እንደሆንኩ ባታምኑ በኃጥያታቸሁ ትሞታላቸሁና አላቸው" (ዮሐንስ 8:24) ክርስቲያኖቸ መንፈስ ቅዱስ በብዙ መቶ ለሚቆጠሩ ዓመታት የእግዚአብሄርን ቃል እንዲፅፉ አነሣስቷቸዋል ብለው ያምናሉ ስለዚህም የእግዚአብሄርን ቃል እንዲፅፉ (2ኛ ጴጥሮስ 1:21፣ 2ኛ ጢ፣ሞቴዎስ 3:16~17፣ ማቴዎስ 24:35) ቤተክርስቲአይኒቱን የመሰረተው ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ እናምናለን እሷም አንዲት ቤተክርስቲያን ናት የዳኑት ሁሉ የተጨመሩባት (ማቴዎስ 16:18፣ ኤፌሶን 4:4~6፣ የሐዋሪያት ሥራ 2: 47) በክርስቶስ ሞት መቀበርና ትንሣኤ እናምናለን፣ ይህም የምሥራቸ በመላው ዓለም ይሰበካል፣ ክርስቶስ እንዲህ ሲል አዟል "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ 16:15~16) ጌታን የሚታዘዙ እንደሚድኑ ክርስቲያን ብቻ የሆኑ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሄርን እንደሚያመልኩ እናምናለን እናም ለክርስቶስ ዕለት ዕለት እንደሚኖሩ እናምናለን (ማቴዎስ 7:21፣ 1ኛ ጴጥሮስ 4:16፣ ዮሐንስ 4: 24፣ የሐዋሪያት ሥራ 20:7፣ ሉቃስ 9:23)።

ክርስትና በክርስቶስ ያመኑትን ሁሉ በአንድነት ይደግፋል (1ኛ ቆሮንቶስ 1:10) እና ሁሉም በክርስቶስ አንድ መሆናቸውን ጳውሎስ

እንዲህ ሲል ፅፏል "በእምነት ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጆቻ ናችሁና ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" (ገላቲያ 3፡26~28)

ሰው በሥጋ ከጌታ ሊወለድ አይችልም ስለዚህ ክርስትና የሚያድገው በሥጋዊ ልደት ሳይሆን በመንፈሳዊ ልደት ነው (ዮሐንስ 3፡3~5)። በሌላ አገላለፅ ጌታ ደቀማዛሙርቱን ስለእሱ እንዲያስተምሩ ይልካቸዋል ስለእሱ ሰዎቸ እንዲያስተምሩ፣ ይህም ወንጌልን እንዲሰሙ፣ በክርስቶስ እንዲያምኑ፣ እርሱን እንዲታዘዙ እንዲጠመቁ ለማድረግ ይልካቸዋል፣ ከዚያም በመንፈስ ተወልደው የእግዚአብሄር ልጆች ይሆናሉ፣ ምክንያቱም እምነት የሚመጣው በመስማት ነው (ሮሜ 10፡17) ዕብራዊ ፀሐፊ ደግሞ ያለ እምነት እግዚአብሄርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ይላል (ዕብራዊያን 11፡6) አሁንም የዕብራዊያን ፀሐፊ ይቀጥልና "እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና እንባ ጋር ፀሎትንና ምልጃን አቀረበ፣ እግዚአብሄርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት፣ ምንም ልጅ ቢሆን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፣ ከተፈፀመም ቦኋላ በእግዚአብሄር እንደ መልኬ ፄዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ተጠራ" (ዕብራዊያን 5፡7~9) ያም ማለት ሕፃናት ወይም ትንንሽ ልጆች ክርስቲያን ወይም የቤተክርስቲያን አባል ሊሆኑ አይችሉም፣ ማደግ አለባቸው በትክክል ክፉ እና በጎን የሆነውን መለየት አለባቸው የክርስቶስን ትምህርት ለመስማት፣ ክርስቶስን ለማመን አምነው ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ እራሳቸው መወሰን እስከሚችሉ ድረስ ነው።

ክርስትና ሁሉም በመጨረሻ እንደሚነሡ፣ ለሁሉም ፍርድ እነደሚመጣ፣ እና ሁሉም ዘላለማዊነትን በገነት ወይም በሲኦል እንደሚያሳልፉ ያስተምራል፣ ክርስቶስ ሲናገር "በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ" ብሏል (ዮሐንስ 5፡28~29) ሌላም እንዲህ ይላል "ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ ቦኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው" ይላል (ዕብራዊያን 9፡27) ጳውሎስም ሲያውጅ "መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል" (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡10) ከፍርድ ቦኋላ ክፉዎቾ ወደ ዘላለማዊ ቅጣት ፣ ጻድቃን ደግሞ ወደ ዘላለማዊ ህይወት ይሄዳል(ማቴዎስ 25፡46)

ክርስትና የሚቃወማቸው ነገሮቾም አሉ፣ ሰይጣንን፣ ዓለምንና የሥጋን ሥራ ትቃወማለቾ (1ኛ ዮሐንስ 2፡15~17፣ ገላቲያ 5፡19~21)፣

በተለይም ጦርነትን፣ ጉቦን፣ ማጨስን፣ ቁማርን፣ መጠጥን፣ አደንዛዥ እፆችን፣ ፅንስ ማስወረድ፣ ግብረ ሰዶማዊነትን፣ እና ሌሎች እነዚህን የመሣሣሉትን ነገሮች አለአግባብ መጠቀምን ትቃወማለች፣ ሥር ዓተ ጣኦትን ማምለክ፣ ሁሉንም የሐሰት ኃይማኖቶችን ፣ እና ራሳቸውን እንደ አምላክ አድርገው የሚያዩትን አትቀበልም፡፡ አባላቱን ሥጋ እንዳይበሉ አይከለክልም ጳውሎስ አንዳንድ ሰዎች ማግባትን ይከለክላሉ እና ከሥጋም እንዲርቁ ያዛሉ ይላል "እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ፣ አምነውም እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሄር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፣ ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፣ በእግዚአብሄር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና " (1ኛ ጢሞተዎስ 4፡3~5)

ክርስቶስን የምንከተል እንደመሆናችን መጠን በእግዚአብሄር ቃል ያልተጠቀመጡትን ሁሉንም ዓይነት ክርስትና እንቃወማቸዋለን፣ በሌላ አነጋገር፣ ዓለም እንደክርስትና  የሚመለከታቸው አብዛኛው የውሸት ክርስትና ነው፡፡ ክርስቲያን ሲጣሉ እንሰማለን፣ ክርስቲያኖች ይህን ሲያደርጉ እና ክርስቲያን ያን ሲያደርጉ ይህ ሁሉ መጥፎ እና ስህተት ነው፣ እንደገና ይህ እውነተኛ ክርስትናን አይወክልም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና እና እንደዚህ ያሉትን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች የሚታወቁት በሚያደርጉት መልካም ነገር ብቻ ነው እና በዚህም ዓለምን የተሻለች የመኖሪያ ቦታ  በማድረግ፣ ስለዚህ የእግዚአብሄር ቃል በሰው ሰራሽ ክርስትና፣ ቤተ እምነቶች እና ኑፋቄዎች ላይ እውነትን ያስተምራል፡፡

ክርስቶስን እንከተላለን በሚሉ የሰዎች ቡድኖች አናምንም ነገር ግን በኃይማኖት ነጻነት እናምናለን፣ እግዚአብሄር እራሱ የዓለምን የሐሰት ኃይማኖቶች አልፈቀደም፣ ግን ዝም ብሎ ተቶታል፡፡ እያንዳንዱ ሰው እሱን እንደሚያገልግለው ወይም እንደሚቃወመው እንዲወስን ማንም ሰው ኃይማኖቱን በሌሎች ላይ የማስገደድ መብት የለውም፡፡ የሰው ልጅ እንደፈለገው በነፍሱ የማድረግ ነጻነት እስካላገኘ ድረስ በእውነት ነፃ አይሆንም፣ እውነተኛ ነፃነት የሚመጣው በእግዚአብሄር ቃል ነው (ዮሐንስ 8፡32) ሰውን ከእግዚአብሄር ጋር የሚያስተዋውቅና ከኃጥያት እንዴት ነፃ እንዲሚኮን የሚያስተምር የእግዚአብሄር ቃል ብቻ ነው፣ እሱም እውነት ነው፣

አንተ የትኛውን ኃይማኖት ነው የምትከተለው?  ለምን ተለማመድከው? የተወለድከው በአካል ነው? ወይንስ በማስተማር እና ይህ እውነተኛውን መንገድ የሚወክል መሆኑን በማመን ነው የተቀበልከው?

ኃይማኖትህ ላንተ ትርጉም አለው? እንደዛሬው  ዓለም ዘመናዊ ነው ወይንስ ወደ ቀድሞው ህይወት ይወስደሃል? ምን የሚፈጥርብህ ነገር አለው?

ሰዎቹ የማንበብ፣ የመማር እና የራሳቸው ውሳኔ ለመወሰን እድል እስካገኙ ድረስ ክርስትና ምንም የሚያስፈራ ነገር የለውም፣ ክርስትና አመክኞአዊ እና አስተዋይ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በተጨማሪም በክርስቶስ የሚያምኑትን እና የማያምኑትን ተመልከቱ እና ኃይማኖት ምን እንደሚያደርግላቸው ተመልከቱ፡፡ ክርስትና ሲተገበር ህዝቡን ወደ መልካም እንደሚለውጥ እና ወደ ተሻለ አካላዊ እና መንፈሳዊ ህይወት እንደሚመራቸው በርግጠኘት ማየት ትችላላቸሁ፣

በክርስቶስ ያላመንክ ከሆንክ ክርስትናን እንድታስብ ላበረታታህ፣ ስለሱ በአዲስ ኪዳን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ አንብብ፡፡፣ ከዚህም በተጨማሪ በእግዚአብሄርና በክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ በማመን ከኃጥያትህ ንሰሃ በመግባት ክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን በአፍህ በመመስከር ለኃጥያትህም ሥርየት በውኃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ (ዕብራዊያን 11፡6፣ ዮሐንስ 14፡1~3፣ የሐዋሪያት ሥራ 17፡30፣ ሮሜ 10፡10፣ የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ ይህን ስታደርግ ጌታ ያድንሃል፣ ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምርሃል እናም አንተ ክርስቲያን እና የክርስትና አንዱ አካል ትሆናለህ (የሐዋሪያ ሥራ 2፡47) 1ኛ ጴጥሮስ 4፡16) ያ ቀላል አይደለም ? በጣም እና ያልተወሳሰበ ነውና እባክህን አትሰናከልበት አሁኑኑ ወስን፡፡